# እስላምን ለመገንዘብ

## مبادئ الإسلام

باللغة الأمهرية

ትርጉም

ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር


አሣታሚ

International Islamic Federation
of Student Organizations

አለም አቀፍ እስላማዊ መጽሐፍት አሣታሚ ድርጅት

ሣዑዲ አረቢያ፥ ፖ.ሣ.ቁ 55195 ሪያድ 1153

ስልክ 4650818– 4547213

ፋክስ 4633489

الإتحاد الإسلامي العالمي للمنظمات الطلابية

بسم الله الرحمن الرحيم

حقوق الطبع محفوظة
للاتحاد الإسلامي العالمي
للمنظمات الطلابية
١٤١٩هـ - ١٩٩٨م

International Islamic Federation
of Student Organizations

አለም አቀፍ እስላማዊ መጽሐፍት አሣታሚ ድርጅት

ሳዑዲ አረቢያ፥ ፖ.ሣ.ቁ 55195 ሪያድ 1153

ስልክ 4650818– 4547213

ፋክስ 4633489

تطلب جميع منشورات الاتحاد من:

**الدار العالمية للكتاب الإسلامي**

نشر وتوزيع الكتاب والشريط الإسلامي بسبعين لغة
الإدارة العامة: ص.ب. ٥٥١٩٥ ـ الرياض ١١٥٣٤
هاتف ٤٦٥٠٨١٨ ـ ٤٦٤٧٢١٣ ـ فاكس ٤٦٣٣٤٨٩
المكتبات: الرياض ٤٦٢٩٣٤٧ ـ ١/ جدة ٦٨٧٣٧٥٢ ـ ٢/الخبر ٨٩٤٥٨٢١ ـ ٣

World Wide Distributor of IIFSO Publications

**INTERNATIONAL ISLAMIC PUBLISHING HOUSE**

I.I.P.H.

Publishing And Distributing Islamic Books And Tapes in 70 Languages

HEAD OFFICE: P.O Box 55195 - Riyadh 11534 - Saudi Arabia

Tel: (966-1) 4650818 - 4647213 - Fax: 4633489

BOOK SHOPS: Riyadh 1-4629347/ Jeddah 2-6873752/ Khobar 3-8945821

E-Mail: **iiph1@hotmail.com**

**Please take part in this noble work by conveying your comments to IIPH through E-Mail or Fax or mail address.**

# ማውጫ

አርዕስት ገጽ


## ምዕራፍአንድ

እስላም ምንድን ነው?.....7

እስላም የሚለው ቃል.....7

የእስላም ምንነት.....8

የክህደት /ኩፍር/ምንነት.....11

የኩፍር ጉጅነትና መጥፎ ውጤት.....12

የእስላም ፀጋ.....17

## ምዕራፍ ሁለት

እምነትና ታዛዥነት.....25

የእምነት ትርጉም.....27

እውነተኛው የእምነት ዕውቀት የሚቀሰምበት መንገድ.....30

ከሕዋሳዊ ስሜት በራቀው ማመን.....32

## ምዕራፍ ሶስት

ነቢይነት.....35

የነቢይነት እውነታ፣ ባህሪና አስፈላጊነቱ.....35

# ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| ነቢይን ማወቅ | 39 |
| ነቢይን መታዘዝ | 40 |
| በነቢይነት የማመን አስፈላጊነት | 42 |
| የነቢይነት አፈታሪክ | 45 |
| የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይነት | 51 |
| የሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይነት | 53 |
| የነቢይነት መደምደሚያ | 64 |
| የነቢያት መደምደሚያነት ማስረጃዎች | 65 |


# ምዕራፍ አራት


| | |
|---|---|
| እምነት በዝርዝር | 69 |
| በአልላህ ማመን | 70 |
| የላኢላሀ ኢለሏህ ትርጉም | 72 |
| የላኢላሀ ኢለሏህ ጽንሰ–ሃሳብ | 73 |
| የተውሂድ እምነት በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ያለው ተጽእኖ | 80 |

## ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
| --- | --- |
| በአላህ መላእክት ማመን | 87 |
| በአላህ መጻሕፍት ማመን | 90 |
| በአላህ ነቢያት እና መልዕክተኞች ማመን | 95 |
| በመጨረሻው ቀን /በትንሣኤ/ማመን | 99 |
| በትንሣኤው ቀን የማመን አስፈላጊነት | 100 |
| የመጨረሻው ዓለም ሕይወት እርግጠኛነት | 104 |
| መልካሙ ቃል | 109 |


# ምዕራፍ አምስት


| | |
| --- | --- |
| አላህን መገዛት ‹አልዒባዳ› | 111 |
| የመገዛት /ዒባዳ/ ትርጉም | 112 |
| ሰላት | 113 |
| ፆም | 118 |
| ዘካት | 121 |
| ሐጅ | 123 |
| እስላምን መጠበቅ | 125 |
| እስላምን መጠበቅ ዘርፎች አንዱ | 127 |

# ማውጫ


አርዕስት ገጽ

## ምዕራፍ ስድስት

ዲንና ሸሪዓ........................................129

የዲንና ሸሪዓ ልዩነት ........................................129

የሸሪዓ ሕጐች ምንጭ ........................................130

ፊቂህ ........................................132

ተሰውፍ /ሱፊዝም/ ........................................134

## ምዕራፍ ሰባት

የሸሪዓ ሕጐች ........................................138

የሸሪዓ መርህ ........................................138

ግዴታዎችና አራቱ መደባቸው........................................142

ለአላህ መፈጸም ያለብን ግዴታ ........................................143

ለገዛ ራሳችን ያለብን ግዴታ ........................................147

ለሌሎች ሰዎች ያለብን ግዴታ ........................................149

ለሌሎች ፍጡራን ያለብን ግዴታ ........................................159

ዘለዓለማዊው ዩኒቨርሳል ሸሪዓ ........................................160

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ «ሪሳላህ ዲኒያት» በሚል ርዕስ ፖኪስታናዊው መውላና አቡል አዕላ መውዱዲ በ1932 በኡርዱ ቋንቋ ተዘጋጅቶ «ዓለም አቀፍ እስላማዊ የተማሪ ማህበራት ፌዴሬሽን» ወደ አረብኛ ቋንቋ ከተረጐመው እትም ወደ አማርኛ ቋንቋ የተመለሰ ነው።

መጽሐፉ ስለ እስላም ምንነት፣ ስለ እምነትና እምነትን ተግባራዊ ስለማድረግ፤ ስለሰላትና ስለዒባዳ ወይም አምልኮ፣ ስለ ሃይማኖት፣ ስለሸሪዓ ሕግና ስለሸሪዓ መሠረታዊ መርህ፣ የመጀ መሪያ ደረጃ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የእስልምና መግቢያ ነው። መጽሐፉ ለተራ አንባቢና ለተማሪዎች ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑ ውስብስብ ከሆነ ፍልስፍናዊ የአቀራረብ ስልት የራቀ ነው።

የእስላም መግቢያ በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያዊ አንባቢ ዛሬ የማቀርበው ይህ መጽሐፍ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ለውጦ ወደ እስልምና ጐዳና ከመሩት መጽሐፎች አንዱ ሲሆን በተለያዩ የዓለም ቋንቋዎች ታትሞ በሚሊየን የሚቆጠሩ ቅጂዎች በመላው ዓለም ተሰራጭተዋል።እስከ 1986 ድረስ /እንደ አውሮፖ አቆጣ ጠር ነው/ መጽሐፉ ከተተረጐመባቸው የዓለም ቋንቋዎች ከነዚ ህም መካከል እንግሊዝኛ፣ዐረብኛ፣ ህንድኛ፣ ፋርስኛ፣ ጀርመ ንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ታሚልኛ፣ ፑሽቶኛ፣ ቤንጋልኛ፣ ጉጁራትኛና ስንድኛ ይገኙበታል።

መጽሐፉን ወደ አማርኛ ተርጐሜ ሳቀርብ ለተራው አንባቢ በተለይም ለጀማሪ ወጣቶች የእስላምን ትርጉምና መልዕክት ግልጽና ቀላል በሆነ መንገድ የሚያስረዳ የመማሪያ መጽሐፍ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ። በተጨማሪም አንባቢያን የሚጠ

ቀሙበትና ሌሎችን የሚጠቅሙበት እንዲያደርግልኝ ሀያሉን አሏህ (ሱ.ወ) እለምነዋለሁ።

---

ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር

አዲስ አበባ

1982

# ምዕራፍ አንድ

## እስላም ምንድነው?

በዓለም ላይ የነበረውም ሆነ ያለው እያንዳንዱ ሃይማኖት ስያሜውን የወረሰው ከመሥራቹ ስም ነው፤ አሊያም ሃይማኖቱ ከተጀመረበት ማህበረሰብና አገር ነው። ለምሣሌ ያህል፣ ክርስትና ከነቢዩ ስም ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ ነው። ቡድሂዝም ከመሥራቹ ከጉተማ ቡድሃ ስም የተወረሰ ነው። ዞሮስትያኒዝም /የፓርሺያ ሃይማኖት/ ከመሥራቹ ከዞሮስተር በኋላ የተሰየመ ነው። የአይሁድ ሃይማኖት /አይሁዳዊነት/ ደግሞ በመካከሉ ከተጀመረበትና አይ ሁድ ከተባለ ነገድ የተገኘ ስያሜ ነው። የተቀሩት ሃይማኖቶችም እንደዚሁ ናቸው። እስላም ግን ከዚህ የተለየ ነው። እስላም ከማንም የተለየ ግለሰብ ወይም ሕዝብ ጋር እንዲህ ያለ ተዛምዶ የሌለው በመሆኑ ልዩ መለያ አለው። ያንድ የተለየ ግለሰብ ሕዝብ ወይም ሀገር ንብረት አይደለም። በዚህም ምክንያት እስላም የሚለው ቃል እንደዚህ ያለ ተዛምዶን አያመለክትም። እስላም የማንም ሰው ጭንቅላት ውጤት ወይም ያንድ የተለየ ሕዝብ ግኝትም አይ ደለም። ዓላማው በሰው ልጅ ልቦና ውስጥ የእስላምን ይዘትና ባህሪ የተካኑ ያለፉ ያሉና የሚመጡ ሙስሊሞች ሁሉ ነው።

## እስላም የሚለው ቃል:- የቃሉ ምንነት:-

የቋንቋ መዝገበ ቃላትን ብናገላብጥ እስላም የሚለው ቃል ትርጉሙ፤ «ያለ ተቃውሞ ለአዛዥ ትእዛዝና እገዳ መገዛትና መመራት» መሆኑን እንረዳለን። ሃይማኖታችን እስላም ተብሎ

የተሰየመውም ለአላህ መታዘዝና ያለተቃውሞ ለርሱ መገዛት በመሆኑ ነው።

እስላም የሚለው ቃል የባህሪ መጠሪያ ነውና በዚህ ባህሪ የተዋበ ማንኛውም ሰው፣ የማንኛውም ዘር፣ የማንኛውም ማህበረሰብ፣ የማንኛውም አገር ወይም ጐሣ አባል ቢሆንም ሙስሊም ነው።ቁርአን በሚናገረው መሠረት በማንኛውም ዘመንና በሁሉም ሕዝቦች ዘንድ በዚህ ባህሪ የተካኑ ደጋግና አማኝ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ሙስሊሞች ነበሩ፤ ወደፊትም የሚመጡትና አሁን ያሉትም ይህን ባህሪ እስከተላበሱ ድረስ ሙስሊሞች ናቸው።

## የእስላም ምንነት:-

በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር ላንድ ለተወሰነ ደንብና ለተለየ ሕግ የሚገዛ ነው። ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለተቀናበረ ሕግ የተገሩ ናቸው። ቅንጣት ያህል ከዚህ ሊንቃነቁና ሊያፈነግጡ አይችሉም። መሬት በዛቢያዋ ዙሪያ ትዞራለች። ከተወሰነላት ጊዜ፣ ንቅናቄና መንገድ ውጭ ፍንክች የለም። ውሃ፣ አየር፣ ብርሃን፣ ሙቀት ወ.ዘ.ተ. ሁሉም ለተለየ ሥርዓት የተገዙ ናቸው።

ግዑዝ አካላት፣ እጽዋትና እንስሳት ከተሰጣቸው ደንብ ውጭ ማደግ፣ መቀነስ፣ መኖርና መሞት አይችሉም። አስተውለን ሁኔታውን ስንመለከት ሰው ራሱ ለአላህ ሕግጋት በተሟላ ሁኔታ የሚገዛ መሆኑን እንረዳለን። የሚተነፍሰው፣ የውሃ፣ የምግብ፣ የብርሃንና የሙቀት ፍላጐት የሚሰማው፤ የሕይወቱ አቀናባሪ በሆነው በአላህ ሕግ መሠረት ብቻ ነው። የሰው ልጅ የልብ ትርታ፣ ዑደተደሙና አተነፋፈሱ በዚሁ ሕግ የሚመሩ ናቸው። እንደ ጭንቅላቱ፣ ጨጓራው፣ ሳንባው፣ ጅማቶቹ፣ ጡንቻዎቹ፣ እጆ

ቹና እግሮቹ፣ ምላሱና ዓይኖቹ፣ አፍንጫውና ጆሮው ወዘተ ያሉ አካላቱ በሙሉ በዚሁ ይመራሉ። እነዚህ አካላት የሚያከናው ኗቸው ተግባሮቹ ሁሉ አላህ የወሰነላቸውን ብቻ ሲሆን የሚፈ ጽሙትም በተደነገገላቸው መንገድ ብቻ ነው።

ጠፈር ውስጥ ካለው ግዙፍ ኮከብ አንሥቶ እስከ አነስተኛዋ የመሬት ብናኝ ድረስ ያለው በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ የሚገኝ ነገር ሁሉ የሚገዛለትና የሚንበረከክለት አጠቃላይ ሕግ፡ ቻይ የሆነው ሃያል ገዥ ያኖረው ሕግ ነው። በምድርና በሰማይ ያለው ሁሉ በዚህ ሕግ የሚመራ በመሆኑ ዓለም ሁሉ ይህን ሕግ ለደነገገው ኃያል ገዥ ታዛዥና የትእዛዙም ተከታይ ነው። ከዚህ አመለካከት ስንነሳም እስላም የፍጥረታት ሁሉ ሃይማኖት መሆኑ ግልጽ ይሆ ናል። ይኸውም ቀደም ሲል እንደተረዳነው ሁሉ እስላም ማለት የአዛዡን ትእዛዝና እገዳ ያለተቃውሞ መቀበልና መገዛት ማለት ስለሆነ ነው። ጸሐይ፣ ጨረቃና መሬትም «ሙስሊሞች» /ተመ ሪዎች/ ናቸው። አየር፣ ውሃ፣ ብርሃን፣ ጨለማና ሙቀትም «ሙስሊሞች» /ተመሪዎች/ ናቸው። ጌታውን የማያውቅ ሕል ውናውን የሚያስተባብልና ጉልህ ምልክቶቹን የሚክድ ወይም እርሱን ትቶ ሌላ አምላክ የሚገዛ፣ ከርሱ ጋርም ባዕድ አማልክት የሚያመልክ ሰው እንኳ ከተፈጠረበት ተፈጥሮው አኳያ «ሙስሊም» /ተመሪ/ ነው። ይህም ለልደቱ፣ ለሕይወቱና ለሞቱ አላህ ከደነገገው ሕግ ውጭ የማይወለድ በሕይወት የማይኖርና የማይሞት በመሆኑ ነው። የሥራ አካላቱ ቢሆኑ እንደዚሁ ከዚሁ መለኮታዊ ሕግ ውጭ የማይታነጹ፣ የማያድጉና የማይንቀሳቀሱ ስለሆነ ከእስልምና በስተቀር ሌላ እምነት የላቸውም። ይልቁንም የማጋራትና የመካዳት ሃሣቦችን ባለማወቅና በጅልነቱ የሚገልጸው ምላሱ ራሱ ከእስልምና በስተቀር ለሌላ የማይገዛ መሆኑም ሌላው ሐቅ ነው። ከአንድ አላህ በስተቀር ለሌላ እንዲያጐነብስ የሚያስገድደው ራሱም እንደዚሁ በተፈጥሮ በታነጸበት ግፊት

ለእስላም ሃይማኖት እንጂ ለሌላ አይገዛም።ባለማወቅና በጅልነቱ ከአላህ በስተቀር ሌሎችን በመውደድና በማክበር የተገነባው ልቡም በተፈጥሮውና በባህሪው «ሙስሊም» /ተመሪ/ ነው። ሁሉም በአላህ ይገዛል፤ በሕጐቹ ይመራል።

ይህን ከተገነዘብን ነባራዊውን ሁኔታ ደግሞ እስኪ በሌላ አመለካከት እናጢን:- የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ ሁለት ጐኖች አሉት።አንደኛው ለተፈጥሮ ሕግ ተገዥና እሱን በመከተል ላይ የታነጸ ነው።

ሌላው ደግሞ አእምሮ የተሰጠው በመሆኑ የመረዳት፣ የማ ስተዋልና የርዕዮት ብቃት /ኃይል/ ያለው ነው። በዚህም አንዱን ነገር ይቀበላል፤ ሌላውን ያስተባብላል። አንዱን መንገድ ይወ ዳል፤ ሌላውን ይጠላል። ለተለያዩ የሕይወት ፈርጆች ከገዛ ራሱ መቆጣጠሪያ /መመዘኛ/ ያኖራል። ወይም ሌሎች ያኖሩትን የኑሮ ሥርዓት ይቀበላል። የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ላይ ያልተወሰነና በገደብ ያልተከለለ የማሰብ ነጻነት፣ በርዕዮትና በተግባር የመምረጥ ነፃነት ተሰጥቶታል።

እነዚህ ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች በየፊናቸው በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ይኖራሉ። ከመጀመሪያው አንፃር በእስልምና ላይ የተፈጠረና እሱን ለመከተል በተፈጥሮው የተመቻቸ ሙስሊም ነው። ቀደም ሲል እንደተረዳነው በዚህ በኩል የሰው ልጅ ያለው ሚና በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያሉት ሌሎች ፍጥረታት ያላቸው ሚና ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሙስሊም ለመሆንና ላለመሆን ምርጫው የራሱ ነው። ይህ የምርጫ ነፃነትም ሰው በሁለት ዓይነት ይከፈላል። አንደኛው ዓይነት ፈጣሪውን የሚያውቅ፣ ጌታው ገዥውና መሪው መሆኑን የሚያምን፤ ከፍላጐቱና ከምርጫው ውጭ ባለው ሕይወቱ

ተፈጥሮያዊ ሕጉን እንደሚከተል ሁሉ በፍላጐቱና በገዛ ምርጫው በሚመራው ሕይወቱ ውስጥ ሸሪዓዊ /ድንጋጌያዊ/ ሕጉን የሚከተል ሰው ነው። ይህ ዓይነቱ ሰው እስልምናው የተሟላ ምሉእ የሆነ ሙስሊም ነው።በዚህ ሁኔታ ላይ ሕይወቱ እንዳለ ራሱ እስላም ሆኗልና። ቀደም ሲል ሳይታወቀው ለሕጉ ይታዘዝና ይገዛ ለነበረው ኃይል በፍላጐቱና በውዴታው እጅ ሰጥቷል። ቀደም ሲል ሳይፈልግና ሳያስብ ይታዘዘው ለነበረው ጌታው አሁን ፈልጐና ሆን ብሎ አሰቦ ታዛዥ ሆኗል። የማወቅና የመማር ኃይል የለገሰውን ፈጣሪውን ስላወቀም ዕውቀቱ እውነተኛ ሆኗል። በግን ዛቤና ነገሮችን በማስተዋል ተሰጥኦ ካነፀው አላህ በስተቀር ሌላውን ላለመገዛት ወስኖ አእምሮውን ስላሠራውም አእምሮው በስኗል፤ አመለካከቱም ትክክለኛ ሆኗል። የመናገርና አንደበትን የመጠቀም ኃይል ከለገሰው ከሃያሉ አላህ በስተቀር ለሌላ ጌትነትን የማያረጋግጥ በመሆኑም አንደበቱ ርቱዕ፣ እውነተኛና ሐቅ ተናጋሪ ሆኗል። የመምረጥ መብት ባለው ጉዳይም ለአላህ ሕግ የሚመራ በመሆኑም ሕይወቱ በሙሉ ከእውነት በስተቀር ሌላ ነገር የለበትም። ፍጥረታት በሙሉ የሚገዙበትን ትእዛዞች የሚቀበሉትንና በሕግጋቱ የሚመሩትን ጥበበኛውንና በጣም አዋቂውን አላህ ብቻ እንጂ ሌላ ስለማያመልክም በርሱና በተቀሩት ፍጥረታት ሁሉ መካከል የመተዋወቅና የመግባባት ገመድ ተዘርግቷል። አሁን እርሱ የአላህ ተተኪ /ተጠሪ/ ነው። ማለትም በምድር ላይ ተጠሪው እሱ ነው። በዓለም ላይ ያለው ማንኛውም ነገር የርሱ ነው፤ እርሱ ደግሞ የአላህ ነው።

## የክህደት /ኩፍር/ ምንነት:-

በአንፃሩ ደግሞ ሙስሊም መሆኑ ሳይሰማውና ሳይታወቀው ሙስሊም ሆኖ የተወለደና ሙስሊም ሆኖ እድሜውን በሙሉ

የኖረ፤ ሆኖም ማን እንደፈጠረው ለማወቅ የማስተዋል ችሎታውንና የማወቅ ሕሊናውን በብቃት ያልተጠቀመ ሌላ ሰው ይገኛል። ፈጣሪውን ለማወቅ የተለገሰውን አእምሮ ባለማሠራቱ ሕልውናውን ይከዳል። ለርሱ መገዛት ይኮራል። በሕይወቱ ውስጥ የመወሰንና የመምረጥ መብቱ የራሱ በሆኑት ጉዳዮች በፈጣሪው ሕግ /ሸሪዓ/ መመራቱን እምቢ ይላል፤ ወይም ከአላህ ጋር ባዕድ አማልክትን ያሻርካል። የአላህን አንድነት በሚያረጋግጡ ምልከቶችን አላምንም ይላል። ይህ ነው እንግዲህ ከሃዲ /አስተባባይ/ የሚባለው። «ኩፍር» የሚለው የዐረብኛ ቃል ትርጉሙ «መሸፈን፣ መሸሸግና መደበቅ» ማለት ነው። ከዚህ በመነሣትም እንደዚህ ያለው ሰው ተፈጥሮውን በማይምነትና በጅልነት ሸፋን ስለጋረደው «ካፊር» ይባላል። በእስላም/በተመሪነት/ ተፈጥሮ የተወለደ መሆኑን፤ እያንዳንድ የአካሉ ክፍል በእስላም /ተመሪነት/ ተፈጥሮ ብቻ የሚሠራ መሆኑን እንዲሁም እሱን የከበቡት ዓለማት በሙሉ በእስላም ሕግጋት ብቻ የሚመሩ መሆናቸውን አውቀናል። እሱ ግን በማይምነትና በጅልነት መጋረጃ ተሸፍኖ የዓለምና የገዛ ራሱ ተፈጥሮ ተሰውሮበት የማሰብ ችሎታውና የማስተዋል ብቃቱ የራሱን ተፈጥሮ ተፃሮበት እንመለከታለን። በመሆኑም የሚያስበው ተፈጥሮውን የሚጻረር ነገር ብቻ ነው። የሚፈጸመው ተግባርም ተፈጥሮውን የሚቃወም ነገር ብቻ ነው።

አንባቢ ራሱ ካፊር ሰው የተዘፈቀበትን ግልጽ ጥመትና የከፋ ስህተት አሁን መገመት ይችላል።

## የኩፍር ጐጅነትና መጥፎ ውጤት:-

ከሃዲነት /ኩፍርነት/ ማይምነት ነው። ይልቁንም እውነተኛ ማይምነት ማለት ኩፍርነት ነው። ጌታውን ከማያውቅ ሰው ማይ

ምነት የበለጠና የባሰ ምን ማይምነት አለ? ...የዚሁ ግዙፍ ዩኒቨርስ ፋብሪካ ሌት ተቀን ሥራውን ሲያከናውን እየተመለከተ እሱ ግን የፈጠረውንና በሥራው ላይ እንዲጸና ያደረገውን አያውቅም። ከሰልን፣ ሐይድሮጂንን፣ ኦክስጂንን፣ አዙትን፣ ሶዲየምን፣ ካልሺ የምንና ሌሎችንም ሕይወትና አእምሮ የሌላቸውን ንጥረ ነገሮች በማዋሃድ ሰውን የመሰለ ታላቅና ከባድ ፍጥረት ማን አስገኘ? በተፈጥሮ የተለያዩ ገጽታዎች ውስጥ አቻ በሌለው ሁኔታ የሚ ታየውን ረቂቅነትና ውበት በምሕንድስና፣ በማቲማቲክስ፣ በኬ ሚስትሪና በሌሎችም ሳይንሶች ውስጥ እያስተዋለ ሀያሉን፣ ጥበበ ኛውንና አዋቂውን ፈጣሪ ለማወቅ አእምሮው የማይመራው መሆኑ አያስገርምም? ትንሽ አስቡ እስኪ ከዕውቀት መርህ እንኳ የተዛ ነፈው ይህ ሰው የትክክለኛ ዕውቀት በር ሊከፈትለት ይችላልን? በመሠረቱ በማይምነት ጨለማ ውስጥ ነውና የፈለገውን ያህል ቢያስብና ቢመራመር በማንኛውም የኑሮ መስክ ውስጥ ለእው ነተኛው ዕውቀት ወደሚያደርሰው ቀጥተኛ መንገድ ሊመራ አይች ልም። በመጨረሻ የሚገጥመውም ይኸው ብቻ ነው።

ኩፍር /ከሃዲነት/ ግፍ ነው። ከግፍም ሁሉ የበለጠና የከፋ ግፍ ኩፍር ነው። ይኸውም ግፍ ማለት አንድን ነገር ያለ ተገቢ ቦታው በማዋል ከተፈጥሮው ጋር በማይስማማ መንገድ በግድ መጠቀም ማለት በመሆኑ ነው። በሰማያትና በምድር ያሉት ነገሮች ሁሉ ለአላህ ትእዛዝ ተገዥ መሆናቸውንና በእስላም /መመራት/ ባህሪ የተፈጠሩ መሆናቸውን አውቀናል። ሰውና የሰራ አካላቱ በመላ የተፈጠሩት በዚሁ ተፈጥሮ ነው። እርግጥ ነው የሰው ልጅ በነዚህ አካላቱ ላይ የማዘዝ ከፊል መብት በአላህ የተሰጠው መሆኑ ጥርጥር ባይኖርም የአካላቱ ተፈጥሮ የሚወሰነው ግን አላህ በሚ ወደው መሠረት ብቻ መብቱን እንዲጠቀም ነው። አላህን የሚክድ ሰው የሰውነቱን አካላት የሚጠቀመው ከተፈጥሮአቸው ጋር በማይ ጣጣም መንገድ ነው።ልቡ ከአላህ በስተቀር ያሉትን አማልክት

በማክበር፣ በማፍቀርና በመፍራት ጨለማ የተመላ ነው። ልቡ የተፈጠረበት ባህሪ ግን የሁሉም መጠጊያ የሆነውን አላህን ብቻ በማክበር በማፍቀርና በመፍራት ብርሃን እንዲሞላ ነበር የሚጠ ይቀው። እሱ ግን በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያሉትን ነገሮችና በእጅ ውስጥ ያሉትን የተቀሩትን የአካለን ክፍሎች በሙሉ የሃያሉን አላህ ውዴታ በሚጻረር ሁኔታ ይጠቀምባቸዋል። እነዚህ የአካሉ ክፍሎ ችና የተቀሩት ነገሮች የተፈጠሩበት ባህሪ ግን በጌታ ሕግ መሠረት ብቻ እንጂ እንዳይጠቀምበት ተወስኖበታል። በፈጠራችሁ እስኪ ንገሩኝ... በዚህ ዓለም ላይ ዕድሜውን በሙሉ ሁሉንም ነገር ራሱንም እንኳ ሣያስቀር በመበደል ከሚያሳልፍ ሰው የበለጠ ግፈኛ ማነው?!

ኩፍር ግፍ ብቻ ሣይሆን ዕብሪት፣ ወሰን አላፊነት፣ ማስተ ባበልና መፈርጠጥም ነው። የሰው ልጅ ያሉት ነገሮች ሁሉ ንብረቱ ናቸው ወይ? አእምሮውንና ጭንቅላቱን ማን ፈጠረ? እሱ ራሱ ነው ወይስ ሃያሉ አላህ ነው? ልቡንና ምላሱን፣ ዓይንና ጆሮውን፣ እግርና እጆቹን፣ የተቀሩትንም አካላቱን የፈጠረው ማነው? እሱ ራሱ ነው ወይስ ሃያሉ አላህ ነው? የነዚህን ነገሮች አፈጣጠር ያሣመረ፣ እንዲጠቀምባቸውና እንዲረዳባቸው ያስቻለው ማነው? እሱ ራሱ ነው ወይስ አላህ /ሱ.ወ/ ነው?

ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስግልጽና ቀጥተኛ ነው። እነዚህ ነገሮች በሙሉ የአላህ ናቸው፤የፈጠራቸውና ያሳመራቸ ውም እሱው ብቻ ነው፤ ንብረትነታቸውም የአላህ ነው፤ ለሰው ልጅ መጠቀሚያ እንዲሆኑ የለገሳቸውም ሃያሉ አላህ ነው። ይህ ስለ መሆኑ አያጠያይቅም። ሓቁ ይህ ሆኖ ሳለ (ያለ ጥርጥርም ይኸው ነውና) አእምሮውን የአላህን ውዴታ ለሚጻረር አስተሳሰብ ከሚጠቀም፣ ልቡን የአላህን ቁጣ በሚያስከትሉ ሃሣቦች ከሚ ሞላ፤ ምላሱን፤ ዓይኖቹን፤ እጆቹንና እግሮቹን የአላህን ሕግጋትና

ትእዛዞች የሚጻረር ነገር እንዲሰሩ ከሚያስገድድ ሰው ይበልጥ የበደለ፣ ጥመትና ግፍን አራማጅ የሚሆን ማን አለ? በጌታው ቀለብ አድጐ የሚገባውን ግዴታ ያላሟላ አገልጋይ ላይ ከሃዲነት እንፈ ርዳለን፤ በጁ ያለውን ሥልጣን የመንግሥቱን ጥቅም በሚጎዳ መንገድ የሚጠቀመውን ሠራተኛ በአፈንጋጭነትና በመንግሥት ላይ በማመጽ እንወነጅላለን። የወዳጅን ውለታ የተዘናጋውን ሰውም በውለታቢስነት እንመድባለን። ..ለመሆኑ የሰው ከሃዲነት፣ አመጸኛነትና የሌላውን ሰው ውለታ ዘንጊነት ምንድነው? ...ይህ ሰው ለሌላው ሰው የሚቸረውን ሲሣይ ከዩት አመጣ? የሥልጣንና የትእዛዝ ኃይል የሰጠው ሃያሉ አላህ ብቻ አይደለም ወይ? ... ሰው መሰሉ ለሆነ ሰው በጐ ውሎለት መመጻደቅ እንዴት ይችላል?... ይህን ያስቻለው ሃያሉ አላህ ብቻ አይደለም ወይ? በዚህ ዓለም ላይ በሰው ላይ ያለው ትልቁ ኃላፊነት ለወላጆቹ መፈጸም ያለበት ግዴታ ነው። ለመሆኑ በወላጆች ልብ ውስጥ የልጆችን ፍቅርና ርህራሄ ያደረገ ማነው? እናት በችግር አር ግዛው፣ በችግር ለወለደችው ሕፃን ርህሩህ እንድትሆን ያደረጋት ማነው? ...በደስታና በዕርጋታ የግንባሩን ላብ አንጠፍጥፎ ያፈራ ውን ሀብት ለቁራጭ ሥጋ (ለጽንሱ) እንዲያወጣ፤ ከተወለደ በኋላም ለማሣደግና ለማስተማር ብዙ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ደስታ ውን መስዋዕት እንዲያደርግ ማን ነገረው?

በሉ እስቲ ንገሩኝ! ... በአላህ ከማያምነው ሰው ክህደት፣ አምላክነቱንና ጌታነቱን መቀበል አሻፈረኝ ብሎ ለርሱ ከመገዛትና ትእዛዞቹን ከመፈጸም ካፈነገጠ ሰው ክህደት ይበልጥ አስከፊ የሆነ ክህደት አለ ወይ?.. ከርሱ አመጽ የከፋ፥ አመጽ ከሆነ ክህደት የከፋ ክህደት ይገኛል ወይ? ከርሱ ማስተባበል የበለጠ ማስተባበል አለ ወይ?

ሰው አላህን ቢክድ ምንም ዓይነት ጉዳት አላህ ላይ ያደርሳል ብለህ አትገምት! ሃያሉ አላህ የሰው ልጅ ባደረጋቸው ተከታታይና አስቸጋሪ ጥረቶች ሁሉ ላይና ለዚሁ ዓላማ በተጠቀማቸው ግዙፍ መሣሪያዎች ሁሉ ላይ ወሰን የለሽ ታላቅ ባለንብረት ነውና። ጥራትና ልዕልና ይግባውና መሬት፣ ጸሐይ፣ ማርስና ሌሎቹም ቁጥር የሌላቸው ትናንሽ ኳሶች መሰለው በግዛቱ ውስጥ የተበታተኑ ግዙፍ ከዋክብት ለርሱ ይሰግዳሉ። የሰማያትና የምድር ሀብቶችም ያለ ምንም ተጋሪና ያለአንዳች ተቀናቃኝ የርሱው ናቸው። ሁሉም ከርሱ ረድኤት የሚጠብቁ ሲሆኑ እርሱ ግን ከማንም እርዳታ የማይጠብቅ፣ ራሱ የተብቃቃ ቸርና ለጋሽ ጌታ ነው። ታዲያ ይህ አቅመቢስና ደካማ ፍጡር ‹ሰው› አላህን ቢክድ ከየት መጥቶ ነው አላህን ሊጐዳ የሚችለው? ካመነም ለራሱ ነው። ከካደም በራሱ ላይ ነው።

ከክህደትና ከአመጸኛነት ውጤቶች አንዱ የከዳውና ያመፀው ሰው ላይ ክስረትና ውድቀት ተወስኖበት በፍጹም ወደ ትክክለኛው የዕውቀት ጐዳና የማይመራ መሆኑ ነው። ጌታውን የማያሳውቅ ዕውቀት ከየት መጥቶ ሌላውን በትክክል ሊያሣውቅ ይችላል? አእምሮውም በአጠቃላይ የሕይወት ጉዳዮቹ ላይ የተወላገደ መንገድን የግድ ይከተላል። ፈጣሪውን ለማወቅ ያልተመራ አእምሮ ከየት መጥቶ ሌላውን ትክክለኛ የሆነ ዕውቀት ማወቅ ይችላል? እንደዚሁም ግራ ተጋብቶ በሚሰራባቸው ጉዳዮች ሁሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውድቀት ይደርስታል። ሥነ ምግባሩም፣ ሥልጣኔውም፣ ማህበራዊ ኑሮውም፣ አስተዳደሩም፣ ፖለቲካውም ብልሽትሽት ይልበትና በምድር ላይ ደም በማፍሰስ፣ የሌሎቹን መብት በመርገጥ፣ ግፍና ጭቆናን ያራምዳል። በዚህ ዓይነትም በብልሹ አስተሳሰቦቹና በውጉዝ ተግባሮቹ ምክንያት በራሱ ላይ ኑሮውን ያደፈርሳል። ይህ እንግዲህ በዚች ዓለም ላይ የሚገጥመው አበሳ ሲሆን፣ በወዲያኛው ዓለም ሕይወቱ ደግሞ በዚህ ዓለም ሕይወቱ

ግፍ የፈጸመባቸው ሁሉ ይነሱበትና ይመሰክሩበታል።.. በአስ ተካካዩ የአላህ ችሎት ፊትም አእምሮው፣ ልቡ፣ ዓይኖቹና ጆሮዎቹ፣ እጆቹና እግሮቹ፣ እንዲሁም የተቀሩት አካላቱ በሙሉ «ጌታችን ሆይ! ይህ ግፈኛ በቅርቢቷ ዓለም ሕይወቱ ባንተ ላይ ያመጸ፣ አንተን ከማውሳት ያፈነገጠ፣ ትዕዛዝህን በመጣስ በግድና በሃይል የተጠቀመብን ነው። » በማለት ይከሱታል። በዚህ የፍትህ ችሎት ላይም የአላህን ትእዛዝ በመጣስ የሄደባትና የኖረባት መሬት፣ እርም በሆኑ መንገዶች የሰበሰበውና አላህ በከለከለው ተግባር ላይ ያዋለው ገንዘብ፣ የግፍና የዕብሪት ድርጊት የፈጸ መባቸው ነገሮች ሁሉ፣ ለግፍና ለጭቆናው የተገለገለባቸው መሣሪ ያዎችና ሃይሎች በሙሉ ይከሱታል። አላህ /ሱ.ወ/ ከርሱ በላይ ፍርድ አስተካካይ የለምና በዚህ ዕብሪት የተሞላበት ግፍ አንፃር ለነዚህ ከሳሾቹ ሁሉ ተገቢውን ብይን በመስጠት የውርደትና የቅሌት ሥቃይ ለሠራው ግፍና አመጹ መቀጫ ያቀምሰዋል።

# የእስላም ፀጋ:-

ከላይ የተመለከትነው የክህደት ጉዳኝነትና መጨረሻው ነበር። አሁን ደግሞ እስላምን ብንመርጥና ፈለጉን መከተል ብንወድ ምን ጥቅም እንደሚያስገኝልን እንመለከታለን።

ካለፈው ማብራሪያ ይህ ዩኒቨርስ የአላህን አምላክነትና ጌትነት የሚያመለክቱ በየፈርጁ የተሰራጩ ምልክቶችና ታምሮች ያሉበት መሆኑን ተረድተናል። ይህ ለተሟላ ሥርዓትና ለቋሚ ሕግጋት ተገዝቶ በተቀነባበረ ሁኔታ ሲጓዝ የምናየው ግዙፍ የዩኒቨርስ ቤተሙከራ /ላብራቶሪ/ ፈጣሪውና አቀናባሪው፣ ታላቅ፣ ኃይልና ሥልጣን ያለው በሰማይም ሆነ በምድር ምንም ነገር ከቁጥጥሩ ሥር የማይወጣ ክቡር ገዥ መሆኑን ሁኔታው ይመሰክራል። እንደ

ዚሁም ሰውም እንደተቀሩት ፍጡራን ሁሉ በተፈጥሮው ለአላህ መታዘዝ እንዳለበት፣ ሳያስበውም በቀንና ሌሊት እንደሚታዘዘው የሰው ልጅ የተፈጥሮን ሕግ ከጣሰ በሕይወት መቆየት እንደ ማይችል አውቀናል።

አላህ /ሱ.ወ/ አንጻራዊ የሆነ የመምረጥ ነጻነት ለሰው ልጅ ሰጥቶታል። በግንዛቤና በማስተዋል ኃይሉ መልካሙንና መጥ ፎውን በመለየት ብቃቱ የፍጡራን ሁሉ የበላይ አድርጐታል። ሰው ዕውቀቱ፣ አእምሮው፣ የማስተዋል ኃይሉ፣ በዚህ ነፃነቱ ለተመከሮ የተጋለጠ ነው። ይህን ነፃነት እንዴትና በምን ላይ እንደሚጠቀም ዘወትር አላህ ይቆጣጠረዋል። በዚህ መፈተኛ ምክንያት ሰው አንድ የተወሰነ መንገድ እንዲከተል አልተገ ደደም። ቢገደድ ኖሮ የፈተናው ዓላማ ውድቅ በሆነ ነበር። ይህም ለመረዳት አንዳች ችግር የሌለበት ግልጽ ነገር ነው። በፈተና ወረቀት ላይ የተለያየና የታወቀ ውስን መልስ እንዳንጥበት የተገደ ድንበት ጥያቄ ከቀረበልን ፈተናው ምን ጥቅም ይሰጣል? ሐቁን ለመናገር የፈለግነውን መልስ ለመስጠት የተሟላ ነፃነት ካልተ ሰጠን በስተቀር ብቃታችን ሊታወቅ አይችልም። መልሳችን ትክክ ለኛ ከሆነ ፈተናውን አልፈን የዕድገትና የሙሉነት በር ለወደፊት ሕይወታችን ይከፈትልናል። መልሳችን ትክክለኛ ካልሆነ ግን ቅኑን የዕድገት በር ይዘጋብናል። በዚህ ዓይነትም አላህ ለሰው ልጅ ባዘጋጀለት ፈተናው ነፃነት ሰጥቶት በሕይወቱ ውስጥ የሚጓዝበትን የፈለገውን መንገድ ለራሱ እንዲመርጥ አድርጐታል።

የራሱን ተፈጥሮም ሆነ የዚህን ዩኒቨርስ ተፈጥሮ የማያውቅ፣ ፈጣሪውንና ባህሪያቱን የማያውቅና የጥመትና የግፍን መንገድ የሚመርጥ ሰው የተሰጠውን የፈለገውን የመምረጥ ነፃነት በአግባቡ አይጠቀምም። በዕውቀቱ፣ በአእምሮው፣ ጥሩና መጥፎን በመ ለየት ኃይሉና በኃላፊነት ስሜቱ በተሰጠው ፈተና ግልጽ ውድቀት

ደርሶበታል። በሁሉም አንፃር ውዳቂ ሰው መሆኑን በራሱ ላይ መስከሯል። መጨረሻውም ከላይ የተጠቀሰው መሆን ይገባዋል።

በዚህ ፈተና የቀናው ደግሞ አእምሮውን አሠርቶ በተሰጠው ዕውቀትና ግንዛቤ በትክክል የተጠቀመና ፈጣሪውን አውቆ ያለ ምንም ማስገደድ በርሱ ያመነ ሰው ነው። ይህ ሰው ጥሩውንና መጥፎውን በመለየቱ በኩልም አልተሳሳተም። ካስፈለገው ወደ መጥፎው ነገር ከማዘንበል የሚያግደው ምንም ነገር ሣይኖር በነፃ ፍላጐቱ መልካሙን ነገር የመረጠ ሰው ነው። ተፈጥሮውን ተገ ንዝቦ፣ ጌታውን አውቆ የመታዘዝና ያለ መታዘዝ አማራጭ እያ ለው የፈጣሪውን ትእዛዝ የመረጠ ሰው ነው። በዚህ ፈተና ድል እንዲቀዳጅና ፍላጐቱን እንዲያገኝ ያበቃው ምንድነው? .. አእም ሮውን በሚገባ ስለተጠቀመበት፤ ዓይኑን፣ ጆሮውንና ጭንቅላቱን በጥሩ ሁኔታ ስለተገለገለባቸው ነው። በውስጣዊ ሕሊናው ትክ ክለኛ ቃላትንና ተግባራትን ብቻ ለመከተል በመወሰኑ ነው። በዚህም ፈጣሪውን ማወቁንና በቅን ታዛዥነቱም በተግባር ያደ ረለት መሆኑን ያረጋገጠ ሰው ነው።

እንደዚህ ባሉ ታላላቅ ባህሪያት የተካነ ሰው በዛሬው አላፊ ሕይወትም ሆነ በነገው ቀሪ ዓለም ድልን ቢቀዳጅ ምን ያስገርማል? በዕውቀትም ሆነ በተግባር መስክ ትክክለኛና ቀጥተኛ የሆነ ጐዳና ብቻ ነው የሚመርጠው። ፈጣሪውን ያወቀና ባህሪያቱን የተረዳ ሰው የዕውቀትን መነሻና መድረሻ ያውቃልና። የመጀመሪያ እርም ጃውን የተራመደው በዕውቀትና በግንዛቤ ስለሆነ እንዲህ ያለው ሰው በሕይወት ጉዞው ላይ አሳሳችና ጠማማ በሆነ መንገድ ይዞ ሊደናገር አይችልም። ለመድረስ ያሰበበት ግቡም አይሰ ወርበትም።

በፍልስፍና ረገድም የፍጥረተ ዓለም ምስጢሮችን የሚያስስ፣ የተፈጥሮን ድንቅ ተአምር የሚመራመር፣ የዩኒቨርሱን ጥልቅ ምስጢሮች የሚያጠና እንጂ እንደ ኢአማኝ ሣይንቲስቶች በጥር ጣሬ ጨለማ ውስጥ የማይዋዥቅ፣ ተግባራዊ ሳይንሶችን፣ የተፈ ጥሮን ሕግጋት ለማወቅና ተፈጥሮን ለሰው ልጆች ጥቅም እንዲገራ ለማድረግ በዚህች ዓለምና በገዛ ራሱ ውስጥ ሃያሉ አላህ ያኖረውን ኃይል ለመረዳትና በምድርና በሰማያት ባሉት ሀብቶች የተሻለ መገልገል የሚቻልበትን መንገድ የሚጠቁም ሰው ነው። ይህን ሁሉ ሲያደርግና የማስተዋልና የመገንዘብ ብቃቱን በተግባር ሲጠ ቀምበት ለሃያሉ አላህ ያለው ቅን ታዛዥነትና ነገ ከፊቱ የመቅረብ ፍራቻው እነዚህን ዕውቀቶች ያለ አግባቡ እንዳይጠቀም በያን ዳንዱ እርምጃው ይከለክሉታል። በዚህ የሕይወት ጉዞው እያን ዳንዱ ደረጃ ላይ እነዚህ ነገሮች የግል ንብረቱ እንደሆኑ በፍጹም አይገምትም። ተፈጥሮንም በቁጥጥሩ ሥር አድርጌያለሁ ብሎም ጭራሽ አይኩራራም። ሙስሊም ሳይንቲስት በሳይንቡ መስክ በተራመደ ቁጥር፣ በጥበቡ በተራቀቀ መጠን፣ የተፈጥሮን ምስ ጢር ጠልቆ በተገነዘበ ቁጥር በአላህ ያለው እምነት ይጨምራል። አንድነቱንም ያረጋግጣል። በሰጠው ታላቅ ፀጋም ፈጣሪውን ያመሰግናል። ይህን ሁሉ የገራለት ለፍጡራኑ አገልጋይ እንዲሆን ስለመረጠው መሆኑን በመረዳት ለራሱና ለመላው የሰው ልጅ ጥቅም በሚያስገኝ ተግባር ላይ ይሰማራል። ይህም አላህ ለለገሰው ጸጋ እውነተኛው ተግባራዊ ምሥጋና ነው።

በታሪክ፡ በኢኮኖሚክስ፣ በፖለቲካ፣ በሕግ፣ ወዘተ ዕው ቀቶችም ሙስሊም ከኢአማኙ ወደ ኋላ አይቀርም። ቢሆንም በአመለካከታቸው ሁለቱም የተለያዩ ናቸው። ሙስሊሙ እነዚህን ዕውቀቶች የሚያጠናው ለቀና ዓላማና ለበጐ ምግባር ሲሆን ውጤቱና ግቡም መልካም ነው። በታሪክ ጥናቱ ስለቀድሞዎቹ ሕዝቦች ልምድ ይቀስማል። ለሕዝቦች መነሳትና መውደቅ እው

ነተኛው ምክንያት ምን እንደሆነ ይገነዘባል። ከባህላቸውና ከሥል ጣኔያቸው መካከል ከጠቃሚና መልካም ሥራዎችና ንግግሮች ትምህርት ይወስዳል። እነዚህን ሕዝቦች ለውድቀት ያደረሱትን ደካማና መጥፎ ጐኖች ነቅቶ ይጠነቀቃል።

በኢኮኖሚክስ ዕውቀት ደግሞ ሀብት ለማፍራትና ለማሰ ራጪት በአድልኦ ላይ የተመሠረተ ሣይሆን የምድሪቱን ነዋሪዎች ሁሉ የሚያካትትና የጋራ ጥቅም የሚያስገኝ ስልቶችን ያጠናል።

በፖለቲካ ዕውቀትም ዓላማው የሰላም፣ የጸጥታ፣ የፍትህ፣ የክብር መርሆዎች በዓለም ላይ እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል። ከሰው ጫንቃ ላይ አይወጣም። ሰዎችን አያዋርድም። ማንንም ግለሰብ ሆነ ቡድን የራሱ ተገዥ አያደርግም። ሥልጣን፣ የመን ግሥት መሣሪያዎችና ገዥነት የአላህ አደራ እንደመሆናቸው መጠን የአላህን ፍጡራን ደህንነት ለመጠበቅና ድል ለማቀዳጀት ማገልገል ይኖርባቸዋል ከሚል አመለካከት ይነሣል።

በሕግ ዕውቀት ረገድ ያለው አመለካከትም ቢሆን ለመላው የሰው ልጆች መብታቸውንና ግዴታቸውን ፍጹም ፍትህና ታማ ኝነት በተመላበት ሁኔታ የሚያረጋግጥ አላማ ይዞ ይነሳል። በምንም ዓይነት አንድም ሰውመጨቆን እንደሌለበት ያሳል።

እውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ ቁጥብነት፣ አላህን መፍራትና ሐቅን መከተል...እነዚህ ሁሉ የሙስሊሙ ሥነ ምግባር ጭማቂ ናቸው።በዚህች ዓለም ላይ የሚኖረው ሃያሉ አላህ የዚህ ዩኒቨርስ ጌታ መሆኑን፣ በዓለማት ላይ የሚገኙ ነገሮች በሙሉ የርሱ ንብረት መሆናቸውን፣ በርሱ ዘንድና በሌሎች ሰዎች ዘንድ ያለው ሁሉ ምንጩ ከአላህ ዘንድ መሆኑን፣ ራሱና አካላዊ ኃይሉ እንኳ ሣይቀር አንድም ነገር የርሱ የግል ንብረት አለመሆኑን፣ በእጁ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ አላህ እነርሱ ዘንድ ያስቀመጣቸው አደራዎች ስለሆኑ

ሃያሉ አላህ በሚወደውና በሚቀበለው መልክ ብቻ እንጂ በምንም ዓይነት በጥቅም ላይ ማዋል የማይፈቀድለት መሆኑን፣ ሃያሉ አላህ ያስቀመጠውን አደራ መልሶ የሚቀበለውና መምጣቱ ጥርጣሬ በሌለው በትንሣኤው ቀን የረቀቀ ምርመራ የሚያደርግበት መሆኑን በሚገባ ያውቃል።

ወደገዛ ራስ መለስ ብሎ ሕሊናውን ትክክለኛ ካልሆኑ ጥርጣሬዎች፣ አእምሮውን ከመጥፎ ሃሣቦች ስለሚያጸዳውና ዓይኑን ከተሳሳተ እይታ፣ጆሮውን ከመጥፎ ቃላት፣ አንደበቱን እውነትን የሚጻረር ነገር እንዳይናገር ስለሚጠብቅ፣ ሆዱን እርም /ሀራም/ ከሆነ ሲሣይ ከሚሞላ በረሃብ መሞትን ስለሚመርጥ የራሱ ወዳልሆነ ነገር እጁን በግፍ ስለማይዘረጋ፣ እግሩ መጥፎና ተገቢ ያልሆነአልባሌ ቦታ ስለማይረግጥ፣ ቢሰቀልና ገላው ቢቆራረጥ እንኳ ን ለውሸትና ትክክለኛ ላልሆነ ነገር ራሱን ዝቅ ስለማያደርግ፣ ምኞቱን ወይም ጉዳዩን በተንኮል፣ በግፍና በጭቆና መንገድ በፍጹም ስለማያስፈጽም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከሁሉም የበለጠ ለሱ ውድ ነገር ሀቅ፣ እውነትና ታማኝነት ናቸው። በርሱ አመለካከት ከሁሉም የከፋ መጥፎ ነገር ግፍ፣ ውሸት፣ ክህደት ሲሆኑ ራሱን ከጉዳት ለማዳን ወይም ለራሱ ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ግፍን ውሸትንና ክህደትን መደገፍ ወይም መምረጥ አይፈልግም።

እንዲህ ያለው ሰው ነው በዚህ ዓለም ላይም ድልን የሚቀዳጀው። አዎ! ከዚህ ዓይነቱ ሰው የበለጠ ኩሩ፣ ከርሱ ክብር፣ ከርሱ የተሻለ ደረጃና ምጥቀት ያለው በዚህች ዓለም ላይ አይገኝም። ራሱን ከአላህ በስተቀር ለሌላ ዝቅ የማያደርግ፣ እጁን ወደ አላህ ብቻ የሚዘረጋ ነውና ውርደትና ሃፍረት በየት በኩል ያግኘው?

ከአላህ በስተቀር ሌላ ስለማይፈራ ከርሱ በስተቀር በሌላ ተስፋውን ስለማይጥልም በዚህ ምድር ላይ ከርሱ የበለጠ ኃይለኛ፣ ደፋርና ጀግና የለም። እንዲህ ያለውን ሰው ምንም ኃይል ከሐቅ

ጉዳና አያዛንፈውም። የእምነት ሀብቱንም መግዛት የሚችል ማንም ቱጃር የለም።

ለዚህች ዓለም ስግብግብና ለጠፊ ፀጋዋ ጉጉ፣ ለስሜታዊ ዝንባሌው ተገዥ ስላልሆነም በዚህች ዓለም ላይ ከርሱ የበለጠ ሀብታምና ከርሱ የላቀ ባለጸጋ በፍጹም የለም። በሕጋዊ መንገድ በሚያደርገው ጥረቱ ባፈራው ነገር ብቻ ይረካል። እርም ወደሆነ ሀብት ዓይኑን አይሰቅልም። አላህ እርም ያደረገው ሀብት ካለበት ተሰባስቦ ያለገደብ ቢመጣለት እንኳ አንቋሾና አዋርዶ ፍጹም አልቀበልም ባይ ነው። ይህ ነው እንግዲህ የእርካታና የእርጋታ ሀብት! በዚህ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ ከዚህ ይበልጥ ውድ የሆነ ሀብት ከቶውኑ የለም።

በሰዎች ዘንድ ከርሱ ይበልጥ የሚወደድና ከሁሉም ይበልጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ማንም ሰው አይኖርም። ይኸውም ለያንዳንዱ ሰው የተሟላ መብቱን ስለሚያከብር፣ የማንንም መብት ጭራሽ የማይዳፈር፣ ለሰው ልጅ ቅን አሣቢና ማንንም ሰው የማያስከፋ፣ ለሰው ደህንነት ዘወትር ስለሚጥርና በሚያደርገው በጐ ተግባር ሁሉ ከማንም ምሥጋናም ሆነ ዋጋ የማይሻ ስለሆነ ነው።...ይህ ሁሉ የሰዎችን ልብ እንዲማርከና እያንዳንዱ ሰው እንዲወደው፣ እንዲያከብረውና ከፍተኛ ግምት እንዲሰጠው ያስገድዳል።

አደራቸውን በፍጹም የማይከዳ፣ ዘወትር ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት በእውነተኛነትና በመልካም ሁኔታ በመሆኑ፣ ቃል የገባላ ቸውንም ሁሉ ስለሚፈጽም ከርሱ ይበልጥ እምነት የሚጣልበትና ሰዎች የሚተማመኑበት ማንም ሰው በዚህ ዓለም ላይ የለም። አላህ እንደሚመለከተው እርግጠኛ በመሆኑ በዚህ ምድር ላይ ማንም ሰው ሊያየው በማይችልባቸው ሁኔታዎቹ እንኳ ቢሆን ከእው ነተኛነትና ከታማኝነት ፍንከች ማለት አይፈልግም። ስለዚህም

ሰዎች ለርሱ ያላቸው ፍቅር፣ በርሱ ላይ ያላቸው እምነት ወሰን የለሽ ነው።

አንድ ሙስሊም በዚህች ዓለም ላይ ሳለ ያለውን ሥነምግባር አጭር ታሪክ ካወቅን ሙስሊም በዚህች ዓለም ላይ ተዋራጅ፣ አቀርቃሪና ተሸናፊ ሆኖ በፍጹም የማይኖር መሆኑን እርግጠኛ እንሆናለን። የግዴታ በሕይወቱ ኩሩ፣ ጠንካራና ደፋር ሆኖ መኖር አለበት። እስልምና የሚያጐናጽፈውን ባህሪያት አንድም ምድራዊ ኃይል ሊያሸንፍ አይችልምና።

ይህ የአማኙ ሙስሊም ዓላማዊ ሕይወት ሲሆን በነገው የመጨረሻ ዓለም ሕይወቱ ደግሞ አላህ በውዴታው ምህረት ሰጥቶት በሥራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ውስጥ ያስገ ባዋል። በዚያ ውስጥም አደራውን በሚገባ ጠብቆ በመፈጸሙ፣ በመጀመሪያው ሕይወት የተሰጠውን ፈተና በማለፉ የሥራውን ዋጋ አላህ ነፍሱ የፈለገችውን ሁሉ ይሰጠዋል። ይህም አማኙ ሙስሊም በዚህች ምድራዊ ዓለምና በነገው ዘለዓለማዊ ዓለም የሚቀዳጀው ታላቅ ድል ነው።

ይህ ነው እስልምና– የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሃይማኖት! ላንድ የተለየ ሕዝብ ብቻ ያልተወሰነው። ላንድ ሀገር ብቻ ያልተከለለው። ላንድ ዘመን ብቻ በተለይ ያልታዘዘ ሃይማኖት። አላህን ያወቀ፣ ሕጉን የተከተለና በቀጥተኛ መንገዱ የተመራ ሰው ሁሉ በሁሉም ዘመን ወይም ሕዝብ ወይም አገር የኖረ ሰው ሁሉ ሃይማኖቱን እስላም ብሎ ሰየመም ወይም በራሱ ቋንቋ በሌላ ስም ጠራ የተመራበት ሃይማኖት እስላም ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## እምነትና ታዛዥነት

እስልምና በሃያሉ አላህ መታዘዝ ማለት መሆኑን፣ ለሕግጋቱና ለትእዛዛቱ መገዛት መሆኑን አውቀናል። ቀጥለን ማብራራት የምንሻው ደግሞ የሰው ልጅ የተወሰኑ መሠረታዊ ጥብጦችን ካላወቀና እውነተኛ እውቀት ካልቀሰመ በስተቀር አላህን ለመታዘዝ፣ ሕጉቹን ለመከተልና በመንገዱ ለመመራት የማይችል መሆኑን ነው።

በዚህ አኳያ ሃያሉ አላህ መኖሩን እርግጠኛ ሆኖ በልቡ አምኖ መቀበል የመጀመሪያ ደረጃ ግዴታችን ነው። መኖሩን በእርግጠኛነት አውቆ ያላመነ ሰው እንዴት አድርጐ ሊታዘዘውና ሕግጋቱን ሊከተል ይችላል?

እንደዚሁም የሃያሉን አላህ ባህሪያት ማወቅዎ ግዴታ ነው። አላህ አንድ መሆኑንና በአምላክነቱ አምሣያ የሌለው መሆኑን ያላወቀ ሰው ለባዕድ አማልክት ከማጎንበስና እነሱን ከመለመን እንደምን መታቀብ ይቻላል? በተመሣሣይ ሁኔታም አላህ ሰሚ፣ ዓዋቂና ተመልካች መሆኑን በእርግጠኝነት የማያውቅ ሰው ትእዛዙን ከመጣስና መመሪያዎቹን ከመተላለፍ ራሱን እንዴት ይቆጥባል? ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ነገር ቢኖር:- በቀጥተኛው የአላህ መንገድ ለመመራት በሃሣቡ፣ በተግባሮቹና በሥነ ምግባሮቹ መላበስ ያለበትን አስፈላጊ ባህሪያት፣ የሃያሉን አላህ ባህሪያት እስካላወቀና የተሟላ ትክክለኛ ዕውቀት እስካልኖረው ድረስ ሰው እንዴት መላበስ ይችላል? ይህ ዕውቀት እንዲሁ ዕውቀት መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም። ልቦናውን ከተሳሳቱ ጥርጣሬዎች ለመጠበቅና

ተግባሩም የተሳሳተ መንገድ እንዳይከተል በሚረዳው መልኩ ዕውቀቱ በልቡ ውስጥ ጠልቆ መግባት ይገባዋል።

በዚህች ምድራዊ ዓለም ሃያሉ አላህ በሚወደው መሠረት ሕይወትን ለመምራት የትኛው መንገድ ትክክለኛ እንደሆነ፣ አላህ የሚወደው ነገር ምን እንደሆነ አውቆ መምረጥ፣ የሚጠላውንም ለመራቅ የትኛው እንደሆነ አውቆ መምረጥ፣ የሚጠላውንም ለመራቅ የትኛው እንደሆነ አውቆ መተው መቻል የሰው ልጅ ግዴታ ይሆናል። ለዚህም ሲባል የሰው ልጅ የግዴታ የአላህን ሕግጋት ማወቅ፣ ሕግጋቶቹም ከአላህ ዘንድ የተላኩ መሆናቸውን መቀበል ይኖርበታል። አዎ የአላህን ህግጋት በሕይወቱ ውስጥ በተሟላ ሁኔታ የሚከተል ካልሆነ በስተቀር የአላህን ውዴታ እንደማይታደል ማወቅ አለበት። ታዲያ ይህን ሕግ በመሠረቱ የማያውቅ ከሆነ በኑሮ ውስጥ እንዴት ሊከተለው ይችላል? ይህን ሕግ ተግባራዊ ማድረጉ ባእርግጠኝነት ደረጃ ያልደረሰ ከሆነ ወይም በዓለም ላይ በትክክለኛነቱና በቀጥተኛነቱ እንዲህ ያለ ሌላ ሕግ ሊኖር ይችላል ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ይህን ሕግ በትክክል አዘውትሮ እንዴት ሊከተልስ ይችላል?

የሰው ልጅ አላህን ከመታዘዝ ይልቅ ትእዛዙን መጣስ ከመረጠና ቀጥተኛውን የአላህ መንገድ ካልተከተለ ወይም ትእዛ ዙን ዘወትር የሚያከብርና በሕይወቱ ውስጥ ሕግጋቱን የሚከተል ከሆነ በመጨረሻ ሊደርስበት የሚችለውን ውጤት የሚያውቅ መሆን አለበት።

ለዚህ ዓላማም ሲባል ከዚህች ዓለማዊ ሕይወት በኋላ ሌላ ዘለዓለማዊ ሕይወት– ትንሣኤ– መኖሩን፣ በትንሣኤው ቀን በሃያሉ ጌታ ፊት ቀርቦ በሥራው ዓይነት መልካም ከሠራ መልካም፣ መጥፎ ከሠራም መጥፎ ዋጋውን የሚቀበል መሆኑን በእርግጠኝነት ማወቅ ግዴታ ይሆናል። ለመጨረሻው ዓለም ሕይወት ዕውቀት

የሌለው ሰው ለአላህ መታዘዝም ሆነ ትእዛዙን መጣስ ለርሱ አንድ ነው። ምንም ልዩነት የለውም። ሁለቱ የሚያስከትሉትን የተለያዩ ውጤቶች ለይቶ ማየት አይችልም። አላህን የሚታዘዝና ትእዛዙን የሚጥስ ሰው ከሞት በኋላ የሚጠብቀው ውጤት ተመሣሣይ ይመስለዋል። እንዲህ ያለው ሰው በዚህች ዓለም ሕይወት ራሱን መጉዳት የማይፈራ እስከሆነ ድረስ ኃጢአት ከመፈጸም ራሱን አይቆጥብም ወይም አላህን ከልታዘዙና በትእዛዞቹም ራሱን በትእ ግሥት እስካልመራ ድረስ ምን ይጠበቅበታል?

በመጨረሻው ዓለም ሕይወትና በትንሣኤ ቀን ለፍርድ ሃያሉ አላህ ፊት የሚቀርብ መሆኑን በቁርጠኝነት የማያውቅ ሰው በአላህ ታዛዥነቱና ሕግጋቱን በመከተሉ ላይ ሊጸና አይችልም። ጥርጣሬና ማመንታት ካለ ሰው ባንድ ነገር ላይ ሊጸና አይችልም። በአንድ ነገር ላይ መጽናት የሚችለውና በታዛዥነቱ መሰንበት የሚችለው ለራሱ የሚጠቅም ነገር መሆኑን በተሟላ ሁኔታ ያረጋገጠ ሲሆን ነው። እንደዚሁም ካንድ ነገር ራሱን የሚያርቀው ያ ነገር ለራሱ ጐጂ መሆኑን በቁርጠኝነት የሚያውቅ ሲሆን ነው።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው አንድ መንገድ መርጠን ለመከተል ስንፈልግ የሚያስከትለውን ውጤትና የምንደርስበትን መድረሻ የግዴታ ማወቅ ያለብን መሆኑን ነው። ይህ ዕውቀታችንም እርግ ጠኝነትና ቁርጠኝነት ደረጃ ላይ የደረሰ አስተማማኝ ዕውቀት መሆን ይገባዋል።

## የእምነት ትርጉም :-

ከላይ እውነተኛና እርግጠኛ ዕውቀት ያልነው «እምነት» ነው። እምነት የሚለው ቃል ትርጉሙ ባጭሩ ይኸው ነው። የአላህን ተውሂድ /አንድነቱን/፣ እውነተኛ ባህሪያቱን፣ ሕግ

ጋቱንና በትንሣኤው ቀን ሰዎችን እንደየሥራቸው የሚከፍላቸው መሆኑን ያወቀና ከውስጣዊ ልቡናው ይህን ሁሉ በቁርጠኝነት አምኖ የተቀበለ እያንዳንዱ ሰው «አማኝ» /ሙእሚን/ ነው። ከእምነት ውጤቶች መካከል አንዱ የግለሰቡ ሙስሊም መሆን ማለትም ለአላህ ታዘዥና ለሕግጋቱ ተመሪ መሆን ማለት ነው።

አንድ ሰው አማኝ ካልሆነ በስተቀር ሙስሊም መሆን እንደማይቻል ከዚሁ ራሣችን ሳንረዳ አንቀርም። እምነት ከእስ ልምና /ከታዛዥነት/ ጋር ያለው ግንኙነት የዛፍ ፍሬ ከዛፉ ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ዛፍ መብቀል የሚችለው ከተዘራው ዘር ብቻ ነው። ዘሩ አፈር ላይ ተዘርቶ መብቀል የማይችል ወይም በቅሎ ጉድለት ያለው ተክል ከሆነ ምክንያቱ ወይ የመሬቱ ለም አለመሆን ወይ ደግሞ የአየሩ ሁኔታ ተስማሚ አለመሆን ነው። እንደዚሁም አንድ ሰው በልቡ ውስጥ እምነት ካልኖረ ሙስሊም መሆን አይችልም። እምነት በልቡ ውስጥ ኖሮ ቆራጥ ባለመሆኑ ወይ ትምህርትና አስተዳደጉ በቂ ባለመሆኑ ወይ ደግሞ በአካባቢው ተጽእኖ ምክንያት እስልምናው የተሟላ ላይሆን ይችላል።

ይህን ካወቅን እነዚህን ሁለት መሠረቶች በሚመለከት ረገድ ሰው በአራት ደረጃዎች የሚመደብ መሆኑን መረዳት ይገባል።

1. ለአላህ ታዛዥ የሆኑ፤ ለሕግጋቱ ሙሉ በሙሉ ተገዥ የሚያደርጋቸው እምነት ያላቸው፤ የከለከላቸውን ቁም ነገር የእሳት ፍም በእጁ መንካትን እንደሚጠነቀቅ ሰው የሚጠነቀቁ፤ ሀብትን ለማፍራት ሰው ጥረት እንደሚያደርግ ሁሉ አላህ የሚወደውን ነገር ለመሥራት የሚጥሩ፤ እነዚህ ዓይነቶቹ እውነተኞቹ አማኞች ናቸው።

2. በአላህ የሚያምኑና ሆኖም እምነታቸው ለአላህ ትዕዛዞች ተገዥ የማያደርጋቸው፤ ሕግጋቱን በተሟላ ሁኔታ የማይከተሉ፤

እነዚህ ዓይነቶቹ እምነታቸው የምሉእነት ደረጃ ባይደርስም ለማን ኛውም ሙስሊሞች ናቸው። በጥፋታቸው /ኃጢአታቸው/ መጠን ይቀጣሉ።የገኘውን ጌትነት ስለሚያውቁና ወደዱም ጠሉ ለሕ ግጋቱ ስለሚንበረከኩ እንደ ሕገ ወጥ አመጸኞች ሣይሆን እንደ አጥፊ ወንጀለኞች ይታያሉ።

3. በአላህ የማያምኑ፤ ሆኖም የሙስሊሞችን ተግባር የሚ መስል ሥራ የሚሰሩ፤ እነዚህ ዓይነቶቹ አመጸኞች ናቸው። መልካም መስለው ላይ ላዩን የሚታዩ፤ ሥራዎቻቸውም የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም ሕጐቹን ለመገዛት ያልታለሙ በመሆናቸው ምንም ግምት አይሰጣቸውም። ምሣሌያቸው ያንድ ገዥ ገዥነት እንደማይቀበለውና ትእዛዞቹን እንደማያከብረው ሰው ዓይነት ሲሆን፣ የገዥውን ሕጐች የማይጻረሩ አንዳንድ ሥራዎች ቢሠሩ ለገዥው ታማኝና ለሕጐቹ ተመሪ ናቸው ብሎ መፍረድ አይቻልም። አመጸኛና ሕጐቹን የማያከብሩ መሆናቸው ይታወቃልና።

4. በአላህ የማያምኑ፤ ሕጐቹንና መመሪያዎቹንም የሚጻረሩ፤ እነዚህም መጥፎ ተግባሮች የሚፈጽሙ ዓይነቶች ሲሆኑ ከሰዎች ሁሉ የከፋ አጥፊ አመጸኞች ናቸው።ከዚህ አመዳደብ የምን መለከተው እምነት ለሰው ልጅ ስኬት ለዛሬውና ለነገው ሕይወቱ ተድላና ደስታ ወሳኝነት ያለው መሆኑን፤ እስልምና– ሙሉም ሆነ ያልተሟላ–መወለድ የሚችለው ከእምነት የዘር ፍሬ ብቻ መሆን ነው።እምነት በሌለበት ክህደት /ኩፍር/ ይኖራል። ኩፍር ደግሞ ጸረ እስልምና ነው።ይህ ማለት ደግሞ በተለያየ እርከኑ በአላህ ትእዛዞች ላይ ማመጽ ማለት ነው።

# እውነተኛው የእምነት ዕውቀት የሚቀሰምበት መንገድ

ለእምነት ታዛዥነት የግድ አስፈላጊ መሆኑን አውቀናል። ትክ ክለኛውን ዕውቀት የሃያሉን አላህ ባህሪያትና ተቀባይነት ያለውን ሕጉን፤ የመጨረሻውን ዓለም ሕይወት በሚገባ ለረመዳት የሚያ ስችልና የማያወላውል እውቀት የማግኛው መንገድ የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ አሁን ይነሳ ይሆናል።

የአላህ እዝነትና የድንቅ ሥራው ምልክቶች በያንዳንዱ የዚህ ዩኒቨርስ ገጽታ ውስጥ የተሰራጩና ይህን ዩኒቨርስ ያስገኘው አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን በአኳኋናቸው ሁሉም የሚመሰክሩ መሆ ናቸውን ቀደም ሲል መጥቀሳችን ይታወሣል።ይህ ዩኒቨርስ የሚያ ቀናብረው፣ የሚያስተዳድረውና የሚመራው አንድ አምላክ ብቻ ነው።እነዚህን ምልክቶች ያስተዋለ ሰው የሃያሉ አላህ ባህሪያት በተሟላ መልካቸው ይንጸባረቁለታል።ሁሉም ዓይነት የጥበብ፣ የዕውቀት የፈጣሪን የመሐሪነት፣ የቸርነት፣ የሩህሩህነት፣ የጌ ትነት፣ የአስገዳጅነት፣ የአሸናፊነትና የመሳሰሉት የላቁ ባህሪያቱ በዚህ ግዙፍ ዩኒቨርስ ውስጥ ከሚታዩት እጹብ ድንቅ ሥራዎች ውስጥ በጉልህ ይንጸባረቃሉ።ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አእምሮና ብቃቱ በአጠቃላይ እነዚህን ምልክቶች ከመመልከትና ትክክለኛ ምንነታቸውን ከማስተዋል ተዛንፈዋል። እነዚህ ጉልህ ምልክቶች ከሰው ልጅ ዓይን ላይ የተደገኑ ቢሆኑም፤ ባህሪያቱን ሁሉ ያካተተ የአላህ አንድነት /ተወሂድ/ የሚመሰክሩ ቢሆንም፤ አንዳንድ ሰዎች አንድ አምላክ ብቻ ሣይሆን ሁለት አማልክት ይገኛሉ ብለዋል። ሌሎቹ ደግሞ፣ ይህ ፍጥረተ ዓለም ሶስት አማልክት አሉት ብለዋል። ሥፍር ቁጥር የሌላቸው አማልክት የያዙም ብዙ

ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ አምላክነትን ለበርካታ አማልክት በማከፋፈል፤ ለዝናም አንድ አምላክ፤ ለእሳት አንድ አምላክ .... ለያንዳንዱ የተፈጥሮ ኃይል የራሱ ልዩ አምላክ መድበው ለሁሉም አማልክት ሹም የሆነ ትልቅ አምላክ በመሰየም ወደርሱ ይማጸናሉ። በትእዛዙም ይመራሉ። በዚህ መልክ ነው የሰው ልጅ አእምሮ የሃያሉን አላህ እሱነት ለመረዳትና ባህሪያቱን ለማወቅ እዚህ ላይ መዘርዘር በማይቻል ሁኔታ የተደናገረው።

በዚሁ ዓይነትም የተለያዩ ሰዎች ስለመጨረሻው ዓለም ሕይወት የተሳሳቱ ጥርጣሬዎችንና ከእውነት የራቁ አመለካከቶችን ይዘው ቀረቡ። ከፊሉ የምንኖረው ይህቺኑ ዓለም ብቻ ስለሆነ ከሞት በኋላ መቀስቀስ አይኖርም አሉ። ሌላው ክፍል ደግሞ የሰው ልጅ በተደጋጋሚ በዚህች ዓለም ላይ በየጊዜው ይወለዳል፤ ይሞታል የሥራውን ዋጋም እዚሁ ዓለም ላይ ብቻ ነው የሚያገኘው ብለው አመኑ።

አላህ በሚወደው መሠረት ሕይወቱን ለመምራት የሰው ልጅ መከተል ያለበትን ሕግ፤ የሃያሉን አላህ እሱነትና ባህሪያቱን ማወቅ ያልቻለ ከሆነ እንዴት ለራሱ ሊደነግግ ወይም በራሱ አእምሮ ሊደርስበት ይችላል?

የሰው ልጅ አእምሮ ምንም ያህል ቢበስል፤ ያሻውን ያህል የመጠቀ የእውነት ደረጃ ቢቀዳጅ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሃሣብ ወይም ሃሣብ የሚመስል ነገር ከረዥም ዘመናት ልምድና ከብዙ ምርምር በኋላ ካልሆነ በስተቀር ሊኖረው አይችልም። ከዚህ ሁሉ በኋላም ቢሆን እንኳ በራሱ ላይ የሚተማመን ስለመሆንና እውነታውን በተሟላ ሁኔታ ስለመረዳቱ አፉን ሞልቶ መናገር አይችልም። የሰውን አእምሮና እውቀቱን ለመፈተን ያለ ምንም የበላይ መመ ሪያ እድሉን እንዲሞክር መልቀቅ ለገዛ ራሱ ሐቅንና እውነትን እንዲፈልግ፤ ጥረቱና ብቃቱ የቀናው ሰው ስኬትን ማግኘት፤

ጥረቱና ብቃቱ ያልተሟላለት ሰው ደግሞ ከስረት ዕጣው እንዲሆን መተው የተለመደው የጥፋተኛ መንገድ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ሃያሉ አላህ ግን ለፍጡራኑ ሩህሩህ መሆንን ስለፈለገ ለእንዲህ ዓይነቱ አስቸጋሪ ፈተና አልዳረጋቸውም። ስለዚህ ከራሣቸው መካከል የአላህን ባህሪያት ትክክለኛ ዕውቀት የተካኑ፤ ጌታው በሚወደው መሠረት በዚህች ዓለም ላይ ሕይወቱን እንዴት መም ራት የሚችልበትን መንገድ ያሳወቃቸውን ነቢያት ላከባቸው። ለነዚህ ነቢያትም ስለመጨረሻው ዓለም ሕይወት ትክክለኛ ዕው ቀት ሰጥቶ ዕውቀቱን ለሰዎች ሁሉ እንዲያደርሱ አዘዛቸው። እነዚህም የአላህ መልዕክተኞችና ነቢያቱ ሲሆኑ ይህን ዕውቀት ከሃያሉ አላህ ያገኙበት መንገድም ራእይ /ወህይ/ ነው። ይህ ዕው ቀት ያለበት መጽሐፍ ደግሞ «የአላህ መጽሐፍ ወይም ቃል» ይባላል። አሁን የሰው ልጅ አእምሮና ብቃቱ የመልእክተኛውን መልካም ሕይወትና የላቀ መመሪያውን ካስታዋለ በኋላ በነቢዩ በማመኑ ወይም በማስተባበሉ በኩል ካልሆነ በስተቀር ፈተና የለበትም። እውነትን ለማወቅና ለመከተል ዝግጁ የሆነ ሰውም ሐቁን አውቆ የእውነተኛውን መልዕክተኛ መመሪያዎች ያስተባበለ ሰውም እውነትንና ትክክለኛነትን የማወቅና የመቀበል ብቃት ራሱን የነፈገ ሰው ነው። ይህም ፈተናውን እንዲወድቅ ያደርገዋል። ስለ አላህ፣ ስለሕጐቹና ስለመጨረሻው ዓለም ሕይወት ትክክለኛ ዕውቀት እንዳይቀስም ያግደዋል።

## ከሕዋሳዊ ስሜት በራቀው ማመን:-

አንድን ነገር ለራሣችን የማናውቀው ከሆነ የሚያውቅ ሰው እንፈልግና እርሱ ባለው መሠረት ቃሉን ተቀብለን ሃሣቡን እንከ ተላለን። ለምሣሌ ያህል ብንታመም ራሣችንን በራሣችን አናክ ምም። ሐኪም እንጠይቃለን እንጂ። ይህ ሐኪም በሕክምና ጥበብ

የረቀቀ ብቃቱን የሚመሰክር ከፍተኛ ምስክር ወረቀት ያለው ከሆነ፣ በእጁ ብዙ ሰዎች መፈወሳቸውን ካየን እኛን ለማከም አስፈላጊ የሆነ ብቃት እንዳለው እናምናለን። በዚህ እምነት ላይ በመመርኮዝም ይህ ሐኪም ያዘዘልንን መድሃኒት ብቻ ነው የምን ወስደው። ሐኪሙ ከከለከለን ነገር ሁሉም እንርቃለን። በዚሁ መልክም በሕግ ነክ ጉዳዮች ላይ የሕግ ጠበቃን አምነን እንታዘ ዛለን። በትምህርት ጉዳዮች ላይም መምህሩን አምነን የሚያስ ረዳንን ሁሉ እንቀበላለን። ወደማናውቀው ቦታ ለመሄድ ስንፈ ልግም መንገዱን የሚያውቀውን ሰው እናምናለን።ቃሉንም ተቀብ ለን በሚመራን መንገድ እንሄዳለን። በሁሉም የኑሮ ፈርጆች ውስጥ መሰል ሁኔታዎች ይገጥሙናል። ይህ ነው እንግዲህ ከሕዋሳዊ ስሜት በራቀው /በገይብ/ ማመን ማለት።

ከሕዋሳዊ ስሜት በራቀው ማመን ማለት ትርጉሙ በማና ውቀው ነገር የሚያውቀው ሰው የነገረንን መቀበልና ማመን ማለት ነው። የአላህን እሱነትና ባህሪያቱን አናውቅም። መላኢኮቹ በርሱ ትእዛዝ የፍጥረታትን ጉዳዮች የሚያከናውኑና በሁሉም አቅጣጫ ሰዎችን የከበቡ መሆናቸውን አናውቅም። ሃያሉ አላህ በሚወደው መሠረት ሕይወትን ለመምራት ትክክለኛው መንገድ የቱ እንደሆነ አናውቅም። ስለ መጨረሻው ዘለዓለማዊ ሕይወትና እዚያ ስለሚ ገጥመን ነገር ዕውቀት የለንም።እነዚህን ነገሮችና መሰሎቻቸውን በሙሉ ማወቅ የሚቻለው በእውነተኛነቱ፣ በንጹሕነቱ፣ በአላህን ፈሪነቱ፣ በአጠቃላይ ሕይወቱ ለአላህ ፍጹም ተገዥ በመሆኑ፣ ልባዊ እምነት ከሚጣልበት በጠሩ ሥራዎቹና በጥበበኛ ቃላቱ መዝነን እውነትን እንጂ ምንም እንደማይናገር ከሚታመን በዚህም ምክንያት የሚናገራቸውን ሁሉ ተቀብለን ለማመን ተገቢ ከሆነ ሰው ነው። ይህ ነው ከሕዋሣዊ ስሜት በራቀው /ገይብ/ ማመን ማለት። የሃያሉን አላህ ትእዛዝ ለማክበርና እሱ የሚወደውንና የሚቀበለውን መሥራት ከፈለግን ይህ እምነት የግዴታ አስፈላጊ

ነው። ስለነዚህ ነገሮች ትክክለኛ የሆነ ዕውቀት ማግኘት የሚቻለው በመልዕክተኛ /ነቢይ/ አማካይነት ብቻ ሲሆን፤ ያለዚህ ትክክለኛ ዕውቀትም ወደ ቀጥተኛው የእስልምና ጐዳና መመራትና መጓዝም አይቻልም።

# ምዕራፍ ሶስት

## ነቢይነት

ካለፈው ምዕራፍ ሶስት ነጥቦችን ተረድተናል። እነሱም አንደኛ:- የሰው ልጅ ስለአላህ እሱነት፣ ስለባህሪያቱና ስለሚ ወዳቸው መንገዶች ትክክለኛ የሆነ ዕውቀት የሚያስፈልገው ፤ የመጨረሻው ዓለም ሕይወት ምርመራና ምንዳዎች ለአላህ በመታ ዘዝ፣ መመሪያዎቹን በማክበርና ለሕጐቹ በመገዛት መሆኑ።ይህ ዕውቀት ደግሞ በጥንካሬውና በጽናቱ ፍጹም አስተማማኝና ጭብጥ ከመሆን ደረጃ የደረሰ መሆን ያለበት መሆኑን። ሁለተኛ:- ሃያሉ አላህ ሰዎች በገዛ ጥረታቸው ይህ ዕውቀት እንዲኖራቸው ሳያስገ ድድ ከመካከላቸው ሰዎችን – ነቢያቱን– በመምረጥ ይህን ዕው ቀት አጎናጽፏቸው በምድር ላሉት ሰዎች ሁሉ እንዲያደርሱ ያዘዛቸው መሆኑን። ሶስተኛ:- ከዚያ በኋላ እውነተኞቹን የአላህ ነቢያት ከማወቅ በስተቀር ከሰዎች ምንም የማይጠበቅ መሆኑን፣ ወደነርሱ የተላከ የአላህ ነቢይ መሆኑን አምኖ መቀበልና ትእዛዙን መከተል፤ በቃሉም መመራት፣ በአጠቃላይ ሕይወታቸው የርሱን አርአያነት መከተል ያለባቸው መሆኑ ናቸው።ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የነቢያትን ምንነትና እንዴት ማወቅ እንደሚቻል ማብራራት እንፈልጋለን።

## የነቢይነት እውነታ:- ባህሪና አስፈላጊነቱ

ሃያሉ አላህ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ፈጥሮአል።የሰው ልጅ ሲወለድ ጀምሮ ለመ መልከት ሁለት ዓይኖች፣ ለመስሚያ ሁለት ጆሮዎች፣ ለመተ

ንፈሻና ለማሽተቻ አፍንጫ ተፈጥረውለታል። ለመዳሰስ ስሜት ‹የመዳሰስ› ኃይል በቆዳው ውስጥ አለው። ለመጓዝ ሁለት እግሮች፣ ለሥራ ሁለት እጆች፣ ለግንዛቤ አእምሮና የመሳሰሉትን ሌሎች አያሌ አካላት አነስተኛው ሰውነቱ አጠቃሎአል።ሃያሉ አላህ ይህን ሁሉ የለገሰው የተለያዩ ፍላጐቶቹን በመመልከት ነው።ለኑሮው የሚረዱና ሕይወቱን የሚያግዙ ቁጥር ስፍር የሌላቸው መገልገያዎችና መጠቀሚያዎች በሰፊው ተዘርግተውለታል። አየሩ፣ ውሃው፣ ብርሃኑ፣ ሙቀቱ፣ በናት ጡት ያለው ወተት፣ በወላጆቹ፣ በዘመዶቹና በሌሎቹም ልብ ያለው ፍቅር ሁሉ በዚሁ የአላህ ችሮታ ናቸው። ባደገና በጠነከረ ቁጥርም የዚህችን ዓለም ሕይወት ፍላጐቶቹን የሚያረኩ ነገሮች እያደጉና እየጨመሩ ይመጣሉ።ይህ ሁሉ ሲታይ በሰማያትና በምድር ያለው በርካታ ኃይሎች እርሱን ለማሣደግ እሱን ለማገልገል ብቻ የተፈጠሩ ይመስላሉ።

አንድ ተጨማሪ እርምጃ ወደፊት ስንራመድም በዚህች ዓለም ላይ የሚሠራበትንና አስፈላጊው የሆኑ ተሰጥኦዎችን፣ ብቃትና ችሎታን ሃያሉ አላህ ለሰው ልጅ የለገሰ መሆኑን እንረዳለን። እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ይብዛም ይነስ አካላዊ፣ ሕሊናዊ ብቃት የመገንዘብ የብልህነትና የመናገር ችሎታ አለው። አላህ /ሱ.ወ/ በፍጥረታቱ ውስጥ ድንቅ ነገሮች አሉት። ከርሱ በስተቀር በዚህ የሚመሰገንና ውዳሴ የሚገባው አንድም የለም። በዚህ የብቃትና የተሰጥኦ ድርሻ ለሁሉም እኩል አላደረገም። በድርሻው ሁሉንም ሰው እኩል ቢያደርግ ኖሮ አንዱ ከሌላው ፍጹም በተብቃቃና ምንም ዓይነት ተራድኦና መተሳሰብ በሰዎች መካከል ባልኖረ ነበር። ስለዚህም የሰው ዘር በጥቅሉ የሚያስፈልገውን የተሰጥኦና የብቃት ድርሻ መጥኖ በተለያዩ ግለሰቦች አከፋፍሎአል። ይኸውም ስርጭት አንዱ የሌለውን ብቃት ለሌላው በመለገስ ያንዱን እጣ ፈንታ ከሌላው ዕጣ ፈንታ የተለየ በማድረግ

ነው። ከዚህ የተነሣም አንዳንድ ሰዎች በአካላዊ ኃይል ከሌሎች ልቀው ሲገኙ ሌሎቹ ደግሞ ባንድ ዓይነት ጥበብ ወይም ሙያ የተካኑ ሆነው እናያለን። አንዱ ዘንድ የምናገኘውን የአእምሮ ብስለትና የግንዛቤ ጥራት በሌላው ዘንድ አናገኘውም።አንዱ የወታደራዊ ዝንባሌ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ሲኖረው ሌላው ደግሞ በአመራርና በአስተዳደር ልዩ ተሰጥኦ ያለው ሆኖ እናያለን። አንዱ ድንቅ የመናገር ችሎታ ሊኖረው ሌላው ደግሞ የድርሰት ልዩ ተሰጥኦ ሲታደል ይታያል። አንዳንዶቹ ብሩህ አእምሮ ኖሮአቸው በሂሣብና በፊዚክስ መስክ ብዙ ነገሮችን በቀላሉ ሲፈቱና እጅግ አስደናቂ ግኝቶችን ለዓለም ሲያስተዋውቁ ይታያሉ። ሌሎቹ ደግሞ በሕግ ሙያ የበሰሉና የበቁ በመሆን ሌሎች ዓመታት የሚፈጅባቸውን ጉዳዮች በቀላሉ ይደርሱበታል።ይህ ሁሉ የአላህ ችሮታ ሲሆን ከፍጡራኑ መካከል ላሻው ሰው የሚሰጥ ነው።አንድ ሰው እነዚህን ተሰጥዖዎች በገዛ ራሱ ውስጥ ማነጽ አይችልም። በትምህርትና በልምድ የሚቀሰሙም አይደሉም። ላሻው ሰው የሚለግሣቸው ተፈጥሮአዊ ተሰጥኦዎች ናቸው።

በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያዩ ብቃቶችና ተሰጥኦዎች መኖራቸውን ስንመለከት በሰዎች መካከል የኖረው እያንዳንዱ ብቃትና ልዩ ተሰጥኦ ለሰው ዘር በሚያስፈልገው መጠን ብቻ የተደረገ በመሆኑ ሃያሉ አላህ ለከፍተኛ ጥበብ የመጠነው መሆኑን እንገነዘባለን። ወታደሮችን፣ አራሾችን፣ አናጢዎችን፣ አንጥረኞችን፣ ሸማኔዎችንና ሌሎች መሰል ሙያዎችን አኑሮአል። ምሁራዊ ብቃትና የፖለቲካ የአስተዳደር ተሰጥኦ ያላቸው ክፍሎች ደግሞ ከመጀመሪያዎቹ በቁጥር ያንሣሉ። በተወሰኑ መስኮችና ጥበቦች ልዩ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሰዎች ቁጥር ደግሞ በተራው ከሁለተኛው ወገን በጣም ያነሱ ናቸው። ይኸውም ሥራዎቻቸው የሰውን ልጅ ለዘመናትና ለብዙ ትውልዶች ከልፋት የሚያድኑ በመሆናቸው ነው።

ለመሆኑ የሰውን ልጅ ፍላጐት ለማርካትና ዓለማዊ ሕይወቱን ለማሳካት በምህንድስና በማቲማቲክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሕግ፣ በፖለቲካ፣ በምጣኔ ሐብትና በተቀሩት ሙያዎች የተራቀቁ ጠቢባን ብቻ መገኘታቸው በቂ ነው ወይ? በፍጹም አይደለም። ከነዚህ ሙያዎች ሁሉ ይበልጥ አስፈላጊና ወሳኝነት ያለው የሰዎችን እጅ ይዞ ወደ ቀጥተኛው የአላህ መንገድ የሚመራው ሰው ነው። እርግጥ ነው የነዚህ ጥበቦች ምሁራን የሰው ልጅ በዚህች ዓላማዊ ሕይወቱ ምን ማድረግ እንዳለበት፤ የተፈጥሮን በረከት እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚችል ይመሩታል። ቢሆንም «ጌታው ማን እንደሆነ፤ በምድርና በሰማያት ያለውን ሁሉ ማን እንደለገሰው፤ በዚህ ለጋሽ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ነገር እንዴት መሥራት እንደሚችል፣ ሕይወቱን በርሱ መመሪያ መሠረት በመምራት ዘለዓለማዊ ስኬት ማግኘት እንዴት እንደሚችል፤ የሚያስረዳው ሰው ግን ከሁሉም በላይ ፍጹም አስፈላጊው ነው።ሃያሉ አላህ ለሰወ ልጅ በዚህች ዓለም ላይ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረለትን ያህል፣ ወደቀጥተኛው የርሱ መንገድ የሚመራውን ሰውም ሰጥቶታል ይህ ጉዳይ እንደምናውቀው ሁሉ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ዋነኛውና ቀዳሚው ሁኔታ ነው።በዚህም ምክንያት አላህ እርሱን ለማወቅ ከፍተኛ የሆነ ብቃት ያላቸውን ሰዎች ከሰው ዘር ውስጥ ፈጥሯል። ከራሱ ዘንድ የሃይማኖት የሥነ ምግባርና የሕግጋት ዕውቀት ሰጥቶአቸው በምድረ ዓለሙ የሚገኙትን ሰብዓዊ ፍጡራን እንዲያስተምሩ ኃላፊነት ጥሎባቸዋል። እነኚህ ሰዎች የአላህ ነቢያትና መልዕክተኞች /ዐ.ሰ.ወ/ ብለን የምንጠራቸው ሰዎች ናቸው።

# ነቢይን ማወቅ:-

በሳይንስ ጥበባት የተካኑ ባለ ብሩህ አእምሮ ምሁራን ከሌሎች የሚለዩባቸው ልዩ አእምሮአዊ ብቃትና ያልተለመደ ባህሪ ይዘው እንደሚወለዱ ሁሉ በነቢያትም እንደዚሁ ከሰዎች ልዩ የሚያ ደርጋቸው ልዩ ባህሪ ይዘው ይወለዳሉ።

ተሰጥኦ ያለውን ገጣሚ ግጥሙን ብቻ ስንሰማ በተፈጥሮው በሥነግጥም ልዩ ተሰጥኦ ያለው መሆኑን እንገነዘባለን። ሌላ ሰው የፈለገውን ያህል ጥረት ቢያደርግ እንደርሱ ሊገጥም አይችልም። የንግግር ተሰጥኦ፣ የመጻፍ ተሰጥኦ፣ የመፈልሰፍ ተሰጥኦ የመሪነት ተሰጥኦ ያላቸውን ግለሰቦችም እንደዚሁ ከሥራዎቻቸው ማወቅ እንችላለን። እያንዳንዳቸው ሌሎች ዘንድ የማይታወቅ ልዩ የፈ ጠራ ብቃቶቻቸውን በተሠማሩበት ተግባር ላይ ይንፀባረቃል። በዚሁ ዓይነት ለነቢይነት በአላህ በተመረጠው ሰው ልቦናው ውስጥ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ታስበው የማያውቁ አዳዲስ ሃሣቦች ይጸነሱና ሌላው ሰው ማብራራት የማይችላቸውን ርእሶችና ጥያቄዎች ለሰዎች አቅርበው ያብራራሉ። ሌሎች ሰዎች ለዓመታት ጥረት ቢያደርጉ እንኳ የማይደርሱባቸውንና የማይረዱዋቸውን ረቂቅ ጉዳዮች ይገነዘባሉ። ይህ ነቢይ የሚናገረውን ሁሉ ጤነኛ አእምሮ ያለማመንታት ይቀበለዋል። እውነተኛ አገላለጡን ሕሊናው ይመ ሰክራል። የዓለማዊ ሕይወት ልምዶችና የተፈጥሮ ክስተቶችም እያንዳንዱ የነቢይ ቃል ትክክለኛ መሆኑን ይመሰክራሉ። ሌላ ሰው ግን የርሱን ቃል አስመስሎ ማቅረብ ቢፈልግ በፍጹም አይችልም። ለነቢይነት የሚመረጥ ሰው ንጹሕ ተፈጥሮ፣ የጠራ ባህሪ ያለው ሰው ሲሆን አጠቃላይ ሕይወቱ ከእውነት፣ ከቁጥብነት፣ ከክብር መንገድ ውጭ በፍጹም አይሆንም። በቃሉም ሆነ በተግባሩ ሐቅንና እውነትን የሚጻረር ነገር ጭራሽ አይፈጽምም። ወደ ቀጥተኛው

ጉዳና ይመራል። ሰዎች እንዲያደርጉ የሚያዘውን ለራሱ ቀድሞ ተግባራዊ ያደርጋል። ቃሉና ተግባሩ የሚለያይበት አንድም ምሣሌ በመላ ሕይወቱ ውስጥ መጥቀስ አይቻልም። ለሌሎች ጥቅም ሲል ለራሱ ችግር ይቀበላል እንጂ ለራሱ ጥቅም ብሎ ሰዎችን አይ ጉዳም።ሕይወቱ በሙሉ እውነት፣ ታማኝነት፣ ክብር፣ ንጽ ሕና፣ የሕሊና ጥራት ነው፤ የመጠቀ አስተሳሰብ ነው፤ የላቀ ሥነ ምግባር ነው፤ ነውርና እንከን በፍጹም የማያውቁት የጠራ ሕይወት ነው። እንዲህ ያለው ሰው ሰዎችን ለመምራት ከአላህ የተላከ እውነተኛው የአላህ ነቢይ መሆኑን እነዚህ ሁሉ ባህሪዎቹ በተጨባጭ ይመሰክራሉ።

## ነቢይን መታዘዝ :-

አንድ ሰው ከአላህ የተላከ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን ካወቅን የሚያዘውን መፈጸምና የሚከለክለውንም መተው ይገባናል። አን ድን ሰው ነቢይ ነው ብለው ከተቀበሉ በኋላ ትእዛዙን አለመፈጸም ሰብአዊ አእምሮ የማይቀበለው ነገር ነው። ነቢይነቱን መቀበል ማለት ግላዊ ስሜቱን የማይናገር ፣ ከአላህ የተላለፈለትን ብቻ የሚያስተላልፍ፣ አላህ የማይወደውን የማይፈጽም ማለት ካልሆነ እምነቱ ትርጉም የለሽ ይሆናል። ከዚህ ነቢይ መመሪያ ጋር የማይጣጣም ቃልና ተግባር ሁሉ አላህን በመጻረር የሚፈጸም ነው። አላህን የሚጻረር ነገር ሁሉ በምንም ዓይነት እውነተኛ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም በነቢይ ያለን እምነት ነቢዩ ባዘዘንና በከለ ከለን ነገር ሁሉ ትእዛዙና እገዳው ያዘለውን ጥበብና ፋይዳ አወቅንም አላወቅን በመከተልና በመፈፀም ላይ ይወሰናል። ይህን የአላህን –ያላንዳች ተቃውሞና ያለምንም ማቅማማት በተሟላ ሁኔታ መታዘዝ ያለብን መሆኑን መረዳት ቢሳነን በራሣችን የግን ዛቤ ችሎታ ላይ በሚኖር ብልሽት ወይም ውስንነት ምክንያት እንጂ

መመሪያው እንከን ስላለው አይደለም። ስለ አንድ የጥበብ ፈርጅ በቂ ግንዛቤና የረባ ዕወቀት የሌለው ሰው ጥበቡ ያቀፈውን ምስጢርና ፋይዳ መረዳት ሳይችል ቀርቶ በጥበቡ የተካነው ባለሙያ የሰጠውን ትንተና የማይቀበል ሰው ከመጠን ያለፈ ጅል መሆኑ በጣም ግልጽ ነው። እያንዳንዱ ዓለማዊ ጉዳይ የረቀቀ ዕውቀትና የጠለቀ ግንዛቤ ያለው ሰው ይጠይቃል። ታዲያ እንዲህ ያለው ሰው ሲገኝ ሰዎች ዋቢ አድርገውት እውነተኛነቱን ይቀበላሉ። በርሱ ላይ ይተማመናሉ። ቃሉን አይቃወሙም። በጒራዎቹ ውስጥ ጣልቃ አይገቡበትም። ይህም የሆነው በሁሉም የዕውቀትና የሥነ ጥበብ ፈርጆች ሰዎች ሁሉ እኩል የጠለቀ ግንዛቤ ኖሮአቸው ዓለማዊ ጉዳዮችን በሙሉ የመረዳት ብቃት ሊኖራቸው አይችልም ከሚል እውነታ በመነሣት ነው። የማሰብ ችሎታችንና የግንዛቤ ኃይላችን መወሰን የጠለቀ ዕውቀት ያለውን ሰው እንድንፈልግ ያስገድደናል። እንዲህ ያለውን ሰው አግኝተን በጠቢብነቱ ካመን እምነታችንን ሙሉ በሙሉ በርሱ ላይ መጣል አለብን። ሥራዎቹን መቃወምና የራሣችንን ሃሣብ የሙጥኝ ብለን መያዝ በፍጹም አይገባም። ይህ ሥራህ ምን እንደሆነ ምስጢሩንና ጥቅሙን ካላሳወቅኸኝ በስተቀር በጠቢብነትህ አላምንም ማለት ተራ ጅልነት ነው። ፍርድ ቤት ጉዳይ ሲኖረን ጉዳዩን ለሕግ ጠበቃ እንተው የለም ወይ? እንዲህ ባለ ጣልቃገብነት የጠበቃውን ተግባር ብንቃወም ከቢሮው አያባርረንም ወይ? ለያንዳንዱ የምርመራ እርምጃውና መግለጫው ትክክለኛነት ማስረጃ እንዲያቀርብልን የሚያ ክመንን ሐኪም ብንጠይቅ እኛን ከማከም አይቆጥብም ወይ? የሃይማኖት ጉዳይም ልክ እንደዚሁ ነው።አላህ በሚወደው መሠረት ሕይወታችንን ለመምራት ትክክለኛውን መንገድ ማወቅና አላህን ማወቅ ያስፈልገናል። ይህን እውቀት ለማግኘትና መንገዱንም ለማወቅ ግን እኛ አንችልም።ስለዚህም እውነተኛውን የአላህን ነቢይ መፈለግና አላህ የሰጠንን የአእምሮ ችሎታ፣

የማስተዋል፣ የግንዛቤና የብልህነት ኃይላችንን ሙሉ በሙሉ ማሰራት አለብን።አላህ ያልላከውን ሰው ነቢይ አድርገን ከያዝን ሀቁን መንገድ ያሳስተናል። ጠማማውን መንገድ ይመራናል። ከጥልቅ ምርምር፣ ፍተሻና ሙከራ በኋላ አንድ ሰው ከአላህ የተላከ ነቢይ መሆኑን በቁርጠኝነት ካረጋገጥን ሙሉ በሙሉ በርሱ ላይ መተማመን አለብን። በሚያዘንና በሚከለክለን ነገር ሁሉ ፍጹም በተሟላ ሁኔታ መታዘዝ ይኖርብናል።

## በነቢያት የማመን አስፈላጊነት:-

ቀጥተኛው የእስልምና መንገድ በአላህ ትእዛዝ ነቢዩ የሚመራበት መሆኑን ካወቅን፣ የሰው ልጅ በመላ በነቢዩ ማመን፣ ነቢዩን መከተልና ትእዛዙን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፣ ነቢዩን የሚቃረን፣ ትእዛዙን የሚጥስ፣ የራሱን ግላዊ መንገድ የሚፈጥር ሰው ያለ ጥርጣሬ የጠመመ ሰው መሆኑን በሚገባ እንረዳለን።

ይህን በሚመለከት ሰዎች አያሌ አስገራሚ ነገሮች ይፈጽማሉ። የነቢዩን እውነተኛነት እየተቀበሉ ነገር ግን የማያምኑና የማይታዘዙ ሰዎች አሉ።እነኚህ ዓይነቶች ከሃዲዎች ብቻ ሣይሆኑ ጅሎችም ጭምር ናቸው።የነቢዩን እውነተኛነት መቀበል፣ ከአላህ ዘንድ የተመረጠ መሆኑን ማወቅና ትእዛዙን አለመቀበል ማለት ከሐቅ ይልቅ ውሸትን ማብለጥ፣ ሆን ብለው ቀናነትን በጥመት መለወጥ ከማለት በስተቀር ሌላ ትርጉም የለውም። ከዚህ ጅልነት የበለጠ የሚያስበረግግ ጅልነት አለመኖሩም ግልጽ ነው።

ወደ ቀጥተኛው መንገድ ሊመራን የሚችል አእምሮ ስላለን ነቢይን መከተል አያስፈልገንም የሚሉ ክፍሎችም አሉ።ይህም እንደዚሁ ከፍተኛ ስህተትና የከፋ ጥመት ነው።በማቲማቲክስ ትምህርት ውስጥ ሁለት ነጥቦችን የሚያገናኝ ቀጥተኛ መስመር

አንድ ብቻ መሆኑን ሁላችንም ተምረናል።ከዚህ ያነሰ ማንኛውም መሥመር ቀጥተኛ አይደለም። ወይም ሁለቱን ነጥቦች የሚያገናኝ አይደለም።በዚህም መሠረት እስልምና ውስጥ ቀጥተኛው መንገድ /ሲራጠልሙስተቂም/ በመባል የሚታወቀው የእውነት መንገድ ሰብአዊ ፍጡርን ከፈጣሪው የሚያገናኘው መሥመር በዚህ የጂኦ ሜትሪ ሕግ መሠረት ከአንዱ በላይ ሊሆን አይችልም። ከዚህ ውጭ ያለው ማንኛውም መንገድ ቀጥተኛ አይደለም። ወይም ደግሞ ሰውን ከፈጣሪው ጋር አያገናኝም።

ሌላ ተጨማሪ እርምጃ ወደፊት እንራመድና ወደ አላህ የሚያደርሰው መንገድ አንድ መሆኑንና እሱም የአላህ ነቢይ የመሩበት መንገድ መሆኑን ተረድተናል።ከዚህ መንገድ የተዛነፈና ሌላ መንገድ ለመፈለግ ራሱን የታከተ ማንኛውም ሰው ቀጥሎ ከተመለከቱት ሁለት ገጽታዎች ካንዱ አያመልጥም።

ወደ አላህ የሚያደርስ መንገድ ከነጭራሹ አላገኘም። ወይም ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆነ ረዥም መንገድ አግኝቷል።የመጀመሪያው ውጤቱ ጥፋትና ውድመት መሆኑ ጥርጥር የለውም።ሁለተኛው ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ጅልነትና ጥመት ያለበት መሆኑ እንደዚሁ ጥርጥር የለውም። አንድ እንስሳ አንድ የተወሰነ ቦታ ለመድረስ ሲፈልግ ለጊዜው ቀጥተኛውን መሥመር ይመርጥ የለም ወይ? ታዲያ አላህ አእምሮ የለገሰውና ወደ ጌታው እንዲጠራው፤ ቀናውንና መልካሙን ጐዳና እንዲመራው ከመካከሉ ነቢይ ልኮ ለት ሣለ የለም አልከተልህም፤ በምትመራኝ መንገድም አልጓ ዝም፤ ለራሴ ጥረት አድርጌ ካሰብኩት እስከደርስ ድረስ በጽልመት በተሸፈኑ መንገዶች ልደናገር የሚለውን ሰው ምን እንበለው?!

መቼም ይኸ ማንም ሰው በቀላሉ የሚረዳው ጉዳይ ነው።ጥቂት ብናሰላስል በነቢዩ የማያምን ሰው ወደ አላህ ለመድረስ ቀጥተ ኛውንም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነውን መንገድ ማግኘት እንደማይችል

ግልጽ ይሆንልናል። ወይ የአእምሮ እንከን ያለበት፣ ወይ በተፈ ጥሮው ጥመት ያለበት ዕብሪተኛ ሰው፣ሐቅን መቀበል የማያስ ደስተው ሰው፣ ወይ በአባቶች ጭፍን ተከታይነት የሰመጠ ከነሱ ከወረሳቸው አስተሳሰቦችና ቅርጾች የሚያስወግድን አንድም ቃል መስማት የማይፈቅድ ሰው፣ ወይም የራሱን ግላዊ ዝንባሌ አምላኩ አድርጐ የያዘ ሰው፣ የነቢዩን ትምህርቶች የመቀበል ዝንባሌ ባለመኖሩ ትምህርቱን ከተቀበለ የኃጢአትና የመጥፎ ሥራዎች ልምድን ለማራመድ መድረክ የማያገኝ፣ በነዚህ ምክንያቶች ሐቅን ከመቀበል በሚያግድ ነገር አእምሮው የተነካ ሰው መሆን አለበት።ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ያለበት ሰው ወደ አላህ መንገድ ሊመራ አይችልም።ከነዚህ እንከኖች ነፃ የሆነ ሰው ግን ከእውነተኛው ነቢይ ትእዛዝ ማፈንገጥና ትምህርቶቹን ከመቀበል ማፈግፈግ በፍጹም ሊሆንለት አይችልም።

እነዚህን በተመለከተ መርሣት የሌለብን ነቢዩን የሚልከው ሃያሉ አላህ መሆኑን፣ በነቢዩ እንዲያምኑና ትምህርቶቹን እንዲ ከተሉ የሚያዘውም አላህ መሆኑን ነው።በነቢዩ የማያምንና በትእ ዛዙ ላይ የሚያምጽ ሰው ልክ በአላህ በራሱ ላይ እንዳመጸ የሚቆጠር ነው።በምንተዳደርበት መንግሥት እኛን እንዲያስተዳ ድር የተሾመውን ሰው የግዴታ መታዘዝ ያለብን መሆኑ አስተዳ ዳሪነቱን አንቀበልም— አሻፈረን ብንል በራሱ በመንግሥት ላይ እንዳመጽን ስለሚቆጠር ነው።መንግሥቱን መቀበልና መንግሥት የሾመውን አስተዳዳሪ እምቢ አልቀበልም ማለት ሊጣጣሙ የማይ ችሉ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው።በአላህና በሚልከው ነቢይ መካከል ያለውምሁኔታ ይኸው ዓይነት ነው። አላህ የሰዎች ሁሉ እውነተኛው ንጉስ ነው።መሪ አድርጐ እንዲከተሉ የላከላቸውን ሰው ሊያምኑበትና ከማንም በላይ ለርሱ በቅንነት መታዘዝ ግዴታ ነው።ከትእዛዙ የሚወጣ ሁሉ በአላህ አመነም አላመነ ከሃዲ —ካፊር— ነው።

# የነቢይነት አጭር ታሪክ:-

አሁን ደግሞ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ነቢይነት እንዴት እንደተጀመረና የነቢያት መላክ ሂደት እንዴት ተከናውኖ በታላቁ የመጨረሻ ነቢይ እንዴት እንደተቋጨ እናብራራለን።

እንደሚታወቀው ሁሉ ሃያሉ አላህ በመጀመሪያ የፈጠረው አንድ ሰው ብቻ ሲሆን ከርሱ ከፍሎ መቀናጆው ፈጠረ። ከሁለቱም ዛሬ በምድሪቷ ተሰራጭተው የሚታዩት የተለያዩ ሕዝቦች ተፈ ጠሩ። የሁሉም ሕዝቦች ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ መዛግብት የሰው ልጅ የትውልድ ሰንሰለት የተጀመረው ከአንድ ሰው በመሆኑ ተስማምተዋል። ሳይንሳዊ ጥብጦችም እንደዚሁ በተለያዩ የዓለም ሀገሮችና ሥፍራዎች ዛሬ ተራብተው የሚገኙ እነዚህ ዝርያዎች ሕዝቦች የመነጩባቸው የተለያዩ ግለሰቦች እንደነበሩ አያረጋ ግጡም። አብዛኖቹ ሳይንቲስቶች ያላቸው ግምት በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ሰው ብቻ የተፈጠረና ከዚሁ ሰው ዛሬ የሚገኙት የሰው ዝርያዎች የተራቡ ናቸው የሚል ነው።

የሰው ዝርያ ምንጭ የሆነው ይህ አንድ ሰው በኛ ቋንቋ አዳም ነው። በምድር ላይ አላህ የመጀመሪያ መልዕክተኛ አድርጐ የመረጠውና ልጆቹን እስልምና እንዲያስተምር ያዘዘውም አደም /ዓ.ሠ/ ነው። የናንተም ሆነ የዚህ ዩኒቨርስ አምላክ አንድ አላህ ብቻ ነውና ከርሱ በስተቀር ሌላ አታመልኩ፤ ከርሱ ብቻ ረድኤት ፈልጉ፤ ለርሱ ብቻ ስገዱ፤ ሐቀኞችና ጻድቃን ሆናችሁ እርሱ በሚፈልገው መንገድ ብቻ ሕይወታችሁን ምሩ፤ ይህን ካደረ ጋችሁ ምንዳችሁ የደጋግ ጻድቃን ምንዳ ይሆናል። ካፈነገጣችሁም ቅጣታችሁ የእርኩሳን አጥፊዎች ቅጣት ይሆናል፤ በማለት አደም ልጆቹን እንዲያስተምር አላህ መረጠው።

ከአደም ዝርያዎች ደጋጐቹ አባታቸውን ተከትለው በመመ ሪያው መሠረት ቀጥተኛውን መንገድ ይዘዋል። ጠማሞቹ ግን ትእዛዙን አንቀበልም ብለው ግላዊ ዝንባሌያቸውን ስለተከተሉ ቀስ በቀስ መጥፎና አስከፊ ነገሮች ተዛመተላቸው። .....

ከፊላቸው ጸሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ማምለክ ያዙ። ሌሎቹም ዛፍ፣ ድንጋይ ወይም ወንዝ ወይም እንስሳትን ማምለክ ጀመሩ። እንደ ውሃ፣ እሳት፣ በሽታ፣ ጤንነትና የመሣሰሉት የተፈጥሮ ክስተቶችና ጸጋዎች እያንዳንዳቸው ልዩ አምላክ አላቸ ውና የሰው ልጅ እነዚህን አማልክት በሙሉ ማምለክና ደግ ችሮታቸውን ይለግሱ ዘንድ እያንዳንዳቸውን ለማስደሰት መጣር አለበት ብለው ገመቱ። በዚህ ሁኔታ ነው አለማወቅ የተለያዩ የማጋራት /ሽርክ/ የጣኦታትና የቅርጻቅርጾች አምልኮ መልኮችን ፈጥሮ የተለያዩ ሃይማኖቶች በምድር ላይ የተሰራጩት። ይህ ሁሉ የሆነው የአዳም ልጆች በተለያዩ የምድር ማዕዘናትና አካባቢዎች ተራብተው የተለያዩ ህብረተሰቦችና ሕዝቦች ሆነው በመጡበት ጊዜ ነው። እያንዳንዱ ስብስብም የራሱ የሆነ እምነት፣ ከሌሎች የተለየ የራሱ የሆነ ቅርጽና ሥነ ሥርዓት ያለው ሃይማኖት መሠ ረተ። በአጠቃላይ አነጋገር ሰዎች ፈጣሪ ጌታቸውን ሲረሱ በአባታ ቸው አማካይነት የተላለፈላቸውን የአላህን ሃይማኖት /እስልምና/ ዘነጉና የራሣቸውን ስሜታዊ ዝንባሌ ተከተሉ። መጥፎ አምል ኮዎች፣ ልማዶች በያይነቱ ተጋባባቸው። የተሳሳቱ አስተሳሰቦችና የማይምነት ሃሣቦች በመካከላቸው ሰፈኑ። ጠቃሚውን ከጐጂው፣ እውነትን ከውሸት መለየት ተሳናቸው። ስለዚህም ሃያሉ አላህ ነቢያቱንና መልዕክተኞቹን ለየሕዝቡ መላክ ያዘ። ነቢያቱም ቀደም ሲል አዳም /ዐ.ሰ/ ያደረሰውን መልዕክት ለሰዎች ለማብራራትና ትምህርት ለመስጠት፣ የረሱትን ለማስታወስ፣ አንዱን አምላክ ብቻ እንዲያመልኩ ለመምራት በአላህ ከማጋራት፣ ጣኦታትንና ቅርጻቅርጾችን ከመገዛት እንዲታቀቡ ለመምከር፣ የተንሰራራባቸ

ውን መጥፎ ልማዶችና የተሳሳቱ አምልኮዎች ለማስወገድ፤ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መንገድ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ትክክለኛ ሕግጋትን በማብራራት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመርዳት ሃያሉ አላህ ወደ ሰው ልጆች ነቢያትን መላክ ጀመረ። ማንኛውም የዓለም ክፍል ሕንድ፣ ቻይና፣ ፋርስ፣ ኢራቅ፣ ግብፅ፣ አፍሪቃ ወይም አውሮፓ የአላህ ነቢያትና መልዕክተኞች ያልተላኩበት አገር የለም። እነዚህ ነቢያት በሙሉ አንድ ዓይነት ተመሣሣይ ሃይማኖት ብቻ ነበራቸው። እሱም ዛሬ «እስላም»(1) ብለን የምንጠራው ሃይማኖት ሲሆን በአመራርና በዓለማዊ ኑሮ ሕግጐቻቸው ቅርጽ በተለያዩ ነቢያት መካከል መጠነኛ ልዩነት ነበር። ይህም ማለት እያንዳንዱ ነቢይ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠውና ጥረት የሚያደርገው በራሱ ሕዝብ ውስጥ በተለይ የተንሰራፋውን መጥፎ ጐን ከሥሩ ለመፈንቀልና የተሳሳቱ አመለካከቶችን በማረም ላይ ነበር ማለት ነው። እነዚህ ሕዝቦች በስልጣኔ፣ በትምህርትና በአስተሳሰብ ጨቅላ ደረጃ ላይ በነበሩበት ዘመን ነቢዮቻቸው ቀላል የሆኑ ትምህርቶችንና ሕግጋትን ይዘው መጡ። በሥልጣኔ፣ በዕውቀትና በአስተሳሰብ እየተራመዱ .... በመጡ ቁጥር የሃይማኖቱ ትምህርቶች ሕግጋትና ስርዓት ከዕድገት ደረጃው ጋር አድማሳቸው ሰፋ። በተለያዩት ነቢያት መካከል የነበረው ይህ ልዩነትም ቅርጻዊ እንጂ ይዘታዊ አይደለም። የነዚህ

---

1 ተራው ሰውና እንዲያውም ብዙዎቹ ምሁራንም ጭምር እስልምና ከነቢዩ መሐመድ መላክ በኋላ የተጀመረ ነው በሚለው የተሳሳተ ግምት ውስጥ ተዘፍቀዋል። ይህ ከጭንቅላታችን መወገድ የሚገባው አስከፊ ጥፋት ነው። እስልምና ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በሰው ዘር ብቸኛው እውነተኛ ሃይማኖት መሆኑን፣ አላህ የላካቸው ነቢያት በሙሉ በሁሉም ዘመንና ሥፍራ ይህንኑ ሃይማኖት ብቻ ያስተማሩ መሆናቸውን ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል።

ሕግጋትና ትምህርቶች መንፈስና መሠረታቸው አንድ ሲሆን፣ ባንድ አምላክ ብቻ ማመን፣/ተውሂድ/ ለርሱ ታማኝ መሆን፣ ሥራን ለርሱ ፍጹም ማድረግና ከዚህች ዓለም ሕይወት በኋላ ሌላ ዘለዓለማዊ ሕይወት መኖሩን ማመን ነው።

የሰው ልጅ እነኚህን ነቢያት የተቀበሉበት ሁኔታ በጣም የሚገርም ነው። ሰዎች ነቢያቱን አስቸግረዋል። ትእዛዛቸውን ከመቀበል አፈንግጠዋል፤ አንዳንዶቻቸውንም ገድለዋል፤ ሌሎቻቸውን ከሃገራቸው እንዲወጡና ለስደት እንዲዳረጉ አድርገዋል። አንዳንዶቹ ነቢያት ዕድሜያቸውን በሙሉ ሰዎቹን ወደ አላህ በመጥራት ቢያሳልፉም ከጥቂት ሰዎች በስተቀር ያመኑላቸው አልነበሩም። እነኚህ ምርጥ የአላህ ተገዥዎች ግን ተልእኮአቸውን ከማራመድ አልቦዘኑም። ትምህርታቸው በመጨረሻ ተሰሚነት አግኝቶ ብዙዎቹ የዓለም ሕዝቦች ተከተሏቸው። ከዚህ በኋላ ሕዝቦቹ ትምህርቶቻቸውን ለወጡ። መጽሐፎቻቸውንም በሐሰት በረዙት። ከራሣቸው ዘንድ አዳዲስ የአምልኮት ሥርዓቶችን ፈለሰፉ፣ ከፊሎቻቸውም አላህ በነቢያቱ ቅርጽ ተመስሎ ወደ መሬት ወረደ አሉ። ከፊሎቻቸው ደግሞ ነቢዩን የአላህ ልጅ አደረጉ። አንዳንዶቹም ነቢዩን ከአላህ ጋር በአምላክነት ያዙ። በዚህ ዓይነት ሰዎች በተለያዩ ዘመናትና በሁሉም ሥፍራ ከነቢያቱ ሞት በኋላ በትምህርቶቻቸው አፈዙ። ቀደም ሲል ሲሰባብሩ ለኖሩት ነቢያት ጣኦትና ምስል ሰርተው አመለኩ። የነቢዮቹን ትምህርቶችና ሕጎቻቸውን በተለያዩ የጅልነት ወግና ልማዶች፣ በተለያየ የሐሰት አምልኮዎችና መሠረት የለሽ ትረካዎች በረዙ። የሰው ልጅ ለራሱ ከፈጠራቸው ምድራዊ ሕጎች ጋር ቀላቀላቸው። ከብዙ ዘመናት በኋላ የነቢያቱን መመሪያና ድንጋጌዎች ከነሱ በኋላ የነበሩት ሰዎች ከከለሱበት ነገሮች መለየት እንኳ አዳጋች እስኪሆን ድረስ ትምህርቶቹን አጣመሙ። እንደዚሁም የነቢያት ሁኔታዎች፣ እውነተኛ ሕይወት ታሪካቸው ከየትም

በተቀራመቱ አፈታሪኮች ውስጥ ቀለጡና እምነት የሚጣልበትና መሠረት ያለው አንዳች ነገር ከሰው ዘንድ ጠፋ። ቢሆንም የነቢያቱ ጥረትና ልፋታቸው ከነአካቴው ከንቱ ስላልቀረ በሁሉም ሕዝብ ዘንድ ሐቅና እውነት በከፊል ተረፈ። የነቢይነቱን ትምህርቶች ቢሰርዙም፣ እንዳስፈለጋቸው ቢከልሉም በአላህ አንድነትና በትን ሣኤ ማመን በሁሉም ሕዝቦች አንድ በሆነ መልኩ ተዛመተ። የዓለም ሕዝብ በጥቅሉ የተወሰኑ የቅንነት፣ የእውነትና የሥነ ምግባር መርሆችን ተቀበለ። እያንዳንዱ ነቢይም ሕዝቡ ሐቅን ለመቀበል እንዲችል አሰልጥኖ አዘጋጀው። ዓለምን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አንድ ወጥ በሆነ ኃይማኖት ይኸውም ለሰው ልጆች በአጠቃላይ ብቸኛ ኃይማኖት እስላም መሆኑን አስተምረው አል ፈዋል።

በዚህ ዓይነት በያንዳንዱ ሕዝብ የተለየና የራሱ የሆነ መል ዕክተኛ ነቢይ ይላክ እንደነበረና መልዕክታቸውም በዚያ በተላ ኩበት ሕዝብ ብቻ ላይ ይወሰን እንደነበር ቀደም ሲል አብራ ርተናል። ይኸውም በዚያን ዘመን ሕዝቦች የተለያዩና የተበታተኑ ሁሉም በራሱ የግዛት ክልል ብቻ የተወሰነ ስለነበር ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በዓለም ላይ በሚገኙት ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የጋራ የሆነና አጠቃላይነት ያለው አንድ ወጥ ሃይማኖት ማሰራጨት አስቸጋሪ ነበር። በተጨማሪም የያንዳንዱ ሕዝብ ሁኔታ ከሌላው ይለያል። አለማወቅ ምድረ ዓለሙን በድፍኑ ያጥለቀለቀ ነበር። ከዚህ አላዋቂነት የሚመነጩ የእምነትና የሥነ ምግባር ብልሹቶች በቅር ጻቸው እንደ የቦታውና ዘመኑ ይለያዩ ነበር። ለዚህ ሁሉ ሲባል ለያንዳንዱ የዓለም ሕዝብ የራሱን ሕዝብ ለማስተማር፣ ወደ ሐቅ መንገድ ለመምራት የሚጥሩ፣ የተሳሳቱ ግምቶቹን የሚያስወግዱ፣ በቦታቸው ትክክለኛ አስተሳሰቦችን ደረጃ በደረጃ የሚተኩ፣ ከጠማማ መንገዶች የሚያግዱትና የላቁ የፍትሕ ሕግጋትን እንዲ ከተሉ የሚጠቀሙ፣ የሕብረተሰቡን አባላት እናት ሕፃን ልጅዋን

እንደምታሣድገው ሁሉ የሚያሣድጉ፣ ነቢይና መልዕክተኛ መላክ የግዴታ አስፈላጊ ነበር። በዚህ ዓይነት ዘዴ የዓለምን ሕዝቦች የማሳደጉና የመንከባከቡ ሂደት ለስንት ሺህ ዓመታት እንደቀጠለ ከአላህ በስተቀር የሚያውቅ ሰው የለም። ሁኔታው በዚህ ቀጥሎ የሰው ልጅ የጨቅላነት ዘመኑን የሚያልፍበት ጊዜ ደረሰ። የሕፃ ንነት ዘመኑ አልፎ ከብስለት ዕድሜ መድረስ ተጀመረ። ብዙዎቹ ማህበራዊ ግንኙነቶች ከኢንዱስትሪና ከንግድ ምጥቀት ጋር ተዛ ምደው ሰዎች ከጃፓንና ከቻይና ሃገር ራቅ ወዳሉት የአውሮፓና የአፍሪቃ ሃገሮች በባህርና በየብስ መጓጓዝ ጀመሩ። ማንበብና መጻፍ በአብዛኞቹ የዓለም ሕዝቦች ዘንድ ተስፋፋ። ሥነ ጥበባትና ሥልጣኔ ተሰራጨ። በሕዝቦች መካከል ንድፈሃሣቦች፣ አስተሳ ሰቦችና ሳይንሣዊ ጉዳዩች ተለዋወጡ። ለተጐራባች ሃገሮች ራስ ምታት የሆኑ ታላላቅ ጦረኞችና የሚፈሩ አቅኚዎች ተነሱ። ብዙ ሃገሮችን የሚያጠቃልሉና የተለያዩ ሕዝቦች የሚኖሩባቸውን ታላ ላቅ ግዛቶች በዓለም ላይ መሠረቱ። በዚህ ዓይነት ከአንድ የበለጡ ሕዝቦች ባንድ ፖለቲካዊ ሥርዓት ሥር ተሰባሰቡና ቀደም ሲል የነበረው መራራቅና አለመተዋወቅ መክሰም ጀመረ። አንድ ወጡ የእስልምና ትምህርትና ብቸኛ ሕጉ ለዓለም በመላ መምጣቱ የሚቻል ሆኖ ተገኘ። የሰው ልጆችን የሁለት ሺ– ዓመታት ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ብናገላብጥ ለሰው ዘር በመላ ሃይማኖት ለመሆን ብቃት ያለው የተሟላ ሃይማኖት ስለመኖሩ ጥያቄ ሲያቀ ርብ እናገኝ ነበር። የቡድሂዝም ሃይማኖት ሥነ ምግባራዊ መርሆ ችን የሚያጠቃልል እንጂ የተሟላ ሃይማኖት አልነበረም። ይሁን እንጂ በቻይና፣ በጃፓንና በመንጐሊያ ሃገር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአፍጋኒስታንና በቡካራ በኩል ተሰራጭቶ ነበር። ከብዙ ዘመናት በኋላም ዛሬ ክርስትና ተብሎ የሚጠራው ኃይማኖት መጣ። ነቢዩ ዒሳ ያስተማሩት ግን ያለጥርጥር የጠራ የእስልምና ትምህርት ነበር።ከርሣቸው በኋላ የመጡት ሰዎች ይህን ሃይማኖት ከራሣቸው

ዘንድ ባመጡት ሐሳብ እንዳሻቸው ከለሱትና ውጤቱ «ክርስትና» ብለው የሰየሙት ያልተሟላ እምነት ብቻ ሆነ። ይህም ሆኖ ግን ክርስትና በፋርስ፥ በአፍሪቃና በአውሮፖ ተስፋፋ። ይህም በዚያን ዘመን ዓለም፣ በሁለንተናዊ መልኩ የተሟላ ሃይማኖት የተጠማ እንደ ነበረ፤ ነገር ግን ይህን የተሟላ ሃይማኖት ስላላገኘ ያልተሟሉ ሃይማኖቶችንም ለመከተል መገደዱን ያሳያል።

# የነቢዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ ነቢይነት:-

ከላይ በገለጽነው ዘመን ለምድረ ዓለምና ለሕዝቦች በመላ አንድ መልዕክተኛ ነቢይ ተላከ። እሣቸውም መሪያችን ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሲሆኑ ከዐረቢያ ተነስተው ለዓለማት በሙሉ ያተሰጡትን መመሪያ፣ እውነተኛ ሃይማኖትና የተሟላ ሕግ እንዲያ ደርሱ አላህ ኃላፊነት ጣለባቸው።

የዓለምን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ብንመለከት የዐረቢያ ሃገር ለዓለም አቀፋዊ መልዕክቱ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ አካባቢ መሆኑን እንረዳለን። ይህ ሐገር በኤሽያና በአፍሪካ መካከል የሚገኝና ለአውሮፓም የቀረበ ነው።በተለይም የሰለጠኑት የአውሮፖ ሕዝቦች ወደ ደቡባዊ የአውሮፖ ክፍል በሚኖሩበት ዘመን ከዐረቢያ የነበረው ርቀት በዐረቢያና በሕንድ መካከል የነበረውን ርቀት የሚመጣጠን ነበር።

ስለዚያ ዘመን የታሪክ መጻሕፍት የዘገቡትን ብናነብ ከዐረብ ሕዝብ ይበልጥ ለዚህ ዓለም አቀፋዊ መልዕክት /ሃይማኖት/ ተስማሚና ተገቢ የሆነ አንድም ሕዝብ በዓለም ላይ እንዳልነበረ እንገነዘባለን። ቀደም ሲል ዓለምን ተቀራምተው ሲገዙ የነበሩት የዘመኑ ኃያላን ኃይሎች እየከሰሙ የመጡ ሲሆን በወቅቱ የነበረው የሀረብ ሕዝብ ግን ወኔው የደነደነና የተሟላ የሞራል ጥንካሬ

ነበረው። ሌሎች ሕዝቦች የሥልጣኔ ምጥቀትና የልማት እርምጃ ስገኙላቸውን ልምድና ባህሎች ተከተሉ። የዐረብ ሕዝብ ግን እስከዚያን ጊዜ ድረስ ለመንደላቀቅና ለዕብሪት የሚያበቃ ሥልጣኔ ላይ አልደረሰም ነበር። ወደ ተልካሻና ርካሽ ባህሪያት ያዘነበለ ሕዝብም አልነበረም። ይህ ሕዝብ በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የተቀሩት የዓለም ስልጡን ሕዝቦች ከተዘፈቁባቸው አስከፊ ሁኔታዎች ሁሉ ፍጹም የጠራ ሕዝብ ነበር። ሥልጣኔ በሞገዱ ያልመታው አንድ ሕዝብ ሊኖረው የሚችለው ሁለንተናዊ ሰብዓዊ ባህሪያት በሙሉ የነበረው ሕዝብ ነበር። ዐረቦች ለፍርሃትና ለስጋት ምንጭ ቁብ የሌላቸው ደፋር ጀግኖች፣ ድህነትን የማይፈሩ ለጋሾች፣ ቃልኪዳን አክባሪዎች፣ ነፃ አሣቢዎች፣ ነፃነት አፍቃሪዎች፣ ከሁሉም በላይ አርነትን የሚያበልጡ፣ ለባዕድ ሕዝብ ገብረው የማያውቁ፥ ክብራቸውን የማስጠበቅ ስሜት በደምሥራቸው ውስጥ የሚመላለስ ኩሩ ሕዝብ ነበሩ። መንደላቀቅና መቀማጠልን የማያውቅ ቀላል ኑሮንም ይኖሩ ነበር።እርግጥ ነው ብዙ መጥፎና አስከፊ ነገሮችም ነበሩባቸው። ታዲያ ለዚህ መጥፎ ገጽታቸው መንስኤው ከሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ጀምሮ ነቢይ ከአላህ ያልተላከላቸው መሆኑ ነው።[2] የሚያሻሽላቸው፣ ሥነ ምግባራቸውን የሚገራና ለሥልጣኔ የሚያበቃቸው መሪም በመካከ ላቸው አልተነሣም። ለዘመናት ነፃ ሆነው በበረሃ ስለኖሩም ማይ ምነት ተስፋፍቶባቸው ነበር። በዚሁ ኋላ ቀር የማይምነት ኑሮ

---

2 ነቢዩ ኢብራሂምና የነቢዩ ኢስማዒል /ዐ.ሰ/ ዘመን ከነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ መላክ በፊት 2500 ዓመታት በፊት ነበር። በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ በዐረብ ውስጥ የአላህ መልዕክተኛ አልተነሣም። መልእክት /ሃይማኖት/ ተልእኮውን ለማድረስና ጥሪውን ለመላው የዓለም ሕዝብ ለማድ ረስ ይፈልግ የነበረው።

በመቀጠል ከእንስሳዊ የጨለማ ሕይወት ወደ ሰብአዊ ብርሃን የሚያወጣቸው ሰው አልነበረም። ይህ ሁሉ ሆኖ ብሩህ አእምሮ ያለው ሰው ካሻሻላቸውና ካስተማራቸው እነሱም ጥሪውን ተቀብ ለው ለላቀ ዓላማና ክቡር ለሆነ ተልእኮ መመሪያውን ከተከተሉ ዓለምን ለመምራት ብቃት ነበራቸው። እንዲህ ያለ ደፋር ጀግናና ታዳጊ ሕዝብ ነበር።

የዐረብኛን ቋንቋ እናስተውል። ይህን ቋንቋ ብናነብና ሥነ ጽሁፉን ብናጠና የመጠቁ አመለካከቶችን ለመግለጽ፣ የመለኮታዊ ዕውቀት ትርጉሞችን በረቀቀ ሁኔታ ለማስተላለፍ፣ ለሕሊና ጠልቆ ለመስማት ከዚህ ቋንቋ ይበልጥ ተስማሚ የሆነ ምንም አይነት ቋንቋ በዓለም ላይ ሊኖር እንደማይችል ያለ ምንም ጥርጣሬ እንገ ነዘባለን።የዚህ ቋንቋ አጭር ፀረፍተ ነገር ከፍተኛ ርዕሰ ጉዳዮችን ይገልጻል። በልቦና ላይ ኃይለኛ ተጽእኖ ያሣድራል።

እንዲህ ያለውን ቋንቋ ነበር በቅዱስ ቁርአን ትርጉም የሚያስ ፈልግ የነበረው። የሃያሉ አላህ የረቀቀ ጥበብና በፍጡራኑ ያለው አጠቃላይ ርህራሄው ሆኖ የዐረብን አገር ለዓለም አቀፋዊው ነቢይነት ከተቀ ሩት የዓለም ክፍሎች ሁሉ ለመምረጥ ፈቀደ።ለዚህ ነቢይነት አላህ የመረጠውን ሰው በዚህች ምድር ላይ አቻ የማይገ ኝለት ክንዋኔውን ቀጥለን እናብራራለን።

## የሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ ነቢይነት

የዓለምን ታሪክ 1400 ዓመታት ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ቴሌግራም፣ ቴሌፎን፣ ባቡር፣ መኪናም ሆነ ማተ ሚያ መሣሪያ ያልነበረ መሆኑን፤ ጋዜጦችና መጽሔቶች የማይታ ተሙበት፣ መጻሕፍት የማይሰራጩበት፣ እንደዛሬው ዘመን ከአ ንዱ ቦታ ወደ ሌላው ለመንቀሣቀስ ትራንስፖርት ያልነበረበት መሆኑን እንረዳለን። ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር መጓዝ የፈለገ

ሁሉ ብዙ ወራት መጓዝ ነበረበት። በዚህ ሁኔታ ዐረቢያ ከተቀሩት የዓለም አገሮች የተቆራረጠች ነበረች። እርግጥ ነው በአካባቢው የፋርስ፣ የሮምና የግብጽ ሀገሮች ይገኙ ነበር። ይሁን እንጂ ሰፋፊ የአሸዋ ክምሮች የዐረቢያን አገር ከነዚህ አገሮች ሁሉ ይለያት ነበር።

እርግጥ ነው የዐረብ ነጋዴዎች ለንግድ ወደነዚህ አገሮች በግመሎቻቸው ጀርባ ላይ ሆነው በመጓዝ መንገዱን ለማቋረጥ ብዙ ሳምንታትና ወራት ይወስድባቸው ነበር። የዚህ ጉዞ ዓላማ ግን ሸቀጦችን ከመሸጥና ከመግዛት የሚያልፍ አልነበረም። የዐረብ ሀገር የመጠቀ ከተማ የትምህርት ማዕከልም ሆነ ቤተመጻሕፍት አልነበረበትም። በሕዝቡ መካከል ዕውቀትም ሆነ ትምህርት አልተ ሰራጨበትም ነበር። ማንበብና መጻፍ ያውቁ የነበሩት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ነበሩ። እነዚህም ቢሆኑ ዕውቀታቸው ከሀገራቸው ውጪ የነበሩትን የዘመኑን ሳይንሶችና ሥነ ጥበቦች የሚያካትት አልነበረም። በአንድነት የሚያስተሳስራቸው መንግ ሥትም ሆነ የሚገዛቸው ሕግ አልነበራቸውም። እያንዳንዱ ጐሣ የራሱ ጌታ ስለነበር ሰዎችን እንዳሻቸው ይዘርፉ ነበር። አጥፊ በሆነ የማይቋረጥ የርስ በርስ ጦርነት ዘወትር ደም ይፈስ ነበር። ለሰው ልጅ ነፍስ ምንም ግድ አልነበራቸውም። የፈለገ ሰው ያስፈለገውን ሰው ይገድልና ንብረቱን በቁጥጥሩ ሥር ያውላል። ምንም ዓይነት የሥልጣኔ ፍንጭ አልነበረባቸውም። ዝሙት፣ መጥፎ ሥራዎች ሁሉ፣ አስካሪ መጠጥና ቁማር ገበያቸው የደራ ነበር። ያለምንም ችግርና ያላንዳች ሀፍረት በአደባባይ ራቁታቸውን ይታዩ ነበር። ሴቶቻቸው እንኳ የተከበረውን የመካ መስጊድ ራቁታቸውን ይዞሩ ነበር። መሥራት የሚፈቀደውንና የተከለከለውን /ሀላልና ሀራምን/ አይለዩም ነበር። በአንዳች መርህ ሕግ ወይም የሕሊና ዳኛ የማይታቀብ ልቅ ነፃነት ስለነበራቸው ለማንም ገዥ መታዘዝንና መመራትን እምቢ አሻፈረ ያሉ ነበሩ። በተጨማሪም ማይምነት

ሥር የሰደደባቸው፣ ለጣኦታት የሚገዙና የሚሰግዱ ጅሎች ነበሩ። መንገድ ሲሄዱ ጥሩ ድንጋይ ያለበት ሥፍራ ካገኙ ጌታቸው አድርገው በመያዝ ያመልኩበታል። ይሰግዱለታል። ይህም ማለት ለማንም ሰው አላጐነብስም ያለው አንገት ለድንጋዮችና ለጣኦታት ይሰግድ ነበር። እነዚህ ግዑዝ ድንጋዮችና ቅርጻቅርጾች ችግራችንን ያስወግዱልናል፣ ምኞታችንንና ተስፋችንን እውን ያደርጉልናል ብለው ይገምቱ ነበር ማለት ነው።

ይህን በመሰለ ሕዝብና እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ከመወለዱ በፊት አባቱ የሞተበት አንድ ሕፃን ተወለደ። ከዚያም እናትና አባቱ በሕፃንነት ዘመኑ ሞቱበት። እንዲህ ባለ የአካባቢ ሁኔታ ውስጥ ወላጆቹና አያቱ በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ ማግኘት የሚችለውን እንክብካቤና አስተዳደግ እንኳ አላገኘም። ሲያድግም ከመሰሎቹ የዐረብ ልጆች ጋር ፍየል ጠበቀ። ለወጣትነት ዕድሜ ሲደርስም ንግድ ሥራ ሠራ። የሚኖረውና የሚውለው ቀደም ሲል የነበሩትን ሁኔታ ከገለጽነው ዐረቦች ጋር ነበር። ማንበብና መጻፍ የማይችል ማይም ነበር። ቢሆንም ግን ልማዶቹ፣ ሥነ ምግባሩ፣ ባህሪውና አስተሳሰቡ ከሕዝቡ ባህል፣ ሥነ ምግባር፣ አስተሳሰብና ባህሪ ፍጹም የሆነ ልዩነት ነበረው። ሲናገር በፍጹም አይዋሽም። በአንደበቱም ሆነ በእጁ አንድም ሰው አያስቀይምም። ለስለስ ያለ ሽጋ ፀባይ፣ አንደበተ ጣፋጭና አንድ ቀን አብሮት የተቀመጠ ሰው ሁሉ የሚወደው ምግባረ ሰናይ ነበረው። ተገቢ ባልሆነ መንገድ የማንንም ንብረት በፍጹም አይነካም ነበር። የታማኝነት፣ የእውነተኛነት የባህሪ ጥራት ዕጣ ክፍሉ ከፍተኛ ነበር። የሀገሬው ሰው ለውድ ንብረታቸው ከፍተኛ እምነት የሚጥሉበት፣ አደራቸውን የሚያስቀምጡበት እሙን ሲሆን እሱም የሰጡትን አደራ ልክ የራሱን ነፍስና ንብረት የሚጠብቀውን ያህል ይጠብቅላቸው ነበር። ሰዎች ሁሉ ከፍተኛ እምነት ይጥሉበትና ይተማመኑበት ስለነበር «አልአሚን» ወይም «ታማኙ» ብለው ይጠሩት ነበር። ላቅመ

አዳም ከደረሰ በኋላ ገላውን ለማንም ሰው ገልጦ የማያውቅ ዓይነ አፋር ነበር። ከተንኮለኛና ከመጥፎ ሠሪ ሰዎች መካከል ተወልዶ ቢያድግም ከተንኮልና ከክፋት ሠሪዎች የራቀ ምግባረ ሠናይ ነበር፤ በተሠማራበት ሥራ ሁሉ ንጹሕና የጠራ፣ ልቦናው የጸዳ፣ ሕዝ ባቸው ሲዘርፍና ደም ሲያፈስ በጣም የሚያዝን፣ በመካከላቸው አለመግባባት ተፈጥሮ ለጦርነት ሲሰለፉ ሕዝቡን ለማስታረቅ የሚጥር፣ ሩህሩህና አዛኝ፣ በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን ችግር የሚካፈል፣ የሙት ልጆችና ሚስቶችን የሚረዳ፣ ረሀብተኛን የሚያበላ፣ መንገደኛ እንግዳን የሚያስተናግድ፣ ችግሩን የሚካ ፈልለት ሰው ነበር። ንቁ ሕሊና የነበረው፣ አርቆ አስተዋይ፣ ጣኦታዊነት መለዮአቸውና ከአባቶቻቸው የወረሱት እምነታቸው ከሆነ ሕዝብ ጋር አብሮ ቢኖርም ግዑዝ ቁሣቁስና ጣእታትን ማምለክ ይጸየፍ ነበር። አላህ ሸሪክ የሌለው አንድ አምላክ መሆኑንና ሊኖረውም የማይገባ መሆኑን፣ በምድርም ሆነ በሰማይ አምልኮት የሚገባው ምንም ነገር አለመኖሩን ልቡ የነገረው ይመስል ለአንድ ፍጡር ራሱን አጐንብሶ አያውቅም ነበር። ይህ ሰው በዚህ ማይም ሕዝብ መካከል በብዙ ድንጋዮች መካከል እንደሚያብረቀርቀው ዕንቁ ወይም መብራት በሌሉት ጨለማ ውስጥ እንደሚበራው ያበራ ነበር።

በሕዝቡ መካከል ንጹህና የመጠቀ ኑሮ ከኖሩ አርባ ዓመት ከሞላቸው በኋላ ሕብረተሰባቸው ላይ ከየአቅጣጫው በሸፈነው በዚህ ጨለማ ተጨንቀው ከዚህ የጅልነትና የሥርዓት የለሽነት፣ የሥነ ምግባርና የሞራል ብልሽት፣ የማጋራትና የጣኦታዊነት ማዕበል ራሣቸውን ለማዳን ፈለጉ። ከተፈጥሮአቸው ጋር የሚስ ማማ አንዳች ነገር የሚያገኙበት አልሆነም። ስለዚህም ከመካ ወጥተው በብቸኝነትና በገለልተኛ ሥፍራ መንፈሳቸውንና ልቦና ቸውን በረሃብ በማጥራት በሕዝባቸው ላይ የሰፈረውን ጨለማ የሚያስወግድ ብርሃን በተስፋ በመጠበቅና በመፈለግ በዝቅጠት፣

በጥፋትና በሥርዓተ አልባነት የተሞላችው ይህች ዓለም የምትሻ ሻልበትን ነገር በመፈለግ ረዥም ቀናት ማሳለፍ ጀመሩ።

ከዚያም ሁኔታቸው ላይ ለውጥ ይከሰታል። ተፈጥሮአቸው ይጓጓለት በነበረው በዚያ ብርሃንም ልቦናቸው በድንገት ይበራል። ቀደም ሲል ባልታየባቸው ኃይልም ይሞላል። ከዚያም ከገለል ተኛው ዋሻ ይወጡና እነኚህ የምታመልኩዋቸውና የምትገዙ ዋቸው ጣኦታት አይጠቅሙም፤ አይጐዱምና ተውዋቸው። ይህ ችን መሬት፣ ጸሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን፣ በሰማያትና በም ድር ያሉትን ኃይሎች ሁሉ ከአንድ አላህ በስተቀር ማንም አልፈጠራቸውም። እናንተንም የፈጠረውና ሲሳይም የሚለግ ሳችሁ እሱ ብቻ ነው። ከርሱ በስተቀር ሌላ አትገዙ። ከርሱ በስተቀር ከሌላ ረድኤት አትፈልጉ፣ ችግራችሁን ከርሱ በስተቀር ሌላ እንዲያስወግድላችሁ አትፈልጉ። የምታካሂዱትን የዝርፊያ፣ የሥርቆት፣ የዝሙት፣ የአስካሪ መጠጥ፣ የቁማር ሥራዎች ሁሉ አቁሙ። በቃላችሁና በሥራዎቻችሁ ሁሉ እውነተኞች ሁኑ። ፍርድ አስተካክሉ፤ ያለአግባብ ነፍስ አትግደሉ፤ የሰውን ንብረትን አትቀሙ፤ ያለ አግባብ ምንም ነገር አትውሰዱ፤ አትስጡም፤ ሁላችሁም ሰዎች ስትሆኑ ሰው ሁሉ ደግሞ እኩል ነው። ክብርና ብልጫ በዘር፣ በቀለም፣ በልብስ፣ በማዕረግ ወይም በሀብት ሣይሆን አላህን በመፍራት በመልካም ሥራነትና በምግባረ ሠናይነት ብቻ ነው። መልካም ሠሪ ሆኖ አላህን በመፍራት ራሱን ከመጥፎ ሥራ ያገደ ሰው ክቡርና በሰብዓዊነቱ ሙሉ የሆነ ሰው እሱ ነው። እንደዚህ ያልሆነ ሰው ግን ምንም ከበሬታና ብልጫ የሌለው ሲሆን በመጪው ዘለዓለማዊ ሕይወትም ዕጣ ቢስ ነው። ሁላችሁም ከሞታችሁ በኋላ ጌታችሁ አላህ ፊት ቀርባችሁ ትጠየቃላችሁ ፍትህ በተሞላበት ችሎቱ ላይ አማላጅ፣ ወዳጅነት ወይም ጉቦ አይጠቅማችሁም። እሱ ዘንድ ስለ ዘር ግንዳችሁ ትልቅነት አትጠ የቁም፤ የሚጠቅማችሁ እምነታችሁና መልካም ሥራችሁ ብቻ

ነው። አማኝ ሆኖ መልካም ሥራ የሰራ ሰው ገነት ሲገባ ይህን ያላደረገ ሰው ግን የከፋ ክስረት ደርሶበት ከእሳት ጓዶች ጐራ ይሰለፋል፤ በማለት ለሕዝባቸው ጥሪ ያደርጋሉ።

ሕዝባቸው ግን ለሌላ ነገር ሣይሆን ከአባቶቻቸው የወረሱትን የጅልነት ባህላቸውንና ወጋቸውን ስለሚያንቋሽሹ፣ ሰዎችን ከጣኦታትና ከቁሳቁስ አምልኮ በመከልከል ለአላህ ብቻ እንዲታዘዙ /ለእስልምና/ ጥሪ ስለሚያደርጉ ብቻ ያስቸግራቸው ጀመር። ያን ባሉም ሰደቡዋቸው፤ አዋረዱዋቸው፤ በድንጋይ መቱዋቸው፤ መላወሻ አጠበቡባቸው። ሊገድሏቸውም አሴሩ። ማድረግ የሚችሉትን አስከፊ የችግርና የሥቃይ ዓይነቶች በነቢዩ ላይ ማድረስን ቀጥለው ከአሥራ ሶስት ዓመት በኋላ ከትውልድ ሀገራቸው ለመሰደድ ተገደዱ። ከዚያም በኋላ ቢሆን ወገናቸው በዚህ ለስደት በዳረገ ሥቃይ ብቻ የሚረኩ አልሆኑም። ነቢዩ ሀገራቸውን ጥለው በተሰደዱበት መዲና ድረስም ማሰቃየቱንና ማወኩን ቀጠሉበት።

እኚህ ቅን፣ የአላህ ታዛዥና አገልጋይ ከወገናቸው የተሰነዘረባቸውን ይህን ሁሉ ሥቃይና መከራ ለምን ቻሉና ታገሱ? ወደ እውነተኛው ቀጥተኛ መንገድ ሊመሯዋቸው ስለፈለጉ ነው። ሕዝባቸው ነቢዩን ከራሣቸው ላይ ንጉስ እናድርግህ ወይም ደግሞ ሀብት ፈልገህ ከሆነም ሀብታችንን ሰብስበን ከሁላችንም በላይ ሀብታም እናድርግህና የያዝከውን ነገር፣ አላህን ብቻ ተገዙ ማለቱን ተወው የሚል ሃሣብ አቅርቦላቸው ነበር። ነቢዩ ግን ይህን ሁሉ እምቢ በማለት ጥሪያቸውን ቀጠሉ። ይህን ሁሉ ስቃይና መከራ የሚቀበሉት ለገዛ ራሣቸው ጥቅም ሣይሆን ለሌሎች ሰዎች ብለው ነው። በድንጋይ እየመቱዋቸውና በመጥፎ ቃላት እየዘለፉዋቸው ነቢዩ ግን ወደ ቀና መንገድ አላህ እንዲመልሳቸው ብቻ ይጸልዩላቸው ነበር። ታዲያ በዚህች ዓለም ላይ ከዚህ ሰው የበለጠ ቅን፣

ሐቀኛና ከራሱ በፊት የሌሎችን ጥቅም የሚያስቀድም ሰው ሊኖር ይችላል ወይ?

ከዋሻው ከወጡ በኋላ በራሣቸው ላይ ስለደረሰው ታላቅ ለውጥ ትንሽ አስተዋሉ። ለሰዎች ይናገሩ የነበረው ንግግር እጅግ በጣም የረቀቀ አገላለጽና የጠለቀ ይዘት ነበረው። ይህን የሚመስል ቃል ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ መሰሉን አንድም ሰው አላቀረበም። እንደሚታወቀው ሁሉ ዐረቦች በቅኔያቸው፣ በዲስኩራቸውና በአንደበተ ርቱዕነታቸው ይኩራሩ ነበርና እንዲህ ያለውን አነጋገር አንድ ምዕራፍ እንኳ እንዲያመጡ ለውድድር ተጋብዘው በመሸነፍ አንገታቸውን ደፉ። ከዚህ ይበልጥ የሚያስደንቀው ደግሞ ይህ ሰው የሚጠቀሙበትና ከሰዎች ጋር የሚነጋገሩበት የቋንቋ ስልት ከሌላው የንግግር ቋንቋ ጋር በአገላለጽ ብሩህነቱም ሆነ በቋንቋ ጥልቀቱ የማይመጣጠን መሆኑ ነው። የዚያን ቃልና የነቢዩን ንግግሮች፣ ዲስኩሮችና ከሰዎች ጋር ያደርጉት የነበረውን ቃለ ምልልሶች ብናነጻጽር በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በጣም ጉልህ ሆኖ ይታያል።

እኚህ የማያነቡና የማይጽፉ በማይሞች መካከል በበረሃ ተወልደው እዚያው ብቻ የኖሩ ነቢይ /ሰ.ዐ.ወ/ ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አንድም ሰው ተናግሮት የማያውቀውን እንዲያውም ከራሣቸውም አንደበት ቢሆን ከአርባ ዓመት ዕድሜያቸው በፊት ሰዎች ሰምተውት የማያውቁትን ንግግሮችና ምክሮች ይዘው መቅረብ ጀመሩ።

እንደዚሁም እኚህ ነቢይ /ሰ.ዐ.ወ/ የሥነ ምግባር፣ የማህበራዊ ኑሮ፣ የፖለቲካና የተቀሩትንም ሰብዓዊ ጉዳዮች ሕግጋት አኖሩ። የሕግጋቱን ምስጢሮችና ጥበባት የበቁ ጠቢባንና የመጠቁ ፈላስፎች የአመለካከት ጥልቀትና የበለጸገ ልምድ ቢኖራቸውም ከከፍተኛ ችግር በኋላ እንጂ ሊደርሱበት አይችሉም። እንዲያውም

ወደፊት የሕግጋቱ ምስጢርና ያለሟቸው ትልሞች ምንነት ለዓላማችን የጠቢባኑ ዕውቀትና ልምድ ከቀን ወደቀን እያደገ በመጣ መጠን እየተገለጸ ይሄዳል። እኝህ የማያነቡና የማይጽፉ ነቢይ ሕጎቹን ከአሥራ አራት ምዕተ አመታት በፊት ያኖሩ ሲሆን ዛሬም ለውጥ ወይም ማሻሻያ የሚያስፈልግ አንድም ቦታ ልናገኝበት አንችልም። አንዲት አንቀጽም መሰረዝ ወይም ማስወገድ አንችልም። ሌሎች ሰው ሰራሽ ሕጎች ግን ብዙ ጊዜ የሚረቁና በተደጋጋሚ የሚሻሻሉ መሆናቸውን ሁሉም ያውቃል።

በ23 ቱ ዓመት አጭር ጊዜ ውስጥ በተጠንቀቅ ይጠባበቁዋቸው የነበሩ፣ ሊገድሏቸው ያሴሩባቸውና ነቢዩን በማሰቃየት ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ አብዛኞቹ ጠላቶቻቸው ነፍስ የሚሰውላቸው ወዳጆቻቸው ለመሆን በቅተዋል። ይህ ሁሉ የሆነው በሥነ ምግባራቸው፣ በታላቅነታቸውና በአርቆ አስተዋይነታቸው እንደዚሁም በመጠቁ መሪ ትምህርቶቻቸው ምክንያት ሲሆን፤ ታላቅና እብሪተኛ የሆኑ ኃይላትን ተጋፍጠው አንበርክከዋል። ድል ሲቀዳጁ ነቢዩ አንድም ሰው አልተበቀሉም። በችሮታቸው፣ በአክብሮታቸውና በጸጋ ነው የተቀበሉዋቸው። አጎታቸውንና የጡት ወንድማቸውን ሐምዛ ኢብኑ አብዱል ሙጠሊብን ገድለው ሆዳቸውን ዘንጥለው ጉበታቸውን ያኘኩትን እንኳ ይቅር ብለዋቸዋል። በድንጋይ የወገሩአቸውንና በማንም ላይ ሳያሴሩ፣ የማንንም ቃል ኪዳን ሳያፈርሱ፣ በማንም ላይ ጦርነትን ሳያካሂዱ፣ ከትውልድ አገራቸው ያሳደዱዋቸውን ሁሉ የምህረትና የአጠቃላይ ይቅርታ ሸማ አጎናጽፈዋቸዋል። ይህን የመጠቀ ባህሪያቸውን በመረዳት ከሁሉም የከፉ ጠላቶቻቸው የነበሩት እንኳ ደፍረው በቃል ኪዳን አፍራሽነት፣ በግፈኝነት፣ በከሀዲነት በፍጹም አይወነጅሏቸውም። በትምህርታቸውና በመመሪያቸው፣ ከአረማዊነትና ከማይምነት ጨለማ አውጥተው በሥርዓትና በስልጣኔ መስከ የፉክክር ቁንጮ የጨበጠ ሕዝብ እስከማድረግ ያደረሱ

ዋቸውን የዐረቦች ልብ የገራላቸውም ይኸው ነበር። ምንም ዓይነት ሕግ ያልገዛቸውን ዐረቦች በከፍተኛ ደረጃ ሥነ ሥርዓትና ሕግ የገዛውና በዓለም ታሪክ ውስጥ አቻ የማይገኝለት ሕዝብ ሆኖ እንዲመጣ አድርገዋል። የማንንም ትእዛዝና መመሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነው የማያውቁትን ዐረቦች በሕይወታቸውና በገንዘ ባቸው ለሚንከባከቡት ታላቅ መንግሥት በቅንነት የሚመሩ ታዛ ዦች አድርገዋል። ምንም ዓይነት ሥነ ምግባርና ሥርዓት ያልነበ ሯቸውን ዐረቦች በሁሉም ሥነ ምግባር የተገሩና በመልካም ባህሪያት የበለጸጉ አድርገዋቸዋል። ዛሬ የዓለም ሕዝብ ዐረቦች ከነቢዩ/ሰ.ዐ.ወ/ በፊት የነበሩበትን ሁኔታና አኗኗራቸውን ከታሪክ መጻሕፍት ገጾች ሲያነብ አድናቆቱ መጠን የለውም። ለኚህ ነቢይ ተጽእኖ፣ በረከትና ለ23 ዓመት ጥሪያቸው ምሥጋና ይገባውና የፋርስን፣ የሮምንና የግብፅ መንግሥታት ያንበረከከላቸውን ኃይል ተጐናጽፈው፤ ክቡርነትንና ሥልጣኔን፣ ሥነ ምግባርና ሰብአ ዊነትን ለዓለም በማስተማር የእስልምናን ትምህርትና ድንጋጌውን /ሸሪአውን/ በኢስያ፣ በአፍሪቃ፣ በሩቅ አውሮፖ ለማስፋፋት ተሰማርተዋል።

ይህ እንግዲህ የማያነቡና የማይጽፉት ነቢይ/ሰ.ዐ.ወ/ በዐረቦች ሕሊና ውስጥ የቀረጹት ስሜት ነበር። ይህ ትምህርት በተቀሩት የዓለም ሕዝቦች ሕሊና ያሣደረው ስሜት ግን ከዚህ የበዛና ይበልጥ የሚያስደንቅ ነበር። በዓለም ሕዝቦች አስተሣሰብ፣ በልምድና በሕጐቻቸው ላይ ታላቅ ለውጥ አስከትሏል። ነቢዩን የተከተለና አርአያቸው ያደረጉትን ትተን ነቢዩን ከመከተል ያፈነገጡ፣ ትእዛዛቸውን የጣሱና በግልጽ ጠላትነት የተጋፈጡዋቸውን እንኳን አስተውለን ብንመለከት ከዚህ የማያነብና የማይጽፍ ትምህርት ተጽእኖ ራሣቸውን ለመከላከል ያልቻሉ መሆናቸውን እናገኛለን። ዓለም የአላህን አንድነት /ተውሂድ/ ረስቶ የነበረ ሲሆን እኚህ የማያነቡና የማይጽፉ ነቢይ /ሰ.ዐ.ወ/ ናቸው እንደገና ያደሱት።

ሌላው ቀርቶ የጣኦታውያንና የአጋሪዎች እምነቶች እንኳ ሣይቀሩ ለአላህ አንድነት /ለተውሂድ/ ለይምሰልም ቢሆን ጥሪ ከማድረግ አይርቁም። በሥነ ምግባርና በሥነ ሥርዓት ረገድ ያስተማሩት መርሆችም እንደዚሁ ብርቱ ኃይል ያላቸው ሲሆኑ በተቀሩት የዓለም ሕዝቦች ሥነ ምግባር ላይም ተጽእኖው ቀጥሏል። በሕግ፣ በፖለቲካ፣ በሥልጣኔና በማህበራዊ ኑሮ ያኖሩት መርህም እንደዚሁ በትክክለኛነቱ፣ በእውነተኛነቱና በጥብቅነቱ ደረጃ አስ ተባባይ ጠላቶቻቸው ሳይቀሩ እውነተኛነት እንዲቀበሉና ከአብነቱ እንዲቀስሙ አድርጉአቸዋል። ይህ ብቻም ሣይሆን እስከዛሬም ከአብነቱ እንደጨለፉ ናቸው።

ይህ ሰው ቀደም ሲል እንዳብራራነው ሁሉ ማይምነትና አርማዊነቱ ሥር በሰደደበት ሕዝብ መካከል የተወለዱ፣ ከፍየል እረኝነትና ከንግድ ሥራ በስተቀር አርባ ዓመት እስከሞላቸው ድረስ ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠሩና ምንም ዓይነት ትምህርት ያላገኙ ሲሆን፣ ይህንን ሁሉ የሙሉእነት ገጽታ እንዴት በአንድ ጊዜ ከአርባ ዓመት በኋላ ማጠቃለል ቻሉ? ይህ ሁሉ ዕውቀትና ጥበብ ከየት መጣላቸው? ይህ ያልተለመደ እንግዳ ኃይል ከዬት ተገኘ? ከጦር መሪዎች ሁሉ አቻ የማይገኝለትና የወጣለት የጦር መሪ፣ ከዳኞች ሁሉ ጠለቅ ያለ ዕውቀት የተካነ ዳኛ፣ ከሕግ አውጪዎች ሁሉ የላቀ ሕግ አውጪ፣ ከፈላስፎች ሁሉ የተራቀቀ ብሩህ ፈላስፋ፣ ከሥነ ምግባርና ከሥልጣኔ አራማጆች ሁሉ የበለጠ መሥራችና አሻሻይ፣ ከሁሉ የተሻለ የፖለቲካ መሪ ሆነው እናገ ኛቸዋለን። ከዚያም የቀኑ ከባድ ሥራና ኃላፊነት ሳያውካቸው ሌሊቱን በሙሉ ለረዥም ሰዓት ጌታቸውን ሲገዙ እናያለን። ለሚስቶቻቸው፣ ለልጆቻቸው፣ ለቤተዘመዶቻቸው ያለባቸውን ግዴታ ተወጥተው፣ ድኾችንና ችግረኞችን ሲያገለግሉ፣ አደጋ የደረሰባቸውንና የሙት ልጆችን ሲያጽናኑ ይታያል። ታላቅ ሥል

ጣን ቢኖራቸውም የድኾችን ሕይወት እንጂ አልኖሩም። ሰሌን ላይ ይተኛሉ። ሻካራ ልብስ ይለብሣሉ። ቋንጣ ይበላሉ። እንዲያውም ምንም ሳይበሉ ብዙ ቀኖች ያልፋሉ።

ከነዚህ አስደናቂ ነገሮች በኋላ –እኔ እንደናንተ አይደለሁም። እኔ ከሰብዓዊ ዝርያ ውጭ ነኝ ብለው ለሰዎች ቢናገሩ እንኳ ማንም ሰው ሊያስተባብለውና ቃሉን አልቀበልም ብሎ መናገሩ ያዳግት ነበር። ሆኖም ግን ይህን አላሉም። ይህ ከተለምዶ ውጭ የሆነ ተሰጥኦ ከገዛ ራሴ ነው አላሉም። ከነዚህ ተሰጥኦዎች አንድም የገዛራሴ አይደለም፤ ያለኝ ነገር ሁሉ የአላህና ከአላህ የተገኘ ብቻ ነው።ይህ ያመጣሁላችሁ ቃልም መሰሉን ለማምጣት ሰውን፣ ጋኔንም ያቃታቸው ይህ መጽሐፍ ከራሴ ከገዛ ጭንቅላቴ የፈለቀ፣ ከአእምሮዬ የመነጨ ሣይሆን የሃያሉ አላህ ብቻ ነው። የምሠራው ማንኛውም ነገር የግላዊ ብቃቴ ውጤት ሣይሆን ሃያሉ አላህ ያደለኝ ነው።ጌታዩ በሚያዘው መሠረት ብቻ እንጂ ምንም ነገር አልሠራም፤ አንዳች ቃልም አልናገርም፤ በማለት ዘወትር ያስረዱ ነበር። ከዚህ ሁሉ በኋላ እንዲህ ባለው እውነተኛ ሰው የማናምን ለምን እንደሆነ፣ ከሃያሉ አላህ የተላከ መልዕክተኛ ነቢይ መሆኑን የማን ቀበልበት ምክንያት ምን እንደሆነ እስኪ ንገሩኝ? ተሰጥ ኦዎቹን ባንድ በኩል ተመልከቱ፤የሰው ልጅ ከርሱ በፊትም ሆነ ከርሱ በኋላ መሰሉን አላፈራም። የእውነተኛነትና የታማኝነት ጐኑንም ተመልከቱ:- ባመጣው መመሪያ አይመጻደቅም። ይህን በማስገኘቱ ዝናና ሙገሳ አይፈልግም። በዚህ ታላቅ በረከት ያከበረው አላህ ስጦታ መሆኑን ይገልጻል። ከዚህ በኋላ የማናም ንበትና የማናረ ጋግጥለት ምን ምክንያት አለ? እነዚህ ብቃቶችና የምሉዕነት ገጽታ ዎች ከአላህ ዘንድ የተሰጠኝ ነው ሲለን፤ የለም አንተው ራስህ የፈጠርከውና ከገዛ ሕሊናህና ከአእምሮህ የመነጨ ነው! የምንለው ለምን ይሆን? ይህ እውነተኛና ታማኝ ሰው በቀላሉ የራሱ አድርጐ ማቅረብ የሚችላቸው ውብ ተግባሮችና የላቁ ብቃቶች ምንጫቸው

ከየት እንደሆነ የሚያውቅ ሰው እንደሌለ እየታወቀ የራሴ ነው ማለቱን እምቢ ብሏል። ከተራው ሰው የተለየ ልዩ የሆነ ተፈጥሮ አለኝ ብሎ የሚናገር ቢሆን ኖሮ ማንም ሰው አባባሉን ማስተባበል የማይችል መሆኑ የታወቀ ነው። ታዲያ ከዚህ ሰው ይበልጥ እውነተኛ ከርሱ ይበልጥ ታማኝና ንጹህ የሆነ ማን አለ?

እኒህ ሰው መሪያችንና ነቢያችን ሙሐመድ አባት አብደላህ /ሰ.ዐ.ወ/ ናቸው። የእውነተኛነታቸው፣ የነቢይነታቸው ማረጋገጫ ነው። ታላላቅ ሥራዎቻቸውና የመጠቁ ግብረገብነታቸው፤ በብሩኩ የሕይወት ዘመናቸው የተከሰቱት ድርጊቶች ...ሁሉም በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ የተረጋገጡ ናቸው። ሐቅንና እውነትን ለመሻት በአመዛዛኝ ሕሊና የሚያነበው ሁሉ ከሃያሉ አላህ የተላኩ ነቢይና መልዕክተኛ መሆናቸውን የገዛ ሕሊናው ያለ ጥርጥር ይመሰክርበታል። ለሕዝቡ ያቀረቡት ቃልም ዛሬ የምናነበው ቅዱስ ቁርአን ሲሆን ትርጉሙን ተገንዝበው በሰፋ ሆድና በማስተዋል የሚያነበው ሰው ሁሉ ከሃያሉ አላህ ዘንድ የተላለፈና የሰው ልጅ መሰሉን ማምጣት የማይችል መጽሐፍ መሆኑን የግዴታ አምኖ ይቀበላል።

## የነቢይነት መደምደሚያ :-

እስልምናን ለማወቅና ቀጥተኛ ጉዳዩን ለማወቅ ከነቢዩና ከቅዱስ ቁርአን ከመማር በስተቀር ሌላ መንገድ አለመኖሩን አሁን ማወቅ ይገባናል። ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ወደ መላው የሰው ልጅ የተላኩ ነቢይና መልዕክተኛ ሲሆኑ በራዕይ፣ በነቢይነትና በመልዕክተኛነት ሰንሰለት የመጨረሻው ቀለበትና መደምደሚያ ናቸው። ሃያሉ አላህ ወደ ሰው ልጆች ማስተላለፍ የሻውን መመሪያና ብርሃን በርሣቸው አማካይነት አስተላልፎአል። በእውነት ሐቅን የሚፈ

ልግና ለሐያሉ አላህ እውነተኛ ታዛዥ /ሙስሊም/ መሆን የወደደ ሰው ሁሉ የግዴታ በነቢያት መደምደሚያ ማመን፤ ያመጡትን መመሪያና ግልጽ መብራሪያዎች በቅንነት መቀበልና መንገዳ ቸውን መከተል ይኖርበታል።

## የነቢያት መደምደሚያነት ማስረጃዎች:-

የነቢይነትን እውነታ የተገነዘብን ከሆነ ነቢያት በየቀኑ የማይ ወለዱ መሆናቸው ግልጽ ይሆንልናል። እንደዚሁም ለያንዳንዱ ሕዝብ በየጊዜው የግዴታ ነቢይ ይኖረዋል ማለትም አይደለም። ያንድ ነቢይ ሕይወት ማለት የሚያስተምረው የመስራትና የማስተ ማር ሕይወት ማለት ነው። መመሪያውና ትምህርቶቹ እስካሉ ድረስ ነቢዩ ሕያው ነው። ሰዎች ከነሱ በኋላ ትምህርታቸውን ስላጠመሙና እንዳሻቸው በስሜታዊ ዝንባሌያቸው ስለበረዙ የቀ ድሞዎቹ ነቢያት ሞተዋል፤ ዛሬ ከመጽሐፎቻቸው ውስጥ አንድም ጥንታዊ ይዘቱንና መሠረታዊ ገጽታውን የያዘ መጽሐፍ አይገ ኝም፤ ተከታዩቻቸውም ቢሆኑ በኦሪጅናል መልኩ የሚገኝ መጽ ሐፍ አለን ብለው የሚናገሩ አይገኙም ማለት ይቻላል። የነኚህ ነቢያት የሕይወት ታሪክም ቢሆን እንደዚሁ ተዘንግቷል። አስተ ማማኝነት ያለው ትክክለኛ አኗኗራቸውን መረዳትም አዳጋች ሆኗል። ሌላው ቀርቶ የተወለዱበትም ዘመን ወይም ሥፍራ፣ የፈጸ ሙዋቸው ክንውኖች እንኳ በቁርጠኝነት መናገር አይቻልም። እን ደ ዚሁም ነቢያቱ ሕይወታቸውን እንዴት እንዳሣለፉ ምን ያዙና ምን ይከለከሉ እንደነበረ ዛሬ ሰዎች በፍጹም ማወቅ አይችሉም። ይህ ነው እንግዲህ ሞታቸው።ነቢያችን ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ግን መመሪያቸውና ትምህርታቸው ዛሬም ሕያው በመሆኑ አሁንም ሕያው ናቸው። አላህ ያወረደላቸው ያ ቅዱስ ቁርአን በኦሪጅናል ቃላቱ አንዲት ፊደሉ ላይ ወይም አንዲት ነጥቡ ላይ ወይም ቀንድ

እና ጋሪው ላይ አንዳች ለውጥ ዝር ሣይልበት መሠረታዊነቱን ጠብቆ ዛሬም በእጃችን እንዳለ ነው። ታሪካቸው፣ አኗኗራቸውና ጠቅላላ ሥራዎቻቸው በመጻሕፍት ተመዝግበውና ተጠብቀው እንዳሉ ናቸው። እነዚህን መጻሕፍት ስናገላብጥ ልክ ዛሬ ነቢዩን በዓይናችን አይተን ንግግራቸውን በጆሮአችን እንደምንሰማ ዓይ ነት ስሜት ይሰማናል።በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እንደ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የሕይወት ክንዋኔዎች ዝርዝር ሁኔታ ተመዝ ግቦ አልተጠበቀም። ስለዚህም በማንኛውም የዕለታዊ ኑሮአችን ሂደት ውስጥ በማንኛውም ጉዳይ እና ሁኔታ ላይ ምን ጊዜም ምሣሌያቸውን መከተልና ከአብነታቸው መቅሰም እንችላለን። ዛሬ የሰው ልጅ ከአላህ ዘንድ የሚላክ ነቢይና መልዕክተኛ ከነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በኋላ መቆሙ ያስፈለገ ለመሆኑ ማስረጃው ይኸው ነው።

አንድ ነቢይ ከሌላው ነቢይ በኋላ የሚላከው ቀጥሎ ካሉት ሶስቱ ምክንያቶች ውስጥ በአንዱ ነው።—

1. ቀድሞ የነበረው ነቢይ ያስተማረው ትምህርት መንምኖ በመከሰሙ እንደገና ለሰዎች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ።

2. ቀድሞ የነበረው ነቢይ ያስተማረው የተሟላ ሣይሆን ቀርቶ ማሟላቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

3. የቀድሞው ነቢይ ትምህርት ባንድ በተወሰነ ሕዝብ ወይም ብሔር ላይ ብቻ የተወሰነ ሆኖ ሌላው ሕዝብ ወይም ሕዝቦች መሰል መልዕክተኛ ነቢይ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ፣ ናቸው የነዚህ ሶስት ምክንያቶች መካከል ዛሬ አንድም አይገኝም።[3]

---

3 አራተኛ ምክንያት ደግሞ አንዱ ነቢይ ጋር ሌላ ነቢይ

1. የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ትምህርት ዛሬም ሕያው ነው። በማንኛውም ጊዜ ሃይማኖታቸው ምን እንደነበረ፣ ከአላህ ዘንድ የመጡት ቅን መመሪያ የቱ እንደሆነ፣ ለሰዎች ያስተጋቡት የኑሮ ዘይቤ የቱ እንደሆነና፣ ሰዎችን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ለመምራት የታገሉባቸው ስልቶች ምን እንደነበሩ ለማወቅ የሚያስችለን ዘዴ ዛሬ በእጃችን ይገኛል። ስለዚህም ትምህርታቸው ሕያውና በቀላሉ ሊደረስበት እስከተቻለ ድረስ ለሰዎች የሚያቀርብ ሌላ አዲስ ነቢይ አስፈላጊ አይሆንም ማለት ነው።

2.ዓለም የተሟላውን የእስልምና ትምህርት በሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይነት የተጐናጸፈ ስለሆነ ትምህርቱ ተጨማሪ ወይም

3. የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይነት ለመላው ዓለም ነው እንጂ ላንድ የተወሰነ ሕዝብ ብሔር ወይም ላንድ ለተወሰነ ዘመን አይደለም። ስለዚህም በተለይ ነቢይ እንዲላክለት የሚያስፈልግ አንድም ሕዝብ የለም። በዚህ ሶስተኛው ምክንያት ይወገዳል።

ከዚህ ሁሉ በመነሣትም ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ማለት የነቢያት ሁሉ ማጠቃለያ ነቢይ

---

የመጀመሪያውን ለማገዝና ለማረጋገጥ አብሮ መላክ የሚችል መሆኑን ነው። ቁርአውስጥ ለዚህ ዓይነቱ ከሁለት ምሣሌዎች በስተቀር ያልተመለከተ በመሆኑና በነዚህ ሁለት ምሣሌዎች ልዩ ሁኔታ ብቻ ላይ በመመርኮዝ አላህ ነቢያት ልክ እነርሱን ለማገዝና ለማጠናከር ከርሱ ጋር ሌሎች ነቢያትን እንደ ሕግ አድርጐ ይልካል ከሚል ማጠቃለያ ላይ መድረስ ስለማይቻል እዚህ ላይ አራተኛ ምክንያት አድርገን አልጠቀስንም። ተቀናሽ አያስ ፈል ገውም። ከነቢዩ በኋላ ሌላ ነቢይ ሊያሟላው የሚያስ ፈልግ ምንም ዓይነት ጉድለትም የለውም። ስለሆነም ሁለተኛው ምክኒያትም ተወግዷል ማለት ነው።

ተብለዋል። ስለዚህም ዓለም ዛሬ ሌላ ነቢይ አያስፈልጋትም። የሚያስፈልጓት ነቢዩ ሙሐመድን ተከትለው ሰዎች ሁሉ ነቢዩን እንዲከተሉ ጥሪ የሚያደርጉ፣ ትምህርታቸውን በሚገባ የሚረዱና ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ በምድር ላይ ነቢዩ ሙሐመድ ባስተማሩት የአላህ ሕግ መሠረት የሚተዳደር መንግሥት የሚመሠርቱ ሰዎች ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## እምነት በዝርዝር

ይህን ምዕራፍ ከመጀመራችን በፊት ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ ያገኘናቸውን ልብጦች እንደገና ጠቅለል አድርገን ማየቱ ተገቢ ይሆናል።

1.እስልምና የአላህን ትእዛዝ መፈጸምና መመሪያውን መከ ተል መሆኑ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን አላህንና ባህሪያቱን፣ ሰዎች እርሱ በሚወደው መሠረት ኑሮአቸውን እንዲመሩ የሚችሉበትን መንገድ፣በመጪው ዘለዓለማዊ ሕይወት በሥራቸው መሠረት የሚከተላቸውን ምንዳም ሆነ ቅጣት እንዴት እንደሆነ በትክክለኛ ሁኔታ ለመረዳት የሚቻለው ከአላህ ዘንድ በተላከ ነቢይ አማካ ይነት ብቻ ነው። የእስልምና ሃይማኖት ትክክለኛ ትርጉም «የነቢዩን ትምህርቶች አምነን በመቀበል በመመሪያው መሠረት አላህን መገዛት » ማለት ነው። ከነቢዩ መመሪያ ያፈነገጠና አላህንና ሕግጋቱን ለማወቅ ነቢዩን እንደ አገናኝ ድልድይ ያልወሰደ ሰው ሁሉ ለአላህ ታዛዥና ለሕጉ ተገዥ ነኝ ቢል እንኳ ሙስሊም ሊሆን አይችልም።

2. ቀደም ባሉት ዘመናት ለተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ነቢዮች ሲላኩ ለያንዳንዱ ሕዝብም ነቢይ ይላክ ነበር። አንዳንድ ጊዜም ላንድ ሕዝብ በተከታታይ በርካታ ነቢዮች ይላኩ ነበር። ለማን ኛውም ሕዝብ ነቢዮች ያስተማሩት ሃይማኖት መጠሪያው «እስልምና» ማለትም «ለአላህ ትእዛዝ ማደር» የሚል ነው።እስልምና በሁሉም ዘመናትና በሁሉም ሕዝብ ዘንድ አንድ ወጥ የሆነ እውነታ ሆኖ የቆየ ሲሆን በተለያዩ ሕዝቦች የድንጋጌ

ማለትም የሕግ አፈጻጸምና የአምልኮ ክንውኖች ላይ አንዳንድ ልዩነቶች ነበሩ። ለዚህም አንድ ሕዝብ በሁሉም የአላህ ነቢያት የማመን ግዴታ ቢኖርበትም የግዴታ ሌላውን ሕዝብ አይከተልም ነበር።

3. ሃያሉ አላህ ነቢዩ ሙሐመድን /ሰ.ዐ.ወ/ ወደ መላው የሰው ልጅ ሲልካቸው አንድ ወጥ የሆነ ድንጋጌ ይኖር ዘንድ ለመላው የሰው ዘር የመረጠውን የእስልምናን ትምህርቶች የተሟላ አድርጓል። የነቢዩ ተልእኮም ባንድ የተለየ ሕዝብ ላይ የሚወሰን ወይም ለተለየ ዘመን ብቻ የተወሰነ ሣይሆን ለሁሉም የሰው ዘርና ለሁሉም ዘመናት ነው። በነቢዩ ሙሐመድ ተልእኮ ከርሣቸው ቀደም ብሎ የተለያዩ ነቢያት ወደ ተለያዩ ሕዝቦች ይዘው የመጡት የተለያዩ የእስልምና ድንጋጌዎች የሚሻሩት ተሽረዋል። እስከ ትንሣኤው ቀን ድረስም ሌላ ነቢይ ወይም ሌላ ድንጋጌ በፍጹም አይኖርም። እስልምናም ዛሬ ከርሣቸው በኋላ ከአላህ ዘንድ የተላከና በርሱ ማመን ግዴታ የሚሆንን ሰው በፍጹም የማይመጣው የነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች ብቻ የሚመሩበት ሃይማኖት ነው። አንድ ሰው በዚህ ካላመነ ከሃዲ /ኢአማኝ/ ይሆናል።

ቀጥለን ደግሞ እንድናምንባቸው ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ያዘዙንን ነገሮች እናብራራለን።—

## በአላህ ማመን:-

ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ እንድናምንበት ያዘዙን የመጀመሪያውና ዋነኛው ነጥብ «ላኢላሀ ኢለሏህ» የሚለው ቃለተውሂድ ሲሆን ትርጉሙም «ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም» ማለት ነው። ይህ የእስልምና እምነት የታነጸበት፣ ሙስሊሙን ከከሃዲው፣

ከአጋሪውና ከአማኙ የሚለይ መሪ ቃል ነው። በሚያምንበትና በማያምንበት ሰው መካከል ከፍተኛ ልዩነት የሚያስከትል መሠረታዊ ቃል ነው። የሚያምኑበት ሰዎች በዛሬው ሃላፊ ዓለም ሕይወትም ሆነ በነገው ዘለዓለማዊ ቀሪ ዓለም ሕይወት ድል፣ ስኬት፣ ተድላና ልዕልና ከተቀዳጁት ክፍል ሲሆኑ፤ ይህን ቃላት የሚያስተባብሉና ያፈነገጡ ደግሞ በዛሬውም ሆነ በነገው ዓለም ሕይወት ከስረትና ውርደት ከሚከናነቡ ክፍል ናቸው።

ይህ ከፍተኛ ልዩነት በሁለቱ ክፍሎች መካከል የሚከሰተው አንደኛው ሰው ቃሉን በአንደበቱ ስለተናገረ ብቻ አይደለም። ለምሣሌ በወባ በሽታ ብንያዝ «ክሎሮኩዊን» «...ኪኒን» ብለን በምላሳችን ስለተናገርን ብቻ በተግባር መድኃኒቱን ካልወሰድን በስተቀር ሚሊዮን ጊዜ ቃሉን ብንደጋግም አንፈወስም። እንደ ዚሁም «ላኢላሀ ኢለሏህ» የሚለው ቃልም ትርጉሙን በሚገባ ተገንዝበን ወይም አውቀን ግን ያመንበት ምን እንደሆነ ሳናውቅ ወይም በዚህ እምነታችን በራሣችን ላይ የወሰድነውን ታላቅ ኃላፊነት ካልተረዳን ምንም አይጠቅመንም። ሀቁን ለመናገር እውነተኛውን ልዩነት መረዳት የምንችለው የዚህ ቃል ትክክለኛ ትርጉም በሕሊናችን ተቀርጾ እውነተኛነቱን ያለ ምንም ማወላወል በቁርጠኝነት ስናረጋግጥ ብቻ ነው። ስለእውነተኛነቱ ያለን እምነት እሳት የሚያቃጥል ነገር ስለመሆኑ ወይም መርዝ የሚገድል ነገር ስለመሆኑ ካለን እምነት ያላነሰ የጸና መሆን አለበት። ይህም ማለት ስለ እሳት ምንነት ያለን ግንዛቤ እጃችንን እንዳንከትበት እንደ ሚያግደን ሁሉ ስለ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ያለን ግንዛቤም ምንም ዓይነት በአላህ የማጋራት፣ የማስተባበል ወይም የመካድና በእምነትም ሆነ በተግባር ከዚህ የእምነት ግዴታዎች እንዳንወጣ ራስን ማገድ አለብን ማለት ነው።

# «የላኢላሀ ኢለሏህ» ትርጉም:-

«ላኢ.ላሀ ኢ.ለሏህ» ማለት ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ማለት መሆኑን ተናግረናል። አሁን ደግሞ «አምላክ» /ኢ.ላህ/ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ አለብን። «አምላክ» ማለት በቋንቋ ትርጉሙ «አምልኮት የሚገባው» ማለት ሲ.ሆን በልዕ ልናው በግርማ ሞገሱና በሃያልነቱ አንጻር ሰዎች ሊ.ገዙትና ሊ.ያመ ልኩበት የተገባ ማለት ነው። እንደዚ.ሁም «መጠኑና ወሰኑን የሰብአዊ አእምሮ መረዳት የሚያዳግተው ሃያልነት ያለው ኃይል የሚ.ል ትርጉሙንም ያጠቃልላል። በተጨማሪም «ከማንም» ፍጡር አንዳች ጉዳይ የሌለውና ፍጡራን በሙሉ ለአጠቃላይ ጉዳዮቻቸው ላይ ሁሉ የርሱን ረድኤት ለመፈለግ የሚገደዱበት የሚል ትርጉምም ይዟል። በዚ.ህ ትርጉም ሥር «ከሰዎች እይታ የተሰወረ ማለትም ኃይሉ በዓይን የማይታይ» የሚ.ለውም ይጠ ቃለላል። «ኸዳ» የሚ.ለው የፔርሽያ ቃል «ዴኻ» የሚለው የሕንድ ቃልና «ጐድ» የሚለው የእንግሊ.ዝኛ ቃል ከሞላ ጐደል ይህንኑ ትርጉም ያስተላልፋሉ። እንደዚ.ሁም በተቀሩት የዓለም ቋንቋዎችም መሰል ቃል ይኖራል።

«አሏህ» የሚለው የዓለማት አንድ ፈ.ጣሪ አምላክ የተጸውኦ ስም ነው። «ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም» ማለት በዚ.ህ ዩኒቨርስ ውስጥ ሰዎች ሊገዙት፣ ትእዛዙን ሊ.ፈ.ጽሙና ሊ.ያመ ልኩበት የሚገባ ከአላህ በስተቀር ማንም የለም። የዚ.ህ ዩኒቨርስ ባለቤትና ገዥው እርሱ ብቻ ነው። ከርሱ ውጭ ያለው ሁሉ የርሱን ረድኤት የግዴታ መጠበቅ አለበት። ከሕዋሳዊ ስሜቶች ግንዛቤ ውጭ በመሆን እርሱነቱን ለመገንዘብ ሰብአዊ አእምሮ ግራ ይጋባል ማለት ነው።

## የ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ጽንሰ ሃሣብ:-

ከላይ የተመለከትነው «የላኢላሀ ኢለሏህ» የቋንቋ ትርጉም ሲሆን የጽንሰ ሃሣብ ይዘቱን ደግሞ ቀጥለን እናብራራለን:- ከጥን ታዊ የታሪክ ዘመኑ ጀምሮ ስለ ሰው ልጅ ሁኔታ የደረሱንና በዚህ ዓለም ላይ የተስተዋሉት ሁኔታዎች – ያለፉትም ሆኑ አሁን ያሉት የሰው ልጅ ለራሱ የሚያመልከው አምላክ ያልያዘበት አንድም ዘመን እንዳልነበረ ያመለክቱናል።እንደዚሁም ዛሬ በተለያዩ የዓ ለም ክፍሎች የሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ የሰለጠኑትም ሆኑ ያልሰ ለጠኑት ለራሣቸው የሚያምኑትና የሚገዙት አምላክ አላቸው። ይህም አምላክን የማሰብ ዝንባሌ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ የተጸነሰና የተደላደለ ነገር መሆኑ ከአማልክቱ መካከል ለራሱ አንድ አምላክ ይዞ እንዲገዛው የሚያስገድደው ነገር እንዳለበት በሚገባ ያመለክተናል። ለዚሁ ሁሉ ምክንያት ምንድነው? ይህን ማወቅ የምንችለው የገዛ ራሣችንና የመላውን የሰው ልጅ ሁኔታ ስናስተውል ነው።

ሰው የተፈጠረው በተገዥነት ላይ ሲሆን በተፈጥሮው ራሱን የማይችል፣ ለሕልውናው በራሱ ላይ የማይተማመን፣ ረድኤት የሚሻና ደጋፊ የሚፈልግ አቅመቢስ ፍጡር ነው። ለመኖር የሚያስ ፈልጉት ነገሮች በሙሉ እንዳሻው በጁ የማይገኙ ስለሆኑ አንዴ ቢያገኛቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲነፈግ ይኖራል። ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችም እንደዚሁ አንድ ጊዜ ሲያገኛቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ ከቁጥጥር ሥር ባለመሆናቸው ማግኘት ሣይችል ሲቀር ይስተ ዋላል። ይህም ማለት የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ ዝግጁ ሆነው በቁጥጥሩ ሥር አይገኙምና አቅመ ውስን ነው።

ጉጂ፣ ተስፋ አስቆራጭና ፐረቱን ከንቱ የሚያስቀሩ በርካታ ነገሮች የሥቃይ፣ የመከራና የበሽታ ውርጅብኝ ሲያደርሱበት ከራሱ ለመከላከል ይፈልጋል ታዲያ አንድ ጊዜ ሲወገዱለት ሌላ ጊዜ ደግሞ ተሸንፎ ሲንበረከክላቸው ይታያል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የነዚህ አፍራሽ ነገሮች በሰው ላይ መድረስና አለመድረስ ማስወገድ የመቻልና ያለመቻል ሁኔታ በራሱ በሰው ልጅ ቁጥጥር ሥር አለመሆኑን ነው።

አያሌ የተፈጥሮ ክስተቶችን ሲመለከት በግርማ ሞገሳቸው፣ በግዙፍነታቸውና በሐያልነታቸው ከፍተኛ የአድናቆት ስሜት ይመስጣል። ተራሮችን፣ ወንዞችን፣ አስፈሪ የሆኑ ጉጂ አራዊትን ሲመለከት፣ የአውሎ ነፋስ፣ የወንዞች መውረድና የመሬት መንቀጥቀጥን ሲያስተውል፣ የነጐድጓድና የመብረቅ፣ የደመና ጥቁ ረት፣ የዝናም ... ትእይንቶች ከፊቱ ሲደቀኑ እነዚህ ክስተቶች ምን ያህል ሃያልና ብረቱ እንደሆኑ ይገነዘባል። የሰው ልጅ ከነዚህ የተፈጥሮ ክስተቶች አንፃር ደካማና አቅመቢስ መሆኑን ይረዳል።

እነዚህን የተለያዩ ትእይንቶች ሲያስተውል፣ ስለ ራሱ ድክመትና አቅም የለሽነት ሁኔታ ሲመለከት፣ ከሌላ ረድኤት የሚጠብቅ ተረጂና ደካማ ፍጡር የመሆኑ ስሜት በውስጡ ይጸነሣል። ይህ ስሜት በልቡ ውስጥ በመፈጠሩም እነዚህን ግዙፍ ነገሮች የመቆጣጠር ኃይል ያለው አምላክ የመኖር ግንዛቤ ይጸነስ በትና ለኃያልነቱና ለግርማ ሞገሱ ያለው ስሜት ለዚህ አምላክ ራሱን ዝቅ አድርጐ እንዲገዛ፣ ለትእዛዙ እንዲያድር፣ ጠቃሚ ነቱን በመረዳት ረድኤቱን ለመለመን እጁን ወደርሱ እንዲዘረጋ፣ ጉጂነቱንም በማወቅ ከቁጣው እንዲርቅና እንዲፈራው ያስገድደዋል።

ሰው በዝቅተኛው የማይምንት ደረጃ ላይ እያለ እነዚህ የተፈጥሮ ክስተቶች ኃያልና ታላቅ መስለው ይታዩታል። ባንዱ

ወይም በሌላ መልኩ የሚጠቅሙት ወይም የሚጐዱት ይመስ ለውና እነሱን «አማልክት» አድርጐ ይወስዳቸዋል። ስለዚህም እንስሳትን፣ ወንዞችንና ተራሮችን ሲያመልክና ሲሰግድላቸው፣ መሬትን፣ እሳትን፣ ዝናምን፣ ንፋስን፣ ጨረቃን፣ ጸሐይን፣ ከዋክብትን ወዘተ ሲገዛ ይስተዋላል።

ይህ ማይምነት ትንሽ ለቀቅ አርጐት የዕውቀትና የብርሃን ጨረፍታ ሲነካው ግን እነዚህ ክስተቶች በሙሉ እንደሰው ደካሞ ችና አቅመቢሶች መሆናቸውን፣ ትላልቅና ግዙፍ እንስሳት ጥቃ ቅን እንስሳት እንደሚሞቱ ሁሉ መሞታቸውን፣ ታላላቅ ወንዞች የሚደርቁ፣ ውሃቸው የሚጠፋና ሁልጊዜ ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ የተጋለጡ መሆናቸውን፣ ሰው ተራሮችን ንዶ እንደሚ ያፈራርሳቸው፣ መሬትም ለራሷ ለምታ ከእርሷ እጽዋትን ማው ጣት እንደሚችልና ውሃ እንደሚያስፈልጋት፣ በቂ ውሃን ካላገኘች እንደምትደርቅ፣ ውሃም በራሱ ከደመና እንደማይወረድና ደመና ውን የሚነዳ ነፋስ እንደሚያስፈልገው፣ ንፋሱም ቢሆን ተገዛ ራሱ መንፈስ የማይሻልና ሌሎች ምክንያቶች የሚያስፈልጉት መሆኑን ይገነዘባል። እንደዚሁም ጸሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለተወሰኑ ሕጐች የሚገዙና ከተዘረጋላቸው ውስን ቅንብር ቅንጣት ያህል ዝንፍ ብለው መንቀሣቀስ የማይችሉ መሆናቸውን ይረዳል። በዚ ህን ጊዜም እነዚህ የተፈጥሮ ክስተቶች ኃይላቸውን የሚያመነጩት በዩኒቨርሱ ውስጥ ከተፈጠሩት፣ ክስተቶችን በቁጥጥራቸው ስር አውለው ከሚመሩትና ሁሉንም ነገር ከሚያስተዳድሩት ኃይሎች ነው ወደሚል ጭብጥ ያመራል። በዚህም በሰው አእምሮ ውስጥ በርካታ በሆኑና በተሰወሩ አማልክት የማመን ዝንባሌ ይጸነሣል። ብርሃን፣ አየር፣ ውሃ፣ በሽታ፣ ጤንነት፣ ውበት፣ አስቀያሚነት ...እያንዳንዳቸው የራሣቸው የሆነ ልዩ አምላክ አላቸው የሚል ስሜት ያድርበትና በሃሣብ የፈጠረውን ቅርጽ ያመልካል።

ከዚያም የዕውቀት ብርሃኑ እየጨመረ ሲሄድ የዩኒቨርስ ሥርዓት በሕግ የሚመራ፣ የተጠናከረና የጸና ቅንብር ያለው መሆኑን ይረዳና:- ንፋስ እንዴት እንደሚነፍስ፣ ዝናም እንዴት እንደሚጥል፣ ከዋክብት በሰማያት ውስጥ እንዴት እንደሚጓዙ፣ ወቅቶች እንዴት እንደሚለዋወጡ፤ አትክልትና አዝርዕት እንዴት እንደሚያፈሩ፣ የተለያዩ ብዙ ኃይሎች በዚህ ሥርዓት ውስጥ እርስ በርሳቸው በመተጋገዝ እንዴት እንደሚሰሩ ያስተውላል። ይህ ሕግ ፍጹም የጸና ከመሆኑ የተነሣ በዩኒቨርስ ውስጥ ለሚከ ናወነው ለያንዳንዱ ተግባር በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ ሣቢያና ውጤ ቶች ያላንዳች መዘግየትና መሰናከል ሲቀናበሩና አንዱ ሌላውን ሲያሟላ ይመለከታል። በዚህም ዓይነት የዩኒቨርስን አንድ ወጥ የሆነ ጠንካራ ሥርዓት በማስተዋል አጋሪ /ሙሽሪክ/ የሆነ ስሙም ይህ ዩኒቨርስ አንድ አምላክ ብቻ ያለው መሆኑንና አምላኩም ከአማልክቱ ሁሉ ታላቁ እነሱን የሚያስተዳድርና የሚመራቸው መሆኑን፤ እነኚህ አማልክት የየራሣቸው ነፃ ስልጣን ቢኖራቸው ኖሮ የዩኒቨርስ ሥርዐት ተዛብቶ ጥፋትና ሥርዓተ አልባነት ያንሰ ራፋ እንደነበር ለመቀበል ይገደዳል። ይህን ታላቅ አምላክም «አላህ» ወይም «ፔርሚሸዋር» ወይም «ኹዳይ ኹዳይጋን» ወይም «እግዚአብሔር» ወይም «ጐድ» .. ወዘተ ብሎ ይጠራል። ይሁን እንጂ እነዚያን ትናንሽ አማልክት በአምልኮት ከርሱ ጋር ያጋራቸዋል።አምላክነትን ልክ እንደዚህች ዓለም ንጉሥነት አድ ርጐ ይወስዳል።ልክ የዚህ ዓለም አንድ ንጉስ የሚተማመንባ ቸው ግዛቱን ለማስተዳደር እንደሚያማክራቸውና ብዙ የሥልጣን ቦታ ዎችን እንደሚሰጣቸው አያሌ ሚኒስትሮች አይነት ኖሮት ትልቁ አምላክ ዩኒቨርስን ለማስተዳደር በታናናሾቹ አማል ክት ይታገ ዛል፤ ስለሆነም እርሱ ዘንድ ለመድረስ ወይም ለመቅረብ እነኚህን ትናንሽ አማልክት ማስደሰት አስፈላጊ ስለሆነ የሰው ልጅ እነሱን ማምለክ፣ ለነርሱ መገዛት፣ ቁጣቸውን መጠንቀቅና ወደ ትልቁ

አምላክ ለመድረስ እንደአገናኝ አድርጐ መውሰድ፣ እንዲረዱትና እንዲደግፉት የጥያቄ እጁን ወደነርሱ መዘርጋት፣ በስለትና በቁርባን እነርሱን ማስደሰት አለበት ብሎ ያስባል። ከዚያም የሰውልጅ እውቀት እየመጠቀና ግንዛቤው እየጨመረ ሲሄድ የአማልክቱ ቁጥር እየቀነሰ ይታየዋል። ማይሞች አማልክት አድርገው የያዟቸውን አማልክት አንድ በአንድ መፈተሸና መመ ራመር ይጀምራል።አማልክት ሣይሆኑ እንደተቀሩት ፍጡራን በኃይልና በእኳኋን ከነሱ ያነሱ ባይሆኑም እነሱም ፍጡራን መሆናቸውን ይረዳል። በዚህም ይተዋቸውና አንድ በአንድ እነሱን ማምለክ ያቆማል። በመጨረሻም ካንድ አምላክ በስተቀር ሁሉንም እያስቀረ ይመጣል። ቢሆንም ስለዚህ አንድ ብቸኛ አምላክ ያለው የተሳሳተ አመለካከት ጭንቅላቱ ውስጥ መኖሩ ይቀጥላል። አንዳ ንድ ሰው አላህን እንደኛው ያለ አካል አድርጐ አጥን ጥግ ይዞ ሰዎች ሲያመልኩትና ሲያጐነብሱለት የሚመለከት ይመስለዋል። ሌሎቹ ደግሞ አላህ ሚስትና ልጆች ኖረውት /ሰው እንደሚኖረው ሁሉ/ የሚዋለድ ይመስላቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ አላህ በሰው ቅርጽ ወደ ምድር ይወርዳል ይላሉ። አላህ ዓለምን ፈጥሮ እን ዲሠራ ካደረገው በኋላ ስለዚህ ዩኒቨርስ ጉዳይ ምንም የሚያገባው የለም ብሎ በሆነ ቦታ ዕረፍት ላይ ይገኛል የሚሉም ይገኛሉ። አላህ ዘንድ የጻድቃንና የቅዱሳን መናፍስት አማላጅነት መያዝ የግዴታ አስፈላጊ ነው የሚሉ ክፍሎችም አሉ። በአምልኮት ጊዜ የግዴታ እፊታችን መደቀን አለበት የሚሉ የአላህ /ሱ.ወ/ ቅርጽ በሕሊናቸው ውስጥ የሚመላ ለስባቸው ሰዎችም አሉ።በአላህ አንድነት /ተውሂድ/ የሚያምን ቢሆንም እንኳ እነዚህን የመሳሰሉ ደካማ ሃሣቦች ሕሊናው ውስጥ ይቀራሉ። በነሱም ምክንያት በማጋራት /በሽርክ/ እና በክህደት /በኩፍር/ እና በክህደት ረግረግ ውስጥ ይዘፈቃል። ይህ ሁሉ ያለማወቅ ውጤት ነው።

የነዚህ ደረጃዎች ሁሉ መጨረሻና ከፍተኛው «ላኢላሀ ኢለሏህ» ነው። ይህም ሃያሉ አላህ ወደ ነቢያቱና ወደ መልዕክተኞቹ በሙላ በየዘመኑና በየአገሩ ለሰው ልጆች ያደርሱ ዘንድም ያስተላለፈው ዕውቀት ነው። ይህ ዕውቀት በመጀመሪያ ለአዳም ተሰጠ። ከዚያም ለኑህ፣ ለኢብራሂም፣ ለሙሣና ለሌሎቹም ነቢያት ተሰጠ። በመጨረሻም የነቢያቱ መደምደሚያ የሆኑት ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ይዘውት መጡ። ዕውቀቱ አንዳች የማይ ምንት ነውር ያልደረሰበት ፍጹም የነጠረ ዕውቀት ሲሆን የሰው ልጅ ከላይ ባወሳናቸው የክህደት፣የማጋራትና የጣኦታት አምልኮ መልኮች የተለከፈው ከነቢያት ትምህርት በማፈንገጡና በራሱ ስሜታዊ ግንዛቤና በአእምሮው ላይብቻ በመመርኮዙ ነው። ይህች ጠቅለል ያለች አንቀጽ ያቀፈችውን ቋሚ እውነታና የመጠቀ

ትርጉሙን ቀጥለን እንመልከት:-

1. ከሁሉም የሚቀድመውና ዋነኛው ነጥብ ስለመለኮት ያለው አመለካከት ይሆናል። ይኸውም ይህ ከሰው ልጅ አእምሮ ግንዛቤ በላይ በመሆኑ መነሻና መድረሻውን ማወቅ አዳጋች የሆነው፣ ቀደም ሲል ተፈጥሮ ከቁጥር በላይ የሆኑ ፍጡራን ያሉበት፣ በየዕለቱ የሰውን አእምሮ የሚያጥለቀልቁ ክስተቶችና ፈጣሪዎች የሚከሰቱበትና የሚደጋገሙበት፣ ግዙፍ ዩኒቨርስ አምላክ የማይ ሞት ሕያውና ወሰን የለሽ ከፍጡራኑ ምንም የማይፈልግ፣ ራሱን በራሱ የተብቃቃ፣ ሁሉንም ቻይ፣ የማይሳሳት፣ ጥበበኛ፣ ምንም የማይሰወረው አዋቂ፣ ምንም የማያቅተው አሸናፊ ወሰን የለሽ ኃይል ያለው፣ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ የጠራና በርሱ ነገር ውስጥ ማንም ጣልቃ ሊገባ የማይችል አምላክ መሆን አለበት።

2. እነዚህ የአምላክነት ባህሪያት በሙሉ ባንድ እርሱነቱ ውስጥ ብቻ የግዴታ መጠቃለል አለባቸው። ሁለት አማልክት በእኩልነት የሚገለጹበት ባህሪያት ሊሆኑ አይችሉም። ሁሉንም አሸናፊና በሁሉም የበላይ ሊሆን የሚችለው አንድ ራሱ ብቻ መሆን ይኖርበታል። እነዚህ ባህሪያት በተለያዩ አማልክት ዘንድ ሊከፋፈሉም በፍጹም አይችሉም። አንዱ አስተዳዳሪ፣ ሌላው ዐዋቂ፣ ሌላኛው ደግሞ ሲሣይ መጽዋች ከሆነና በመካከላቸው ህብረት ካልኖረ ዓለም የግዴታ ውድመትና ጥፋት ይከተለዋል። እንደዚሁም ባህሪያቱ ካንድ ወደ ሌላ የሚተላለፉ ማለትም አንድ ጊዜ አንዱ አምላክ ሆኖ ሌላ ጊዜ ደግሞ በተራው ሌላው አምላክ ሊሆንም አይችልም። ሕልውናውን ማስጠበቅ የማይችል አምላክ ከየት መጥቶ ለሌላው ሕይወት መለገስ ይችላል? አምላክነቱን ማስከበር የማይችልም ይህን ዩኒቨርስ ማስተዳደርና እንዳሻው ማድረግ አይችልም። በአጠቃላይ የሰው ልጅ በቀሰመው የዕውቀት ብርሃን መጠን የአምላካዊነትን ባህሪያት ካንድ በላይ የሆኑ አማል ክት አጠቃለው መያዝ በፍጹም እንደማይችሉ ያለው እርግጠ ኛነትና ግንዛቤ እየጨመረ ይሄዳል።

3. ስለ አምላክ ይህን የተሟላ ትክክለኛ ግንዛቤ በአእምሮአችን ውስጥ ይዘን ይህን ዩኒቨርስ ብንመለከት የምናያቸው ወይም የምንዳስሳቸው ወይም የምናውቃቸው ነገሮች ሁሉ በነዚህ መለኮ ታዊ ባህሪያት የማይገለጹ መሆናቸውን፣ በዩኒቨርሱ ውስጥ የሚ ገኙ ነገሮች በሙሉ ራሣቸውን የማይችሉና ከሌላ ረድኤት የሚፈ ልጉ፣ ኖረው የሚሞቱ በጉም መጥፎም የሚሆኑ፣ ባንድ ዓይነት ሁኔታ ላይ ብቻ ጸንተው የማይቀሩ፣ በገዛ ራሣቸውና በገዛ ፍቃዳቸው ምንም ማድረግ የማይችሉ፣ በነርሱ ላይ ተፈጻሚነት ካላቸው የተፈጥሮ ሕግጋት ውጭ መሆን የማይችሉ፣ ሁሉም በአኳኋናቸው ማንኛቸውም አምላክ እንዳልሆነ የሚመሰክሩ፣ አንዳች ዓይነት የአምላክነት ባህሪ እንደሌለባቸው፣ ይብዛም ይነስ

በዚህ ውስጥ ምንም ሚና የሌላቸው መሆኑን እንረዳለን። ይህ ነው ከ... በስተቀር አምላክ የለም ለሚለው ትርጉሙ።

4. በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ካለው ነገር ሁሉ አምላክነትን ይብዛም ይነስ ከነጭራሹ ካስወገድን ዘንዳ የአምላክነትን ባህሪያት በሙሉ የሚያጠቃልል፣ ከሁሉም በላይ የሆነና እርሱ ብቻ በነዚህ ባህሪያት የተካነ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን አምኖ መቀበል የግዴታ ይሆናል። ይህም የ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ትርጉም ነው። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ማለትም ይህ ነው።

የላቀው ዕውቀትና የተሟላው ዐዋቂነትም ይህ ነው። በዚህ ረገድ የበለጠ በተመራመርን ቁጥር የዕውቀት መነሻና መድረሻውም ይኸው መሆኑን እንገነዘባለን።ስለ ዩኒቨርስ እውነታዎች የሚያጠኑትን እንደ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ አስትሮኖሚ /ሥነፈለክ/፣ ጂኦሎጂ፣ ባዮሎጂ፣ ዚኦሎጂ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ፖለቲክስ፣ ሶሺኦሎጂ .....ያሉትን የሳይንስ ዘርፎች ብንወስድና በጥልቀት ብናጠናቸው ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን የበለጠ ማመንና ማረጋገጥ እንችላለን። በያንዳንዱ የሳይንሳዊ ምርምር እርምጃችን ይህን ወሣኝ እውነታ ካስተባበልን በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር ትርጉም የለሽ መሆኑ ይገለጽልናል።

# የተውሂድ እምነት በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ያለው ተጽእኖ

ቀጥለን ደግሞ በተውሂድ ማመን በሰው ልጅ ሕይወት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንዳለውና በዚህ ተውሂድ የማያምን ሰው ውድቀትና ክስረት ለምን ዕጣው እንደሆነ እናብራራለን።

1. በዚህ ቃለ ተውሒድ የማያምን ሰው አስተሳሰበ ውስን መሆን አይችልም። ሰማያትንና ምድርን በፈጠረውና በዓለም ላይ ያለው ሁሉ ንብረቱ በሆነው፣ ሲሣይን ሰጭና ተንከባካቢ በሆነው የዓለማት ጌታ ያምናል። ከዚህ እምነት በኋላ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ባለው በማንኛውም ነገር አይደነቅም። በውስጡ ያለው ሁሉ የፈጣሪው ንብረትና ተገዥው ነውና። በዚህ ዓለም ላይ እፊቱ ተደቅኖ የአማኙንና የፍቅር፣ የመተሳሰብና የአገልጋይነት ስሜቱን የሚያጣብብ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉ የአማኙንም አመለካከት የሚያጣብብ ባለመኖሩ አመለካከተ ሰፊ ነው። በብዙ አማልክት የማያምን ወይም አላህ ጉዶሉና ውስን የሆነ የሰው ባህሪያት አለው ብሎ የሚያምን ሰው ግን ይህን አይታደልም።

2. በዚህ ቃለ ተውሒድ በሰው ልቦና ውስጥ ኩሩነትንና ልበ ሙሉነትን በከፍተኛ ደረጃ ያንጻል። አንድ አላህ ብቻ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ላሉት ኃያላት በሙሉ እውነተኛው ባለቤት መሆኑን፣ ከርሱ በስተቀር መጥቀምና መጉዳት፣ ማኖርና መግ ደል፣ ከርሱ በስተቀር የሥልጣን፣ የገዥነትና የጌትነት ባለቤት አለመኖሩን አማኙ በሚገባ ያውቃል። ይህ እውነተኛ እውቀት ከአላህ በስተቀር ካሉት ሁሉ ያብቃቃዋል። ከርሱ በስተቀር የሌሎችን ፍርሃት ከልቡ ያስወግዳል። ለማንም ፍጡር ራሱን ዝቅ እንዳያደርግ፣ ለማንም እንዳይንበረከክና ለማንም ፍጡር እንዳ ያደገድግ፣ የማንንም ዕብሪትና ኃያልነት ከመጤፍ እንዳይቆጥር ያደርገዋል። እንዲህ ባሉት ባህሪያት የሚካነው በዚህ ቃለተውሒድ የሚያምን ሰው ብቻ ነው። ለፍጡር ራስን ዝቅ ማድረግ፣ መጥ ቀምና መጉዳት ይችላል ብሎ ማመን፣ መፍራትና ተስፋውን በርሱ ላይ መጣል አጋሪነትን፣ ከሃዲነትንና ኢአማኝነትን ያስከትላል።

3. ከኩሩነትና ከልበ ሙሉነት ጋርም በዚህ ቃለ ተውሒድ ማመን በሰው ውስጥ የትሁትነት ባህሪ ያንጻል። ከአላህ በስተቀር

ሌላ አምላክ አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ሰው ትእቢተኛና ቀባጭ ሊሆን አይችልም። አታላዩና አሳሳቹ ሰይጣንም ልቡን ሊያሳ ብጠው በኃይሉና በብቃቱ ሊያስበረግገው አይቀርብም። ያገኘውን ሁሉ አላህ የሰጠውና ከፈለገ ሊነጥቀው የሚችል መሆኑን በእርግ ጠኛነት ያውቃል። በአላህ የማያምን ከሃዲ ሰው ግን ይንበጣ ረራል። ይቀብጣል። ዓላማዊ ጸጋ ሲያገኝም በትእቢት አፍንጫው ይወጠራል። ጸጋ ያገኘው በጥረቱ ወይም በብቃቱ ብቻ ይመስ ለዋልና። አጋሪም /ሙሽሪክ/ እንደዚሁ ከአማልክት ሁሉ የርሱው ልዩ የሆንና ሌሎች የሌላቸው ኃይል አለው ብሎ ስለሚገምት ዓለማዊ ጸጋ ሲያገኝ ይኩራራል።

4. በዚህ ቃለ ተውሂድ የሚያምን ሰው ድልና መድህን ለማግኘት፣ ባህሪን በማጥራትና በጎ በመሥራት ብቻ እንጂ በሌላ መንገድ አለመኖሩን ፍጹም በሆነ ሁኔታ ያውቃል። ከሁሉም በተብቃቃ፣ ባለጸጋና ከማንም ፍጡር ጋር በምንም በማይዛመድ፣ ማንም በአምላክነት ሥልጣኑ ውስጥ ጣልቃ መግባትም ሆነ ማስፈጸም በማይችል አምላክ ያምናል። አጋሪዎችና ከሃዲዎች ግን የሕይወት ዘመናቸውን በባዶ ተስፋና ተምኔት ብቻ ይጨርሳሉ። አንዳንዶቻቸው የአላህ ልጅ በአባቱ ዘንድ የኃጢአታችን ቤዛ ሆኗል ሲሉ ሌሎቻቸው ደግሞ እኛ የአላህ ልጅ በአባቱ ዘንድ በኃጢአታችን አይቀጣንም ይላሉ። ታላላቆቻችንና ጻዲቆች አላህ ዘንድ ያማልዱልናል የሚሉም አሉ። ከፊሎቻቸውም ለአማልክ ቶቻቸው ስለትና መስዋት በማቅረብ የፈለጉትን ለመሥራት ፈቃድ አግኝተናል ብለው ያወራሉ።

እነዚህና መሰል ብልሹ እምነቶች እነኛን ሰዎች አሁንም በኃጢአትና በጥፋት ጭቃ ውስጥ እንዲዳክሩ እያደረጋቸው ነው። ሥነ ምግባራቸውን እንዳያጠሩና በጎ እንዳይሠሩ – በነሱ ላይ በመተማመን – እያዘናጓቸው ነው። ከነርሱ በላይ የሆነ፤ ምን

እንደሠሩ የሚጠይቃቸው፣ መልካሙን በመልካም፣ መጥፎውን በመጥፎ የሚመነዳቸው ፈጣሪ አምላክ መኖሩን ከነጭራሹ የማይቀበሉት ኢአማኞች ደግሞ ምንም ዓይነት መለኮታዊ ሕግ የማይገዛቸው ነጻዎች አድርገው በዚህ ዓለማዊ ሕይወት ላይ ራሣቸውን የሚገምቱ ሲሆኑ አምላካቸውን የሚገዙለት ጌታቸው ስሜታዊ ዝንባሌያቸውን ማርካት ብቻ ነው።

5. በቃለ ተውሂድ የሚያረጋግጥ ሰው በማንኛውም ሁኔታ ተስፋ መቁረጥና ወኔ ቢስነት በፍጹም አይነካውም። የሰማያትና የምድር መጋዘኖች ባለቤት፣ ጸጋውና ችሮታው ከቁጥር በላይ፣ ኃይሉ ወሰን የለሽ በሆነው አምላክ ያምናልና። ይህም እምነት ልብን በእርጋታና በብሩህ ተስፋ የሚያጥለቀልቅ ልዩ እርካታ ያስገኝለታል። በዚህች ዓለም ላይ ተዋርዶ ቢንገላታና የኑሮ ችግር ገጥሞት ቢጠበውና ቢጨንቀው እንኳ አላህ በጥበቃው አይዘነጋውም። ቸል አይለውም። ስለዚህም በአላህ ላይ በመተማመን ተከታታይ ጥረት ያደርጋል። በሁሉም እንቅስቃሴው የአላህን ረድኤት ይጠይቃል። ይህን ዓይነት የልብ እርካታና የሕሊና ሠላም ማግኘት የሚቻለው በአላህ ተውሂድ በማመን ብቻ ነው። ከሃዲዎች፣ አጋሪዎችና ኢአማኞች መንፈሰ ደካሞች በመሆናቸው ውስን በሆኑ ኃይሎች ላይ ብቻ ስለሚተማመኑ በቀላሉ በተስፋ መቁረጥ አደጋ ይከበባሉ። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሟቸው የሞራል ውድቀትና የመንፈስ ድክመት ያይልባቸውና አንዳንድ ጊዜ ራስን እስከማጥፋት ይደርሳሉ።

6. በቃለ ተውሂድ ማመን የቁርጠኝነት፣ የደፋርነት፣ የታጋሽነት፣ የዓላማ ጽናትና በራስ የመተማመን ባህሪያትን ያጐለብታል። የአላህን ውዴታ ለመሻት በዚህች ዓለም ላይ ራስን ለታላላቅ ተልእኮዎች ሲያጭና ከፉ ሲሰማራ ከኋላው የሰማያትና የምድር ጌታ ኃይል በመኖሩ ረዳት እንዳለው በያንዳንዱ የተግባር

እርምጃውም እጁን ይዞ የሚመራው መሆኑን በፍጹምነት ያረጋግጣል። ከዚህ ግንዛቤው የሚያገኘው እርጋታ፣ ጽናትና ጥንካሬ ከተራ እርጋታ ጽናትና ጥንካሬ የማያንስ ነው። የፈለገው ዓይነት ዓለማዊ ችግር፣ የፈለገው ዓይነት ምድራዊ ኃይል በቁርጠኝነት ከተሰማራበት ዓላማው አያስቀረውም። አጋሪነት፣ ከሃዲነትና ኢአማኝነት ግን በፍጹም እንዲህ ዓይነት የዓላማ ጽናት ሊኖራቸው አይችልም።

7. ቃለ ተውሂድ ጀግንነትን በማጐናጸፍ ሰውን ልበ ሙሉና ደፋር ያደርጋል። ሰውን ፈሪ የሚያደርገውና መንፈሱን የሚያዳክመው ራሱን፣ ገንዘቡና ቤተሰቡን ወዳድ ሲሆን ነው። ሞትን መፍራትና ሕይወትን የሙጥኝ ማለት ሰውን ፈሪ የሚያደርግ ቢሆንም የዚህም መነሻው ከአላህ በስተቀር ሌላ ሕይወት ነሽ እንዳለና አንዳንድ ነገሮችን በማድረግ ከተወሰነለት ቀን የሚያመልጥ ስለሚመስለው ነው። አንድ ሰው በ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ካመነ ግን እነዚህን ነገሮች ከልቡ ውስጥ ጠራርጐ በማስወጣት ያጠራዋል። የሰው ነፍስና የሀብቱ እውነተኛ ባለቤት አላህ መሆኑን በእርግጠኝነት ስለሚያሳውቀው ያፈራቸውን ውድና ርካሽ ነገሮች በሙሉ አላህ በሚወደው መንገድ እንዲሰዋ ዝግጁ ያደርገዋል። በዚህም ለገንዘብና ለሀብት ያለው ውዴታ በተውሂድ ይወገድለታል። ሰውን መግደልና ነፍሱን ማውጣት ማንም ሰው፣ የትኛውም አውሬ፣ ቦምብም ሆነ መድፍ፣ ጐራዴም ሆነ ድንጋይ ወይም እንጨት ... በፍጹም እንደማይችልና ይህን ማድረግ የሚችለው እውነተኛው ፈጻሚ አላህ ብቻ መሆኑን ቃለ ተውሂድ በሰው ልብ ውስጥ ያንጻል። የትኛውም ምድራዊ ኃይል ሊለውጠው የማይችል የሞት ቀነ ቀጠሮ የተጻፈለት መሆኑን በፍጹምነት ስለሚያውቀው በሃያሉ አላህ ብቻ የሚያምን ሰው በዚህ ዓለም ላይ ከርሱ የበለጠ ጀግና ከርሱ የተሻለ ደፋርና ቆራጥ አይኖርም። የሠራዊት መትመም፣ የጦሮች መሰበቅ፣ የጥይትና የቦንብ ውርጅብኝ አያስበ

ረግጉትም። ለአላህ መንገድ ለመታገል ሲነሣ ከርሱ ኃይል በአሥር እጥፍ የሚበልጡ የጠላት ኃይሎችን ድል ይመታል። ከሁሉም በላይ ነፍሳቸውን ብርቅ አድርገው የሚያዩ ሞት ጠላት ሲመጣ መጥቶ ጠላት ሲሄድ ፊቱን የሚያዞር አድርገው የሚያምኑ አጋሪዎች፣ ከሃዲዎችና ኢአማኞች እንዲህ ያለ ኃይል በምንም ዓይነት አይኖራቸውም።

8. በ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ማመን የሰውን ደረጃ ከፍ በማድረግ በተገኘው የመርካት የመብቃቃትና ከስግብግብነት የመራቅ ባህሪን ያንጽበታል። ሁሉንም ከመጐምጀት፣ ለሁሉም ከመጓጓትና ከመስገብገብ፣ ከቅናት፣ ከተልካሻነትና ከወራዳነት ቆሻሻዎች ልብን ያጠራል። ካሰበው ለመድረስና ፍላጐቱን ለማግኘት መጥፎና ሕገወጥ የሆኑ መንገዶችን ለመጠቀም አያስብም። ሲሣይ በአላህ እጅ ውስጥ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ላሻው ሰው አሳፍቶ ላሻው ሰው የሚያጠበው እሱው ብቻ መሆኑን ይረዳል። የበላይነት ኃይል፣ ታዋቂነት፣ ሥልጣን፣ ተሰሚነትና አሸናፊነት በአላህ እጅ ብቻ ነው። ለሚፈልገው ሰው በጥበቡ ይሰጣል። ስለዚህም ከሰው የሚጠብቀው አቅሙ በፈቀደለት መጠን ሕጋዊ የሆነ ጥረት ማድረግ ብቻ ነው ውጤታማ መሆንና አለመሆን ግን በአላህ ችሮታ ላይ ብቻ ይወሰናል እሱ የከለከለውን የሚሰጥ፣ እሱ የሰጠውን የሚከለክል ኃይል አለመኖሩን ሁሉ አማኙ በሚገባ ያውቃል። ከሃዲዎች፣ አጋሪዎችና ኢአማኞች ግን ውጤት ማግኘታቸውንና ከስረት ላይ መውደቃቸውን በዓለማዊ ኃይሎች መታገዝና አለመታገዝ ላይ የሚወሰን አድርገው ስለሚገምቱ የስግብግብነት፣ የሁሉንም ለኔ-ባይነትና የራስ ወዳድነት ተገዥዎች ናቸው። ፍላጐታቸውን ለማሳካት ጉቦኝነትን፣ አድርባይነትን፣ ሴረኛነትንና የመሳሰሉትን ተልካሻ ዘዴዎች ከመጠቀም አይቆጠቡም። ሌሎች ስኬት ካገኙ በቅናት አረው ጣታቸውን ይነክሳሉ። የሚቀ

ኑባቸውን ወይም የሚቃረኑዋቸውን ሰዎች ለመጉዳት ሕጋዊም ሆነ ሕገ ወጥ የሆነ መንገድ ያለሀፍረት ከመጠቀም አይመለሱም።

9. በ «ላኢላሀ ኢለሏህ» የማመን ዋነኛውና አቢይ ውጤት ሰው በአላህ ሕግ እንዲገዛና እንዲመራ ማድረጉ ነው። አላህ ሁሉንም ነገር ውስጠ አዋቂ፣ ከደም ስር ይበልጥ የቀረበ በሌሊት ጨለማ ወይም ለብቻ የተሠራን ሥራ ሁሉ የሚያውቅ፣ በልብ የታሰበን ጥሩ ያልሆነ ነገር የሚያውቅ፣ በዚህ ዓለም ካሉት ፍጡራን ሁሉ ሥራዎችን መሸሸግ ቢችል እንኳ ከሱ መሸሸግ በፍጹም እንደማይቻል መሆኑን፣ ከማንኛውም ምድራዊ ኃይል እርምጃ ማምለጥ ቢቻል ከአላህ እርምጃ ማምለጥ እንደማይችል በዚህ ቃለ ተውሂድ ያመነ ሰው በእርግጠኝነት ያውቃል። ይህ እምነት በሰው ውስጥ ሥሩን ሰዶ በተጠናከረ በሕሊናው ውስጥ ተቀርጾ በጸና መጠን ግለሰቡ የአላህ ድንጋጌዎች ተከታይና የትእዛዞቹ አክባሪ ይሆናል። አላህ የከለከላቸውን ነገሮች ከመፈጸም የሚቆጠብ፣ በጐ ሥራዎችንና አላህ ያዘዛቸውን ተግባሮች ደግሞ በሌሊት ጨለማ ወይም ለብቻው ቢሆን እንኳ ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም ። ምንጊዜም የማይለዩት ዘበኞችና ጠባቂዎች ከርሱ ጋር መሆናቸውን ያውቃል። ሰው ከምርመራው ማምለጥ የማይችልበት ያ ታላቅ ችሎት ዘወትር ከፊቱ ይደቀናል። ከዚህ በመነሣት ነው በ «ላኢላሀ ኢለሏህ» ማመን አንድ ሰው ሙስሊም እንዲሆን የመጀመሪያውና ዋነኛው መስፈርት የሆነው። ትርጉሙን በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ እንዳብራራነው ሁሉ ሙስ ሊም ማለት ለሃያሉ አላህ የተገዛና የታዘዘ ሰው ሲሆን፣ አንድ ሰው ለሃያሉ አላህ ታዛዥና ተገዥ ለመሆን ደግሞ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን ከልቡ አምኖ የሚቀበል አማኝ መሆን ይኖር በታል።

በ «ላኢ.ላሀ ኢ.ለ3ሀ» ማመን የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ትምህርት መሠረታዊውና ዋነኛው ማዕዘን ሲሆን የእስልምና ማዕከል፣ መሠረቱና የኃይሉ ምንጭ ነው። ከዚህ እምነት ውጭ ያሉት የእስልምና እምነቶች፣ ድንጋጌዎችና ሕግጋት በሙሉ በዚህ መሠረት ላይ የሚቆሙ ኃይላቸውንም ከዚሁ ብቻ የሚያገኙ ናቸው። ይህ የእምነት መሠረት ከቦታው ቢነሳ ከእስልምና ምንም የሚተርፍ ነገር አይኖርም።

## በአላህ መላእክት ማመን:-

በአላህ ካመን በኋላ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያዘዙት ነገር የአላህ መላዕክት /መላኢካህ/ መኖራቸውን እንድናምን ነው። የዚህ እምነት ትልቁ ጥቅም የተውሂድ እምነት ከአጋሪነት ነውሮች፣ እድፍና አደጋዎች ሁሉ እንዲጸዳ ማድረግ ነው።

ከአላህ ጋር ያሻረኩ አጋሪዎች ሁለት ዓይነት ፍጡራንን እንዳሻረኩ መሆናቸውን ቀደም ሲል አውቀናል። አንደኛው ዓይነት ቁሣዊ አካል ያላቸው፣ በዓይን የሚታዩ እንደ ጸሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ እሳት፣ ውሃና ታላላቅ ሰዎችን ወዘተ የመሳሰሉ ፍጡራን ናቸው። ሌላው ዓይነት ደግሞ ቁሣዊ አካል የሌላቸው ከዓይን እይታ የተሰወሩ፣ ከእይታ ውጭ ሆነው የዩኒቨርስን ጉዳዮች የሚያቀናብሩ፣ ከፊላቸው ንፋስና አየርን የሚመሩ፣ ሌሎቹ ደግሞ ደመናን በመንዳት ዝናም የሚያዘንቡ ከፊላቸውም ብርሃን የሚያዘጋጁ ... ወዘተ ፍጡራን ናቸው። የመጀመሪያው ዓይነት ፍጡራን ለሰው እይታ የተጋለጡ ሊሆኑ «ላኢ.ላሀ ኢ.ለ3ሀ» በሚል ቃለ ተውሂድ ብቻ አምላክነታቸው ሊስተባበል ይችላል። የሁለተኛው ዓይነት ፍጡራን ከሰው እይታ የተሰወሩ፣ ከሰው ስሜታዊ ሕዋሳት ውጭ የሆኑ ናቸው፣ አጋሪዎች በአጠ

ቃላይ የሚጎንላቸው አማልክትና ተመላኪዎችን ለራሣቸው የሚያዘጋጁት፣ ወይም የአላህ ልጆች ናቸው የሚሏቸውን የሚመድቡት፣ ሃሣባዊ ቅርጾችን የሚያንጹላቸው የሚሰግዱላቸውና ስለት የሚያቀርቡላቸው ከዚህኛው የፍጡራን ዓይነት ክፍል የሆኑትን ነው። ለዚህ ነው እስልምና የሰውን የተውሂድ እምነት ከዚህ ከሁለተኛው ዓይነት የማጋራት ዘርፍ ለማጥራት ይህን የተለየ እምነት ያቀረበው።

እነኚህ አንዳንድ ሰዎች አማልክት አድርገው የሚይዟቸውን ወይም የአላህ/ሱወ/ ዝርዮች አድርገው የሚወስዷቸውን ብርሃናዊ ፍጡራን የሃያሉ አላህ መላዕክት /መላኢካ እንጂ በአምላክነቱ ውስጥ አግባብ የሌላቸው፣ የአላህን ትእዛዝ በቅንነት የሚፈጽሙና ትእዛዙን በፍጹም የማይጥሱ፣ አላህ በነርሱ አማካይነት ፍጥረቱን የሚያቀናብር፣ ለራሣቸው አንዳች ነገር ማድረግ የማይችሉ፣ በጉልበታቸው አንድም ነገር ለአላህ ሃሣብ ማቅረብ፣ ለማንም አላህ ዘንድ ማማለድ የማይችሉ ፍጡራን መሆናቸውን ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ አብራርተዋል።ስለዚህም የሰው ልጅ እነዚህ ፍጡራን ማምለክ ወይም ከነሱ ረድኤት መፈለግ ውርደትና ቅሌት ነው። ሃያሉ አላህ አዳምን ሲፈጥር መላእክት እንዲሰግዱለት አድርጓቸዋል።ለመላእክት ያልሰጠውን ዕውቀት ለአዳም በመስጠት እነሱን ትቶ አዳም በምድረ ዓለም የርሱ ተጠሪ እንዲሆን አድርጓል። ታዲያ ቀደም ሲል ለሰገደለት መላእክት ማጐንበስ ለሰው ልጅ ከሁሉም የከፋ ውርደት ነው።

በአንድ በኩል ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ መላእክትን እንዳናመልክና የአላህን አምላክነት የሚጋሩ አድርገን እንዳንወስድ ሲከለክሉን በሌላ በኩል ደግሞ እነኚህ መላእክት ምርጥ የአላህ ሎሌዎች፣ ከስህተትና ከኃጢአት የጠሩ፣ በተፈጥሮአቸው የአላህን ትእዛዝ ላለመጣስና የታዘዙትን ሁሉ ለመፈጸም የተፈጠሩ፣

ዘወትር አላህን ለመገዛት ብቻ የተሰለፉ መሆናቸውንና ከመካ ከላቸውም ሃያሉ አላህ ጅብሪል–ገብሬል– የሚባል ክቡር መልአክ ለአላህ ነቢያትና ለመልእክተኞቹ የሚተላለፈውን መልዕክት /ራእይ/ እንዲያደርስ የመረጠው መሆኑን አብራርተው አስተምረዋል። የአላህን ቃል ቅዱስ ቁርአንን ለነቢያችን ለሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያደረሰውም ይኸው መልአክ ነበር። ከነኚህ መላእክት መካከል ዘወትር ከሰዎች ሣይለዩ ሰዎች የሚፈጽሙትን መልካምም ሆነ መጥፎ ተግባር የሚከታተሉ፣ ከሰዎች አንደበት የሚሰሙትን መጥፎም ሆነ በጐ ቃል የሚመዘግቡ መላእክት ይገኛሉ።የያንዳንዱ ሰው የሠራቸውን ሥራዎችና የፈጸማቸውን ተግባራት፣ ከአንደበቱ የወጡ ቃላት ሁሉ የሚያሰፍሩበት መዝገብ አላቸው። በትንሣኤው ቀን ሰዎች በሃያሉ አላህ አስተካካይ ችሎት ሲቀርቡም መዝገቡን በማቅረብ በዛሬው ዓለማዊ ሕይወት ዘመኑ በግልጽም ሆነ በስውር መልካምም ሆነ መጥፎ የፈፀማቸውን ድርጊቶች በመግለጽ ይመሰክሩበታል።

ስለ መላእክት ትክክለኛ ምንነትና አፈጣጠራቸው እንዴት እንደሆነ የተነገረን ምንም ነገር የለም። የታዘዝነው ሕልውናቸውን እንድናምን ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ ስለአኳኋናቸው የምናውቅበት መንገድ የለም። ስለ አፈጣጠር ባህሪያቸው ከራሳችን ዘንድ የሌለ ነገር መፍጠር አላዋቂነት ሲሆን፣ ሕልውናቸውን ማስተባበል ደግሞ ከሃዲነት /ኩፍር/ ነው። ለዚህ ማስተባበያም ማንም ሰው ማስረጃ ማቅረብ አይችልም። የመላእክትን መኖር ማስተባበል ማለት ነቢዩ ሙሐመድን /ሰ.ዐ.ወ/ ማስተባበል ማለት ነው። በመላእክት መኖር የምናምነውም እውነተኛው ታማኙ የአላህ ነቢይ እንድናምን ስላዘዙን ነው።

# በአላህ መጻሕፍት ማመን:-

በነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ አማካይነት እንድናምንበት የታዘዝነው ሶስተኛ ነገር ደግሞ ሃያሉ አላህ ወደ ነቢያቱና ወደ መልዕክተኞቹ ያስተላለፋቸው መለኮታዊ መጻሕፍቱ ናቸው።

ሃያሉ አላህ ቁርአንን ወደ ነቢያችን ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እንዳስተላለፈው ሁሉ ከርሣቸው በፊት ወደነበሩት ነቢያቱም እንደዚሁ ቀደም ሲል አስተላልፎአል።በነዚህ መጻሕፍት አንዳንዶቹን ስሞች የተነገረን ሲሆን እነሱም የነቢዩ ኢብራሂም ጽሑፎች፣ የነቢዩ ሙሣ ኦሪት /ተውራት/፣ የነቢዩ ዳውድ መዝሙረዳዊት /ዘቡር/ እና የነቢዩ ኢሣ ወንጌል /ኢንጂል/ ናቸው። ወደተቀሩት ነቢያት ስለተላለፉት መጻሕፍት ስሞች ግን የተነገረን ነገር የለም።ከዚህ ውጭ ያለው ማንኛውም ሌላ የሃይማኖት መጽሐፍ ከሃያሉ አላህ ዘንድ የተላለፈ ነው ወይም አይደለም ብለን በቁርጠኝነት መናገር አንችልም። ይሁን እንጂ ከአላህ ዘንድ የተላለፈ መጽሐፍ ሁሉ በአጠቃላይ እውነት መሆኑን ግን እናምናለን።

ስሞቻቸው ከተነገሩን ከነዚህ መጻሕፍት መካከል የኢብራሂም ጽሑፎች ደብዛቸው ከዓለም ላይ ጠፍቷል። ኦሪት፣ መዝሙርና ወንጌልን በሚመለከት ግን መጻሕፍቱ ለነገሩ በአይሁድና በክርስቲያኖች ዘንድ የሚገኝ ቢሆኑም በብዙ አዛብተዋቸዋል። ይዞታቸውን ለዋውጠዋል። ከፊሉን አስወግደው በራሣቸው ፈጠራ በርካታ አስተያየት ጨምረውባቸዋል። አይሁድና ክርስቲያኖች እንኳ ዛሬ ጥንት ከአላህ ወደ ነቢዩ ሙሣ፣ ዳውድና ኢሣ የተላለፉ መለኮታዊ መጻሕፍት ኦሪጅናልነታቸው ተጠብቀው እንደማይገኙና አሁን የሚገኙት ለብዙ ምዕተ ዓመታት ለመለወጥ፣ ለመ

ቀያየር፣ ለመጨመርና ለመቀነስ አደጋ እንደተጋለጡ የሚገኙት ትርጉሞቻቸው ብቻ መሆኑን አምነው ይቀበላሉ። እንደዚሁም እነኚህን መጻሕፍት በማንበብ ብቻ ከአላህ ዘንድ ሊሆኑ የማይችሉ አያሌ ነገሮች ይስተዋላሉ። ዛሬ በዓለም ላይ የሚገኙት እነዚህ መጻሕፍት ሃያሉ አላህ ለነቢያቱ ሙሣ፣ ዳውድና ኢሣ ያስተ ላለፉቸው መሠረታዊ መለኮታዊ መጻሕፍት አይደሉም። የሰብአዊ ፍጡራን ንግግር ከአላህ ንግግር ጋር በመጻሕፍት ውስጥ ተቀይ ጧል። ይህም የሰዎችን ቃል ከአላህ ቃል ለመለየት የሚያስችል መንገድ በሰዎች ዘንድ ጭራሽ በማይኖርበት ሁኔታ የተከለሰና የተበረዘ ነው። በቀደሙት መለኮታዊ መጻሕፍት እንድናምን የታዘዝነው ሃያሉ አላህ በቀድሞዎቹ ሕዝቦች ዘንድ ሕግጋቱን የሚያደርሱ ነቢያትና መልእክተኞች ከቁርአን በፊት የላከ በመ ሆኑ፣ እነኚህ ሕግጋትም ቁርአንን ወደ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ካስተላለፈው ከሃያሉ አላህ ዘንድ ተላልፈው የነበሩ ከመሆናቸውና ነቢዩ ሙሐመድም /ሰ.ዐ.ወ/ ሰዎች ቀደም ባሉት ዘመናት አግኝ ተውት ከጊዜ በኋላ ያጠፉትን ወይም የለዋወጡትን ወይም ከሰዎች ንግግር ጋር ያደባለቁትን መመሪያ እንደገና ሕያው ለማድረግ የመጡ ከመሆናቸው አኳያ ነው።

ቁርአን ከሃያሉ አላህ ዘንድ ወደ ሰው ልጆች የተላለፈ የመጨረሻው መለኮታዊ መጽሐፍ ሲሆን፣ በርሱና በቀድሞዎቹ መለኮታዊ መጻሕፍት መካከል ያለው ልዩነት በበርካታ አንጻሮች ነው።

1. ከቁርአን በፊት የነበሩት መለኮታዊ መፍሐፍት ኦሪጂናል ቅጂያቸው ጠፍቷል። ከላይ እንደተረዳነው ሁሉ በሰዎች እጅ የቀሩት ትርጉሞቻቸው ብቻ ናቸው። ቁርአን ግን ከአላህ ዘንድ በተላለፈባቸው ኦሪጅናል ቃላትና ፊደላት እንደነበረ ሆኖ እንደ

ተጠበቀ የሚገኝ ሲሆን አንዳች የመለዋወጥ ሁኔታ በአንዲት ፊደሉ ወይም በአንዲት አናጋሪው ላይ ዝር አላለም።

2. በነባሮቹ መጻሕፍት ውስጥ የፍጡራን ቃላት ከአላህ ቃላት ጋር የተደባለቁ ሲሆን ባንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሰዎች ንግግር፣ ብሔራዊ ታሪክ፣ የጻድቃንና የነቢያት የሕይወት ታሪክ፣ ማብራሪያና ሕግ አዋቂዎች ያመነጩዋቸው ሕግ ነክ ጉዳዮች የአላህን ቃል ከሌላው መለየት በማይቻልበት ሁኔታ ተጠቃለዋል።ቁርአን ግን የሃያሉ አላህ ቃል በሌላ ቃል ምንም ሣይቀየጥ ጠርቶና ተነጥሮ እንዳለ ሆኖ ይገኝበታል። ሙስሊሞች በቁርአን ማብራሪያ /ተፍሲር/ ወይም በነቢዩ ሐዲስ ወይም በነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ የሕይወት ታሪክ ወይም በነቢዩ ጓዶች ሕይወት ታሪክ ወይም በእስልምና ታሪክ ላይ የጻፉዋቸው ነገሮች በሙሉ ከቁርአን ጋር በፍጹም አልተቀላቀሉም። እያንዳንዳቸው ከቁርአን በተለዩ ሌሎች መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግበው ተጠብቀዋል።

3. በተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ዘንድ የሚገኙ መጻሕፍት ሁሉ ታሪካዊነት ባለው አስረጅ አንዱም ወደሚዛመድባቸው ነቢያት ከአላህ የተላለፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አይቻልም። እንዲያውም ከሃይማኖታዊ መጻሕፍት መካከል ብዙዎች ወደየትኛው ነቢይ እንደተላለፈና መች እንደተላለፈ የሚጠቁም አንዳች ፍንጭ የላቸውም። ቁርአን ግን ወደ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ከአላህ የተላለፈና ነቢዩ ለሰዎች ያደረሱት መሆኑን የሚያረጋግጡ የጸኑና ቁርጠኛ የሆኑ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሰው ለጥርጣሬ ቦታ በማይሰጥበት ሁኔታ ለማንም የተትረፈረፉ ናቸው። ከዚህ አልፎ ተር ፎም እያንዳንዱ የቁርአን አንቀጽ የት ቦታና መቼ ወደነቢዩ እንደተላለፈ ይታወቃል።

4. ነባሮቹ ጥንታዊ መጻሕፍት የተላለፉባቸው ቋንቋዎች ከረዥም ዘመናት በፊት ሞተው የከሰሙ በመሆናቸው ዛሬ ቋንቋ ዎቹን የሚናገር ሕዝብ በየትኛውም የዓለም ክፍል አይገኝም። ቋንቋዎቹን እንረዳለን የሚሉም በጣም ጥቂት ግለሰቦች ናቸው። ሌላው ቀርቶ መጻሕፍቱ በጥንታዊ መሠረታቸው እንደነበሩ ሆነው ቢገኙ እንኳ ሰዎች ተረድተው ሕጎቻቸውን መከተል አይችሉም ነበር። ቁርአን የተላለፈበት ቋንቋ ግን ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች የሚናገሩትና በዓለም ላይ በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች የሚረዱት ሕያው ቋንቋ ነው። በብዙ የዓለም አገሮች ሰዎች የሚማሩትና የሚያስተምሩበት፣ መማር የሚፈልግ ሰው በቀላሉ ሊማረው የሚችል፣ ቋንቋውን ለመማር ጊዜ የሌለው ሰውም የቁርአን ትርጉምና ሕግጋቱን የሚያውቁ ሰዎችን የትም ቦታ ማግኘት የሚችል ቋንቋ ነው።

5. ዛሬ በተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ዘንድ የሚገኙ መለኮታዊ መጻሕፍት በሙሉ የታለሙት ለሁሉም ሕዝቦች በአጠቃላይ ሣይሆን እያንዳንዱን ሕዝብ /ብሔር/ በተለይ የሚመለከቱ ናቸው። መጻሕፍቱ ያጠቃለሉትን ድንጋጌዎች ስንመለከትም አብዛኞቹ ለተወሰነ አንድ ዘመን የመጡ፣ ከዘመኑ ሁኔታ፣ ፍላጐትና ችግሮች ጋር የሚመጣጠኑ በመሆናቸው ለዛሬው ሰውና ለዛሬው ዘመን የሚያስፈልጉ፣ ዛሬ ተግባር ላይ ለማዋል አመቺ ያልሆኑ መሆናቸውን ያለ ጥርጥር እናገኛለን። እነዚህ መጻሕፍት ለተወሰነ ዘመንና ለተለየ አንድ ሕዝብ ብቻ የመጡ በመሆናቸው አንዳቸውም ለመላው የሰው ልጅ በአጠቃላይ የተላለፉ አይ ደሉም። መጻሕፍቱ የመጡላቸውን ሕዝቦችም ለዘለዓለም የመጡ ለት ሣይሆን ለተወሰነ ዘመን ብቻ ነው። በዚህ አመለካከት ቁርአንን ብንገመግም ግን ሁሉም ቦታ ላይ ለመላው የሰው ዘር የተላለፈ ጊዜና ቦታ የማይለይ መሆኑንና ማንኛውም አንቀጽ አንድን ሕዝብ ብቻ በተለይ የሚመለከት ስሜት ከአንባቢው ላይ በፍጹም የማያ

ሳድር መሆኑን እንረዳለን። እንደዚሁም ቁርአን ይዞት የመጣው ሕግ በየትም አገርና በሁሉም ዘመን ተግባራዊ መሆን የሚችል ነው። ይህም ቁርአን ለመላው የሰው ልጅ ለዘለዓለሙ የመጣ መመሪያ መሆኑን የሚመሰክር ነው።

6. ጥንታውያን መጻሕፍት እያንዳንዳቸው እውነተኛና በጎ ነገሮችን ቢያጠቃልሉም፣ ለሰው ልጅ የሥነ ምግባርና የመልካም ምግባር መርህ ቢያስጨብጡም፣ አላህ በሚወደው መንገድ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ሰዎችን ወደቀጥተኛው መንገድ ቢያመሩም ማንኛቸውም ቢሆኑ መልካም ነገሮችንና ትሩፋትን ሁሉ ሙሉ በሙሉ አላካተተም። ቁርአን ከነዚህ መጻሕፍት ከሚለዩባቸው ነጥቦች አንዱ በቀደሙት መጻሕፍት ውስጥ የተበታተኑትን በጎ ምግባሮች በሙሉ በውስጡ ከማጠቃለሉም በላይ በመጻሕፍቱ ውስጥ ያልተመለከቱትን በጎ ምግባሮችና የትሩፋት ሥራዎች በሙሉ የተተነተኑበት መሆኑ ነው።

7. በጥንታዊያኑ መለኮታዊ መጻሕፍት ላይ ሰዎች እንዳሻቸው ለውጥና ክለሳ በማድረጋቸው የተነሣ ለሰብአዊ፣ አእምሮና ከእውነት የማይጣጣሙ በግፍና በሐሰት ላይ የተመረኮዙ የሰውን እምነትና ዕውቀት የሚበክሉ በርካታ ነገሮች ሰርገው ገብተውባቸዋል። ይልቁንም ብዙዎቻቸው ከብልግና፣ ከአስከፊ ነገርና ከሞራል መላሸቅ የሚቆጠሩ ነገሮችን ይዘዋል። ቁርአን ግን ከእንዲህ ዓይነት ነገሮች ፍጹም የጠራ፣ ሰብአዊ አእምሮን የሚቃረን አንዳች ነገር የሌለበት፣ በማስረጃና በተመክሮ ስህተቱን ማረጋገጥ የሚቻል አንድም ነገር የሌለበት መጽሐፍ ነው። አንድም ነገር ወይም አንድም ሕጉ ግፍ ወይም ጥቃት የለበትም። ሰውን ወደተሳሳተ መንገድ የሚመራ አንድም ጥመት የለበትም። የብልግና የመጥፎ ነገር የሥነ ምግባር ደንቦችን የመተላለፍ አንዳች አዝማሚያ የለበትም። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ሙሉ

በሙሉ በበቂ ጥበባት፣ በመልካም ተግሣጽ ሰዎችን ፍትህ በማስ ተማር ወደ ቀጥተኛው መንገድ፣ ወደ መልካም ሕግና በድን ጋጌዎች በመምራት የተሞላ ነው።

የምድሪቱ ነዋሪዎች በመላ በቁርአን እንዲያምኑና የተቀሩትን መጻሕፍት ትተው እርሱን ብቻ እንዲከተሉ የታዘዙበት ልዩ መለያዎቹም እነዚህ ናቸው። የሰው ልጅ አላህ በሚወደው መንገድ ሕይወቱን ለመምራት አስፈላጊ የሆነና ሊያስፈልግ የሚችለውን የመጨረሻ ደረጃ መምሪያ ቁርአን ያለ ምንም ጭማሪና ጉድለት ያብራራው ስለሆነ የሰው ልጅ ቁርአን ከመጣለት በኋላ ሌላ መጽሐፍ በፍጹም የሚፈልግ አይደለም።

በቁርአንና በተቀሩት ሌሎች መጻሕፍት መካከል ያለውን ልዩነት ካወቅን ዘንዳ በቁርአን በማመንና በሌሎች መለኮታዊ መጻሕፍት በማመን መካከል ሊኖር የሚገባውን ልዩነት ለይቶ ማወቅ በጣም ቀላል ይሆናል። በጥንታዊያኑ መጻሕፍት ማመን እውነት መሆናቸውን እስከማመን ድረስ ብቻ ነው። ይህ ማለት መጻሕፍቱ ከአላህ ዘንድ የተላለፉ ነበሩ፣ የመጡበት ዓላማም ቁርአን ሊያሟላው ለመጣው ዓላማ ነበር ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በቁርአን ማመን ማለት ፍጹም የሠራ የአላህ ቃል፣ ፍጹም እውነት፣ እያንዳንዱ የቁርአን ፊደል ተጠብቆ ያለ መሆኑ ታም ኖበት እያንዳንዱን የቁርአን ትእዛዝ መከተልም ግዴታ እንደሆነ የርሱን ሕግና ድንጋጌ የሚጻረርና የሚቃወም ሁሉ መወገድ፣ ተቀባይነት ማጣት ያለበት መሆኑን ማመን ማለት ነው።

## በአላህ ነቢያት መልዕክተኞች ማመን

በአላህ መጻሕፍት ካመንን በኋላ በነቢያቱ እንድናም ንታዘናል።

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ እንደተብራራው ሁሉ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ መደምደሚያቸው የሆኑት ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያስተማሩትን እስልምና ያስተማሩ ነቢያት /መልዕክተኞች/ ከአላህ ተልከዋል። የአላህ ነቢያትና መልዕክተኞች በሙሉ አንድ ምንጭ ያላቸው የተቀጣጠሉ ሰንሰ ለቶች ናቸው። ስለዚህም አንዳቸውን ያስተባበለ ሰው ነቢያትን በሙሉ አስተባብሏል። አንዳቸውን ያመነ ሰውም በሁሉም ነቢያት ማመን ግዴታ ይሆንበታል። አንድ ዓይነት ነገር የሚናገሩ አሥር ሰዎች ቢገጥሙን አንደኛቸውን ካመን አሥሩንም እናምናለን። አንዳቸውን ያስተባበልን ከሆነም ከሥሩንም አስተባብለናል ማለት ነው። አሥሩም ተመሣሣይ የሆነ አንድ ነገር ይናገራሉና። በከፊ ላቸው አምኖ በከፊላቸው ላይ ደግሞ በማስተባበል የአላህን ነቢያት የሚለያይ ሰው እውነተኛ ከሃዲ ኋሉ ነው።

ወደ ተለያዩ የዓለም ሕዝቦች የተላኩ የአላህ ነቢያት ቁጥር መቶ ሃያ አራት ሺህ መሆናቸውን ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ አብራርተውልናል። የመሬት ዕድሜና እስከዛሬ ድረስ ያለፉበትን ሕዝቦችና ብሔሮች ብናስብ ይህ የአላህ ነቢያት ቁጥር ብዙ አለመሆኑን እንረዳለን። ከነዚህ ነቢያት መካከል ቁርአን ውስጥ በተተረኩት በቀጥታ ማመን ግዴታ ሲሆን ባልተተረኩት ግን ሕልውናቸውን እንድናምን ታዘናል።አላህ ሰብአዊ ፍጡራን ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንዲመሩና እንዲያስተምሩ የላካቸው የአላህ ነቢያት በሙሉ እውነተኞች ናቸውና። ወደ ሕንድ፣ ቻይና፣ ኢራን፣ ግብፅ፣ አፍሪቃ፣ አውሮፖና የተቀሩት የዓለም ክፍሎችና አገሮች ሁሉ የአላህ መልዕክተኛ ተልከው ክሆነ በሁሉም እናምናለን። ነገር ግን በትክክል እገሌ የአላህ መልዕክተኛ ነበር እገሌ አልነበረም ማለት ግን አንችልም። ስለነሱ ምንም አልተነገረንምና። የተለያዩ የዓለም ሃይማኖተኞች ከሚከተሏቸው መሪዎች መካከል አንዱንም መዝለፍ ወይም በመጥፎ ማንሳት በምንም

ዓይነት አይፈቀድልንም። እነሱ እውነተኛ የአላህ ነቢያት ሆነው ሰዎች ከነሱ በኋላ የሙሣና የኢሣ ተከታዮች ከነርሱ በኋላ እውነተኛ ሃይማኖታቸውን እንደቀየሩ ሁሉ ቀይረው ሊሆን ይችላልና። መሰንዘር የምንችለው አስተያየት ካለ ስለዛሬው የሃይማኖታዊ ክንውናቸውና ስለአምልኮአቸው አፈጻጸም ሁኔታ ብቻ መሆን አለበት። እነዚህን ሃይማኖቶች ስለመሠረቱት ሰዎች ለአንድ የአላህ ነቢይ ያለንን ተገቢ ሥነ ምግባር የሚጻረር ነገር እንዳይወጣን ለመጠንቀቅ ሲባል አንዳች ቃል መተንፈስ የለብንም።

ሁላቸውም ከአላህ ዘንድ በእውነት የተላኩ፣ ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚወስዱና በሁሉም እንድናምን የታዘዝን መልዕክተኞች ከመሆናቸው አኳያ በነቢዩ ሙሐመድና በተቀሩት ነቢያት መካከል ልዩነት የለም። ይሁን እንጂ ይህ ተመሣሣይነት የተጠበቀ ሆኖ በነቢዩ ሙሐመድና በተቀሩት ነቢያት መካከል በሶስት አቅጣጫ ልዩነት አለ:-

1. የተቀሩት ነቢያት የተላኩት እያንዳንዳቸው ላንድ የተለየ ብሔርና ላንድ ለተወሰነ ዘመን ብቻ ነው። ነቢዩ ሙሐመድ ግን የተላኩት ለመላው የሰው ዘርና ባለፈው ምዕራፍ እንደተረዳነው ሁሉ –እስከ ትንሣኤው ቀን እስከ ዓለም ፍጻሜ ነው።

2. የነዚያ ነቢያት ትምህርቶች አንድም ከነጭራሹ ከስመዋል ወይም በዓለም ላይ ዝርዝራቸው ቢቀርም እንኳ መሠረታዊ ይዘታቸውን ጠብቀው በጥንታዊ መልካቸው አይገኙም። የነቢያቱ ታሪክና ክንዋኔዎችም እንደዚሁ አይገኙም። ትክክለኛነታቸው በትረካና በአፈታሪክ ሰዎች ከራሣቸው በፈጠሩትና ሰው ሊከተለው በማይችል ተረት ተውጧል። ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.0.ወ/ ግን ትምህርቶቻቸው፣ ታሪካቸው፣ ቃላቸውና ተግባራቸው፣ ሥነ ምግባራቸው ልምዳቸውና ባህሪያቸው ሁሉ በመጻሕፍት ተመዝ

ግቦ ማንም ሰው እጅ ይገኛል።እውነቱን ለመናገር ከአላህ ነቢያትና መልዕክተኞች ሁሉ ብቸኛው ሕያው ነቢይ ሙሐመድ /ሰ.0.ወ/ ናቸው። ሰዎች ሊከተሉትና በመመሪያው ሊመሩ የሚችሉትም እሳቸውን ብቻ ነው።

3. የቀድሞዎቹ ነቢያት ያስተማሩት የእስልምና ትምህርቶች የተሟሉ አልነበሩም። ከአንዱ ነቢይ ቀጥሎ የሚመጣው ነቢይ የቀደሙት ነቢያት ያስተማሩትን ትምህርቶች፣ ሕጐቻቸውንና ደንቦቻቸውን የአመራር መንገዳቸውንም የሚያሻሽል፣ የሚጨ ምርና የሚቀንስም ነበር። ከነቢዩ ሙሐመድ በፊት የነበሩት ነቢያት በሙሉ የማሻሻል፣ የመለወጥ፣ የመጨመርና የመቀነስ ተግባ ራቸውን በመቀጠል በዚሁ ሁኔታ ሂደቱን ገፋበት። ለዚህ ነው ሃያሉ አላህ የነዚህን ነቢያት ትምህርቶች ከነቢያቱ ዘመን በኋላ ጠብቆ ያላቆያቸው። ሰዎችም የተሟላ አዲስ ትምህርት የሚፈልጉ አልነበሩም። በመጨረሻም ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.0.ወ/ በሁሉም በኩል የተሟላና የበለጸገ የእስልምና ትምህርት ይዘው መጡ። በዚህ ዓይነትም የተቀሩት ነቢያት ትምህርቶች በነቢዩ መሐመድ ትምህርት ተሻሩ። ሙሉ እያለ ጐደሎውን መከተል አእምሮን የሚጻረር ነውና። ነቢዩ ሙሐመድን የተከተለ ሰውም ነቢያትን በሙሉ ተከትሏል። ይህም በቀድሞዎቹ ነቢያት ትምህርቶች ውስጥ ያለው ሁሉ ዛሬ በነቢዩ ሙሐመድ ትምህርቶች ውስጥ ተጠቃሎ ስለሚገኝ ነው። ከሙሐመድ አፈንግጦ ሌላ ነቢይ የተከተለ ሰው ቀደም ሲል በነበሩት ነቢያት ትምህርት ውስጥ ያልነበሩና በኋላ የተጨመሩ በርካታ መልካም ነገሮች ተነፍጓል።

ስለሆነም መላው የሰው ዘር በነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.0.ወ/ የግዴታ ማመንና ትምህርታቸውን መከተል ይኖርበታል። አንድ ሙስሊም በሶስት አንጻሮች በነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.0.ወ/ ማመን አለበት:-

1. ከሃያሉ አላህ ዘንድ የተላኩ እውነተኛ መልዕክተኛ መሆናቸውን፣

2. መመሪያቸው የተሟላና ምንም ዓይነት ጉድለት ወይም ስህተት የሌለበት መሆኑን፣ እና

3. ለመላው የዓለም ሕዝቦች፣ ለአጠቃላዩ የሰው ዘር ከአላህ የተላኩ፣ ትምህርታቸው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቆይ፣ እርሳቸውም የመጨረሻው ነቢይ መሆናቸውን፣ ከርሣቸው በኋላ በርሱ ማመን ከእስልምና መስፈርት አንዱ ሲሆን በርሱ አለማመን ደግሞ ከከሃዲዎች ጐራ የሚያሰልፍ በማሆኑ እንዲህ ሰው በፍጹም የማይመጣ መሆኑን።

## በመጨረሻ ቀን በትንሣኤ ማመን:-

እንድናምንበት የታዘዝንበት አምስተኛው ነገር ደግሞ የመጨረሻው ቀን /የትንሣኤው ቀን/ ነው። ስለትንሳኤ ቀን ማመን የሚገባን:-

1. አላህ ይህን ዓለምና ፍጥረታቱን በመላ የትንሣኤ ቀን በመባል በሚታወቅ ቀን የሚያስወግድ መሆኑን፣

2. ከዚያም ከአጠቃላይ ጥፋት በኋላ እንደገና ሕይወት ዘርቶባቸው ቀስቅሶ የሚሰበስባቸው መሆኑንና ይህም የመሰብሰቢያ ወይም የዳግም ሕይወት መሆኑን፣

3. ከዚያም ሰዎች በመጀመሪያው ምድራዊ ሕይወታቸው የሠሯቸው መልካምም ሆነ መጥፎ ሥራዎች በሙሉ ሣይቀንሱና ሣይጨምሩ እንዳሉ ወደ አላህ ችሎት ለፍርድ የሚቀርቡ መሆናቸውን፣

4. ሃያሉ አላህ የእያንዳንዱን ሰው መልካምና መጥፎ ሥራዎች የሚመዝን መሆኑንና መልካም ሥራው ሚዛን ለደፋለት ሰው ምህረት የሚያደርግለት መጥፎ ሥራው ሚዛን ለደፋለት ሰው ደግሞ የሚቀጣው መሆኑንና፣

5. ምህረት ያገኙ ሰዎች ገነት የሚቀጡት ደግሞ እሳት የሚገቡ መሆናቸውን ነው።

## በትንሣኤው ቀን የማመን አስፈላጊነት፣—

በዚህ በመጨረሻ ቀን ማመን፣ ሌሎች ነቢያትና መልእክተኞች እንዳቀረቡት ሁሉ ነቢዩ ሙሐመድም /ሰ.ዐ.ወ/ ያቀረቡት ሲሆን ይህም እምነት በሁሉም ዘመናት ከእስልምና መስፈርት አንዱ ነው። በዚህ የማያምን ወይም መኖሩን የሚጠራጠር ሰው ከሃዲና ኢአማኝ መሆኑን ነቢያት በሙሉ አረጋግጠዋል። ይህ እምነት ከሌለ በአላህ፣ በመጻሕፍቱና በነቢያቱ ማመን ምንም ትርጉም የለውም። ይህ መቼም በጣም ግልጽና በቀላሉ መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው። አንድ ነገር እንድንሠራ ስንጠየቅ በአእምሮአችን ውስጥ በመጀመሪያ የሚፈጠረው ጥያቄ «የተባልነውን ብንሠራ ምን ጥቅም እናገኛለን! ባንሰራውስ ምን ጉዳት ይደርስብናል?» የሚለው ይሆናል። ይህ ጥያቄ በጭንቅላታችን ውስጥ ለምን ይፈጠራል? ቢባል የሰው ልጅ በተፈጥሮው ጥቅም የማያስገኝለት ነገር ሁሉ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ስለሚረዳ ነው። በመሆኑም ለራሳችን ጥቅም የማያስገኝ ሥራ ለመሥራት ንቃት አይኖረንም። ምንም ጉዳት የማያስከትልብን መሆኑን ካረጋገጥን ሥራ ሥራችንን እናግ ድም። ይህም የጥርጣሬና የማመንታት ሁኔታ ነው። ጥቅም ያስገ ኛል! አያስገኝም ብለን በምንጠራጠረው ነገር ሁሉ ፍላጐት ኖሮን ለመሥራት አንችልም። ጉዳቱን የምንጠራውን ነገርም እንደዚሁ

ከርሱ ለመራቅና ለመጠበቅ አንፕርም። ሕፃናትን ተመልከቱ፤ እጃቸውን እሳት ውስጥ ለምን ይከታሉ? እሳት የሚያቃጥል ነገር መሆኑን ስለማያውቁ ነው። ከትምህርትና ከዕውቀት ገበታ ለምን ይሸሻሉ? ታላቆቻቸው በአእምሮአቸው ውስጥ ለመቅረጽ የሚጥሩትን የትምህርት ጥቅም መረዳት ስለማይችሉና ስለማይገነዘቡት ነው። በትንሣኤው ቀን የማያምነውም ሰው እንደዚሁ ነው። በዚህም ምክንያት በአላህ ማመንና ትእዛዞቹን በዚህች ዓለም መከተል ፋይዳ ቢስና ከንቱ አድርጐ ይመለከተዋል። በርሱ አስተያየት አላህን ምንም ጥቅም የለውም፣ ትእዛዙን መጣስም አንዳች ጉዳት አያስከትልም። እንዲህ ከሆነ አላህ በነቢያቱ አማካይነት በመለኮታዊ መጻሕፍት ውስጥ ያስተላለፋቸውን ትእዛዞች ለመፈጸም እንዴት ራሱን ያስገድዳል? ይገፋፋል ተብሎስ ተስፋ ይጣልበታል? እንዲህ ዓይነቱ ሰው በአላህ ቢያምንም አላህን የማይታዘዝና ሕይወቱን አላህ ለሚወደው መንገድ ስለማይመራ እምነቱ ትርጉም የለውም።

ነገሩ በዚህ ብቻ አያበቃም። አንድ ሰው በመጪው ዘለዓለማዊ ሕይወቱ ላይ የጠበቀ ተጽእኖ አለው። ከላይ እንዳየነው ሁሉ የሰው ልጅ የተፈጠረው አንድ ሥራ ለመሥራት ወይም ላለመሥራት ያለው ዝንባሌ ከግል ጥቅሙ ወይም ጉዳቱ አንጻር ብቻ ነው። ታዲያ አመለካከቱ ከዛሬው ጥቅምና ጉዳት የማያልፍ ሰው ጥቅሙ ለዛሬው ዓለማዊ ሕይወት ይደርሳል ለማይባል መልካም ሥራ መች ይገፋፋል? ወይም በዛሬው ዓለማዊ ሕይወቱ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ ከማይፈራ መጥፎ ሥራስ እንዴት ብሎ ይቆጠባል? አመለካከቱን ከሥራዎቹ ባሻገር ውጤቶቻቸው ላይ የሚያተኩረው ሰው ግን የዛሬዋን ዓለማዊ ሕይወት ጥቅም ወይም ጉዳት እንደሃላፊ ነገር ብቻ ነው የሚመለከተው። ስለዚህም ከሐሰት ሐቁን፤ ከክፋት ደግነቱን፤ በመጨረሻው ቀሪ ዓለም ጥቅምና ጉዳቱን በማገናዘብ ይመርጣል። በጐ ተግባር በዚህች ዓለም ሕይወቱ የከፋ ጉዳት

ቢያስከትልበትም፣ መጥፎው ተግባር ደግሞ ከሁሉም የላቀ ከፍተኛ ጥቅም ቢያስገኝለትም ምርጫው በጐ ተግባር ይሆናል። በነዚህ በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነትና የሰፋ መራራቅ እናስተውል። በመጀመሪያው ሰው አመለካከት መልካም ነገር ማለት በዚህች ጠፊ ዓለም ሕይወት የሚገኘው ጥቅም፣ ሀብት፣ መሬት፣ መልካም ዝና፣ ደስታ፣ ፍስሐ ወይም የስሜታዊ ዝንባሌውን ጥማት የሚያረኩ ነገሮችን ማግኘት የመሳሰለ ነው። መጥፎ ነገር ማለት ደግሞ በዚህች ዓለም ሕይወቱ ላይ መጥፎ ነገር የሚያስከትል ወይም ያስከትላል ተብሎ የሚፈራ ገንዘብ ማጣት፣ ሞት፣ ረሃብ፣ የጤና መጓደል፣ በሰዎች ዘንድ መጥፎ ስም ማትረፍ ወይም የመንግሥት ቅጣት እንደ ሐዘንና ብስጭት ያሉና የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው። በሁለተኛው ሰው ዘንድ መልካም ነገር ማለት ግን አላህን የሚያስደስት ነገር ሲሆን መጥፎ ነገር ማለት ደግሞ አላህን የሚያስቆጣ ነገር ነው። መልካም ነገር በዚህች ዓለማዊ ሕይወት ጥቅም ባያስገኝለትም፣ በጉዳት ቢፈታተነውም በሁሉም ሁኔታ በጐ ተግባር የሚመረጥ መሆኑን ይረዳል። አላህ በመጨረሻው ዓለም ቀሪ ሕይወት ዘለዓለማዊ የሆነ ጥቅም እንደሚሰጠው ፍጹም እርግጠኛ ነው። በዚህች ምድራዊ ዓለም ሕይወት መከራውን ባይቀምስም ወይም እንዳይቀምስ ባይሰጋም፣ የፈለገውን ያህል ጥቅም ቢያስገኝም መጥፎ ሥራ ምንጊዜም ለርሱ መጥፎ ነው። በክፉ ሥራው በዚህ ዓለም ላይ ቅጣት ባያገኘውም በመጪው ዘለዓለማዊ ዓለም ተገቢ ዋጋውን ከማግኘት እንደማያመልጥ በፍጹምነት ያውቃል።

በነዚህ ሁለት የተለያዩ የአመለካከት አቅጣጫዎች አንፃር የሰው ልጅ በሕይወት ውስጥ ከሁለቱ የተለያዩ መንገዶች መካከል አንዱን ይመርጣል። በመጨረሻው ዓለም ሕይወት የማያምን ሰው በእስልምና ጉዳና አንድ እርምጃ መራመድ አይችልም። «የአላህን ምንዳ አስበህ ባለህ የገንዘብ መጠን ለድሆችና ለምስኪኖች ዘካት

ክፈል» ሲባል ዘካት ገንዘቤን ስለሚያጐድል ገንዘቤን አራጣ ሰጥቼ ባተርፍ ይሻለኛል የማይከፍሉኝ ተበዳሪዎች ቢኖሩም ፍርድ ቤት መክሰስ ቤትና ንብረታቸው ላይ አስፈርዳለሁ ይላል። እስልምና «እውነትን ተናገር፣ ሐሰትን ራቅ። እውነትን መናገር የከፋ ጉዳት የሚያስከትልና መዋሸት ታላቅ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆን እንኳ » ሲለው ጉዳት ካመጣብኝ እውነት አልናገርም፤ ጥቅም ካስገኘልኝ ከውሸት አልቆጠብም፤ በሰዎች ዘንድ የሚያተ ርፍልኝን መጥፎ ስም አልፈራም ይላል። .... ተገቢ ባልሆነ መንገድ ይጓዝና ውድ የሆነ ነገር ይገጥመዋል። በዚህን ጊዜ እስልምና:- «ይህ ንብረትህ አይደለምና አትወስደው» ይለዋል። እሱ ግን:- ያለ ምንም ልፋትና ዋጋ የመጣልኝን ነገር ለምን እተዋለሁ? በዚህ መንገድ ላይ አይቶኝ ጉዳዩን ለፖሊስ የሚያ ቀርብ ወይም በፍርድ ቤት የሚመሰክርብኝ ወይም ስሜን የሚያ ጠፋ የለምና በዚህ ገንዘብ ብጠቀምና አገልግሎት ላይ ባውለው ምን አለበት? ይላል።... አንድ ሰው ገንዘቡን በአደራ እሱ ዘንድ ያስቀምጥና ይሞታል። እስልምና:- «አንተ ዘንድ ያለውን የወዳ ጅህን ገንዘብ አትካድ፤ አደራውንም ለቤተሰቡ በታማኝነት አስረክብ» ይለዋል። እሱ ግን «ለምን ? ሟቹ እኔ ዘንድ ገንዘቡን በማስቀመጡ ማስረጃ የለውም። ወይም ወራሾቹ አያውቁም። ይህን ገንዘብ በቀላሉ መብላት ሲችል የመከሰስም ሆነ የስም መጥፋት ስጋት እንደሌለብኝ እያወኩ ለቤተሰቦቹ ብመልስ ሞኝና ተላላ ነኝ ማለት ነው! »ይላል። በአጠቃላይ እስልምና በያንዳንዱ የሕይወት እርምጃው ወደ ቀጥተኛው መንገድ የሚመራው ሲሆን እሱ ግን ይቃወማል። ከራሱ ስሜታዊ ዝንባሌ ጋር የሚጣጣም መንገድ እንጂ ሌላውን አይመርጥም። በእስልምና ውስጥ የማናቸውም ነገር እሴት በመጨረሻው ዓለም ዘለዓለማዊ ውጤት ላይ የተመረኮዘ ሲሆን። የርሱ አመለካከት ግን በዚህች ጠፊ ዓለም ሕይወት ከሚገኘው ውጤት ተሻግሮ አያልፍም። ከዚህ እውነታም አንድ ሰው

በመጨረሻው ዓለም ዘለዓለማዊ ሕይወት ሣያምን ሙስሊም መሆን እንደማይችል እንረዳለን። ይልቁንም የመጨ ረሻውን ዓለም ሕይወት የሚያስተባብል ሰው ከሰብአዊነት ደረጃ ወደ አራዊትነት ውርደት ይዘቅጣል።

# የመጨረሻው ዓለም ሕይወት እርግጠኛነት:-

በመጨረሻው የትንሣኤ ቀን ስለማመን፣ ስለእምነቱ አስፈላጊነትና ለሰው ልጅ ስለሚሰጠው ጥቅም ተረድተናል። ቀጥለን ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያብራሩት ይህ እምነት ሕሊናዊ ማረጋገጫ ያለው እውነት መሆኑንና አእምሮ የሚያረጋግጠው መሆኑን ጠቅለል ባለ ሁኔታ እናቀርባለን። ይህን እምነት የምን ቀበለው በአላህ መልእክተኛ ላይ በመተማመንና ያስተማሩት ሁሉ እውነት መሆኑን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ዓይነቱ የእምነት መሠረት፤ በአእምሮ ላይ የማይመረኮዝ ቢሆንም አእምሮ አችንን ትንሽ ካሠራን ይህ እምነት ከሁሉም የበለጠ ለአእምሮ የቀረበ መሆኑን እንገነዘባለን።

በዚህ ምድራዊ ዓለም ላይ ስለመጨረሻው ዓለም ሶስት እምነቶች ይገኛሉ:-

1. አንዱ ቡድን ሕይወት በዚህችው ምድራዊ ዓለም ላይ ብቻ የተወሰነች ናት፤ እንወለዳለን፤ እንሞታለን። ከሞትን በኋላ ሌላ ሕይወት የለንም ይላል። ይህም የተፈጥሮ ሣይንስ አዋቂዎች ነን የሚሉ ኢአማኞች እምነት አቋም ነው።

2. ሌላው ቡድን ደግሞ የሰው ልጅ በዚህ ምድራዊ ኑሮው ውስጥ የሠራውን ዋጋ ያገኝ ዘንድ ሞትና ሕይወት እዚሁ ይፈራረቁበታል። በመጀመሪያ የሕይወት ዘመኑ ሥራው መጥፎ ከሆነ በሚቀጥለው ዙር ሕይወቱ ዝንጀሮ፣ ውሻ፣ ድመት ወደመሳሰሉት እንስሳት ወይም ወደ ዛፍነት ተለውጦ ወይም ከዝቅተኛ ሰዎች አንዱ ሆኖ ይመጣል። ሥራው መልካም ከሆነ ግን ደረጃው የመጠቀ፣ ክብሩ የላቀ ይሆናል ብሎ ያምናል። ይህን የሚሉት ሃይማኖታዊ ርዕዮታቸው ያልዳበሩ አንዳንድ ሰዎች ናቸው።

3. ሶስተኛው ቡድን ደግሞ በመጨረሻው የትንሣኤ ቀን ለዳግም ሕይወት መቀስቀስ መኖሩን፤ በአላህ ፊት ቀርበው ሰዎች እንደሥራቸው ዋጋ የሚያገኙ መሆናቸውን ያምናል። ይህ እምነት ነቢያት በሙሉ ጥሪ ያደረጉበትና ያስተማሩት እምነት ነው።

እነዚህን ሶስት እምነቶች ትንሽ እናስታውስ:-

የመጀመሪያው ቡድን ሰዎች የሚሉትና እምነታቸውን የሚያቀርቡት ከሞተ በኋላ ደግሞ የተነሣ ሰው አይተው ስለማያውቁ ነው፤ በነሱ እምነት ሰው ከሞተ በኋላ አፈር የሚበላው ትቢያ እንጂ ዳግም ሕይወት አይዘራበትም ነው።.... ታዲያ ይህ ማስረጃ ሊሆን ይችላልን? ከሞተ በኋላ ዳግም ሕይወት የዘራ ሰው ባለማየታችን ማለት የምንችለው ነገር ከሞት በኋላ ምን እንደሚኾን አናውቅም ይሆ ናል። ከሞት በኋላ ሕይወት አለመኖሩን አውቃለሁ የሚለው አባባል ግን ማስረጃ የለውም። ከገጠር አንድ ሰው በዓይኑ አይሮፕላን አይቶ የማያውቅ ከሆነ አይሮፕላን ምን እንደሆነ አላውቅም ማለት ይችላል። አይሮፕላን የሚባል ነገር በዚህ ዓለም ላይ አለመኖሩን አውቃለሁ ካለ ግን ሞኝና ተላላ በመሆኑ ሁሉም ይስማማል። ነገር ግን አንድን ነገር አለማየት ማለት ያ ነገር የለም፤ ሕልውና የለውም ማለት አይደለም። የምድረ ዓለም ነዋሪዎች

በሙሉ በአንድ ቃል አንድ ነገር አላየንም ቢሉ እንኳ ያ ነገር ሕልውና የለውም ወይም ሊኖር አይችልም ብለው መናገር አይፈቀድላቸውም።

ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የሰው ልጅ በአሁኑ ሕይወቱ ውስጥ ሰው ነው፤ ምክንያቱም እንስሳ በነበረበት በመጀመሪያ ሕይወት ዘመኑ መልካም ሰርተዋልና። እንሰሳም በአሁኑ ሕይወቱ እንስሳ ነው፣ ምክንያቱም ሰው በነበረበት በመጀመሪያው ዙር የሕይወት ዘመኑ ከፉ ሠርቷልና ብሎ ያምናል። በሌላ አባባል የሰው ሰው መሆን፤ የእንስሳ እንስሳ መሆን፤ የዛፍ ዛፍ መሆን፤ በመጀመሪያው የሕይወት ዘመኑ የፈጸመው የመልካም ሥራው ወይም የመጥፎ ሥራው ውጤት ነው። በዚህ ሁኔታ ሞትና ሕይወት በዚህ ምድረ ዓለም ላይ ይፈራረቅበታል ማለት ነው።

በዚህ ረገድ የሚነሳው ጥያቄ «በዚህ ምድራዊ ዓለም ላይ በመጀመሪያ የነበረው የቱ ነው? » የሚል ይሆናል። ሰው ነው ከተባለ በዚያ በፊት የግዴታ እንስሳ ወይም ዛፍ ነበረ ማለት ነው። አለዚያ ይህን የሰውነት ቅርጽ በየትኛው በጐ ሥራው ይታደላል? እንስሳ ወይም ዛፍ ነበር ከተባለም የግዴታ ቀደም ብሎ ሰው ነበር ማለት ነው። ይህ ካልሆነ ምን ዓይነት ከፉ ሥራ ፈጽሞ ነው በምላሹ የእንሰሳ ወይም የዛፍ ቅርጽ የተሰጠው? ይህን እምነት የሚያራ ምዱት ሰዎች ይህ ዓለም በአንድ የተወሰነ ዝርያ መጀመሩን ማረጋገጥ አይችሉም።አንዱ ትውልድ የሌላው ትውልድ የሥራ ውጤት ለመሆን እያንዳንዱ ትውልድ ከሌላ ትውልድ የለጠቀ መሆኑ ግዴታ ነውና። ይህ ደግሞ ሰብአዊ አእምሮን የሚቃረንና በፍጹም የማይጣጣም ነው። ቀጥለን ደግሞ ሶስተኛውን እምነት እንውሰድ:-

የዚህ እምነት የመጀመሪያው ነጥብ ሃያሉ አላህ ለፍጥረተ ዓለሙ ፍጻሜና ለዩኒቨርሱ መጨረሻ የተወሰነ ቀን ቀጠሮ ይዟል።

በዚያ ቀን ቀጠሮ ሰማያትና ምድሩ በሌላ ይለወጣሉ የሚል ነው። ይህም አርቆ ማስተዋል የሚችል ሰው ምንም የማይጠራጠረው እውነታ ነው። አንድ ሰው የዚህን ዩኒቨርስ ቤተሙከራ ላይ ያለውን ትኩረት በጨመረ ቁጥር ዘለዓለማዊነት እንደሌለው ይበልጥ ይረዳል፤ የዩኒቨርሱ ኃይሎችና መሣሪያዎች በሙሉ ውስንና ከዕለታት አንድ ቀን የግዴታ የሚጠፉ መሆናቸውንም ይገነዘባል። ከዚህ በመነሣትም የተፈጥሮ ሣይንስ ጠበብት ይህች ፀሐይ ከዕለ ታት አንድ ቀን እንደምትበርድ ብርሃኗን እንደምታጣ፤ ከዋክ ብትና ኘላኔቶችም እርስ በርሳቸው ተጋጭተው ይህ ዓለም ከፍጻ ሜው እንደሚደርስ በአንድ ቃል ይስማማሉ።

ይህም የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ ሌላ ዳግም ሕይወት እንደ ሚኖረው ከዚህ እምነት ያረጋግጣል። ይህ የማይቻል ነገር ነው ወይ? የማይቻል ከሆነ የሰው ልጅ ይህን ዓለማዊ ሕይወት እንዴት ማግኘት ቻለ? ...በዚህ ዓለም ላይ ሰውን መጀመሪያ የፈጠረው ሃያሉ አላህ ሰውን ከሞተ በኋላ እንደገና ሊፈጥረው የሚችል አምላክ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

እንደዚሁም የሰው ልጅ መልካሙም ሆነ መጥፎ ሥራው የሚመዘገብና በትንሣኤው ቀን በሚቀርብለት ግልጽ መዝገብ ውስጥ የሚያዝ መሆኑን ማመን የዚህ እምነት አንዱ አካል ነው። ለዚህም ማረጋገጫው ዛሬም ማግኘት የሚቻል ነገር ነው።

በቀድሞው ዘመን ከአንደበታችን የሚወጣው ድምጽ አየር ሰንጥቆ ሞገዱ ትንሽ ከተርገበገበ በኋላ ይከስማል የሚል ግምት ሰዎች ዘንድ ሰፍኖ ነበር። ከቅርብ ዘመን ወዲህ ግን እያንዳንዱ ድምጽ በአካባቢው ባሉት ነገሮች ላይ ተጽእኖ እንደሚያሣድር፤ ቅሪትም የሚተውና ከጊዜ በኋላም ተቆጣጥሮ እንደገና ድምጹን ማግኘት እንደሚቻል ታውቋል። በዚህ መርህ ላይ በመመርኮዝ ሰው ግራማፎን አስገኝቷል። ይህም በዚህ ምድራዊ ዓለም ከኛ

የሚመነጨው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ባንዱ ወይም በሌላው መልክ በሚርጡበት ነገሮች ላይ የሚመዘገቡ /የሚቀረጹ/ መሆኑን ያመለክታል። ይህን ካወቅን በዚህ ዓለም ላይ የምንፈጽማቸው ሥራዎች በሙሉ የሚቀረጹና የሚመዘገቡ መሆናቸውንና እንደገናም ሕያው አድርጎ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን በተጨባጭ እናውቃለን ማለት ነው።

ሃያሉ አላህ ሰዎችን ወደራሱ በሚሰበስባቸው ቀን ሁሉንም እንደየሥራው መልካምም ከሆነ መልካም መጥፎም ከሆነ መጥፎ ምንዳ ሊከፍለውና ፍትሕ የተመላበት ብይን የሚሰጥ መሆኑን ማመን የዚህ እምነት አንዱ ክፍል ነው። ይህ የማይቻል ነው ማለት የሚችል ማነው? አእምሮ የማይቀበለው ነገር አለበት ወይ? አላህ ሰዎችን ደግሞ ቀስቅሶ አንድ ቀን የተስተካከለ ፍርድ እንደሚሰጣቸው አእምሮም ራሱ ይመሰክራል። ይኸውም አንድ ሰው መልካም ሠርቶ በዚህ ዓለም ላይ ተገቢ ዋጋውን የማያገኝ ሆኖ ወይም ደግሞ ከፉ ሠሪ ሆኖ ተገቢ ቅጣቱን ያልተቀበለ ሆኖ በዓይናችን እናያለን። ደጋግ የአላህ ጻድቃንን ጉዳት ሲደርስባቸው ከፉ ሠሪ ኃጢአተኞች ደግሞ የደስታና የታደለ ኑሮ ሲቀሙ እናስተውላለን። አእምሮ ራሱ በነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ሰው በመልካሙም ሆነ በመጥፎ ሥራው ተገቢውን ምንዳ ማግኘት እንዳለበት ይወስናል።

የዚህ እምነት የመጨረሻ ነጥብ የገነትና የእሳት /የገሃነም/ መኖርን ማመን ነው። ገነትና ገሃነም መኖራቸው አዳጋች ነገር አይደለም። ሃያሉ አላህ ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ማርስንና መሬትን መፍጠር ከቻለ እሳትና ገሃነምን መፍጠር እንዴት ይሣነዋል? ሃያሉ አላህ ወደ ችሎቱ ሰዎችን ከሞት ሲቀሰቅሳቸው መልካም ምንዳ ለሚሰጣቸው ደጋጎች የክብር፣ የደስታ፣ የተድላና የጸጋ

ሥፍራ፣ ለሚቀጣቸውም የውርደት፣ የቅጣት፣ የሐዘንና የጭንቀት ሥፍራ ማኖሩ ተገቢ ይሆናል።

እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስናስተውል ይህ እምነት ዛሬ በዓለም ላይ ከሚገኙትና ከሞት በኋላ ያለውን የሰው ሕይወት ከሚመለከቱ እምነቶች ሁሉ ለሰብአዊ አእምሮ የቀረበ፣ አእምሮን የሚቃረን አንዳች ነገር የሌለበት ወይም ሊኖርበት የማይችል እምነት መሆኑን ያለ ጥርጥር እንረዳለን።

ይህ ጉዳይ የደረሰን ደግሞ በነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ አንደበት ከሆነ –የነቢዩ ታማኝነት፣ እውነተኛነትና ንጽሕና ቀደም ሲል የተወሳ ነውና ከፍተኛ ጥቅም ለራሳችን የምናገኝበት ነው። አእምሮ እንድናምን ይወስንብናል እንጂ ያለ ማስረጃና ያለማረጋገጫ እንድንጠራጠር አይወስንም።

## መልካሙ ቃል:-

ቀጥለው ያሉት የእስልምና አበይት መሠረት የሆኑት አምስቱ የእምነት ማዕዘናት ናቸው። እነሱም «ላኢላሀ ኢለሏህ» ማለትም ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው በሚለው ውስጥ ይጠቃለላሉ። «ላኢላሀ ኢለሏህ» ስንል የተቀሩትን ባዕድ አማልክትን ትተን አምላክነትን ለአንዱ አምላክ ብቻ ማረጋገጣችን ነው። «ሙሐመድን ረሱሉሏህ» ስንልም እንደዚሁ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ከአላህ ወደ ሰዎች የተላኩ መልዕክተኛ መሆናቸውን ማረጋገጣችን ነው። ይህን የነቢዩን ሙሐመድ መልዕክት ማረጋገጥ ማለት ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያስተማሩትን ሁሉ አምኖ መቀበል፣ ስለ አላህ መኖር፣ ስለባህሪያቱ፣ ስለ መላእክቱ፣ ስለ መለኮታዊ መጻሕፍቱ ስለነቢያቱና ስለትንሣኤው ቀን የዘረዘሩትን ሁሉ ከልብ አምኖ በመቀበል

አላህን ለመገዛት፣ ሕግጋቱንና ትእዛዞቹን ለመከተል ነቢዩ በቀየሱት መንገድ መጓዝ ማለት ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## አላህን መገዛት አል ኢባዳት

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ቀጥለው ባሉት የእምነት መሠረቶች እንድናምን አዘውናል።

1. ሃያሉ አላህ አንድና አጋር የሌለው አምላክ መሆኑን፣

2. በአላህ መላዕክት፣

3. በመለኮታዊ መጻሕፍትና በተለይም በቁርአን፣

4. በነቢያቱና በተለይም የነቢያቱ መደምደሚያ የሆኑት በነ ቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/መሆናቸውን

5. ከዚህች ዓለም ሕይወት በኋላ ዘለዓለማዊ የሆነ ዳግም ሕይወት መኖሩን፣ ማመን ናቸው።

እነዚህ አምስቱ የእስልምና አበይት መሠረቶች ናቸው። በነዚህ አምስት ነጥቦች ያመነ ሰው ከሙስሊሞች ጐራ ገብቶ ሙስሊም ሆኗል። ይሁን እንጂ በዚህ ብቻ እስልምናው አይሟላም። አንድ ሰው እስልምናው የተሟላ መሆን የሚችለው ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ከአላህ ዘንድ ያመጧቸውን ሕግጋትና ትእዛዞች ተግባራዊ በማድረግ ሲገዛ ብቻ ነው። ባንድ ነገር ካመን በኋላ እምነታችንን ተግባራዊ ማድረግ ግዴታ ነው።

ይህ ከእምነት የሚቀጥለው ታዛዥነት ነው እስልምና። አምላካችን አላህ ብቻ መሆኑን አምነን ተቀብለናል። ይህም ማለት እሱ ጌታችን ሲሆን እኛ ደግሞ ተገዥ ባሪያው ነን ማለት ነው። እሱ ገዥያችን፣ አዛዣችንና ከልካያችን ሲሆን እኛ ቃሉን ፈጻሚ፣

የሆን ትእዛዙን አክባሪ፣ ታዛዦች፣ ለሕጉ ተመሪዎች ነን ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ትእዛዙን ከጣስን በጌታችንና በአስተዳዳሪያችን ትእዛዝና ሕግ ላይ ማመጻችንን በገዛ ራሣችን ላይ እናረጋግጣለን። ቁርአን የአላህ መጽሐፍ መሆኑንም አምነናል። ይህም ማለት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተመለከቱት ነገሮች ሁሉ እውነት ከአላህ ዘንድ የተላለፉ መሆናቸውን ተቀብለናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ በተራው ጽሑፉን እንድናረጋግጥ፣ ያዘዘውን ሁሉ እንድንፈጽም፣ ከከለከለው ሁሉ እንድንከለከል ግዴታ ይጥልብናል ማለት ነው። እንደዚሁም ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የአላህ ነቢይና መልዕክተኛ መሆናቸውን አረጋግጠናል። ይህ ማለት ደግሞ ነቢዩ የሚያዙንና የሚከለክሉንን ነገሮች ሁሉ ከአላህ ዘንድ የተላለፉ ናቸው ማለት ሲሆን ይህም በተራው ነቢዩን የመታዘዝ ግዴታ ውስጥ ያስገባናል። ስለዚህም እስልምናችን የተሟላ መሆን የሚችለው ተግባራችን ከእምነታችን ጋር ሲጣጣም ብቻ ይሆናል። አለዚያ በእምነታችንና በተግባራችን መካከል ባለው ልዩነት መጠን እምነታችን ያልተ ሟላና ጉደሎ ይሆናል።

ቀጥለን ደግሞ አላህ በሚፈቅደው መሠረት ሕይወታችንን እንድንመራ ነቢዩ ሙሐመድ የቀየሱልንን መንገድ እንመልከት። ይህን በተመለከተ ዋንኛውና ግንባር ቀደሙ ግዴታ አላህን መገዛት /አምልኮ/ ወይም «ዒባዳ» ነው። መገዛት /ዒባዳ/ ማለት የሙስ ሊሙ ማህበረሰብ አባል ነኝ የሚል እያንዳንዱ አማኝ ግለሰብ ማከናወን ያለበት መሠረታዊ ተግባር ነው።

## የመገዛት ኢባዳ ትርጉም

መገዛት /ኢባዳ/ ማለት በቃልም ሆነ በተግባር መታዘዝ ማለት ሲሆን አላህ አዛዥና ገዥ የሰው ልጅ ደግሞ የአላህ ባሪያና ተገዥ

ነው። በዚህ መንፈስ የአዛዡን ትእዛዝ ተግባራዊ በማድረግ ሰው የሚያከናውነው ማንኛውም ነገር መገዛት /ዒባዳ/ ነው። ለምሣሌ ያህል ሰዎችን ከውሸት፣ ከሃሜት፣ ከነውርና ከብልግና በጠራ ሁኔታ እንድንናገር አላህ ያዘዘን መሆኑን በማሰብ ካነጋገርን፤ ሆን ብለን እውነትን፣ ትክክለኛነትን፣ በጐ አመለካከትን፣ ፍትህን በተላበሰ ሁኔታ አላህ እነዚህን ነገሮች እንደሚወድ በማሰብ ከተነጋገርን፤ አጠቃላይ ይዘቱ ስለዓለማዊ ኑሮአችን ቢሆን እንኳ ይህ ንግግራችን ሙሉ በሙሉ አላህን መገዛት /ዒባዳ/ ነው። እንደዚሁም ከሰዎች ጋር ባለን ማህበራዊ ግንኙነት ስንገዛና ስን ሸጥ፣ ከወዳጆቻችንና ከዘመዶቻችን ጋር ስንጫዋወት የጌታችንን ሕግጋትና ድንጋጌዎች በድርጊታችን ውስጥ እስከተከተልን ድረስ፤ ሌሎች የሚገባንን ግዴታ ስንፈጽም አላህ ግዴታችንን እንድንወጣ ስላዘዘንና የሌሎችን መብት እንዳናጓድል ስለከለከለን መሆኑን በማሰብ ከሆነ ሃያሉን አላህ ተገዛን፤ ዒባዳ ፈጸምን ማለት ነው። እንደዚሁም ደሃን ስንረዳ ወይም የተበደለን ሰው ስናግዝ፣ ረሀብተኛን ስናበላ፣ በሽተኛን ስንጠይቅ የአላህን ምንዳና ውዴታውን በማሰብ ብቻ ከመነጨ ፍላጐት፣ ጥቅም፣ ክብርና ዝናን ከማግኘት በራቀ መንፈስ መሆኑን ካረጋገጥን አላህን እንደተገዛን፣ ዒባዳ እንዳደረግን ይቆጠራል። በንግድ ሥራ ወይም በእንዱስትሪ ወይም በአገልግሎት ሰጭነት ተሰማርተን ያለብንን ግዴታ በፍጹ ምነት፣ በታማኝነት፣ በሐቀኝነት አላህን በማሰብ ከተወጣን፤ አላህ በፈቀደው ሀላል ሥራ ላይ ተሰማርተን አላህ ከከለከለው ሁሉም ሥራ ሁሉ ከተቆጠብን ይህ የተሰማራንበት ሥራና ለኑሮአችን የምናደርገው ጥረት ራሣችንን ለማኖር የተደረገ የመኖር ግዴታ ቢሆን እንኳ ይህ ሁሉ አላህን ከመገዛት /ከዒባዳ/ ይቆጠራል።

በአጠቃላይ አነጋገር በዕለታዊ ኑሮአችን በሁሉም ሥፍራና ጊዜ የአላህ ፍራቻ ልባችን ውስጥ እስካለና በምናደርገው ሁሉ የአላህ ውዴታ ካለ፣ ሕግጋቱን ከተከተልን፣ የአላህን ትእዛዝ

በመጣስ የምናገኘውን ወይም ማግኘት የምንችለውን ጥቅም ሁሉ ወደ ጐን ከተውን፣ ትእዛዙን በመፈጸማችን የሚደርስብንን ወይም ሊደርስብን የሚችለውን ጉዳት ሁሉ ከታገስን፣ ይህ ሁሉ አላህን መገዛት /ዒባዳ/ ነው። በዚህ መንገድ የተመራ ሕይወታችን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው አላህን መገዛት ወይም ዒባዳ ነው። እንዲህ ባለ ሕይወት ውስጥ መብላት መጠጣቱም፣ መተኛት መነሣቱም፣ መሄድ መቀመጡም፣ መናገርና ዝምታውም አላህን መገዛት ነው።

ይህ ነው አላህን መገዛት። የዒባዳ ትክክለኛ ትርጉምም ይኸው ነው። የእስልምና ዓላማም የሰው ልጅ ሁልጊዜ ይህን በመሰለ ሁኔታ አላህን የሚገዛ አምላኪ እንዲሆን ማድረግ ነው። ለዚህ ከፍተኛ መገዛት /ዒባዳ/ ይዘጋጅ ዘንድም የተወሰኑና ግዴታ የሆኑ የመገዛትን /የዒባዳ/ ስብስቦችን እስልምና አውጇአል። እነዚህ የዒባዳ ስብስቦችም ለተፈላጊው ከፍተኛ መገዛት እንደ ሥልጠናና ልምምድ የሚቆጠሩ ናቸው። ይህን ስልጠናና ልምምድ በሚገባ የፈጸመ ሰው ሁሉ እውነተኛን ታላቅ መገዛትንም በሚፈልገው ሁኔታ ይፈጽማል። ከዚህም ምክንያት እነዚህ የዒባዳ ስብስቦች በእስልምና ውስጥ የዒባዳ አስኳል ናቸው። የሃይማኖት ማዕዘናትና የታነፁበት መሠረቶች ተብለውም ይጠራሉ። አንድ ሕንጻ በጠንካራ የመሠረት ማዕዘናት ላይ እንደሚታነጸው ሁሉ የእስላ ማዊ ሕይወት በነዚህ መሠረቶች ላይ ብቻ ነው የሚገነባው። እነዚህን መሠረቶች የናደ ሰው እስልምናን ራሱን ንዶአል።

## ሰላት:-

ከእስልምና የመገዛት ግዴታዎች ሁሉ ዋነኛው መሠረታዊ ግዴታ ሰላት ነው።ሰላት ያመንበትን ነገር በሃያ አራት ሰዓት /አንድ

ቀንና ሌሊት/ ውስጥ አምስት ጊዜ በአንደበታችንና በተግባራችን እንደገና ማስታወስ ነው። ጧት ከእንቅልፍ ስንነሳ ሌላ ነገር ከመጀመራችን በፊት ንጹሕና የጠራን ሆነን እጌታችን ፊት እንቆማለን። ከዚያም ተገዥነታችንን ከፊቱ ቀርበን በመቆም፣ በመቀመጥ፣ ቆመን በማጐንበስና መሬት ደርሰን ግንባራችንን ከመሬት አድርሰን ታዛዥነታችንን ለጌታችን እናረጋግጣለን። ረድ ኤቱን እንዲሰጠንና ወደ ዋናው መንገድ እንዲመራን እንለም ነዋለን። በኛና በርሱ መካከል ያለውን የታዛዥነትና የተገዥነት ቃል ኪዳን እናድሳለን።የርሱን ውዴታ የመጐናጸፍና ከቁጣው የመራቅ ምኞታችንን ደጋግመን እንገልጻለን። የመጽሐፉን ጥናት እንደጋ ግማለን። የነቢዩን እውነተኛ ነቢይነት እንመሰክራለን። ወደርሱ ችሎት ቀርበን ስለሥራዎቻችን የምንጠየቅበትና ተገቢ ዋጋችንን የምናገኝበትን ቀን እናስታውሳለን። ... በዚህም አዲስ ቀን እንቀበ ለውና እስከ እኩለ ቀን ድረስ በየሥራችን ላይ እንሰማራለን። ከዚያም አላህን ለማስታወስ እንድንወጣ የሶላት ጥሪ ይተላለፋል። አላህን እንድንዘከር፣ መልመጃው እንደገና እንዲደግም፣ ጌታ ችንን ረስተን ከዘንጊዎች እንዳንቆጠር የሶላቱ ጥሪ ሲተላለፍልን ሰግደን እምነታችንን ካደስን በኋላ ወደ ዓለማዊው ጉዳያችን እንመለሳለን። ከጥቂት ሰዓቶች በኋላም ለሶስተኛ ጊዜ የዐስር ሶላት ጥሪ ይተላለፋል። ከዚያም ቀኑ መሽቶ ሌሊቱ ሲጀመር ጧት ቀኑን በተቀበልነው የአላህ ውዳሴና መገዛት የሌሊት ምልጃችንን እንጓ ንረሳ በሶላት እንቀበላለን። ከዚያም ከጥቂት ሰዓት በኋላ ከመኝታ በፊት የዒሻ ሶላት በመስገድ ጌታችንን ለመጨረሻው የቀኑ መሰና በቻ እናስታውሳለን።የዚህ ሶላት ጊዜ የእርጋታና የጸጥታ ጊዜ ሲሆን በቀኑ ትርምስና የሥራ ውጥረት ውስጥ የተፈለገውን የመንፈስ ዕረፍት እናገኛለን።

ሶላት የእስልምናችንን መሠረቶች በየዕለቱ አምስት ጊዜያት ዘወትር የሚደግፍ ሲሆን ቀደም ሲል ለወሰነው እውነተኛ ስፊ

መገዛት /ኢባዳ/ ያዘጋጀናል። ለመንፈሳችን ጥራት፣ ለሞራላችን ምጥቀት፣ ለሥነ ምግባራችንና ለሥራዎቻችን መቃናት ወሣኝ የሆኑ እምነቶችን ዘወትር ያስታውሰናል። ለሶላት አስፈላጊውን ነጥቦች /ውዱእ/ ስናደርግ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያስተ ማሩትን የተለየ የአፈጻጸም መንገድ ለምን እንደምንከተል፣ በሶላ ታችን ውስጥ የምንደግማቸውንና ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያስተማሩትን ዐረፍተ ነገሮች ለምን እንደምናነብ እንመልከት። የነቢዩን ትእዛዝ መፈጸም ግዴታችን መሆኑን ስለምንረዳ አይደ ለም ወይ? ስንሰግድ የምናነበው ቁርአን ሆን ብለን ለምን አንሳ ሳትም? ቁርአን የአላህ መጽሐፍ ለመሆኑ እርግጠኞች ስለሆን አይደለም ወይ? በሶላታችን ውስጥ ነቢዩ ያስተማሩትን ትተን ሌላ ብናነብ ወይም ከነጭራሹ ባናነብ ማንን ነው የምንፈራው? አነበብን አላነበብን ሰላት ውስጥ ማንም ሰው አያዳምጠንም። ይህ ሁሉ አላህ የሚሰማን፣ ድምጽ ሳናሰማ ብናነብም ከርሱ የማይሰወር መሆኑን ስለምናውቅ አይደለም ወይ? ማንም ሰው ስለ ማያየን ከእንቅልፍ ነቅተን ወደ ሶላት እንድንሰማራ የሚያደርገን ምንድነው? አላህ እንደሚያየን ስለምናምን ብቻ አይደለም ወይ? ሶላት ሲደርስ ያለንበትን ሥራ ትተን ወደ ሶላቱ እንድንሄድ የሚያደርገን ምንድ ነው? አላህ ይህን ሶላት ነፍስ ወከፍ ግዴታ ስላደረገብን መሆኑ ስለሚሰማን አይደለም ወይ? በበጋ ወቅት የማለዳ ሰዓት፣ በክረ ምት ወቅት የዙህር፣ በየለቱ ምሽት በጨዋታና በመዝናኛ ሰዓቶች እንድንሰግድ የሚያስገድደን ምንድነው? የሚሰማን የኃላፊነትና የግዴታ ስሜታችን አይደለም ወይ? ካልሰገድን ወይም ሆን ብለን ሶላታችን ውስጥ ብንሳሳት ለምን እንፈራለን? አላህ ስለምንፈራ ወደርሱ ተመልሰን በትንሣኤው ቀን እፊቱ የምንቀርብ መሆናችንን ስለምናውቅ ብቻ አይደለም ወይ? ታዲያ በዚህ ዓለም ላይ ሰውን እውነተኛ ሙስሊም የሚያደርግ ከሶላት የበለጠ ስልጠና አለ በሉኝ እስቲ? የአላህን ውዳሴና ፍርሃት ከማደስ፣ ውስጠአዋቂና ተመል

ካች መሆኑን በእውነት ተረድቶ እሱን ከማውሳት፣ በትንሣኤው ቀን ከችሎቱ ፊት የሚቀርብ መሆኑን ከማመንና በየቀኑና ሌሊቱ ለብዙ ጊዜ ነቢዩን መከተል፣ በየዕለቱ በጥቂት ሰዓቶች ልዩነት ኃላፊነትና ግዴታ የመወጣት ልምምድና ስልጠና ከማግኘት የተ ሻለ ስልጠና ሊኖር ይችላል ወይ? ይህ ዓይነት ሥልጠና የተሰጠው ሰው ከመስጊድ ወጥቶ ወደ ሥራው ዓለም በሚገባበት ጊዜ አላህን ይፈራል፤ ሕግጋቱን ይከተላል፤ ሰይጣን ወስውሶት የአላህን ትእዛዝ ጥሶ ጥፋት ሲፈጽም አላህ የሚያየውና ከርሱ መሰወር እንደማይችል ያስታውሣል ተብሎ ተስፋ ይጣልበታል። ከዚህ የላቀ ስልጠና በኋላ አላህን የማይፈራ፣ ትእዛዙን ከመጣስ እጁን የማይሰበስብና ሕጐቹን የሚተላለፍ ሰው ካለ ይህ ሰው ከሥረ መሠረቱ አስተዳደጉ የተበላሸ፤ በተፈጥሮው ጥፋት፣ ክፋትና ሸር ስላለበት እንጂ ከስልጠናው አይደለም።

የሶላትን ግዴታ አንድ ቦታ በመሰብሰብ በሕብረት /በጀማዓ/ እንዲፈጽሙ አላህ ሙስሊሞችን አጥብቆ አሳስቦአል። በየሳምንቱ ዐርብ ቀን ደግሞ አንድ ቦታ ተሰብስበው የጁምአ ሶላትን በህብረት መስገድ ግዴታ አድርጐአል። በህብረት መስገድ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ ወንድማማችነትን በሙስሊሞች መካከል ያጐለብታል። ጠንካራ ቡድን ያደርጋቸዋል። አንድ ቦታ ተሰብስበው በሕብረት ለጌታቸው ሲገዙ፣ ሲያጐነብሱና ሲሰግዱ ልቦቻቸው ይቀራ ረባሉ። የወንድማማችነት ስሜት ይታነጽባቸዋል። እንደዚሁም በአንድነት መስገድ ከመካከላቸው ለሚመረጡት አዛዥ የመታዘዝ ልምድ ይሰጣቸዋል። ሥነ ሥርዓትና ለሥነ ምግባር መገዛትን ያለማምዳቸዋል። ጊዜን በአግባቡ የመጠቀምና የመቆጠብ ልምድ ያስገኝላቸዋል። መተሳሰብን፣ መታዘዝን፣ እኩልነትንና መግባ ባትን ስለሚያንጽባቸው ሀብታሙም፣ ደሃውም፣ ትልቁም፣ ትን ሹም፣ ተራውም፣ ባለሥልጣኑም፣ እገሌ ትልቅ ነው፣ እገሌ ተራ ነው የሚባል ነገር ሣይኖር ሁሉም ጐን ለጐን ሲቆሙ እናያለን።

ይህ ሶላት ለአላህ ሣይሆን ለገዛ ራሣችን ከሚያስገኝልን ጥቅሞች ከፊሉ ነው። አላህ ሶላትን የደነገገው ለኛው ለራሳችን ጥቅም ነው። ሶላቱን ባለመስገዳችን የሚቆጣውም እርሱን ስለጐዳን ሣይሆን ራሣችንን የበደልን በመሆናችን ብቻ ነው። በሰላት አማካይነት አላህ የሰጠንን ታላቅ ኃይልና ጸጋ እምቢ ስንል እስቲ አስተውሉ፣ ውርደት ነው! የአላህን አምላክነት፣ የሙሐመድን መልዕክተኛነት፣ ትእዛዛቸውን የማክበር ግዴታና ነገ አላህ ፊት ተጠያቂነት ያለብን መሆኑን በገዛ አንደበታችን እያረጋገጥን ጌታ ችን ያዘዘውን ዋነኛ ግዴታ አለመፈጸም ምን ይባላል? ለዚህ ሁለት ነገሮች ይኖራሉ ማለት ነው። ወይ ሶላት አላህ የደነገገው ግዴታ መሆኑን እናስተባብላለን፤ ወይም ደግሞ ከአላህ የተላለፈ ግዴታ መሆኑን እያረጋገጥን መፈጸሙን ችላ እንላለን። ግዴታነቱን የምና ስተባብል ከሆነ ቁርአንንም እናስተባብላለን ማለት ነው። በሁለ ቱም እናምናለን የምንለው ከንቱና ውሸት አባባል ነው ማለት ነው። ከአላህ ዘንድ የተላለፈ ግዴታ መሆኑን እያረጋገጥን የማንሰግድ ከሆን ደግሞ ሰዎች ስለታማኝነታችን በኛ ላይ ያላቸውን እምነት ከነጭራሹ ለማስወገድ በቂ ምክንያት ነው። አላህ በኛ ላይ የጣለ ውን አደራ በታማኝነት ያልተወጣን የሰዎችን መብትና አደራ ለመጠበቅ እንዴት ብሎ እምነት ይጣልብናል?!

## ጾም፡-

ሁለተኛው የእስልምና የመገዛት ግዴታዎች አቢይ ምሶሶ ጾም ነው። ለመሆኑ ጾም ምንድነው? በአንድ ቀንና ሌሊት ውስጥ አምስት ጊዜያት ሶላት የሚያስገኘውን መልመጃ አንድ ወር ከሚጾመው የረመዳን ወር ጾም በዓመት አንድ ጊዜ እናገኛለን። ረመዳን ሲመጣ ከጧት እስከማታ ድረስ ከምግብና ከሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስንከለከል፤ ማለዳ የሱቢሂ ሶላት አዛን መተላለፉን

ስንሰማ ወዲያውኑ ከምግብና ከመጠጡ እንወገዳለን። ከአዛኑ በኋላ የፈለገው አይነት አስጐምጂ ምግብና መጠጥ ቢሆንም ወይም በጣም የራበን ብንሆንም እንኳ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ በፍጹም አንቀርበውም። ምግብና መጠጡን ከሰዎች እይታ ፊት ብቻ የምንተተወው ሣይሆን ማንም ሰው በማያየንና ለብቻችን በምንሆንበት ጊዜም ቢሆን አንቀርበውም። ከጐህ መቅደድ እስከ ጸሐይ መጥለቅ ባለው የጾም ጊዜ ውስጥ አንድ ጠብታ ውሃ ወይም ጉርሻ ምግብ በፍጹም በአፋችን አናደርስም። ይህ እገዳ ግን ለተወሰነ ጊዜ ማለትም እስከ ፀሐይ መጥለቅ ቆይቶ የመግሪብ ሰላት ጥሪ ሲተላለፍ ጾሙ ይፈሰክና መብላትና መጠጣቱ ይቀጥላል። አርቀን እናስተውል / ምንድነው ይህ የምንጾመው? ይህን የምናደርገው ከኋላው የሃያሉ አላህ ፍራቻ በመኖሩና አላህ አዋቂ፣ ሰሚ፣ ተመልካች መሆኑን በፍጹምነት ስለምናውቅ፤ የመጨረሻው ቀንና ትንሣኤ እንዳለና በዚያን ጊዜ አላህ ችሎት ቀርበን የምንጠየቅ መሆኑን ስለምናምን፤ ለቁርአንና ለነቢዩ ሙሐመድ ፍጹም ታዛዥ ስለሆን ባለን ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት፣ ለትዕግሥትና ለቻይነት ባለን ልምድና በስሜታዊ ዝንባሌዎች ላይ ባለን የአሸናፊነት ብቃት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህን የመሰለ ከፍተኛ ሥነ ምግባር እንድንላበስ የሚያደርገን ስልጠና ለሰላሳ ቀናት ሙሉ እውነተኛና የተሟላ ሙስሊም ሊያደርገን ወርኃ ረመዳን በያዓመቱ ይመጣል። እነዚህ ባህሪያትና ሥነ ምግባሮችም አንድ ሙስሊም በያንዳንዱ የሕይወቱ ደቂቃ ውስጥ መፈጸም የሚገባውን ዋነኛውን መገዛት /ዒባዳ/ ለማከናወን ብቃት እንዲኖረን ያደርጉናል።

ሃያሉ አላህ ሙስሊሞች ሁሉ እንዲጾሙ የደነገገላቸው አንድ የተወሰነ ወር ብቻ ነው።ይህንም ማድረጉ ሳይለያዩ በህብረት እንዲጾሙት ነው። ይህም ብዙ ጥቅሞች አጠቃሏል። የረመዳን ወር ሲመጣ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ አየር ንጽሕና ጥራት እምነት፣ አላህን መፍራትና ሕግጋቱን መታዘዝ፣ የባህሪይ ሸጋነት፣

በጉ ሥራ የሚሞላበት ሲሆን የመጥፎ ሥራ ገበያ ከስሞ የበጉ ሥራና የመልካም ተግባር ገበያ ይደራል። ደጋግ የአላህ ባሮች በመልካም ሥራና በትሩፋት ተግባር ላይ እርስበርሳቸው መተባበር ይጀምራሉ፤ ሲሆን ከፉ ሠሪዎችና ሸረኞች በመጥፎ ሥራቸው ሀፍረት ይከናነባሉ።በባለጸጋዎች ሕሊና ውስጥም ደሃ ወንድሞቻቸውን የመርዳት ስሜት ይቀሰቀሳል፤ ገንዘባቸውን በአላህ መንገድ ይለግሳሉ። ሙስሊሞች በሙሉ ተመሣሣይ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ይሆናሉ። ይህ ሁሉ ሙስሊሞች በሙሉ አንድ ስብስብ የመሆናቸው የጋራ ስሜት እንዲቀረጽባቸው ያደርጋል። የመዋደድ፣ የወንድማማችነት፣የመተሳሰብ፣ የመረዳዳትና የአን ድነት ስሜት በሙስሊሞች መካከል ለማጉልበት ፍቱን መሣሪያ ይሆናል።

ይህ ሁሉ ጥቅም ለገዛ ራሣችን ነው። አላህ በኛ መራብ ምንም አይጠቀምም፤ የረመዳንን ወር እንድንጾም የደነገገውም ለኛው ጥቅም ብቻ ነው። ይህን ግዴታ የማይፈጽሙ ሰዎች፤ ያላንዳች ምክንያት ጾሙን የሚፈስኩ ሰዎች ራሣቸውን ነው የሚበድሉት። ከነዚህ የባሱ ሀፍረት የለሾችና ከሁሉም የከፉ ተልካሾች ደግሞ በወረሃ ረመዳን ቀናት ያለ እፍረትና ያላንዳች ይሉኝታ በይፋ የሚበሉና የሚጠጡ ሰዎች ናቸው። በዚህ ወራዳ ተግባራቸው ከሙስሊሞቹ ጐራ ባለመሆናቸ የሃይማኖታቸውን ሕግጋት አያከ ብሩም። የሃይማኖቱን ህግጋት አናከብርም፣ ከብዙኃኑ ሙስ ሊሞች ብንነጠልም ግድ የለንም የሚሉ ይመስላሉ። የፈጣሪያቸው የመጽዋቻቸውን ትእዛዝ መጣስ ጥቂት እንኳ የማያስፈራቸው፤ ታላቁ መሪያቸው ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የደነገጉላቸውን ሕግ መጻረር ምንም ስሜት የማይሰጣቸው ግድ የለሾች ናቸው። ታዲያ እንዲህ ያሉትን ሰዎች ቃል አክባሪነት፣ ታማኝነት፣ ሥነ ምግባር፣ የሃላፊነት ስሜትና ሕግ አክባሪነት እንዴት ተብሎ ከነሱ ይጠበቃል?!

# ዘካት:-

ከእስልምና ማዕዘናት ሶስተኛው ዘካት ነው። እያንዳንዱ ሙስሊም ገንዘቡ /ንብረቱ/ ከተወሰነ መጠን ከተረፈና አንድ ዓመት ዞሮ ከመጣበት ከዚህ ገንዘቡ ውስጥ የተወሰነ መጠን ለድሆች፣ ለሚስኪናች፣ ለመንገደኞች፣ አዲስ ለሰለሙ ሙስ ሊሞች በዕዳ ለተያዙ ሰዎች፣ በአላህ መንገድ ምጽዋት መክፈልን ሃያሉ አላህ ግዴታ አድርጐአል።

በዚህ ሁኔታም ሙስሊም ባለሀብቶች ከተለያዩ ንብረቶቻቸው ላይ መጠኑ 2.5% የሆነ የተወሰነ ክፍያ ለድሆች እንዲከፍሉ አላህ ወስኗል። ከዚህ የበለጠ ለመስጠት ፍቃደኛ የሆነ ባለሀብት ከፍተኛ ምንዳ አላህ ዘንድ አለበት።

ይህ የድሆች ለአላህ እሚጠቅም እሱ የሚፈልገው አይደለም። ሃያሉ አላህ ለደሃ ወንድሞቻችሁ አንድ ነገር ለኔ ብላችሁና ምንዳዩን በማሰብ በፍጹምነት፣ በሙሉ ፍቃደኝነት ከለገሳችሁት ልክ ለኔ እንደለገሣችሁ ነው። ነገር ግን ዝናን ለማትረፍ፣ ለጉራ፣ ድሃውን ለማንቋሸሽና በለገሳችሁት ነገር በመመጻደቅ መሆን የለበትም። ከደሃው ምላሽም ሆነ ምሥጋና አትጠብቁ፤ ሰዎች እንዲያያችሁና ስማችሁ ገንኖ ጣት እንዲቀሰርባችሁ በመፈለግ አትፈጽሙት። ለድሆች፣ ለሚስኪኖችና ለችግረኞች ከገንዘባችሁ ውስጥ የወሰን ኩላቸውን ድርሻቸውን እንዲህ ካሉት መጥሪያ አስተሳሰቦችና ዝቃጭ ስሜቶች ልባችሁን ንጹሕ በማድረግ ከለገሳችሁ ከታላቁ ጸጋዬ የማያልቅና የማይጠፋ ድርሻ እሰጣችኋለሁ ይላል፤ ሃያሉ አላህ ለባሮቹ።

ሃያሉ አላህ ይህን የዘካት ክፍያ፣ ሰላትና ጾምን ግዴታ እንዳደረገብን ሁሉ እሱንም ግዴታ አድርጐ ደንግጓአል። ከእስ

ልምና ምሶሶዎችም አንዱ አቢይ ምሰሶ ነው። ይኸውም ለአላህ ብሎ ራስን መስዋዕት የማድረግን፣ ከራስ በፊት ሌሎችን የማስቀ ደም ባህሪያትን ሙስሊሞች እንዲካኑ ስለሚያደርግ ነው። ራስወዳ ድነትን፣ ግዴለሽነትን፣ ልበ ጠባብነትን፣ ለገንዘብ ተገዥነትንና የመሳሰሉ ሌሎች ዝቃጭ ባህሪያትን ያስወግዳል። እስልምና ቆንቋ ናና ንፉግ የሆነ፣ ገንዘብን የሚያመልክና ገንዘብ ላይ የሚዋደቀውን ሰው አይፈልግም፤ ለምኑም አይጠቅመውምና። በእስልምና ተመ ርቶ ቀጥተኛውን መንገድ መከተልና በማያቋርጥ ሁኔታ መንገዱን ይዞ መጓዝ የሚችለው አንድ የአላህ ትእዛዝ ሲመጣበት ለፈጣሪው ትእዛዝ ተግባራዊነት ብሎ ጥሮ ግሮ በወዙ ያፈራውን ገንዘቡን ያላንዳች ግላዊ ጥቅሙ የሚሰዋ ሰው ብቻ ነው። ዘካትም ሙስሊ ሙን ለዚህ መስዋዕትነት ያደፋፍራል። ገንዘቡን የሙጥኝ ብሎ እንዳይቀረቀር ያዘጋጀዋል። ሁኔታው አስገድዶ ገንዘቡን ማው ጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ንፉግ ሣይሆን በፍጹም ደስተኛነት እንዲለግስ ብቁ ያደርገዋል።

ዘካት ከዓለማዊ ጥቅሞች መካከል የሙስሊሞች እርስ በርስ መተጋገዝና መረዳዳት፣ የታረዘ፣ የተራበና የተዋረደ በመካከ ላቸው እንዳይኖር፣ ሀብታሙ ደሃውን አስጠግቶ መደገፍና ድሃው ም እጁን ወደ ሀብታሙ ለልመና ከመዘርጋት እንዲቆጠብ ማድ ረጉ፤ ሀብታሞች ገንዘባቸውን ለመቀማጠልና ለመንቦጣረር እንዳ ያወጡና በገንዘባቸው ውስጥ ሕብረተሰባቸው ውስጥ ያሉት ድሆች፣ የሙት ልጆችና ሚስኪኖች የታወቀ ድርሻ ያላቸው መሆኑን እንዲያውቁ፤ መሥራት እየቻሉ መንገድ ያላገኙት፤ ብሩህ አእምሮና ብልህነት በተፈጥሮአቸው እያላቸው በድህነት ምክንያት መማር ያልቻሉ ሕፃናትና መሥራት ለማይችሉ ጡረ ተኞች ድርሻ ያላቸው መሆኑን የማያውቅና ይህን ግዴታ የማይ ቀበል ከበርቴ ሁሉ ግፈኛ ነው። የተትረፈረፈ ሀብትና ቁጥር ስፍር የሌለው ንብረት እያለን፣ በተንጣለሉ ቪላዎች እየኖርን፣ በውድ

አውቶሞቢሎች እየተንፈላሰሰን፣ ቁራሽ ዳቦ ማግኘት የተሣናቸው ብዙ ሺህ ድሆች፣ መሥራት የማይችሉና ሥራ ያጡ ብዙ ሺህ ሰዎች በአካባቢያችን እየተንከራተቱ ከማየት የከፋ ግፍ የለም። እስልምና እንዲህ ያለውን ሰው ይጠላል። እንዲህ ያለው የራስ ወዳድነት ስሜትንም ይዋጋል። እንዲህ ያለው የራስ ወዳድነት ባህሪ፣ በጃቸው የሚገባውን ሀብት ሁሉ የሚያካብቱና የሚያደልቡ በሌሎች ሰዎች እጅ የሚገኘውንም ለራሳቸወ የሚቀሙ የከሃዲዎች /ኩፋር/ ባህሪ ነው። ሙስሊሞች ግን አላህ ሲሣይ ከለገሣችሁና ከፍላጐታችሁ ከተረፈ አታካብቱት፤ ላጡ ወንድሞቻችሁ ስጡና ችግራቸውን ይወጡበት፤ እናንተ የምትኖሩበትን ሠርታችሁ ማግ ኘት እንደቻላችሁ ሁሉ እነሱም ኑሮአቸውን ማሸነፍ እንዲችሉ ስጧቸው ብሎ ነው ሃይማኖታቸው የሚያስተምራቸው።

## ሐጅ:-

ከእስልምና አበይት መሠረቶች አራተኛው ሐጅ ነው። ግዴታነቱም የወጪውን ጣጣ ችለው መካ ደርሶ የመመለስ አቅም ባላቸው ሙስሊሞች ላይ ብቻ ሲሆን ይህም በሕይወት ዘመን ውስጥ አንድ ብቻ ነው።

ነቢዩ ኢብራሂም /ዐ.ሰ/ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ዛሬ መካ ከተማ ባለችበት ቦታ አላህን ለመገዛት አንድ ትንሽ ቤተመቅደስ ሠሩ። ሃያሉ አላህ ይህን የነቢዩ ኢብራሂም ጥረት ተቀብሎ ፍጹምነታቸውንና ወዳጅነታቸውን በማስመልከት ቤተመቅደሱን ከራሱ ጋር አዛመደ። እኔን ለመገዛት የፈለገ ሰው ሁሉ ፊቱን ወደዚህ ቤት አቅጣጫ በማዞር ይገዛኝ። ወደ ቤቱ ለመጓዝ አቅም ያለው ሰውም ቢያንስ በሕይወት ዘመኑ ውስጥ አንድ ጊዜ ይጐ ብኘው። አገልጋዩና ወዳጂ የነበረው ኢብራሂም ቤቱን ይዞር

እንደነበረው ሁሉ ይዙሩ በማለት አላህ አዘዘ። የተከበረውን ቤት ለመጐብኘት አስባችሁ ከቤታችሁ ስትወጡ ልባችሁን አጥሩ፤ ስሜታዊ ፍላጐታችሁን እፍኑ፤ አመጽን፣ ጭቅጭቅን፣ ደም መፋሰስን፣ ብልግናን ራቁ። ጌታችሁ ፊት ለመቆም ስትቀርቡ ሥነ ሥርዓት፣ ትህትና ደካማነትና ተገዥነት የተላበሳችሁ ሁኑ። የሰማ ያትና የምድር ጌታ ወደሆነው ሃያል አምላክ የምታመሩ መሆና ችሁን አስታውሱ። በዚህ ዓይነት የደካማነት፣ የወትዋችነት፣ የፈሪሀነትና የፍጹምነት ሁኔታ እኛ ፊት ቀርባችሁ ያለባችሁን የመገዛት ግዴታ በልባዊ ስሜት፣ በንጹህ ልቦና ከፈጸማችሁ እኛ ታላቅ ምንዳ እንሰጣችኋለን፤ ይላል አላህ።

ሐጅን በሌላ መልኩ ስናየው ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የአላህ መገዛት ከሁሉም የበለጠ ትኩረት የሚስብ መሆኑን እንረዳለን። አንድ ሰው ሥራውን፣ ንግዱን፣ ልጆቹንና ወዳጆቹን ጥሎ ልቡ ውስጥ የአላህ ፍቅር ባይኖር ኖሮ የረዥም መንገድ ችግርና ጣጣ ለምን ይጋፈጣል? አንድ ሰው ከቤቱ ወጥቶ ወደ ተከበረው የአላህ ቤት የሚያደርገውን ጉዞ በሚጀምርበት ጊዜ ያለው ፍላጐት ራሱ በሌሎች ጉዞዎች ላይ ካለው ፍላጐት የተለየ ይሆናል። በዚህ ጉዞ ላይ አብዛኛው ትኩረት ወደ ሃያሉ አላህ የተመለሰ ሲሆን ለተከ በረው የአላህ ቤት ያለው የናፍቆትና የመጓጓት ስሜት ይጨምራል። መንገዱ ባጠረ፣ ለካዕባ መቅረቡ ሰባቱ እጥፍ ድርብ? ይሆናል። ከኀጢአትና ከጥፋት ይርቃል። ባለፉት ኃጢአ ቶቹ ይጸጸታል። በቀሪው ሕይወት ዘመኑ ግን ተገዥ መሆን እንዲያስችለው ይጸልያል፤ አላህን ይማጸነዋል። አላህን ሲያወ ድስና ሲገዛ ልዩ የሆነ የሕሊና ደስታ ማግኘት ይጀምራል። ተነሱን ቀና ማድረግ እንኳ በማያስጠላ ሁኔታ የተመሰጠ ሱጅዶችን ያደርጋል። ቁርአንም የሚያነበው ቀደም ሲል ከነበረው በበለጠ ተመስጠና ከፍተኛ በሆነ መንፈሳዊ እርካታ ነው። ሲጾም ቀደም ሲል ያገኝ ከነበረው የተለየ እርካታ ያገኛል። ወደ ሳውዲ ዐረቢያ

ገብቶ የሄጅዝን ምድር በእግሩ ሲረግጥም በመጀመሪያ ዘመኑ የእስልምናን ታሪክ በዓይን ሕሊናው ይመለከታል። በዚህ የተቀደሰ አገር የሚገኙት ታሪካዊ ሥፍራዎች በሙሉ በገንዘባቸውና በሕይወታቸው ጭምር በአላህ መንገድ የታገሉ፤ የወደዱትንና የወደዳቸውን የመጀመሪያዎቹን የእስላም ግንባር ቀደም ምዕመናን ገድል የሚያንፀባርቁ፤ ሁሉም የእስልምናን ታላቅነት የሚያመለክቱ መሆናቸውን ጉብኚው ያስተውላል። እያንዳንዱ የዚህ የገር የአሸዋ ጠጠር እስልምና ተጀምሮበት፣ ብርሃኑ የተሰራጨበትና ድል ያደረገበት ቅዱስ ምድር መሆኑን ትናገራለች። በዚህ ዓይነትም የአማኙ ልብ በአላህ ውዴታ፣ በሃይማኖቱ ፍቅር ይሞላል። ወደ ሃገሩ በሚመለስበት ጊዜም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ከሕሊናው የማይፋቅ የእስልምና ስሜት ይቀረጽበታል።

ከነዚህ ሃይማኖታዊ ጥቅሞች ባሻገር ሐጅ አያሌ ዓለማዊ ጥቅሞች አሉት። የተከበረችው የመካ ከተማ፣ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች፣ ከተለያዩ ዝርያዎችና ብሔሮች የተውጣጡ ሙስሊሞች የሚያስሙት የሙስሊሞች ማዕከል ነች። በዚህም ወንድማማች የሆነ ያንድ ሕዝብ ስብስብ የመሆን የአንድነት ስሜት ያድርባቸዋል። ሐጅ የሃያሉ አላህ አምልኮ /ዒባዳ/ ከመሆኑ ጐን በመላው ዓለም የሚገኙ አህጉሮችና አገሮች ሙስሊሞች የሚወከሉበት ታላቅ ዓመታዊ ስብስብ ሆኖ ዓለም አቀፋዊ የሆነ እስላማዊ ወንድማማችነት፤ በአንድነት፣ በፍቅርና በተራድኦ መርህ ላይ ለማጉልበትም ከፍተኛ መሣሪያና ውጤታማ መንገድ ነው።

## እስላምን መጠበቅ:-

አላህ በምዕመናን ላይ ከደነገጋቸው ግዴታዎች በመጨረሻ የምናየው እስልምናን የመጠበቅና የመከላከል ግዴታ ነው። ይህ

ግዴታ ከእስልምና መሠረቶች አንዱ ባይሆንም ከእስልምና ግዴታ ዎች አንዱና ከዋነኛዎቹ አንዱ ነው። ቁርአንና ሐዲስ ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ ተደጋግሞ ተወስቷል። ለመሆኑ እስልምናን መጠበቅ ማለት ምንድነው? አላህ በሙስሊሞች ላይ ግዴታ ያደረገው ለምንድነው? ከሚከተለው ምሣሌ መረዳት ይቻላል። አንድ ወዳጅና ጓደኛ ነኝ የሚለን ሰው አለ እንበል፥ ይህ ሰው ግን ችግርና ፈተና በገጠመን ቁጥር ተግባሩ ወዳጅነቱን አያሳይም፤ ለችግራችንና ለደረሰብን ሥቃይ ምንም ግድ አይኖረውም። ጥቅማ ችንም ሆነ ጉዳታችን ምንም አያሳስበውም። የግል ጥቅሙን እስካስገኘለት ድረስ እኛን ሊጎዳና ችግር ሊያስከትልብን የሚች ለውን ማንኛውንም ተግባር ከመፈጸም አይቆጠብም። የሚጠቅ መን ነገርም ቢሆን ራሱን ካልጠቀመው በስተቀር በፍጹም አያደ ርገውም፤ በችግር ወቅት የእርዳታ እጁን አይዘረጋልንም። ከሚነ ቅፉንና ከሚወቅሱን ጋር በመተባበር ያበረታታቸዋል። ቢያንስ ከዘለፋቸው እንዲታቀቡ ከማድረግ እንኳ ይቆጠባል።ጠላቶቻችን እኛ ላይ ሲያሴሩ ያግዛቸዋል። ወይም በሸረቡት ሴራ ላይ ከመው ደቅ እንድንድን እንኳ ጥረት አያደርግም። ታዲያ እንዲህ ያለ ሰው ወዳጃችን ነው፤ ጓደኛችን ነው ብለን ማሰብ እንችላለን ወይ? በፍጹም ሊሆን አይችልም። ወዳጅ ነኝ የሚለው በምላሱ ብቻ ነው። ከልቡ ግን አይወደንም። ወዳጅነት ማለት ተወዳጁን ሰው ከልብ መውደድ ማለት ነው። ፍጹም መሆን፣ መተሳሰብና መፈ ቃቀር ነው። ደስታንም፣ ችግርንም አብረው መካፈል፣ በጠላቶች ላይ መተጋገዝ፣ የወዳጅ ስም በመጥፎ መሰማትን አለመፍቀድ ነው። ይህን ሁሉ ያላጠቃለለ ወዳጅ ነኝ ባይ አስመሳይ፣ መናፍቅና ዋሾ ነው።

አንድ ሰው ሙስሊም ነኝ ካለ ማድረግ የሚፈለግበትን ከዚህ ምሣሌ ጋር ያመዛዝን። ሙስሊም ነኝ ማለት ለእስልምና ቀናኢ፣ ጠባቂና ተከላካዩ ነኝ ማለት ነው። የእምነቱ ታማኝና የሃይማኖቱ

አፍቃሪ ነኝ ማለት ነው። ለሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ ፍጹም ነኝ ማለት ነው። የእስልምና ጥቅምና የሙስሊሞች ደህንነት በዚህ ዓለም ላይ በማደጋቸው ነገሮች ሁሉ ውስጥ አቢይ ትኩረቴ ነው። ለእስልምና ጉጂ የሆነ፣ ሕግጋቱን የሚቃረን ተግባር ዓላማዬን ለማሳካት ወይም ግላዊ ችግሬን ለማስወገድ ብዬ አልፈጽምም ማለት ነው። እንደዚሁም ለእስልምናና ለሙስሊሞች በሚጠቅም ነገር ሁሉ በገንዘባችንና በነፍሳችን መሣተፍ፣ እስላምና ሙስሊሞችን ከሚጎዳ ነገር ሁሉ መራቅ፣ ልዕልናችንን ከእስልምናና ከሙስሊሞች ልዕልና ለይተን አለመመልከት፣ ራሣችንን መርዳት እንደማንታገስ ሁሉ ለእስልምናና ለሙስሊሞች መርዳት አለመታገስ፣ ጠላታችንን እንደማናግዘው ሁሉ ለእስልምናና ለሙስሊሞች ጠላት አለማገዝ፣ ራሣችንን ለመጠበቅ ሁሉንም ዓይነቶች መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንዲሆንን ሁሉ በገንዘባችንና በሕይወታችንም እስልምናን ለመጠበቅና የሙስሊሞችን ሕልውና ለማስጠበቅ መስዋዕት ለመሆን ዝግጁ መሆን ግዴታ ነው። እኔ ሙስሊም ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው ሁሉ በነዚህ ባህሪያት የተካነ መሆን ግዴታው ነው።አለዚያ ከመናፍቃን ጐራ ይሰለፋል፤ በምላሱ የሚናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ውሸት መሆናቸውን ተግባሩ ይመሰክርበታል።

# እስላምን ከመጠበቅ ዘርፎች አንዱ:-

በእስልምና ውስጥ «ጅሃድ» በመባል የሚታወቀው በአላህ መንገድ መታገል ነው። ጂሃድ የሚለው ቃል የቋንቋ ትርጉሙ ላንድ ዓላማ ጥረት ማድረግና ያለውን ኃይል በዚያ ነገር ላይ ማዋል ማለት ነው። በዚሁ መሠረትም የእስልምናን ቃል ከፍ ለማድረግ ባለው ገንዘብ፣ በሕይወቱ፣ በብዕሩና በምላሱ ባለው አቅም ጥረት ያደረገ ሰው፤ በአጠቃይ የጅሃድ ትርጉም ለአላህ መንገድ ታግሏል

ማለት ነው። ይህ ቃል በልዩ ትርጉሙ ሙስሊሞች በእስልምና ጠላቶች ላይ ከማንኛውም ዓለማዊ ጥቅም ነፃ በሆነ ሁኔታ የአላህን ወርታ ብቻ በማሰብ ያላንዳች ሌላ ምክንያት የሚያካሂዱትን ጦርነት ያመለክታል። በእስልምና ሕግ ይህ ጦርነት በሙስሊሞች ላይ የወል ግዴታ ነው። ይህም ማለት /የወል ግዴታ/ ግዴታነቱ ጠቅላላውን የሙስሊም ህብረተሰብ የሚመለከት ቢሆንም የተወሰነ ክፍል ከመካከላቸው ከተሰማራበትና ግዴታውን ከተወጣው ከተ ቀሩት ሙስሊሞች ላይ ግዴታነቱ ይነሣል። ጠላት በአንድ የእስ ላም አገር ላይ ጥቃት ካደረሰ ግን ይህ ጅሃድ በዚያ ሃገር ነዋሪዎች ላይ ልክ እንደ ሰላትና እንደ ጾም በነፍስ ወከፍ ግዴታ ይሆናል። የሃገሩ ነዋሪዎች ራሣቸውን መከላከል ካቃታቸው ተጉራባች አገር ያሉት ሙስሊሞች በገንዘባቸውና በሕይወታቸው የመርዳት ግዴታ አለባቸው። በነርሱ እርዳታ የጠላቶች ወረራ ካልተገታ በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች ሁሉ ልክ እንደ ሰላትና ጾም ግዴታ የመርዳትና የማገዝ ግዴታ ይኖርባቸዋል። ይህም ማለት በየት ኛውም አገር ያለ ሰው ሙስሊም ወንድሞቹን ከጠላት ጥቃት ከመከላከልና ከመርዳት ከተቆጠበ የአላህን ትእዛዝ የጣሰ ኃጢአት ይሆናል ማለት ነው። በነዚህ ሁኔታዎች ለአላህ መንገድ መታገል «ከሰላትና ከጾም ይበልጥ አሳሳቢና ይበልጥ አስፈላጊ ይሆናል። እምነት ከጅሃድ ይፈተናል። እስልምናን የሚገዛ ሆኖ በችግርና በመከራ ወቅት ከሙስሊሞች ጐን ተሰልፎ የማይታገል ሰው አማኝነቱ አጠራጣሪ ሙስሊምነቱም አጠያያቂ ነው። ሰላቱና ጾሙም ምን ፋይዳ ያስገኝለታል? እስልምናን የሚቀናቀንና ጠላ ትን በሙስሊሞች ላይ የሚያስደስት ሙስሊም ስለ መናፍቅነቱ ጥርጥር የሌለው መናጢ ነው። ሰላቱ፣ ጾሙ፣ ዘካውና ሐጅ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው።

# ምዕራፍ ስድስት

## ዲንና ሸሪዓ

ባለፉት ምዕራፎች ያብራራነው ሁሉ የዲን /እምነት/ አካል ሲሆን ቀጥለን ደግሞ ስለነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሸሪዓ አንዳንድ ነገሮችን እናብራራለን። ሸሪዓ ምን እንደሆነ ከማወቃችን በፊት ግን በዲንና በሸሪዓ መካከል ምን ልዩነት እንዳለ ማወቅ ይገባናል።

## የዲንና የሸሪዓ ልዩነት

ሃያሉ አላህ የላካቸው ነቢያት በሙሉ ሰዎችን ያስተማሩት እስልምና ብቻ መሆኑንና እሱም በአላህና በባህሪያት፣ በትንሣኤው ቀን፣ ነቢያቱ በሰጡት መመሪያ መሠረት ማመን፣ በአላህ መጻሕፍት ማመን፣ እውነተኛ መሆናቸውንና በመጻሕፍቱ ውስጥ የተገለጸውን ቀጥተኛ መንገድ ብቻ መከተል፣ እውነተኛ የሆኑ የአላህ ነቢያትን መከተልና ሌላውን አለመከተል፣ አላህን ብቻ መገዛትና በርሱ ምንም አለማሻረክ መሆኑን አብራርተናል።

ከዚህ ዲን /እምነት/ በኋላ ደግሞ ሸሪዓ ይመጣል። ሸሪዓም የእምነቱ ተግባራዊ አፈጻጸም መንገዶችና የኑሮና የማህበራዊ ሕይወት መርህ፣ የሰዎች ማህበራዊ ግንኙነት ሕግጋት፣ የሀላል /የተፈቀዱ/ ነገሮችና የሀራም /የተከለከሉ/ ነገሮች ድንጋጌዎች ነው። ሃያሉ አላህ በመጀመሪያ ላይ እንደየ ሕዝቡ ሁኔታና እንደየ ታሪካዊ ዘመኑ ሁኔታ ለተለያዩ ሕዝቦች የተለያዩ ሸሪዓዎች /ድንጋጌዎች/ በነቢያት አማካይነት ሰጣቸው። እያንዳንዱ ሕዝብም በየፊናው የራሱ የሆነ ሥነ ምግባር፣ ባህልና ስልጣኔ ይዞ በመ

ራመድ ጌታቸው ወደፊት የሚሰጣቸውን አጠቃላይ ሕግ ለመከ ተል እንዲዘጋጁ አደረገ። ይህ ቅድመ ዝግጅት በቀደሙት የተለ ያዩ ነቢያት እጅ ሲጠናቀቅም የነቢያቱ መደምደሚያና መሪ የሆኑት ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እስከ ዓለማት ፍጻሜ ድረስ ለመላው ዓለም ተስማሚ የሆነ ይዘት ያለውን ያን አጠቃላይ ዩኒቨርሳል ሕግ ይዘው መጡ። የዛሬም እምነት ጥንት የቀደሙት ነቢያት ያስተማሩትና መመሪያ የሰጡበት የድሮው እምነት /ዲን/ ነው። ሸሪዓ /ድንጋጌዎች/ ግን ተሸረዋል። በቦታው የአምልኮት /የዒባዳ/ ሥነ ሥርዓቱ፣ የኑሮ መርሁ፣ የማህበራዊ ኑሮና የማህ በራዊ ኑሮ ግንኙነት ሕጋጋት፣ የሃላልና የሃራም ድንጋጌዎች አፈጻጸም የማይለያይበት ዩኒቨርሳል የሆነ የተሟላ ሸሪዓ እስከ ትንሣኤው ቀን ለመላው የሰው ዘር የሚያገለግል ሆኖ ተተክቷል።

## የሸሪዓ ሕጐች ምንጭ:-

የነቢዩ ሙሐመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ሸሪዓ ሕጐች ለማወቅ ሁለት ምንጮች አሉን። እነሱም ቁርአንና የነቢዩ ሐዲስ /ሱና/ ናቸው። እንደም ናውቀው ሁሉ ቁርአን የአላህ ቃል ነው። እያንዳንዱ ቃል ከርሱ ዘንድ የተላለፈ ነው። ሱና ደግሞ ከነቢዩ ሙሐመድ የተላለፈ የቃል ወይም የተግባር መመሪያ ነው። የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሕይወት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው የቁርአን ማብራሪያ ነበር። ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ በነቢይነት ወደ ሰው ልጆች ከተላኩበትና የአላህ ራእይ ከመጣላቸው ጊዜ ጀምረው ሰዎችን በማስተማርና አላህ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መንገድ ሕይወታቸውን ይመሩ ዘንድ ለ23 ዓመታት ሙስሊሞችን በመምራትና በማስተማር ላይ ቆይተዋል። በዚህ በማይናቅ ጊዜ ውስጥ ወንድና ሴት ባልደ ረቦቻቸው፣ የቅርብ ዘመዶቻቸውና ንጹሃን ሚስቶቻቸው እጅግ ከፍተኛ በሆነ ጥንቃቄና ተመስጦ ንግግራቸውን ያዳመጡ፣

ተግባራቸውን ይከተሉ ነበር። በተለያዩ ጉዳዮችና ማህበራዊ ኑሮ ግንኙነቶች ውስጥ የሚገጥሟቸውን የተለያዩ ነገሮችንም ለነቢዩ በማቅረብ ይጠይቋቸው ነበር። ነቢዩም አንዴ አንድ ነገር ሲያዟቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ነገር ይከለክሏቸው ስለነበር በቦታው የነበሩት ሁሉ የነቢዩን ትእዛዞች፣ እገዳዎችና ድንጋጌዎች ተገንዝበው በቦታው ላልነበሩት ያደርሱ ነበር። ነቢዩ አንድ የተለየ ነገር፣ የተለየ ሥራ ሲፈጽሙ በቦታው የተገኙት ለራሳቸው ይረዱትና ላልነበሩት ያስተላልፉ ነበር። ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ባሉበት አንድ ባልደረባቸው አንድ ነገር ካደረገ ነቢዩ ወይም ዝም ይላሉ ወይ ደግሞ ይከለክላሉ። በቦታው የነበሩት ሰዎችም እንደዚሁ ያሉ ተግባራዊ ሁኔታዎችን ያጠኑና ያስተላልፉ ነበር። ከነቢዩና /ሰ.ዐ.ወ/ ከባልደረቦቻቸው /ረ.ዐ/ ትውልድ በኋላ የመጡት ተከታታይ ትውልዶችም ከነቢዩ የተወረሱትን ነገሮች ሁሉ ቃል በቃል ተወራረሱ። ከዚያም እነዚህን የነቢዩን ቃሎች /ሃዲሶች/ ሙሉ በሙሉ በመጻሕፍት መዝግበው ያዙ። ይህም እጅግ በጣም ጥራትና ትክክለኛነት ባለው ሁኔታ ከነቢዩ ያስተላለፉትን ሲናገሩ የሰሙትን የነቢዩን ባልደረቦች የስም ሰንሰለት ሳይቀር ሁሉንም በመጽሐፍ አሰፈሩ። በዚህ መልካም የነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በዙር የሐዲስ ስብስቦች በሰዎች እጅ ሊሻሩ ቻሉ።

ከነዚህ መጻሕፍት መካከል ይበልጥ ዕውቅ የሆኑትና ከሁሉም የበለጠ ክብደት የሚሰጣቸው ኢማሙል ቡኻሪ፣ ኢማም ሙስሊም፣ ኢማም ማሊክ፣ ኢማም ተርሙዙ፣ ኢማም አቡዳውድ፣ ኢማም ኢብን ማጀህና ኢማሙ ነሳኢ የዘገቡዋቸው የሃዲስ መጻሕፍት ናቸው።

# ፊቅህ :-

ፊቅህ በሰው ዕለታዊ ኑሮ ውስጥ የሚያጋጥሙ ጉዳዮችን አስመልክቶ ከቁርአንና ከሐዲስ ሕግጋት ተወስዶ በታላላቅ የእስ ላም የሃይማኖት ሊቆች ቀደም ሲል የተቀናበረ ዝርዝር ሕግ ነው። የሊቃውንቱ ዓላማም ተራው ሙስሊም የሃይማኖቱን ሕግጋት በቀላሉ ተረድቶ እንዲጠቀምበት ነበር። የቁርአንና የሃዲስ ዕውቀት ካልኖረውና አስፈላጊ ነጥቦችን ካላሟላ በስተቀር እያንዳንዱ ሙስሊም ከቁርአንና ከሐዲስ ሕግ ማመንጨት አይችልም። እነኚህ ታላላቅ ሊቃውንት ብዙ ተቸግረው ፊቅህ መጻሕፍትን አሁን ባለው መልካቸው ከረዥም ዘመን እርማትና ከአድካሚ ጥረት በኋላ ስላቀረቡላቸው የእያንዳንዱ ሙስሊም ባለውለታ ናቸው። ዛሬ ተራው ሙስሊሞች የእስልምናን ሸሪአ በቀላሉ መከተልና ሕጐቹንም ማወቅ የቻሉት በነኚህ ታላላቅ ኢማሞች ጥረት ውጤት መሆኑ ጥርጥር የለውም።

የፊቅህ መጻሕፍት በዚህ መልክ መቀናበር ሲጀምሩ ስልቱን ተከትለው ያቀናበሩት ብዙ ሰዎች ነበሩ። በመጨረሻ ላይ ሕልው ናቸውን ጠብቀው የቆዩና ለዛሬ የደረሱት ግን አራት የፊቅህ ፈለጐች / የፊቅህ መዝሐብ/ ናቸው። እነዚህ አራት ፈለጐችም ዛሬ ከዓለም ሙስሊሞች አብዛኞቹ የሚከተሏቸው ሲሆኑ እነሱም:-

1. የሀነፊ ፊቅህ :-

ኢማም አቡ ሀኒፋ እንደ አቡ ዩሱፍ ሙሀመድ ፣ዙፍርና የተቀሩት ሌሎች ታላላቅ ሊቃውንት በመሳሰሉ ባልደረቦቻቸው በመታገዝና በመመካከር ያቀናበሩት ፈለግ ነው።

2. የማሊኪ ፊቅህ :-

ኢማም ማሊክ አቡ አነስ ያቀናበሩት የፊቅህ ፈለግ ነው።

3. የሻፊዒ ፊቅህ :-

ኢማም ሙሃመድ ኢብን ኢድሪስ አሻፊኢ ያቀረቡት የፊቅህ ፈለግ ነው።

4. የሀንበሊ ፊቅህ :-

ኢማም አህመድ ኢብን ሀንበል ያቀረቡት የፊቅህ ፈለግ ነው

የነዚህ አራት የፊቅህ ፈለጎች / የመዝገቦች/ ቅንብር የተጠናቀቀው ከነቢዩ ሙሐመድ / ሰ.ዐ.ወ/ በኋላ በሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ነበር። በፈለጎቹ መካከል ያሉት ልዩነቶች ተፈጥሮአዊ የሆነ ምንነቱን በመረዳት የተለያዩ ሰዎች ጥረት ካደረጉ በመጠኑም ቢሆን እንኳ በዚያ ነገር ላይ ያላቸውን አመለካከትና የደረሱበት ማጠቃለያ የተለያየ እንደማይሆን አይጠረጠርም። ሊቃውንቱ ሁሉም ንጹሐን፣ ጻድቃንና አላህን ፈሪዎች በመሆናቸው፤ ሐቅን ብቻ የሚከተሉ፣ እውነትን የማይለውጡ ስለሆኑ የአራቱም ፈለጎች እውነት መሆናቸውን፤ ትክክለኛ መንገድ ላይ መሆናቸውን ሙስሊሞች በሞላ ያምናሉ።

ከነዚህ አራት ፈለጎች መካከል አንድ ሰው ባንዱ ጉዳይ ላይ መከተል የሚገባው አንዱን ብቻ መሆኑ በጣም ግልጽ ነው። ብዙኃኑ የእስላም ሊቃውንትም ሙስሊሞች ከነዚህ አራት ፈለጎች /መዝሐቦች/ ውስጥ አንዱን መከተል አለባቸው ይላሉ። አንድ የተለየ የፊቅህ መዝሐብ መከተል አስፈላጊ አይደለም፤ ዕውቀቱ የሚፈቅድለት ሰው በቀጥታ ከቁርአንና ከሃዲስ ሕግጋቱን ማመንጨትና መከተል አለበት። ሕጎችን ከቁርአንና ከሱና

ለራሣቸው ማመንጨት የማይችሉት ደግሞ የሚተማመኑበትንና የሚረኩበትን አንዱን የሙስሊሞች ሊቅ መከተል አለባቸው የሚል የሊቃውንት ክፍል አለ። ይህ ክፍልም «አህሉል ሐዲስ » /የሓዲስ ሰዎች/ በመባል ሲታወቅ ይህም ክፍል ልክ እንደተቀሩት አራቱ ፈለጐች ሁሉ ትክክለኛ ፈለግ ነው።

## ተሰውፍ ሱይዝም

ፊቅህ የሚመለከተው በዓይን የሚታየውን ይፋ የሰው ድርጊት ሲሆን የታዘዘው ነገር በተፈለገው ሁኔታ ተፈጽሟል አልተፈ ጸመም? በሚለው ላይ ብቻ ያተኩራል። ስለ ልብ ሁኔታ ስለሕሊ ናዊና ሥነልቦናዊ ሁኔታዎች ፊቅህ ግድ የለውም ። ስለልቡ ሁኔታ እንዲሁምከሱ ጋር ስለተያያዙ ገጠመኞችና ስለሕሊናዊ ጉዳዮች የሚያጠናው ተስውፍ / ሱፊዝም / ነው። ለምሣሌ ያህል ውዱእ በትክክል ፈጽመናል ወይ? ወደ ቂብላ አቅጣጫ አዙረን ሰግደናል ወይ? የሰላትን አበይት ክፍሎች / አርካን / አሟልተናል ወይ? በሰላታችን ውስጥ ማንበብ የሚገቡንን ሁሉ አንብበናል ወይ? በሚሉት ብቻ ነው ፊቅህ የሚያተኩረው። እነዚህን ሁሉ ከፈጸምን በፊቅህ አንጻር ሰላታችን ትክክለኛ ነው። ተስውፍን የሚመ ለከተው ግን ይህን ሰላት ስንፈጽም ልባችን የሚሆንበት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ነው፤ ከልባችን ወደ ጌታችን ተመልሰናል ወይ? በሰላቱ ወቅት ልባችን ከዓለማዊ ጉዳዮችና ሃሣቦች ተላቆ ነበር ወይ? ይህ ሰላት በልባችን ውስጥ አላህ በውስጠ ዐዋቂ ተመልካች መሆኑን አውቀን በእርግጠኛነት አላህን የመፍራትና ለርሱ ፍጹም የመሆንን ስሜት አንጿል ወይ?

ይህ ሰላት መንፈሳችንን ምን ያህል አጥርቷል? ምን ያህልስ ጸባያችንን አሻሽሎአል? እስከምን ድረስ እውነተኛና በእምነቱ መሠረት ግዴታዎችን የሚፈጽም ሐቀኛ አማኝ አድርጐናል?

እነዚህን ነገሮች በአሟላን መጠን፣ /እውነተኞች የሰላት ግቦችና ዓላማዎች እነዚሁ ናቸውና ነው/ በተሰውፍ አመለካከት ሰላታችን የተሟላ ይሆናል። በዚህ አኳያ ጉድለት ካለ ሰላታችን በተሰውፍ ዓይን ጐደሎ ነው። በተቀሩት የሸሪዓ ድንጋጌዎች ውስጥም ፊቅህ የሚያተኩረው አንድ ሰው የሚፈለግበትን ግዴታ በተጠየቀው መሠረት ፈጽሟል አልፈጸመም በሚለው ላይ ብቻ ሲሆን፣ ተሰውፍ ግን በግለሰቡ ፍጹምነትና ንጹሕ ልቦና ግዴታውን ሲፈጽም በሚኖረው ሐቀኛ የአማኝነት መንፈስ ላይ ያተኩራል።

የፊቅህና በተሰውፍ መካከል ያለውን ልዩነት ቀጥሎ ከተመ ለከተው ምሣሌ መረዳት ይቻላል ። አንድ ሰው ስናይ በሁለት መንገዶች እንመለከተዋለን። አንደኛው ጤነኛ አካሉ የተሟላ ነው ወይስ የአካል ጉድለት አለበት? መልከ መልካም ነው ወይስ አስቀያሚ? ጥሩ ለብሶ ወይስ ቡቱቱ? የሚለው ነው። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሥነ ምግባሩን፣ ልማዱን፣ ባህሪውን፣ የዕውቀትና የአእምሮ ምጥቀት ደረጃውን፣ አላህን ፈሪ መሆኑን ማወቅ የምንፈ ልግበት መንገድ ነው። የመጀመሪያው የአመላካከት አቅጣጫ የፊቅህ አመለካከት አቅጣጫ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተሰውፍ የአመለካከት ዘይቤ ነው። አንድን ሰው ወዳጅ ለማድረግ ስንፈ ልግም እንደዚሁ ከሁለቱ የአመለካከት አቅጣጫ እናየዋለን። በቅርጹም ሆነ በይዘቱ ጥሩ እንዲሆን እንፈልጋለን። በእስልምና አመለካከትም እንደዚሁ የሚፈለገው በይዘቱም ሆነ በቅርጹ በሁ ለቱም በኩል የሸሪዓን ሕጐች ትክክለኛና የተሟላ በሆነ ሁኔታ መከተልን ነው። ዒባዳው በቅርጹ ትክክለኛ ሆኖ በይዘቱ ግን እውነተኛ የመገዛት / ዒባዳ/ መንፈስ የሚጐድለው ሰው ሕይወት እንደሌለው መልከ መልካም በድን አይነት ነው። በሥራዎቹ የተሟላ፣ ውስጣዊ ይዘቶችን ያጠቃለለና ላዕላይ ቅርጹ ግን በተፈለገው መልክ ትክክለኛ ያልሆነ ሰው፣ በባህሪው ጥሩ ሰው ሆኖ በተፈለገው መልክ ትክክለኛ ያልሆነ ሰው፣ በባህሪው ጥሩ

ሰው ሆኖ መልከ ጥሩ እውርና አንካሣ የሆነ ሰው ምሣሌ ነው። በዚህ ቀላል ምሣሌ በፊቅህና በተሰውፍ መካከል ያለውን ልዩነትና ግንኙነት መረዳት ችለናል ። በጣም የሚያሳዝነውና የሚያብሰ ለስለው ግን በመጨረሻዎቹ ዘመናት ዕውቀት ሥነ ምግባር የመወገ ድና የማሽቆልቆል አደጋ ሲደርስባቸው፣ በዚህ ምክንያትም ጥፋትና ክፉ ነገሮች ሲከሰቱ የጠራው የተሰውፍ ምንጭ ደፍርሶ ሙስሊሞች ከጠመሙ ሕዝቦች አያሌ እስላማዊ ያልሆኑ ፍልስ ፍናዎችን ተማሩና በተሰውፍ ስም ወደ እስልምና አስገቡዋቸው። በቁርአንና በሐዲስ መሠረት የሌላቸውን ባዕድ ለሆኑ አያሌ እምነቶችና ፈለጎች የተሰውፍ ስም ሰጡ። እነኚህ ሰዎችም ራሣቸውን ከእስልምና ድንጋጌዎች ነፃ ማድረግ ቀጠሉ። ተሰውፍ ከሸሪዓ ጋር ግንኙነት የለውም፤ ተሰውፍ ሌላ፣ ሸሪአ ሌላ ነውና ስለዚህም ሱፊ የሆነ ሰውም ራሱን በሸሪዓ ሕጐችና ደንቦች ሰንሰለት ማወር የለበትም የሚል አቋም ነዙ። መሰል ተራ ግምቶ ችና አሉባልታዎች አላዋቂ ከሆኑ በርካታ ሰፊዎች ብዙ ጊዜ ይሰማል። ሁሉም ግን መሠረት የሌላቸው አፈ.ተረቶችና ቅጥፈቶች ናቸው። አንድ ሱፊ ነኝ የሚል ሰው ከሰላት፣ከጾም፣ ከሐጅና ከዘካት ግዴታዎች ራሱን ነፃ ማድረግ በፍጹም አይፈቀድለትም ። ሱፊ ነኝ የሚል ግለሰብ አላህና ነቢዩ / ሰ.ዐ.ወ/ ስለ ኢኮኖሚ፣ ስለማህበራዊ ኑሮ፣ ስለአኗኗር፣ ስለ ሥነ ምግባር፣ ስለ ማህበራዊ ግንኙነት፣ ስለ መብትና ግዴታ፣ ስለሃላልና ሀራም ካብራሯቸው ሕጐች አንዱንም መቃረን በፍጹም አይገባውም። ነቢዩ ሙሐመድን /ሰ.ዐ.ወ/ በትክክል የማይከተል፣ በሰጡት እውነተኛ መንገድ የማይመራ ሰው እስላማዊ ሱፊ ነኝ ብሎ ራሱን መሰየም አይችልም። እንዲህ ያለ ተሰውፍ ከእስልምና ጋር ምንም ተዛምዶ የለውም። ተሰውፍ በመሠረቱ የአላህና የነቢዩ የእውነተኛ ነቢዩ ፍቅር መግለጫ፣ ፍጹም በሆነ ተመስጦ በነሱ መንገድ ፍጹም መሰዋት ነው። ይህ ጥልቅ ፍቅር ተመስጦና መስዋትነት ደግሞ

ቅንጣት ታህል የአላህንና የነቢዩን /ሰ.ዐ.ወ/ ሕግጋት ከመከተል ዝንፍ አለማለትን ግዴታ ያደርጋል ። የጠራውና ንጹሕ የሆነው እስላማዊ ተሰውፍ ከሸሪዓ የተለየ ነፃ ነገር ሣይሆን ፍጹም በሆነ የጠራ ፍላጐትና የልቦና ንጽሕና የሸሪዓን ሕጐች ተግባራዊ ማድረግ ነው።

# ምዕራፍ ሰባት

## የሸሪዓ ሕጐች

በዚህ የማጠቃለያ ምዕራፍ እስላማዊ ሸሪዓ የሰውን ሕይወት ጥብቅ በሆኑ ማስተካከያ እንዴት እንደሚገዛ ይህም ማስተካከያ / መቆጣጠሪያ/ ያቀፋቸውን ምስጢሮችና ጥቅሞች ማወቅ የሚያ ስችል የሸሪዓ መርሆችንና አበይት ሕጐቹን እናብራራለን።

## የሸሪዓ መርህ:-

የገዛ ራሣችንን አፈጣጠር ስናስተውል ወደዚህች ዓለም የመጣነው እያንዳንዳችን እንድንጠቀምባቸውና ችላ እንዳንላቸው የሚያስገድዱን ብዙ ኃይሎች በራሣችን ውስጥ አዝለን መያዛችንን እንገነዘባለን። አእምሮ፣ ቁርጠኝነት፣ ፍላጐት፣ መስማት፣ ማየ ትና መቅመስ ፣ የመዳሰስ የእጅና የእግር ኃይል፣ የንዴት፣ የቁጣ የናፍቆት፣ የፍቅር፣ የፍርሃት፣ የመጓጓት ስሜቶች አሉን፣ ሁሉም ፋይዳ አላቸው። የተሰጡንም አስፈላጊያችን ስለሆኑ ነው። በዚች ምድረ ዓለም ስኬት ማግኘት ለተፈጥሮአችንና ለገዛ ባህሪያችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች እውን በማድረግ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ይህን ለማድረግ ደግሞ በገዛ ራሣችን ውስጥ የተሸከምናቸውን ተሰጥኦዎች /ብቃቶች/ መጠቀም አለብን።

እነዚህን የታለገሱ ተሰጥኦዎችን መጠቀም የሚያስችለን ዘዴዎችም ተሰጥቶናል። ከነዚህ ዘዴዎች /መሣሪያዎች/ የመጀ መሪያው መሠረታዊ የሆኑ መሣሪያዎች ሁሉ ያሉበት አካላችን ሲሆን ከዚያም የተለያዩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መሣሪያዎች

የተሰራጩበት ይህ የከበበን ምድረ ዓለም ይገኛል። በዚህ ምድረ ዓለም ላይ መሰላችን የሆነ ሰብዓዊ ፍጡር እኛን ለማገዝ፣ ለግልጋሎታችን ደግሞ አራዊትን፣ ዕፅዋት፣ ግዑዝ አካላት፣ መሬት፣ ውሃ፣ አየር፣ ሙቀት፣ ብርሃን፣ የመሳሰሉና ቁጥራቸውን ከአላህ በስተቀር ማንም የማያውቅ አያሌ ነገሮች ይገኛሉ። ሃያሉ አላህ እነዚህን ነገሮች በዩኒቨርሱ ውስጥ የፈጠራቸው እንድንጠቀም ባቸው ነው። ጉዳዩን በሌላ መልኩ እንመልከትና:-

እነዚህን ተሰጥኦዎች የተለገሰ ነው ለጥሙ እንጂ ለጉዳት አለመሆኑን ይረዳል። በነዚህ ተወህቦ የመገልገሉ ትክክለኛ መንገድ ደግሞ የጠቀሜታ መልኩ እንጂ የጐጂነት መልኩ አይደለም። ጉዳት ካለበትም የግዴታ መቅረት በማይችለው መጠን ብቻ መሆን አለበት። ከዚህ ውጭ ያለው ማንኛውም የአጠቃቀም መልክ ትክክለኛ አይደለም ይላል አእምሮ። ለምሣሌ ያህል ራሣችንን የሚጐዳ ተግባር ከፈጸምን ጥፋተኛነን ማለት ነው። እንደዚሁም አንዱን ተወህቦአችንን ሌላውን ሰው በሚጐዳ መንገድ ከተጠቀምንም ከጥፋተኛ እንቆጠራለን ። አንዱን ተሰጥኦአችን /ብቃታችንን/ የተሰጡንን መሣሪያዎች /ማከናወኛዎች/ ችላ እንድንል በሚያደርገን መንገድ ከተጠቀምንበትም አንደዚሁ አጥፊ ስህተተኞች እንሆናለን። ጐጂ የሆነን ነገር የፈለገው ዓይነት ቢሆን መራቅ አንዳለብንና መራቅ የማይቻል ቢሆን ወይም ብዙ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆን እንኳ እንድንታገሰው የገዛ አእምሮአችን ይመሰክርልናል።

ይህን ግንዛቤ በአእምሮአችን ይዘን የሰውን ማህበረሰብ ስንመለከት ሁለት ዓይነት ሰዎች መኖራቸውን እንረዳለን። አንዱ ዓይት ከፊል ተሰጥኦአቸውን ሆን ብለው ሌሎች ተሰጥኦዋቸውን በሚያበላሽባቸው መንገድ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት በሚያስከትል ሁኔታ ይገለገሉበታል። ወይ ደግሞ የተቸሩዋቸውን

መገልገያዎች መጠቀም ችላ ይላሉ። ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ የተባለውን ሁሉ ከገዛ ራሳቸው ፍላጐት ውጭ የሚፈጽሙትን ሰዎች ያጠቃልላል። በመጀመሪያው ዓይነት ውስጥ የሚመደቡት ከፉ ሰዎች ሲሆኑ እጃቸውን እንዲሰበስቡና እንዲታቀቡ የሚያ ደርግ ጠንካራ ሕግ ያስፈልጋቸዋል። በሁለተኛው ዓይነት ሥር የሚካተቱት ደግሞ ምንም የማያውቁ ማይሞች ሲሆኑ የተሰጥኦ መገልገያቸውንና ተሰጥኦዋቸውን በትክክለኛ መልኩ መጠቀምን የሚያሳውቃቸው ዕውቀት ያስፈልጋቸዋል።

እስላማዊው ሸሪዓም ይህንኑ ፍላጐት ለማሟላትና ይህንኑ ዓላማ እውን ለማድረግ የመጣ ስለሆነ ከተሰጥኦ መገልገያችን እንዱ ችላ እንዲባል፣ ከፍላጐታችንም አንዱ እንኳ እንዲታፈን ፣ ውስጣዊ ስሜታችን እንዲወገድ አይፈልግም። ዓለምን ተውና ሕይወታችሁን በተራሮች፣ በጫካዎች፣ በዋሻዎች ዘንድ ግፉ፤ ስሜታችሁን አፍናችሁ በማሰቃየት በችግርና በመከራ አስበ ርክኩ፤ የዓለማዊ ሕይወትን ደስታ ጣዕምና ጸጋውን በራሣችሁ ላይ እርም አድርጉ አይለንም። በፍጹም አይለንም። ይህን ዓለም ለሰው ልጅ መገልገያነት የፈጠረው ጌታ የደነገገው ሸሪዓ ነውና ፍጥረት ዓለሙ እንዲወድም፣ እንዲወገድና እንዲጠፋ እንዴት ይፈቅዳል? ሃያሉ አላህ የማይጠቅመውንና የማያስፈልገውን ተሰ ጥኦ በሰው ልጅ ውስጥ አላኖረም። በሰማያትና በምድር ካሉት ነገሮች አንዱንም በከንቱ አልፈጠረም። ይህ የዩኒቨርስ ቤተሙከራ በተቀናበረ ሥርዓት ሂደቱን እንዲቀጥል፣ በዩኒቨርስ ውስጥ ባሉት ነገሮች ሁሉ የሰው ልጅ እንዲገለገል፣ የተለያዩ አካባቢዎቹንና መገልገያዎቹን ራሱንም ሆነ ሌላውን ሰው በማይጐዳ መንገድ እንዲጠቀም ነው የፈጠረው። ሃያሉ አላህ የሸሪዓ መርሆችንና መቆጣጠሪያዎቹን ያኖረውም ለዚሁ ዓላማ ነው። ከዚህ በመነ ሳትም ይህ ሸሪዓ ጉዳት የሚያመጡበትን ነገሮች ሁሉ በሰው ልጅ ላይ እርም ሲያደርግ ጥቅም የሚያስገኝ ለትንና ሌላውን ሰው

የማይጐዳውን ማንኛውንም ነገር ደግሞ የተፈቀደ /ሃላል/ አድርጐለታል። እስላማዊው ሸሪዓ የሚታነጽበት መርህ፣ የሰው ልጅ የራሱን ፍላጐቶች እውን ለማድረግና ለማርካት፣ ግላዊ ጥቅሙን ለመፈለግ እንዳሻው መጣርና መልፋት መብቱ ነው። ነገር ግን የሌሎችን መብት ባለማወቅ ወይም በከፋት በማይነካ ሁኔታ ብቻ ካልሆነ በስተቀር በዚሁ መብት ያለመጠቀም ግዴታ አለበት። ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው አቅም ሁሉ መረዳዳትና መተጋገዝ ይገባዋል የሚል ነው። ከፊላቸው ጐጂ ከፊላቸው ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች በሚመለከት ረገድ የሰው ልጅ ለከፍተኛው ጥቅም ሲል አነስተኛውን ጉዳት መቻልና ከከባድ ጉዳት ለመጠበቅ ሲል ደግሞ ኢምንት ጥቅምን መተው አለበት ይላል ሸሪዓው።

ሰው ሁሉ በያንዳንዱ ነገር ወይም ሥራ ውስጥ ስላለው ጥቅም ወይም ጉዳት ሁልጊዜ ማወቅ አይችልም። ስለሆነም የፍጥረታት ምስጢር የማይሰዎረው ፍጹም ውስጥ ዐዋቂ የሆነው ሃያሉ አላህ ለሰው ልጅ የሕይወት መመሪያ የተሟላ ትክክለኛ ሥርዓት አኑሮ አል። በጥንት ዘመናት ሰዎች የዚህን ሥርዐት አያሌ ጥቅሞች የሚረዱ አልነበሩም። ባሁኑ ዘመን ግን ዕውቀት መጥቆ የምስ ጢሩን መጋረጃ ገልጧል። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ሰዎች ብዙ ጥቅሞቹን አያውቁም። ሆኖም ዕውቀት በመጠቀና በደረጀ መጠን ምስጢሮቹ ለሰው ልጅ እየተጋለጡ በመሄድ ላይ ናቸው።

ጉድለት ባለው ዕውቀታቸውና በደካማ አእምሮአቸው ላይ በመተማመን ብቻ ለዘመናት በሃሣብ ሲዋልሉ፣ በማይምነት፣ በስህተትና በጥመት ጨለማ ውስጥ የዕውር መደናበር ሲደናበሩ የነበሩ ሰዎች በመጨረሻ የዚህን ሸሪዓ መርህ ለራሣቸው ማወቅ ግዴታ ሆኖ አግኝተውታል። በአላህ ነቢይ /ሰ.ዐ.ወ/ ላይ በመተ ማመን መመሪያቸውን ተቀብለው በብርሃናቸው የተመሩት ግን ከጅልነት መጥፎ ውጤቶችና ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች

ተጠብቀዋል። እነዚህ ዘወትር የሚመረኮዙት ሸሪአ ያቀፈውን ጥቅምና በርሱ መመራት የሚያስገኘውን ጠቀሜታ አወቁም አላ ወቁ በጥሩና በትክክለኛ የዕውቀት መርህ ላይ በታነጸ ሕግ ላይ ነው።

## ግዴታዎችና አራቱ መደባቸው :-

በእስላማዊው ሸሪዓ ድንጋጌ መሠረት በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ላይ በአራት መደብ የተከፈሉ ግዴታዎች አሉበት። እነሱም:-

1. የአላህ መብቶች

2. የራስ መብቶች

3. የሌሎች ሰዎች መብቶች

4. በዚህ ዓለም ላይ የምንገለገልባቸውና የምንጠቀምባቸው ነገሮች መብቶች ናቸው። እነዚህን አራት የመብት ክፍሎች አውቆ በፍጹምነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት መወጣት የያንዳንዱ እው ነተኛ ሙስሊም ግዴታ ነው። እስላማዊው ሸሪዓ እነዚህን ግዴ ታዎች እያንዳንዳቸውን በተናጠል አብራርቷል። ግዴታዎቹን እያንዳንዳቸውን በተናጠል አብራርቷል። ግዴታዎቹን ለመፈጸም ይቻል ዘንድ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ለመወጣት ሰውን የሚያግዝና በተቻለው መጠን አንዱም ሣይቀር የሚፈጸምበትን መንገድና ስልት ቀይሶ አጉሮአል።

# ለአላህ መፈጸም ያለብን ግዴታዎች:-

ለአላህ ያለብን የመጀመሪያው ግዴታ በርሱ ማመን፣ በርሱ አለማጋራት፣ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ ወይም ጌታ አለመያዝ ነው። ይህ ግዴታ ቀደም ሲል እንዳብራራነው ሁሉ «ላኢላሀ ኢለሏህ » በሚለው ቃለተውሂድ በማመን ይፈጸማል።

ሁለተኛው ለአላህ ያለብን ግዴታ ከርሱ ዘንድ ለመጣው ሐቅና መመሪያ ፍጹም በተሟላ ሁኔታ መገዛትና መመራት ነው። ይህ ግዴታ የሚፈጸመው ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ «ሙሀመድን ረሱለላህ» በሚለው የቃለተውሂድ ሁለተኛ ገጽ በማመን ነው።

ሶስተኛው ለአላህ ያለብን ግዴታ ደግሞ እሱን ማምለክና በርሱ መገዛት /ዒባዳ/ ነው። ቀደም ብሎ ምዕራፍ አምስት ውስጥ የተወሱት የመገዛት ግዴታዎች ሁሉ በሰው ልጅ ላይ የተደነገጉት ይህንኑ ግዴታ ለመፈጸም ነው። ይህ ለአላህ ያለብን ግዴታ ከተቀሩት ግዴታዎች ሁሉ የበለጠ ትኩረት ስለሚያሻው ይህን ግዴታ ለመወጣት ሲባል እስከተወሰነ ደረጃ የተቀሩትን ግዴ ታዎች መስዋዕት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ለምሣሌ ያህል አንድ ሰው የሰላት ወይም የጾም ግዴታውን ለመለፈጸም ሲነሣ ለገዛ ራሱ ያለበትን አያሌ ግዴታዎች መስዋዕት አድርጎ ማለዳ ከጣፋጭ እንቅልፉ ይነሳል፤ በቀዝቃዛ ውሃ ለሰላት ዝግጅት ውዱዕ ያደርጋል፤የሰላት ግዴታውን ለመወጣት ሲል በየቀኑና ሌሊቱ ካንድ ጊዜ በላይ አጣጣቢ ከሆኑ ሥራዎቹና ጉዳዮቹ ላይ አቋርጦ ይነሣል። የጾም ግዴታውን ለመፈጸም ብሎም ወሩን በሙሉ ምግብና መጠጡን ይተዋል። ስሜቱን ያፍናል። ለሐጅ ብሎም የመንገድና የጉዞ ችግሮችን ይቀበላል፤ ብዙ ገንዘቡንም ለዚሁ

ግዴታ ብሎ ወጪ ያደርጋል። የጅሃድ ግዴታውን ለመወጣት ብሎም ሕይወቱንና ገንዘቡን ይሰዋል። እንደዚሁም ለአላህ ያለ በትን ግዴታ ለመወጣት ብሎ ይብዛም ይነስ ለሰዎች ያለበትን ግዴታ ይሰዋል። ለምሣሌ ያህል በሰላት ጊዜ ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነ ሰው ታላቁን ጌታውን ለማገልገል ሲል ከቀጣሪ ጌታው አገልገሎት ይቆጠባል። በሐጅ ጊዜም የኑሮውና የሥራው ጉዳዮች ይተጓጐላሉ። ሚስቱን፣ ቤተሰቡንና ልጆቹን ጥሎ ወደ ተከበረው የአላህ ቤት ይሳፈራል። ይህም የብዙዎችን መብት የሚነካ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። በጂሃድ ጊዜም ሰውን የሚገድለውና ለራሱም ለአላህ ያለበትን ግዴታ በፍጹምነት ለመወጣት ነው። በተጨ ማሪም በእጁ ሥር የሚገኙ የሚታረዱ እንስሳትንና ገንዘብን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮችን ለአላህ ያለበትን ግዴታ ለመወጣት ሲል መስዋዕት ያደርጋል። ሃያሉ አላህ ግን ለርሱ ያለንን ግዴታ ለመፈጸም ሲባል የግድ አስፈላጊ ከሆነው ደረጃ ውጭ የሌሎችን መብቶች መስዋዕት ማድረግ እንዳይኖር ለራሱ መብቶች የተወሰነ ክልል አኑሮአል። ለምሣሌ ያህል ሰላትን እንውሰድ። የሰላትን ግዴታ ለመፈጸም አላህ ገራገርን እንጂ ጭንቅን አላዘዘም። ውሃ ካላገኘን ወይም በሽተኛ ከሆን ንጹሕ አፈር /የመሬት ገጽ/ ማሰብ አንችላለን። መንገደኛ ከሆን ሶላታችንን ማሳጠር እንችላለን። ከታመምን ቁጭ ብለን ወይም ተጋድመን መስገድ እንችላለን። በሰላታችን ውስጥ የምናነበው ቁርአን አጠር ያለ በመሆኑ ከጥቂት ደቂቃዎች የበለጠ ጊዜ አይወስድብንም። ጊዜ ካለንና ችሎታ ካለን ደግሞ የፈለግነውን ያህል እንደ አልበቀራ ወይም አዒምራን ወይም አልኒሳእ ያሉትን ምዕራፎች ወይም ሌሎች ረዘም ያሉ ምዕራፎችን ሰላታችን ውሰጥ ማንበብ እንችላለን። በሥራ በምን ያዝበት ጊዜ ግን ሰላታችንን ማርዘም አይፈቀድም። ሃያሉ አላህ ከግዴታ ሰላቶች በኋላ በበጐ ፍቃዱ ተጨማሪ የሆነ የሱና ሰላቶችን በመስገድ ወደርሱ ውዴታ መቅረብን በብዙ የሚወድ ቢሆንም

የሌሊት እንቅልፍ፣ የቀን ዕረፍት፣ በራሣችን ላይም እርም እንድናደርግ ወይም የሥራን ጊዜ በተጨማሪ ዒባዳዎች ላይ እንድናውል፣ከዓለማዊ ጉዳዮች ሁሉ ተቋርጦ በሰላት ብቻ እንድ ንዋጥና ለሌሎች ሰዎች ያለብንን ግዴታዎች ችላ እንድንል በፍ ጹም አይፈልግም።

በጾምም እንደዚሁ አላህ ብዙ ነገሮችን ገር አድርጐልናል። እንድንጾም የደነገገብን በዓመት አንድ ወር ብቻ ነው። በሽተኛ የሆነ ወይም ከሀገር የወጣ መንገደኛ ከሆነ ይህን ጾም አዘግይቶ ሌላ ጊዜ ጹሞ መክፈል ይችላል። ለጾም ከተወሰነው ጊዜ ላይ አንዲት ደቂቃ መጨመር አይፈቀድም። ጾመኛ ሰው የሌሊት መጨረሻ ሆኖ ቀንና ሌሊቱ እስኪለይ ድረስ መብላትና መጠጣት ይችላል። ጾሙን እስከ ፀሐይ መጥለቅ ካደረሰ በኋላ አንድ ሰው ግዴታ ያልሆነ ተጨማሪ ጾም ቢጾም የሚደሰት ቢሆንም ጾሙን አከታትሎ በመጾም አካሉን ማድከምና ከዓለማዊ ሥራዎች መለየቱን ግን በፍጹም አይወድም።

እስልምና ካንድ ሰው ንብረት የሚከፈለውን ዘካም በጣም አነስተኛ መጠን ብቻ ነው የወሰነው ። ግዴታ ያደረገውም የተወሰነ የሀብት መጠን ባላቸው ሰዎች ላይ ብቻ ነው። ከዚህ በበለጠ ለመስጠት ፈልጐ በአላህ መንገድ የቸረን ሰው አላህ ቢወደውና ሥራውንም ቢቀበለውም በዚህ ተጨማሪ የትሩፋት ሥራ ገንዘቡን ሁሉ አሟጦ በመለገስ ያለበትን የራሱን ኃላፊነትና ለቤተሰቦቹ ያለበትን ግዴታ መሰዋቱን ግን አይፈልግም። ምጥንነትና መካከ ለኛነት በጣም አስፈላጊ ይሆንበታል።

ሐጅን ደግሞ እንመልከት። አላህ ግዴታነቱን ያረጋገጠው ስንቅ ባላቸውና የደርሶ መልሱን ጊዜ ወጪና ጣጣዎቹን ሁሉ መሸከም ለሚችሉት ሰዎች ብቻ ላይ ነው። አላህ የበለጠ ገር

በማድረጉ አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲፈጽመው አላስገደደም። በሚጓዝበት መንገድ ላይ ጦርነት ወይ ችግር ካለ ወይም ለሕይወቱ ከሰጋ ችግሮቹ እስኪወገዱ ድረስ ሐጅን ማዘግየት መይም ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላል። እንደ ዚሁም አንድ ሰው ሐጅ ለማድረግ ከፈለገ እሱ በሌለበት በዕድሜ መግፋትና በሽመግልና ምክንያት እንዳይቸገሩ ሲባል የወላጆቹን ስምምነት ማግኘትም አስፈላጊ ነገር ነው። ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ሃያሉ አላህ ለርሱ ያለብንን ግዴታ ስንወጣ ለሌሎች ያለብንን ግዴታዎች እንዳንጫን ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ መሆኑን ነው። አንድ ሰው ሰብአዊ መብቶችን በከፍተኛ ደረጃ መስዋዕት የሚያደርገው በጂሃድ ጊዜ ነው። በጂሃድ ላይ አንድ ሰው ሕይወቱን፣ ገንዘቡንና የሌሎች ሰዎችን ነፍስና ገንዘብ ለአላህ ውዴታ ብሎ ይሰዋል። ቀደም ሲል እንዳብራራነው ሁሉ ከከፍተኛ ጉዳት ለመጠበቅ ሲባል ቀለል ያለ ጉዳትን መታገስ ከእስልምና አበይት መሠረቶችና መርሆዎች አንዱ ነው። ይህን መርህ ካስተዋልንና ከተረዳነው የሐሰት ቃል በዓለም ላይ ከፍ ብሎ የአላህ ሃይማኖት በኩፍር፣ በሽርክና፣ በኢአማኝ ኃይሎች ተሸንፎ ምድሪቷን ጥመት፣ ልቅነትና ሥርዓተ አልባነት ከማዳረሱ ይልቅ የጥቂት መቶ ወይም ሺ ሰዎች መገደል የሚቀል ሆኖ እናገኛለን። ከዚህ አስከፊ ጉዳት ለመጠበቅ ሲባል በርሱ መንገድና ለርሱ ውዴታ ብለው በሕይወታቸውና በገንዘባቸው ላይ የሚደርሰውን ቀላል ጉዳት እንዲታገሱ አላህ ለማኝ አገልጋዩቹን አዟል። ከዚህም ጋር የግዴታ መገደል ካለበት ሰው ውጭ ነፍስ እንዳይገድሉ፣ በደካሞች፣ በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በቁስለኞችና በበሽተኞች ላይ ጥቃት እንዳይሰነዝሩ፣ ውጊትን ለመጠበቅ ብዙ ከሚዋጓቸው በስተቀር ሌሎችን እንዳይዋጉ፣ አስፈላጊነትና ምክንያት ሣይኖር የጠላትን መሬት እንዲያበላሹ፣ ጠላትን አሸንፈው አገራቸውን በድል አድራጊነት ከያዙም ፍትሕ እንዲያስተካክሉ፣ ቃል ኪዳን

የገቡላቸውንም እንዲጠብቁ፤ እጃቸውን ከሰበሰቡ፣ ሐቅን ከመ ጋፋት፣ ከመቃረንና ሐሰትን ከመደገፍ እስከ ተቆጠቡ ድረስ እንዳይጐዱዋቸው አላህ አዟቸዋል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ለርሱ ያለብንን ግዴታ ለመወጣት ሲባል መሰዋት ያለበት የሌሎች ሰዎች መብት የግድ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ መጠን ብቻ መሆኑን ነው።

## ለራሣችን ያለብን ግዴታ :-

አሁኑን ደግሞ በሰው ልጅ መፈጸም ካለባቸው ግዴታዎች ሁለተኛው የሆነውን ለራሣችን ያለብንን ግዴታ እንመረምራለን።

የሰው ልጅ ከሌሎች ይበልጥ የገዛ ራሱን ይበድላል ብንል ምናልባት እንደነቅ ይሆናል። ለምን ቢባል እያንዳንዱ ሰው ከሌላው ይበልጥ የገዛ ራሱን እንደሚወድ ስለሚሰማውና ስለሚ ያስብ የገዛ ራሴ ጠላት እኔው ነኝ ብሎ የሚቀበል ሰው አናይም። ይህን ጉዳይ ትንሽ አስተውለን ስንመለከት ግን ትክክለኛው ነገር ይገለጽልናል።

የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ደካማ ጐኖቹ ሁሉ በጣም ጐልተው የሚታዩት አንድ ዓይነት ስሜታዊ ፍላጐት ባሸነፈው ጊዜ ፍጹም ሆኖ ለሚመራበትና በዚህም ምክንያት በገዛ ራሱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ግድየለሽ በሚሆንበት ጊዜ ነው። በአስካሪ መጠጥ የተለከፈ ሰው ብንወስድ ለመጠጡ ሲል በጤንነቱ፣ በሕይወቱ፣ በገንዘቡና በክብሩ ላይ የሚደርሱትን አስከፊ ጉዳቶች ይቀበላል። በምግብ ፍላጐት ክፉኛ የተመሰጠውን ሰው ስንመለከት ደግሞ ያገኘውን ጠቃሚም ሆነ ጠቃሚ ያልሆነ ነገር ሁሉ በመብላት ለዚህ ጭፍን ፍላጐት ብሎ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል። ለሥነ ልቡናዊ ፍላጐቶቹ ብሎ ወደ ውድመት የሚያደርሱ ሥራዎች የሚፈጽም ሌላ ሶስተኛ

ሰውም እናገኛለን። ሌላው ደግሞ የራሱ መድህን አሳስቦት መንፈሱን በማጥራትና በማምጠቅ ተግባር ላይ አትኩሮቱን አውሎ ለገዛ ስሜታዊ ዝንባሌው ጠላት ሲሆን፣ ነፍሱ የምትጓጓላቸውን ድሎችና ሥጋዊ ፍላጐቶች ሁሉ ከጫማው ሥር ረግጦ ለማለፍ የሚፈልግ፣ የነፍሱን ፍላጐቶች እውን ማድረግ አሻፈረኝ የሚል፣ ከጋብቻ የሚሸሽ፣ ምግብና መጠጥ የሚጠየፍ፣ ልብስ የሚጠላ፣ በርሱ አመለካከት በኃጢአት በተሞላች በዚህች ዓለም ውስጥ ሆኖ መተንፈስ እንኳ እስከ መጥላት የሚደርስ፣ ወደ ጫካና ወደ ዋሻዎች የሚጠለልና ይህ ዓለም ለርሱ ያልተሠራች የሚመስለውንም በሌላው በኩል እናገኛለን።

እነዚህ የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ላይ ከሚያሳያቸው የአክራሪነት ባህሪያት /የተስፈንጣሪነት ዝንባሌ/ ጥቂት ምሣሌዎች ናቸው። ባንድ ሰው ሕይወት ውስጥ በየጊዜው የምናያቸው በርካታ የአክራሪነት /የተስፈንጣሪነት/ ገጽታዎች አሉ።

እስላማዊው ሸሪዓ ለሰው ልጅ መድህንና ተድላን የሚሻ እንደመሆኑ መጠን «ለገዛ ራስህም መፈጸም ያለብህ ግዴታ አለብህ» ለሚለው የጸና እውነታ ትኩረት እንዲሰጥ ይቀሰቅሰዋል። እንደ አስካሪ መጠጥ፣ ሐሺሽ፣ ኦፒያምና የመሳሰሉ አደንዛዥና አስካሪ ነገሮች በሰው ጤንነት፣ በሥነ ምግባሩ፣ በሕሊናዊና መንፈሳዊ ብቃቱ ላይ መጥፎ ተጽእኖ አላቸው። በነዚህ ፈንታ ጠቃሚና ጥሩ የሆኑ ነገሮችን ይፈቅድለታል። በነዚህ በተፈቀደልህ ነገሮች መደሰቱን በራስህ ላይ እርም አታድርግ፤ ለገዛ አካልህም ግዴታ አለብህና ይለዋል።

ራቁት ከመሄድ ይከለክለዋል። በዚች ምድረ ዓለም ላይ አላህ ያወረደለትን አስደሳች ነገሮች እንዲጠቀም መሸፈን ያለባቸውን የአካሉን ክፍሎች እንዲሸፍን ያዛል።

ሥርተን ኑሮን በማሸነፍ ብርቱ እንድንሆን ያዘናል ። ሥራ ፈቶ እቤት መዋልን፣ የሰውን እጅ ማየትን፣ መራብን ይከለክላል። አላህ የለገሰንን ጸጋ እንድንጠቀም በምድርና በሰማይ ለኛ መገልገያ የፈጠራቸውን መጠቀሚያዎች በሕጋዊ መንገድ ለማግኘት ጥረት እንድናደርግ ያዘናል ።እስላማዊ ሸሪዓ ሥጋዊ ፍላጐትና ስሜታዊ ዝንባሌ ከነጭራሹ እንዲታፈኑ ስለማይፈቅድ ጋብቻውን ያዛል።

ራስን ዝቅ ማድረግና የተደላደለ ሕይወትና የተሳካ ኑሮን እንድትኖር ነፍስን ማገድ ሸሪዓው ይከለክላል። በመጪው ቀሪ ሕይወት መድህን ለማግኘት ከፈለጋችሁ ዓለማዊ ሕይወትን መተው አስፈላጊ አይደለም። በዚህም ዓለም ላይ አላህን ማስታወስ፣ ዓላማዊ ደስታን መካፈልና በመገልገያዎቹ መጠቀም፣ የአላህን ትዕዛዝ አለመጣስና ሸሪዓውን መከተል፣ በዛሬው አላፊ ዓለም ሕይወትም ሆነ በነገው ቀሪ ሕይወት ተድላና ደስታ ከሁሉም የበለጠ መሣሪያና ከሁሉም የተሻለ ፍቱን መሣሪያ መሆኑን ሸሪዓው ያስረዳናል።

ራስን መግደል እርም ያደርጋል። ይህች የተሰጠችን ነፍስ የአላህ ንብረት ስለሆነች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ልንገለገልባት እኛ ዘንድ ያስቀመጣት አደራ ናትና እንዳሻን ልናደርጋት፣ በገዛ እጃችን ልንገድላት ምንም ስልጣን እንደሌለን ሸሪዓው ይነግረናል።

## ለሌሎች ሰዎች ያለብን ግዴታ:-

እስላማዊው ሸሪዓ ባንድ በኩል ለገዛ ራሣችን ያለብንን ግዴታ እንድንወጣ ሲያዘን በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ግዴታ የሌሎች ሰዎችን መብት በምንም መንገድ በማይነካ ሁኔታ ብቻ እንድ ንፈጽም ያዘናል። የሌሎችን መብት በሚጐዳ መንገድ ስሜታዊ

ፍላጐቱንና ዝንባሌውን ካሟላ ሰው ራሱን አርክሶ ሌሎች ሰዎ ችንም ይጐዳል። ከዚህ በመነሳትም ሸሪዓው ዝርፊያን፣ ንጥቂያን፣ ሥርቆትን፣ ጉቦኛነትን፣ እምነት ማጉደልን፣ ማጭበርበርን፣ ቃል ኪዳን ማፍረስን፣ አራጣ መብላትን እርም አድርጓል። በነዚህ መንገዶች ሰው የሚያገኘው ጥቅም በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት በማድረሱ ነው። እንደዚሁም ውሸት መናገርን፣ ሃሜትን፣ ማሳ በቅን፣ ስም ማጥፋትን ሸሪዓው እርም አድርጓል። እነዚህ ነገሮችም በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉና ። ቁማርና ሎተሪም እንደዚሁ ጥቅማቸው በሺ በሚቆጠሩ ሰዎች ጉዳት ላይ የተመ ሰረተ ስለሆነ እርም ተደርጓል። በማታለል፣ በማጭበርበርና በመሳ ሰሉት ገንዘብ ነክ አሻጥሮች ላይ የተመረኮዘ ግብይትም እንደዚሁ በአንዱ ወገን ላይ ጉዳት የሚያመጣ በመሆኑ ሀራም ሆኗል። ሰውን መግደል፣ በምድር ላይ ጥፋት ማዛመት፣ ችግር፣ ፊተና እንዲበዛ ማድረግም ሀራም ነው። ማንም ሰው የሌላውን ሰው ገንዘብ ለማግኘት ወይም እርኩስ ፍላጐቱን ለማርካት ብሎ ነፍስ መግ ደልም ሆነ በሌላ መንገድ መጉዳት በፍጹም አይፈ ቀድለትም። ዝሙትና ግብረሰዶም ባንድ በኩል የሰውን ጤንነትና ሥነ ምግ ባሩን የሚያበላሹ በመሆናቸው በሌላ በኩል ደግሞ ልቅነት፣ ቅሌትና ወራዳነት በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፉ ስለሚያደርጉ በመጨረሻም አስከፊ የሆኑ የአባላዘር በሽታዎችን በማምጣት መካንነትን ስለሚያስከትሉ፣ አሳሳቢ ችግሮችን የሚያ ደርሱ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያቃውሱ፣ የባህልና የሥልጣኔ መሠረት የሚያናጉ በመሆናቸው ሸሪዓው ሀራም አድርጓል።

የሰው ልጅ የራስንና የገዛ አካሉን ግዴታዎች ለመፈጸም ብሎ የሌላውን ሰው መብት እንዳይገፍ ለርሱ ያለበትን ግዴታ እንዳ ይነፍገው ወይም እንዳያጓድልበት የእስልምና ሸሪዓ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የጣላቸው ገደቦች ናቸው። የሰውን ሥልጣኔ ተድ ላውን ለማጐልበት ግን አንድ ሰው ሌላውን ሰው በምንም ነገር

አለመጉዳቱ ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ ጋር በሰዎች መካከል ያለው ተዛምዶና ግንኙት ሁሉም በበጐ ዓላማ ላይ የሚረዳዱ፣ በማህበራዊ ጥቅሞች ላይ የሚተጋገዙ እንዲሆኑ በሚያደርጋቸው ሁኔታ ላይ የተመረኮዘ መሆን የግድ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ዓላማ የእስልምና ሸሪዓ የደነገጋቸውን ሕጐች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥለን እናያለን :-

ሀ. የሰብዓዊ ፍጡራን ግንኙነቶች በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ይጀምራል። ሌላውን ከማየታችን በፊት ቤተሰባዊ ሕይወት እንመልከት። ቤተሰብ ደግሞ ባልና ሚስት ከልጆቻቸው ጋር የሚታቀፉበት ስብስብ ነው። እስልምና የቤተሰብን መሠረት በሚመለከት፣ ለቤተሰቡ ኑሮ ገቢ ለማግኘት መሥራትንና ለቤተሰቡ አስፈላጊውን ሁሉ ማዘጋጀትን፣ ቤተሰቡን ከጥቃት መከላከልን የባል ግዴታ ያደርገዋል። ባል ሠርቶ የሚያመጣውን በማዘጋጀትና፣ የቤቱን የውስጥ ጣጣ በማቀናበር፣ ለባሏና ለልጆቹ የተቻለውን ያህል እፎይታ ማስገኘት፣ ልጆችን መንከባከብ የመሳሰለው ደግሞ የሴትየዋ ግዴታ ነው። ወላጆቻቸውን መታዘዝና ማክበር፣ በዕድሜ ሲገፉም ማገልገል የልጆች ግዴታ ነው በሚል መመሪያ ላይ ነው። የቤተሰብ ሥርዓት ቀና በሆነ መልካም መንገድና ትክክለኛ በሆነ ሁኔታ ወደፊት ተጠብቆ እንዲጓዝ እስልምና ሁለት ቅንብሮችን መርጧል። የመጀመሪያው ቅንብር ባልና አባት የቤተሰቡ መሪና አስተዳዳሪ ማድረጉ ነው። ያንድ ሀገር ሥርዓት ያለ አስተዳዳሪና ጉዳይ አስፈጻሚ በትክክል መራመድ እንደማይችል ሁሉ፣ ወይም የአንድ ትምህርት ቤት ሥርዓት ያለ ሥራ መሪው በትክክል መመራት እንደማይችል ሁሉ የቤተሰብ ሥርዓትም እንደዚሁ ያለ አንድ የበላይ አስተዳዳሪና ጉዳይ አስፈጻሚ የሆነ መሪ ተቃንቶ መራመድ በፍጹም አይችልም። እያንዳዱ የቤተሰብ አባል በግሉ ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት፣

ስለሥራው ኃላፊነት የሌለበት ቤተሰብ፣ ሥርዓት አልባ ነትና አለመረጋጋት መስፈኑ፣ ሠላም እርጋታና እፎይታ የማይኖርበት ለመሆኑ በጣም ግልጽ ነው። እነዚህን አጥፊና አፍራሽ ነገሮች ለማስወገድ ደግሞ ለቤተሰቡ ጉዳዮች ሁሉ ተጠ ያቂና ሃላፊ የሆነ አንድ የበላይ አስተዳዳሪ የግዴታ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ቦታም ስለቤተሰቡ እንክብካቤና ጥበቃ ኀላፊነት ያለበት ወንዱ ነው።

ሁለተኛውም ቅንብር:-ከቤት ውጭ ያሉትን ጉዳዮችና ማህበ ራዊ ግንኙነቶች ሁሉ ኃላፊነቱን በወንዱ ጫንቃ ላይ ሲጥል ችግር ወይ ጉዳይ ካልገጠማት በስተቀር ሴት ከመኖሪያ ቤቷ እንዳትወጣ ሸሪዓው አዟታል። እቤት ውስጥ ያለባትን ኃላፊነት በእርጋታና በረጋ መንፈስ በሚገባ እንድትወጣ፣ የቤቱ የሥራ ሰዓትና የልጆቹ እንክብካቤ እርሷ ከቤት በመውጣቷ እንዳይተጓጐል ሲባል ሴት ከቤት ውጭ ባሉት ጉዳዮች ሁሉ በኃላፊነት አትጠየቅም ይህ ማለት ደግሞ ሴት ከነጭራሹ ከቤት መውጣት አይፈቀድላትም ማለት አይደለም። የሚያስወጣት ነገር ካጋጠማት መውጣቱ ተፈቅ ዶላታል። ሸሪዓው ያለመው ቤት ለሴት ልጅ ለተጣሉባት ግዴታ ዎች መፈጸሚያ እውነተኛው ክልል እንዲሆን ነው። የተለገ ሰችውን ኃይልና ብቃት የቤቷን ጉዳዮች በማሻሻል ላይ ብቻ እንዲታወስ ነው።

በደም ዝምድናና በጋብቻ ዝምድና መቀራረብ የቤተሰብ ክልል ይሰፋል። በዚህ ክልል ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚገናኙት ሰዎች በመካከላቸው የሚፈጠረውን አለመግባባት በእርቅ እንዲ ጨርሱና እርስ በርሳቸው ተደጋጋፊዎች እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው ከፍተኛ ጥበብ ያቀፉ የተለያዩ መሰረታዊ ደንቦችን ሸሪዓው ደንግጓል። ከነዚህም መካከል:-

1. እንደ እናትና ልጅ፣ አባትና ልጅ፣ የእናት ባልና የሚስት ልጅ፣ የአባት ሚስትና የባል ልጅ፣ ወንድም፣ እህት በሥጋም ሆነ አብሮ በመጥባት፣ አጐትና የወንድም ልጅ፣ አክስትና የወንድሟ ልጅ፣ የሹማና የእህቱ ልጅ፣ የሹሜና የእህቷ ልጅ፣ የሚስት እናትና የልጅ ባል፣ የባል አባትና የልጁ ሚስት ባሉትና የጠበቀ ቤተሰባዊ ገመድ ባስተሳሰራቸው ዘመዳሞች መካከል በጋብቻ መገናኘት ሸሪዓው ሀራም አድርጓል። ይህ የጋብቻ እገዳ አያሌ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን እንዲህ ያሉ ወንዶችና ሴቶች በመካከላቸው የሚኖረው ግንኙነት የጠራና የጸዳ ሆኖ ይቆያል። ያላንዳች ጭንቀ ትና ጥርጣሬ ይዋደዳሉ ፍጹምነትና መተሳሰብ በተመላበት ሁኔ ታም ይዛመዳሉ።

2. ከነዚህ ውጭ ባሉት የቤተሰብ አባላት መካከል እስልምና መጋባትን ፈቅዷል። ይኸውም ዝምድናቸው በበለጠ እንዲጠ ናከርና እንዲቀራረብ የበለጠ እንዲዋደዱ በማሰብ ነው። ባህል ለባህል፣ ጸባይ ለጸባይ በቅርብ በሚተዋወቁ ሰዎች መካከል የሚፈጸም ጋብቻ በባህልም ሆነ በልማድ ከማይቀራረቡት ሰዎች መካከል ከሚፈጸም ጋብቻ የበለጠ ስኬታማ ይሆናል። የጋራ ባህልና ወግ በሌላቸው መካከል የሚደረጉ ጋብቻዎች በአብዛኛው ጭቅጭቅና አለመግባባት የሚርቃቸው አይደሉም። ስለዚህም በአቻዎች መካከል የሚፈጸመው ጋብቻ ከሌላው ይበልጥ ተመርጧል።

3. በቤተሰብ ውስጥ ሀብታምና ደሃ ባለጸጋና አጥ ይሆናል። ሰለዚህም በአንድ ሙስሊም ላይ ያለው ትልቁ ግዴታ የሥጋ ዘመዶቹ መሆኑን እስልምና ደንግጓል። ይህም «ሲለቱረህም» ወይም « ዝምድና መቀጠል» በመባል በሸሪዓው ዘንድ የሚታ ወቀው ነው። ይህ የዝምድና መቀጠል ጉዳይ ቁርአንና ሐዲስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሟል። ዝምድናን ማቋረጥ ከከባድ

ኃጢአቶች አንድ አንዱ ተቆጥሯል። ችግረኛ በሆነ ዘመድ ላይ አንድ ችግር ወይም አደጋ ቢደርስ የመርዳት አቅም ያላቸው ዘመዶቹ ለችግሩ የመድረስና እርዳታ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። በበጐ ፍቃድ ልገሳም ቤተዘመድ የሆነ ሰው ከሌላው የቅድሚያ መብት አለው።

4. አንድ ሰው ከሞት በኋላ ያፈራው ሀብት ባንድ ሰው እጅ ብቻ እንዳይከማችና እንዳይበሰብስ በማድረግ ዝምድና ያለው ሁሉ ድርሻውን መካፈል በሚችልበት ሁኔታ እስልምና የውርስ ሕግ ደንግጓል። ከሁሉም ይበልጥ የሚቀርቡ ዘመዶች ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ፣ ሚስት ባል፣ አባት፣ እናት፣ ወንድምና እህት ናቸው። ስለዚህም ከሌሎች በፊት የነዚህ ዘመዶች በሸሪዓው ተብራርቷል። ሁሉም ካልተገኙ ቀድሞት ያለውን ዘመድ ድርሻ በቅደም ተከተሉ መሠረት ቀጥሎ ያለው ዘመድ ያገኛል። በዚህ ዓይነትም የሟቹ ሀብት በብዙ ዘመዶቹ መካከል ይሰራጫል። ይህ የእስልምና የውርስ ሕግ በጥንቱም ሆነ በዛሬው ዓለም ሕጐች ውስጥ እምነት የሚጣልበት ነው። ዛሬ አንዳንድ ሕዝቦች በዚህ ሕግ ላይ የእስል ምናን አርአያነት ማጤን ቢጀምሩም ሙስሊሞች ራሣቸው ባለማ ወቅና በጅልነታቸው ምክንያት ይህን ሕግ የሚቃረን መደን ገጋቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። በብዙ አካባቢዎች በተለይም በሀገራችን – ሴት ልጆችን ውርስ የመንፈግ በሽታ በሙስሊሞች መካከል ተዛምቷል። ይህ ደግሞ አስከፊ ግፍና ግልጽ የሆነውን የቁርአን ውሣኔ መቃወም ነው።

ለ–ከቤተሰብ ግንኙነቶች በኋላ ሰው ከወዳጆቹ፣ ከጐረቤቶቹ፣ ከመንደርተኞቹ፣ ከሀገሩና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አብረው ከሚ ሳተፉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል። እነዚህን በሙሉ በፍጹ ምነት፣ በእኩልነትና በመልካም ሥነ ምግባር እንዲቀርባቸው፣ በመጥፎ አነጋገርና በሚያስከፉ አባባል ከማስቀየሙ እንዲቆጠብ

፣ ከነርሱ ጋር እንዲተጋገዝና እንዲረዳዳ፣ ሲታመሙ እንዲጠ ይቃቸው፣ ሲሞቱ እንዲቀብራቸው፣ በችግር ጊዜ እንዲካፈ ላቸው፣ ድሆቹን፣ ችግረተኞቹንና አቅመ ደካሞቹን በስውርና በይፋ እንዲረዳቸው፣ የሙት ልጆችንና ሚስቶችን በርህራሄ እንዲይዛቸው፣የተራበውን እንዲያበላ፣ የታረዘውን እንዲያለ ብስ፣ ሥራ እንዲያገኝና ሠርቶ እንዲኖር ሥራ እጦን እንዲደግፍ፣ አላህ ፀጋውን ከሰጠው ለመንደላቀቂያና ለመቀናጫ እንዳያውለው እስልምና ያዛል። ከወርቅና ከብር በተሠሩ እቃዎች መብላት መጠጣትን፣ ከንፁህ ሐር የተሠሩ ልብሶች መልበስን፣ ገንዘብን ለቅንጦትና ለመንደላቀቂያ ነገሮች ላይ ማባከንን፣ ሸሪዓው ሃራም አድርጓል። ይኸውም ብዙ መቶ ሺህ ሰዎች ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ሀብት አንድ ግለሰብ ብቻ እንደሻውና ፍላጐቱ እንዳዘዘው መጠቀምና መንጠባረር ተገቢ ባለመሆኑ ነው። የብዙ ሺህ መብተኞች ሕይወት ማዳን የሚችለውን ሀብት በጌጥ መልክ አንድ ላይ ማንጠልጠል፣ በዕቃ መልክ ማኖር ወይም ቤት ውስጥ ማንጠፍ ወይም በመብራት መልክ ማባከን ከግፍ የሚቆጠር ነው። ይህም ሲባል ደግሞ እስልምና አንድ ሰው ያፈራውን ሀብት ሁሉ መንጠቅ ይፈልጋል ማለት አይደለም። ሠርቶ ያፈራው ወይም ከወላጆቹ የወረሰው ሀብት ሁሉ ሕጋዊ ንብረቱ ስለሆነ በገንዘቡ መደሰት ይችላል። በሚለብሰው ልብሱ፣በምግቡ፣ በመኖሪያ ቤቱና በሚጠቀምበት ማጓጓዣው የአላህን ጸጋ ማንፀባረቅ ይፈቀድለታል። የእስልምና ትምህርቶች ዓላማ ግን አንድ ሰው መካከለኛ የሆነ ጥሩ ኑሮ እንዲኖርና ከመጠን በላይ መንደላቀቅን ማስቀረት፣ አላህ በሰጠን ጸጋ ሁሉ ለዘመዳችን፣ ለወዳጃችን፣ ለጐረቤቶቻችን፣ ለሀገር ልጆችና ለመላው የሰው ልጆች ያለብንን ግዴታዎች በሚገባ መፈጸም ነው።

ሐ– አሁን ደግሞ ከዚህ ጠባብ ክልል ወጥተን የመላውን ዓለም ሙስሊሞች ወደሚያጠቃልለው ሰፊ ክልል መውጣት

እንችላለን። እስልምና በዚህ ክልል ውስጥ ሙስሊሞችን ሁሉ በበጐ ዓላማና የአላህን ትእዛዝ በመፈጸም ላይ እንዲተባበሩና እርስ በርሣቸው እንዲተጋገዙ የሚያደርጋቸው ሕጐችና ደንቦችን ደን ግጓል። በተቻለ መጠን መጥፎ ሥራዎችና አስከፊ ድርጊቶች በዓለም ላይ እንዲያንሰራሩ በፍጹም አይፈቅድም። ቀጥለን ደግሞ ከነዚህ ሕጐች አንዳንዶችን እናያለን።

1. ለማህበራዊ ሥነ ምግባር ጥበቃ ሲባል ጋብቻን በሚከለክል ዝምድና የማይገናኙ ሴቶችና ወንዶች ነጻና ልቅ በሆነ መንገድ እንዳይቀላቀሉ፣ ሴቶች ከወንዶች የተለየ ቦታ እንዲኖሩ፣ የሴቶች ከፍተኛ ትኩረታቸውን ለቤተሰቡ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ግዴታ ዎችን በመፈጸም ላይ እንዲያውሉ ፣ ከቤታቸው መውጣት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም አጊጠውና አብለጭልጨው እንዳ ይወጡ፣ ተራ የሆነ ልብሣቸውን ለብሰው አካላቸውን በሙሉ እጅና ፊታቸውንም በጣም አስፈላጊ የሆነ ችግር ካልኖረ በስተቀር ሙሉ በሙሉ ተሸፋፍነው እንዲወጡ እስልምና ያዛል። ይህም በሸሪዓው ውስጥ « ሂጃብ » ወይም መሸፋፈን በመባል የሚታ ወቀው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ወንዶችም ከሚስቶቻቸው ውጭ ያሉትን ባዕድ ሴቶች ከማየት እንዲጠነቀቁ፣ ሳያስቡ ዓይናቸው በሴቶች ላይ ካረፈ እይታቸውን ወዲያውኑ እንዲለውጡና በድ ጋሚ እንዳይመለሱበት እስልምና ያዛል። ስለዚህም እያንዳንዱ /ወንድና ሴት/ ሰው ሥነ ምግባሩን መጠበቅ ግዴታው ሲሆን በልቡ ውስጥ ቀለል ያለም ቢሆን ሕጋዊ ትዳርን በመተላለፍ ሥጋዊ ፍላጐቱን የማርካት ዝንባሌ እንዲፈጠርበት ዕድል መስጠት እንኳ አይገባውም።

2. ማህበራዊ ሥነ ምግባርን ለመጠበቅ ሲባል ወንድ ከእን ብርቱ እስከ ጉልበቱ ያለውን የገላውን ክፍል እንዳይጋለጥ፣ ሴት ደግሞ ከፊቷና ከመዳፎቿ በስተቀር የተቀሩትን የአካሏን ክፍሎች

ለሚቀርቧት ሰዎች እንኳ ቢሆን እንዳትጋለጥ እስልምና ክል ከሏል። ይህም በሸሪዓው ውስጥ «ሲትር» ወይም ሽፋን በመባል ይታወቃል። ማንኛውም ሴትና ወንድ ይህን የአለባበስ ደንብ የመከተል ጥብቅ ግዴታ አለበት። በዚህም በሰዎች መካከል የማፈር ስሜት እንዲጸነስ፣ ሰውን በመጨረሻ ወደ ልቅነትና የሥነምግባር መዳሸቅ የሚጐትቱ መጥፎና አስከፊ ድርጊቶች እንዳይዛመቱ በማለም ነው እስልምና ይህን የደነገገው።:

3. እስልምና የሰውን ምግባር የሚያበላሹ ወራዳ ፍላጐቶቹን የሚቀሰቅሱ፣ ጊዜውን፣ ጤንነቱንና ገንዘቡን በከንቱ የሚያባክኑ የጭፈራና የጨዋታ ዓይነቶችን ሁሉ አይወድም። ጨዋታ በመ ሠረቱ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። የሰውን መንፈስ ለማደስና የመሥራት ብቃቱን ከፍ ለማድረግ፣ ለማነቃቃት፣ ለማዝናናት፣ ከሥራ ትጋት ጋር የግድ አስፈላጊ ነው። ታዲያ ንቃት የሚያስገኝ፣ መንፈስን የሚያረካ ጨዋታ መሆን አለበት እንጂ መንፈሱን የሚያስጨንቅና ውጥረት የሚያስከትል ጨዋታ መሆን የለበትም። ወንጀሎች እንዲፈጸሙ የሚጋብዙ፣ ብዙ ሺህ ሰዎች ተሰብስበው የሚመለከቷቸው ዝቃጭ የጭዋታ፣ የጭፈራ ሁኔታዎች ለልቅ ነትና ለሥነ ምግባር ብልሽት የሚያዘጋጁ ሰው ሰራሽ ትእይንቶች ላይ ላዩን የሚያስደስቱና ጥሩ መልክ ያላቸው መስለው ቢታዩም እንኳ የሕዝቦችን ሥነ ምግባርና ባህላቸውን የሚያበላሹ መቅሰፍት ናቸው።

4. የሙስሊሞችን አንድነትና ማህበራዊ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል እርስ በርሳቸው መከፋፈልን እንዲጠነቀቁ፣ ቡድናዊነትንና ልዩነት ከሚያስከትሉ ምክንያቶች እንዲርቁ እስልምና በጥብቅ አዟል። በአንድ ነገር ላይ ከተለያዩ ጉዳዩን ወደ አላህ መጽሐፍ – ቁርአን– ወደ ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲስ ውሣኔ በፍጹ ምነት፣ በጠራ ቅን ልቦና እንዲመልሱ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ስምምነት

ካልተገኘ ግን ነገሩን ለአላህ በመተው እርስ በርስ ከመፋጨት እንዲቆጠቡ፣ በማህበራዊ ደህንነትና መድህን በሆኑ ትሩፋት ሥራዎች ላይ እንዲረዳዱ፣ የመሪዎቻቸውን ትእዛዝ እንዲያ ከብሩ፣ ከተንኰልና ከፈተና ሰዎች እንዲርቁ፣ ኃይላቸውን እንዳያ ዳክሙና ሕዝባቸው በውስጣዊ የርስ በርስ ጦርነት እንዳይጋለጡ እስልምና አበክሮ ያሳስባቸዋል።

5. ሙስሊሞች ሳይንስና ስነጥበብን እንዲቀስሙ፣ ሙስሊም ካልሆኑት ወገኖች ጠቃሚ የሆኑ መንገዶችን እንዲገበዩ ተፈቅዶ ላቸዋል። በግላዊ አኗኗራቸውን ግን እነሱን እንዳይመስሉ ተከል ክለዋል። የራሱን ትቶ ሌላውን መምሰል የሚፈልግ ሕዝብ በራሱ ላይ ዝቅተኝነትን፣ ውርደትን፣ ድክመትን የሚቀበል የሌሎችን ቀደምትነት፣ ኃያልነትና ምጥቀት የሚቀበል ሕዝብ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ከሁሉም የከፋ ዝቃጭ ባርነት ነው። ውርደትና ውድቀትን መቀበል ነው። ውጤቱም የተከታዩ ጀሌ ሕዝብ ባህልና ስልጣኔ ውድመት ነው ። በዚህ ምክንያት ነው ነቢዩ ሙሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ባዕድ ሕዝቦችን መከተልና ባህልና ሥልጣኔያቸውን መምረጥ አጥብቀው የከለከሉት። የማንኛውም ሕዝብ ኃይል በአለባበስ ወጉና በአኗኗር ስልቱ ላይ የሚመሠረት ሣይሆን ባለው ዕውቀት፣ ባለው የድርጅትና የቅንብር ጥራትና በሥራ ብቃቱ ላይ መሆኑን ትንሽ እንኳ ማሰብ የሚችል ሁሉ ይገነዘበዋል። ኃይል፣ ሙሉነትና ምጥቀት የሚፈልግ ሰው ለሃያሉ ለምጥቀቱና ለብቃቱ መንስኤ የሆኑትን ከባዕድ ሕዝቦች ይቅሰም እንጂ ሕዝብን አዋርዶ ወደ ባዕድ ሕዝቦች ተጽእኖ ሥር በማንበርከክ በመጨረሻ ሕልው ናውን ወደሚያሳጣው መንገድ አያዘንብል።

ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች በአድላዊነትና በጠባብነት ዓይን እንዳይመለከቱ፣ አማልክቶቻቸውን እንዳይዘልፉ፣ ሙሁዎቻ ቸውን እንዳይወቅሱ፣ እምነታቸውን እንዳያንቋሽሹ፣ ሙስሊሞች

ተከልክለዋል። ሙስሊም ያልሆኑት በመግባባትና በሠላም ከሙስ ሊሞች ጋር መኖር እስከፈለጉ ድረስ ጭቅጭቅ እንዳይጀም ሩባቸው፣ መብታቸውን እንዳይደፍሩ ከልክሎ በመግባባትና በሰ ላም እንዲይዟቸው አዟል። ሌሎች ሰዎችን በተቻለ ሁሉ በላቀ የፍቅር፣ የሰብዓዊ መተሳሰብ ስሜትና ሥነ ምግባር መያዝ የእስ ላማዊ ክብራችን ግዴታ ነው። ሌሎችን በወገናዊነት፣ በመጥፎ ምግባር፣ በግፍና በጠባብ አመለካከት ማየት የእስልምናን ሕግ ጋትና የሙስሊምነት ተፈጥሮን መጻረር ነው። ሙስሊም የሆነ ሰው በመልካም ሥነ ምግባሩ፣ በጨዋነቱ፣ በልበ ሰፊነቱና ፈሪሃ አላህ በመሆኑ የሰዎችን ልብ በእውነትና በፍትህ ላይ ወደ ተመሠረተው የጠራ መርሆው ለመማረክ መልካም አብነት ያለው ሰው መሆን አለበት።

## ለሌሎች ፍጡራን ያለብን ግዴታ:-

ቀጥለን ደግሞ አራተኛውን ዓይነት ግዴታ እንመለከታለን። አላህ ሰውን ከብዙዎቹ ፍጥረታት ሁሉ አብልጦት ተፈጥሮን ለጥቅሙ እንዲገራ፣ ለግልጋሎቱ እንዲያውለው ፈቅዶለታል። ይኸውም የሕጋዊ መብቱ አካልና በምድር ላይ ከአላህ ፍጥረታት ሁሉ በላጩ ፍጡር በመሆኑ ነው። ይህም ሆኖ ግን የሰው ልጅ ለነዚህ ፍጡራን መፈጸም ያለበትን ግዴታዎች አላህ አኑሮአል። ከነዚህ ግዴታዎች መካከል ፍጡራኑን እንዳያሰቃይ፣ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር እንዳያስቸግራቸውና እንዳ ይጐዳቸው፣ ከጐዳቸው ደግሞ የግዴታ ለራሱ ሕልውና አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንዲሆን፣ በነሱ ሲገለገልና ሲጠቀም የተሻለና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መምረጥን የመሳሰሉ ናቸው። የእስልምና ሸሪዓ እነዚህን በመሳሰሉ የጸኑ ድንጋጌዎች የተሞላ ነው። አንድ ሰው እንስሳትን እንዲገድል የሚፈቀድለት ለምግብ ወይም

ከሚያደርሱት ተንኮል ራሱን ለመከላከል ሲሆን ብቻ ነው። ለመዝናኛና ለጨዋታ ብሎ እንዲያው በከንቱ መግደል በጥብቅ የተከለከለ ነው። ሥጋቸው ለሚበሉ እንስሳት ጠቃሚውን ሥጋ ለማግኘት በሚያስችል መንገድ የአስተራረድ ዘዴ አኑሮአል። ከዚህ የአስተራረድ ዘዴ ውጭ ያሉት መንገዶች እንስሳውን ብዙ የማያሰቃዩ ቢሆኑም እንኳ የሥጋውን ጠቀሜታ በብዙ ይቀንሳሉ። እስልምና ግን እንስሳቱን ከማሰቃየትም ሆነ የሥጋውን ጠቀሜታ ከማሣነስ ነፃ ነው። እንስሳት በሰቆቃና በጭካኔ እንዳይገደሉ እስልምና በጥብቅ ከልክሏል ። ጉጂ የዱር አራዊትና መርዘኛ ነፍሳት እንዲገደሉ የሚፈቅደውም የሰው ልጅ ሕይወት ከአራዊትና ከተባይ ነፍሳት ሕይወት የበለጠ ክቡርና የበለጠ ውድ በመሆኑ ነው። ይህም ቢሆን በማሰቃየትና ከርህራሄ በራቀ ሁኔታ እንዲገደሉ አይፈቅድም። ለትራንስፖርትና ለጭነት የሚያገለግሉ እንስሳትን እንዲራቡና ከአቅማቸው በላይ እንዲሸከሙ ማድረግ፤ እንደዚሁም ያለ ርህራሄ መደብደብ በጥብቅ የተከለከለ ነው። አዕዋፍን አስፈላጊ ሣይሆን ይዘው ማቆየትን እስልምና ይከለክላል ። እንስሳት ቀርቶ ዛፎች እንኳ እንዳይጐዱ፣ አበባና ፍሬያቸው ሲቀጥፍ አስፈላጊ ሣይሆን ከሥር እንዲነቀሉ ወይም እንዲጠፉ በፍጹም አይወድም ። ሕይወት ካላቸው ዕፅዋት እልፎም ግዑዝ አካላት እንኳ እንዲጠፉ እስልምና የማይፈቅድ ሲሆን አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ ውሃ ማፍሰስና ማባከን ከልክሏል።

## ዘለዓለማዊው ዩኒቨርሳል ሸሪዓ:-

ከላይ ያብራራናቸው ሁሉ የዚህ ነቢያችን ሙሐመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ያስተማሩትና ለመላው የሰው ልጅ ለዘልዓለሙ በመሪነት የሚያ ገለግል የጠራ ሸሪዓ ሕግጋትና ድንጋጌዎች ማጠቃለያ ነው። በዚህ ሸሪዓ ዘንድ ሰውን ከሰው የመመዘኛው ነጥብ እምነትና ሥራ ብቻ

ነው። ሐቁን ለመናገር በዘር፣ በብሔር ወይም በቆዳ ቀለም ላይ በመመርኮዝ ሰውን ከሰው የሚለዩ ሸሪዓዎችና እምነቶች በሙሉ ዩኒቨርሳል ሸሪዓ መሆን አይችሉም። የዚህ ዘር አባል የሌላውን ዘር አባል መሆን ወይም እሱነቱን ማጥፋት በፍጹም አይቻልም። የዓለም ሕዝቦች በሙሉ ተሰባስበው ያንድ ዘር ያንድ አገር ሰዎች መሆን እንደማይችሉ በጣም ግልጽ ነው። የአፍሪካዊው ጥቁረት የቻይናዊው ቢጫነት ወይም የፈረንጁ ንጣት ተፈጥሮ ነውና ሊለወጥ አይችልም። በዚህ የሚያምኑ ሃይማኖቶች ከሕዝቦች መካከል በአንድ የተለየ ሕዝብ ዘንድ ብቻ ነው መፈጠርና መኖር የሚችሉት። ባንፃሩ እስልምና ደግሞ ዓለም አቀፋዊ የሆነ ዘልዓለማዊ ሸሪዓውን ይዞ የመጣ ስለሆነ « ላኢላሀ ኢለሏህ » በሚለው ቃለተውሒድ ያመነ ሰው ሁሉ የሙስሊሙ ሕዝብ አንድ አካል ሆኖ የተቀሩት ሙስሊሞች የሚያገኙትን መብቶች ሁሉ ያላንዳች ልዩነት ማግኘት ይችላል። በዚህ ሸሪዓ ውስጥ የዘር፣ የቋንቋ፣ የሀገር ወይም የቀለም ልዩነት በፍጹም ቦታ የለውም ። ሸሪዓውም ዘልዓለማዊ ሸሪዓ ነውና ድንጋጌዎቹ በአንድ በተወሰነ ሕዝብ ልማድ ወይም የተለየ ዘመን ላይ የተመረኮዘ ሣይሆን በሰው ልጅ ተፈጥሮ መርህ ላይ የታነጸ ነው። ይህ የሰው ልጅ ተፈጥሮ በማንኛውም ዘመንና ሁኔታ ነዋሪ በመሆኑ በዚህ ላይ የተመሠረቱት ሕግጋትም በሁሉም ዘመንና ሁኔታ ቋሚና ነዋሪ ናቸው።

ተፈጸመ